# ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን

## ክፍል ኹለት

በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ
የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር፣ በቅድስት ሥላሴ
መንፈሳዊ ኮሌጅ የነገረ መለኮት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቅ
እና በፖስት ግራጁዬት ዲፕሎም(PGD)፤ በፊሎሎጂ
የማስተርስ ዲግሪ (BTH, PGD.MA)

2004 ዓ/ም

www.ethiopianorthodox.org

© መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፤ ይኽነን መጽሐፍ ያላዘጋጁ ፈቃድ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጐም በሕግ ያስጠይቃል።

All Rights Reserved

የመጀመሪያ እትም 2003 ዓ.ም

ኹለተኛ እትም 2004 ዓ.ም

ለማንኛውም አስተያየት እነዚኽን አድራሻዎች ይጠቀሙ

0 911 01 36 67

31274 Addis Ababa, Ethiopia

E-mail: rodastadese@yahoo.com

ከ ______________________

ማስታወሻ ______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

ለ ______________________

ቀን ______________________

## መታሰቢያነቱ

እጅጉን ለምወዳቸውና ለማከብራቸው በሕይወት ሥጋ ከዚህ ዓለም ለተለዩት ለእናቴ ለወ/ሮ በላይነሽ መንገሻ (መዐዛ ድንግል) እና ለሕፃን አቅሌስያ መስፍን (ወለተ ብርሃን)፤ በተጨማሪም በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ላሉት ለታላቁ ሊቅ ለመምህር ዐምደ ወርቅ እስጢፋኖስ ይኹንልኝ።

## ምስጋና

ከኹሉ በማስቀደም ይኽነን ሃይማኖታዊ መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ያነሣሣኝ እንድፈጽመውም የረዳኝን በአንድነቱ ምንታዌ በሦስትነቱ ርባኤ የሌለበትን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን አመሰግናለኊ፤ ዳግመኛም የነገረ ማርያም መጽሐፍን በማዘጋጅበት ጊዜ ኹሉ ርዳታዋ በቀንና በሌሊት ያልተለየኝን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አመሰግናለኊ።

በተጨማሪም የዚኽን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ መምህር ዐምደ ወርቅ እስጢፋኖስን፤ የመጻሕፍተ ሐዲሳት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የአቡሻህር መምህር የኾኑት የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት መምህር መልአከ ፀሐይ ታፈስ ደሳለኝን፤ የዳግማዊ ምኒሊክ መታሰቢያ የቀሳውስትና የመምህራን ማሰልጠኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የሐዲሳት መምሕር መጋቤ ሐዲስ ደምፀ አንበርብርን፤ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት መምህር ለመጋቤ ሐዲስ ደጉ ዓለም ካሣ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለኊ።

በጸሎትና ባቅማቸው የተባበሩትን አቶ ፍቃዱ ዓለሙን፣ መ/ር ብርሃኑ በላይ፣ ዲ/ን ስንታየኊ የሺጥላ፣ መ/ር ወልደ ሐዋርያትን፣ ወ/ሮ መስታወት አክሊሉን፣ ወ/ሮ ገነት ዓለሙን፣ ወ/ት ተስፋነሽ፣ ወ/ት አየሁን፣ እኅቴ ብርሃናዊትን፣ አያቴ ወ/ሮ አሰጋሽ ተሰማን፣ ሲ/ር አብረኸትን፣ እማሆይ ዘነበችንና አቶ ትሕትናው አላምነህ ስማቸውን ላልጠቀስኳቸው ጓደኞቼ ኹሉ ምስጋናዬን አቀርባለኊ።

www.ethiopianorthodox.org

ማውጫ


ገጽ

መግቢያ ........ ii

## ምዕራፍ አንድ

ነገረ ማርያም ከመጽሐፈ ጦቢት እስከ መጽሐፈ ኢዮብ ........ 1

## ክፍል አንድ

- የናቡቴ ርስት ........
ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ጦቢት ........ 5
- የጦቢት የዐይን ብርሃን ........ 5
ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ዮዲት፣ አስቴር፣ ኢዮብ ........ 7
- የዮዲት የጥበብ ቃል ........ 7

## ምዕራፍ ኹለት

ነገረ ማርያም ከመዝሙረ ዳዊት እስከ ማሕልየ መሓልይ ........ 11

## ክፍል አንድ

ነገረ ማርያም በመዝሙረ ዳዊት ........ 11
- ንግሥት ........ 12
- የእግዚአብሔር ከተማ ........ 21
- ክነፈ ርግብ ........ 24
- ዐጺስቲ እንበሳ ........ 27
- ሀምረ ዳዊት ........ 29
- ደብረ ጽዮን ........ 31
- እውነትና ሰላም ........ 33
- እናታችን ጽዮን ........ 35
- ጽዮን ........ 36

## ክፍል ኹለት

ነገረ ማርያም በማሕልየ መሓልይ ........ 41
- የሱፍ አበባ ........ 42
- መሽከሚያ (ዙፋን) ........ 43
- የሊባኖስ ሙሽሪት ........ 45
- የተቈለፈች ገነት፣ የታተመች የውሃ ጉድጓድ ........ 48
- ርግበ ሰሎሞን ........ 54
- ሱላማጢስ ........ 56

## ምዕራፍ ሦስት

ገረ ማርያም በዐበይት ነቢያት ........ 59
ገረ ማርያም በትንቢተ ኢሳይያስ ........ 60

## ክፍል አንድ

- ንጽሕት ዘር ........ 60
- ፍሕመ ምሥዋዕ፣ ረኀርም ዙፋን ........ 64
- ድንግልም እናትም ........ 68
- ነቢይት ........ 70
- የዕሴይ በትር ........ 73
- ፈጣን ደመና ........ 76
- የታተመች መጽሐፍ ........ 77
- የተጠማች ምድር ........ 82
- ንግሥተ ነገሥታት ........ 85
ገረ ማርያም በትንቢተ ኤርምያስ ........ 86

## ክፍል ኹለት

- የአቤሜሌክ በለስ ........ 87
ገረ ማርያም በትንቢተ ሕዝቅኤል ........ 90

## ክፍል ሦስት

- ኪሩባዊት ሠረገላ ........ 90
- የተቈለፈች መቅደስ ........ 94


www.ethiopianorthodox.org

ነገረ ማርያም በትንቢተ ዳን... ...................................... 103

...ት

- የዳንኤል ተራራ ...................................... 103
- የሠለስቱ ደቂቅ የምስጋና ...................................... 106
- የዳንኤል የትንቢቱ ክንው... ...................................... 110
- የአናብስት ጉድጓድ ...................................... 112

...አራት

ነገረ ማርያም በደቂቅ ነቢያት ...................................... 114
ነገረ ማርያም በትንቢተ ሖሴዕ ...................................... 115

...ድ

- ምድር ...................................... 116

ነገረ ማርያም በትንቢተ አሞ... ...................................... 118

...ለት

- የአሞጽ ተቀባይ ...................................... 118

ነገረ ማርያም በትንቢተ ሚ... ...................................... 120

...ስት

- ቤተልሔም ...................................... 120

ነገረ ማርያም በትንቢተ ኢ... ...................................... 126

...ል አራት

- የበረከት ምን... ...................................... 126

ነገረ ማርያም በትንቢ... ...................................... 128

...ፍል አምስት

- የአብድዩ ...................................... 128

ነገረ ማርያም በትንቢተ ዮናስ ...................................... 129

ክፍል ስድስት

- የዮናስ ጠባቂ ...................................... 129

ነገረ ማርያም በትንቢተ ናሆም ...................................... 131

ክፍል ሰባት

- የናሆም መድኀኒት ...................................... 131

ነገረ ማርያም በትንቢተ ዕንባቆም ...................................... 132

ክፍል ስምንት

- የፋራን ተራራ ...................................... 132

ነገረ ማርያም በትንቢተ ሶፎንያስ ...................................... 135

ክፍል ዘጠኝ

- የሶፎንያስ ራእይ ...................................... 135

ነገረ ማርያም በትንቢተ ሐጌ ...................................... 137

ክፍል ዐሥር

- የሐጌ ሽልማት ...................................... 137

ነገረ ማርያም በትንቢተ ዘካርያስ ...................................... 142

ክፍል ዐሥራ አንድ

- የዘሩባቤል የቃሉ ጣዕምና የዮሴፅ(ኢያሱ) የልብሱ ጌጥ ...................................... 142
- የወርቅ መቅረዝ ...................................... 148

ነገረ ማርያም በትንቢተ ሚልክያስ ...................................... 151

ክፍል ዐሥራ ኹለት

- የሚልክያስ ንጽሕት አዳራሽ ...................................... 151

ማጠቃለያ ...................................... 155
ምስጋና ...................................... 159
ዋቢ መጻሕፍት ...................................... 164


www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

ሰማይ ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀኗ የተሸከመች፤ ኪሩቤል ሱራፌል ዙፋኑን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚሸከሙትን ሰማያዊ መለኮትን በገርባዋ ያዘለች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ ሰማይ ምድር ከፊቱ የሚሸሹትን የባሕርይ አምላክን በከናፍሮቿ የሳመችው፤ ፍጥረታትን ኹሉ በዝናብ አብቅሎ በፀሓይ አብስሎ የሚመግበውን፤ ለቅዱሳን መላእክት ርሱ የገለጸላቸው ምስጋና ምግብ ኹኗቸው እንዲኖሩ ያደረገውን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለውን እግዚአብሔር ወልድን የድንግልና ጡቶቿን ያጠባች የርሷን ፍጹም ክብሯን፣ ምሳሌዎቿን፣ ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋንና፣ የዘላለማዊ ድንግልናዋን ነገር ሰማይ ምድር ብራና፤ በዓለም ያሉ ውቅያኖሶች ኹሉ ቀለም፤ መላእክትና የሰው ልጆች ኹሉ ጸሐፍት ቢኾኑ እንኳ ከቶ ሊፈጽሙ አይቻላቸውም።

እኔም አስቀድሜ "ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል አንድ" ብዬ በጻፍኩት ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ መጽሐፈ ነገሥት ያሉትን ሰማንያ ስድስት የቅድስት ድንግል ማርያምን ምሳሌዎችን በያዘው መጽሐፌ መግቢያ ላይ እንደገለጽኩት የነገረ ማርያም ትምህርት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከፅንሰቷ ዠምሮ እስከ ዕርገቷ ያለውን ታሪክ ብቻ የሚያጠና ሳይኾን ስለ አምላክ እናትነቷ፣ ስለ ዘላለማዊ ድንግልናዋ፤ በነገረ ሥጋዌ ስላላት ድርሻ፣ ስለ ንጽሕናዋ ቅድስናዋ፣ ስለተሰጣት ክብር ጨምሮ የሚያጠናና ከነገረ ሃይማኖት ትምህርት ክፍል ጋር ተካትቶ በጥልቀት የሚተነተን የሃይማኖት ትምህርት ክፍል ነው።

ቅድመ ሥጋዌ የነበሩ ቅዱሳን አበውና ቅዱሳን ነቢያት በመንፈስ እግዚአብሔር እየተገለጸላቸው የአምላክ እናትነቷን፣ የማይለወጠው ድንግልናዋንና የተሰጣትን ፍጹም ክብሯን በብዙ ሕብረ ትንቢትና በብዙ ሕብረ አምሳል ሲገልጹ፤ ከነርሱ በመቀጠልም ቅዱሳን ሐዋርያት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ የፈጣሪያቸውን እናት ክብር የልጇን የባሕርይ አምላክነት የርሷን ወላዲተ አምላክነት በዓለም ኹሉ አስተምረዋል።

ከሐዋርያት ቀጥለው ወላዲተ አምላክነቷን ያስተማሩ ተላውያን ሐዋርያት (Apostolic Fathers) በመባል ከሚታወቁት ከቅዱሳን አበው



መኻከል «ምጥው ለአንበሳ» በመባል የሚታወቀው በአንጾኪያ ቤተ ክርስትያን ከቅዱስ ጴጥሮስ በመቀጠል በሦስተኛነት የተሾመው አግናጥዮስና፤ የወንጌላዊ ዮሐንስ ተማሪ የፖሊካርፕ ባልንጀራ የነበረው የኄራጰሊሱ ጳጳስ ፓፒየስ (፷-፻፶ ዓ.ም) ያስተማሩትን ጥልቅ የነገረ ማርያም ትምህርትን፤ ዳግመኛም ከእነዚኽ ቅዱሳን አበው ቀጥለው በክርስቶስ ደም የተመሠረተችውን ቤተ ክርስትያን ከተለያዩ የክሕደትና የምንፍቅና ትምህርቶች የጠበቋት ዐቀብተ እምነት (Apologist) ከሚባሉት አበው ሊቃውንት መኻከል የአቴንሱ አርስቲደስ፣ ሰማዕቱ ጀስቲን (ዮስቲኖስ) (+፻፷፭ ዓ.ም)፣ የሰርዴሱ ጳጳስ ሚሊቶ፣ የአቴንሱ አታናጎራስ፤ የፖሊካርፕ ተማሪ የነበረው ሄሬኔዎስ (፪፻፫ ዓ.ም)፣ እስክንድርያዊዉ ቀሌምንጦስ (፻፶-፪፻፲፭) ዓ.ም፣ የካርቴጁ ጠርጠሉስ (ተርቱልያን) (፻፷-፪፻፳ ዓ.ም)፣ የሄሬኔዎስ ተማሪ የሂፖሊተስ እጅግ አስደናቂ የነገረ ማርያም ጥልቆች ትምህርቶች ይገኛሉ።

በተጨማሪም የወርቃማው ዘመን ሊቃውንት (The Golden Age Fathers) በመባል ከሚታወቁት ውስጥ የእስክንድርያው ሊቅ ቅዱስ አትናቴዎስ (፪፻፺፰-፫፻፸፫ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ (፫፻፳፱-፫፻፸፱ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ጎርጎሬዎስ ዘእንዚናዙ (፫፻፴-፫፻፺ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ጎርጎሬዎስ ዘኑሲስ (፫፻፴፭-፫፻፺፭ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ (፫፻፵፯-፬፻፯ ዓ.ም)፤ የእስክንድርያው ቅዱስ ቄርሎስ (፬፻፲፪-፬፻፵፬ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ (፫፻፮-፫፻፸፫ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ (፬፻፶፩-፭፻፳፩ ዓ.ም)፣ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ (፬፻፷፭-፭፻፵፪ ዓ.ም) እና ሌሎች በርካቶች የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ያስተማሩት ጥልቅ የነገረ ማርያም ትምህርቶች ይገኙበታል።

በቅዱሳት መጻሕፍት ዕወቀት በእጅጉ የተራቀቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንትም ለቤተ ክርስቲያኒቱና ለዓለም ጽፈው ካበረከቱት አስደናቂ የነገረ ማርያም መጻሕፍት መኻከል በ ፭፻፭ ዓ.ም የተወለደው ማሕሌታዊዉ ቅዱስ ያሬድ አንቀጸ ብርሃንና በተለያየ ቦታ በጸዋትወ ዜማው ስለ እመቤታችን ያስተማራቸው ሲገኙ፤ ዳግመኛም ፲፫፻፶፯-፲፬፻፲፯ ዓ.ም ድረስ የነበረው ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም አርጋኖን፣ መጽሐፈ ሰዓታት፣ እንዚራ ስብሐት፣ ኖኅተ ብርሃን፣ መዐዛ ቅዳሴ፣ ሕይወተ ማርያም የተባሉ የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር የሚናገሩ መጻሕፍትን ጽፏል።



www.ethiopianorthodox.org

በተጨማሪም አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታም ምስጢሩ በእጅጉ የሚያስደንቅ ማሕሌተ ጽጌ የተባለ መጽሐፍን ሲያዘጋጁ፤ ከ ፲፱፻፴፬-፲፱፻፷፰ ዓ ም የነበሩት ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብም ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንዴት እንዳበሠረ የሚገልጥ ታላቅ የነገረ ማርያም መጽሐፍን ሲጽፉ፤ በተለያዩ ዘመናት የተነሡ የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ በእጅጉ የበዛላቸው በርካታ ሊቃውንትም ከዐሥር በላይ የቅድስት ድንግል ማርያምን የመላዎቹ ሕዋሳቷን ክብር የሚገልጹ መልኮችን ጽፈው አኑረውልናል።

እኔም በእግዚአብሔር ፈቃድ በእናቴ በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አስቀድሜ በጻፍኩት በክፍል አንድ የነገረ ማርያም መጽሐፌ ላይ ቅዱሳን አበው፣ ቅዱሳን ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ስለርሷ የተናገሩትን ሰማንያ ስድስት (፹፮) ምሳሌዎቿን እንደገለጽኩኝ ኹሉ፤ አኹን በጻፍኩት የክፍል ኹለት የነገረ ማርያም መጽሐፌ ላይም ቅዱሳን ነቢያት በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝተው የተናገሩላትን ከመጽሐፈ ጦቢት እስከ ትንቢተ ሚክያስ ያሉትን ኀምሳ አራት (፶፬) የቅድስት ድንግል ማርያምን ምሳሌዎችን በስፋትና በጥልቀት ስተነትናቸው፤ በክፍል አንድ ላይ ያልተካተተው የናቡቴ ርስትነቷን አስቀምጫለኍ።

ይኽም መጽሐፍ በአራት ታላላቅ ምዕራፍ የተከፈለ ሲኾን የመገ[illegible]መሪያው ምዕራፍ ከመጽሐፈ ጦቢት እስከ መጽሐፈ ኢዮብ ያሉትን የእመቤታችን ምሳሌዎችን ሲያብራራ፤ ምዕራፍ ኹለት ከመዝሙረ ዳዊት እስከ ማሕልየ መሐልይ ያሉትን ምሳሌዎቿን ይዟል፤ ሦስተኛው ምዕራፍ ከትንቢተ ኢሳይያስ ገ[illegible]ምሮ እስከ ትንቢተ ሕዝቅኤል ስለርሷ ዐበይት ነቢያት በብዙ ሕብረ ትንቢትና አምሳል የተናገሩት ሲተነትኑ፤ አራተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ከትንቢተ ሖሴዕ እስከ ትንቢተ ሚክያስ ባሉ በዐሥሩ ኹለቱ ደቂቅ ነቢያት ውስጥ ምሳሌዋ እንዴት እንደተገለጸ ያብራራል፤ በተጨማሪም ይኽ ታላቅ ምስጢር የያዘ መጽሐፍ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን የተገለጸ የቅድስት ድንግል ማርያምን ምሳሌዎቿን ከመያዙም ባሻገር የጽሑፉ የፊደላት መልኮች በሥርዓቱ ሲስተካከሉ፤ አንባቢው በመጽሐፌ ላይ የጠቀስኳቸውን የጥቅሶችን ምንጮች በቀላሉ እንዲያገኝ በግርጌ ማስታወሻ (foot note) ሥር አስቀምጨዋለኍ።

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ





# ምዕራፍ አንድ

# ነገረ ማርያም ከመጽሐፈ ጦቢት እስከ መጽሐፈ ኢዮብ

# ክፍል አንድ

እነሆም ከዛሬ ገ[illegible]ምሮ ትውልድ ኹሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የኾነ ርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው" (ሉቃ ፩፥፵፱) በማለት በትውልደ ሴም፣ በትውልደ ካም፣ በትውልደ ያፌት መመስገኗን እንደተናገረች ንጽሕናዋን ቅድስናዋን በብዙ ሕብረ ትንቢት በተናገሩ፣ በብዙ ሕብረ አምሳል በመሰሉ በአበው ነቢያት ፊንታ፤ ወላዲተ አምላክነቷን በዓለሙ ኹሉ ዙሪያ ያስተማሩ ቅዱሳን ሐዋርያት እንደተተኩ፤ ከነርሱም በመቀጠል ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ እንደ ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ምእመናን ኹሉ ብፅዕት ነሽ እያሉ የፈጣሪያቸውን እናት ዘወትር ያመሰግኗታል ።

ቅድመ ሥጋዌ የነበሩ ነቢያት ኹሉ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ገልጾላቸው ስለ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ፤ ስለ ዘላለማዊ ድንግልናዋና አምላክን ስለ መውለዷ የገለጹትን ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳል ኹሉ ተናግሮ መፈጸም ባያቻልም ከመጽሐፈ ነገሥት የናቡቴ ርስትነቷን በማካተት ከመጽሐፈ ጦቢት እስከ ትንቢተ ሚክያስ ያሉትን ፈድኤተ እግዚአብሔርን አጋኘ በማድረግ ከዚኽ በታች ተንትኘቸዋለኍ።

## የናቡቴ ርስት

በመስቀል ሥር ከሰማዩ አባታችን ዘንድ እናት ትኾነን ዘንድ በአደራ የተሰጠችን ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ታማኙ ናቡቴ ከአባቱ ዘንድ በአደራ በተቀበላት እስከ ሞት ድረስ በታመነባት ርስቱ ትመሰላለች (፩ ነገ ፳፥፩-፳፮)።

ለኢይዝራኤላዊዉ ለናቡቴ በሰማርያው ንጉሥ በአክዓብ ቤት አጠገብ ከአባቱ በአደራ የወረሳት የወይን ቦታ ነበረችው፤ ከዚኽች የወይን ቦታው በግፍ ንጉሡ አክዓብ ሊያስወጣው ስላሰበ የወይን ቦታኽን ስጠኝ በርሱም ፈንታ ሌላ ምትክ እሰጥኻለኍ፤ ወይም ግምቱን ገንዘብ እሰጥኻለኍ፤ በማለት ሰ ጠይቀው ታማኙ ናቡቴ ግን የአባቶቼን ርስት ስጥ የሚል ኀሊና እግዚአብሔር ያርቅልኝ በማለት ቊርጥ ንግግሩን ተናገረው።



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬም የሕይወት መጠጥ፣ የሕይወት ፍሬ ክርስቶስን ያገኘንባት በወይን ሐረግ የምትመሰል፤ በሃይማኖት፣ በምግባር የሐንስን ስምንመስል ለኹላችን ከሰማዩ አባታችን በመስቀል ሥር እናት ትኾነን ዘንድ ከተሰጠችን ክርስታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ለመለየት ዛሬም ልክ ናቡቴ እንደተጠየቀው አውሬው ሰይጣን በግብር ልጆቹ በጥቅማጥቅም በሰከሩ በፀረ ማርያም አስተሳሰብ ባላቸው በመናፍቃን ልብ ውስጥ በማደር ታማኞች ምእመናንን ገንዘብ እንሰጣችኊለን ካዷት የሚል ድምፁን ማሰማቱን ተያይዞታል።

ይኽም አይደንቀንም በጊዜያችን ይኽ እንደሚከሠት በመስቀል ሥር በአደራ የተቀበላት ታማኙ ዮሐንስ በራእዩ ላይ ቀድሞ ዘንዶው የተባለ ዲያብሎስ በተንኰሉ በእባብ በተመሰለ በሄሮድስ ዐድሮ እመቤታችንን ከልጇ ጋር ወደ ግብጽ በረሓ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር እንድትሰደድ እንዳደረገ ኹሉ፤ ዛሬም ኀሲናቸው በዓለማዊ ጥቅም በመታሰሩና ከእምነት ልቡናቸው በመቀዝቀዙ ምክንያት በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ በተመሰሉት በመናፍቃን ልቡና በማደር የልጇ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የርሷን ወላዲተ አምላክነት የሚያምኑ ታማኞች ምእመናንን እንደሚዋጋ ሲገልጽ "ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘሩዋ የተቀሩትን ሲዋጋ ቆመ፤ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ" በማለት ገልጾታል (ራእ ፲፪፥፲፯)።

ዛሬም ምንም ሰይጣን ተቈጥቶ፤ እንኳን ምስጢር ንባብ አጣርተው በማያውቁ በመናፍቃን ዐድሮ በእመቤታችን ላይ ውጊያ ቢያስነሣም ታማኞች የቅድስት ድንግል ማርያም የርስት ሀገሯ የኢትዮጵያ ልጆች ምእመናን ግን ልክ እንደ ናቡቴ የመስቀል ሥር ስጦታችን፣ ርስታችን ቅድስት ድንግልን በገንዘብ እንለውጣት ዘንድ እግዚአብሔር ይኽን ያርቅልን እያሉ በታማኝነት ከቅዱሳን አበው የተረከቧትን እምነት አስጠብቀው አሉ።

ከዚያም አክዓብ የናቡቴን ቃል ከሰማ በኋላ ተቈጥቶና ተናድዶ ወደቤቱ በመግባት እንጀራ አልቀምስም በማለት ባልጋው ላይ ሲጋደም የእግዚአብሔር ነቢያትንና ካህናትን በማሳደድና በማስገደል የታወቀችው የንጉሡ ሚስቱ ኤልዛቤል ለምን እንዳዘነ ብትጠይቀው ምክንያቱን አስረዳት፤ ርሷም ባሏን አጽናንታ ናቡቴ የሚሞትበትን የሐሰት ደብዳቤ በአክዓብ ስም አጽፋ በማኅተሙም





ካተመች በኋላ የሐሰት ምስክር ተመስክሮበት በደንጊያ ተወግሮ እንዲሞት አስወስና ለርስቱ የታመነው ናቡቴ እንዲሞት አስደረጋለች።

የእግዚአብሔር ነቢያትንና ካህናትን በማሳደድና በማስገደል የታወቀችውን ኤልዛቤልንና ሐሰተኞችን ማደሪያ በማድረግ ለርስቱ የታመነ ናቡቴ እንዲሞት ያስደረገ ሰይጣን፤ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በማደሪያው በቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናትነት የሚያምኑ እልፍ አእላፋት ምእመናንን እንደ ኤልዛቤል ባሉ ሐሰተኞች ዐድሮ አስጠፍቷል።

ቅድስት ድንግል ማርያምን በአደራ የተቀበላት ዮሐንስ ይኽነን በኋላ ዘመን የሚኾን የሰይጣን ሥራ ተገልጾለት በራእዩ ላይ "አውሬው ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፤ በአርባ ኹለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው፤ እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ፤ ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፤ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ኹሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው፤ ከዓለምም ፍጥረት ዠምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ኹሉ ይሰግዱለታል፤ ዦሮ ያለው ቢኖር ይስማ፤ ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮኛነት ይኼዳል፤ በሰይፍ የሚገደል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል፤ የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት በዚኽ ነው" በማለት አስጠንቅቋል (ራእ ፲፫፥፭-፲)።

ይኽ ራእይ ሲፈጸም እግዚአብሔርን ማደሪያው ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ መላእክትን ለመስደብ አፉን የሚከፍተውና በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በማደሪያው በቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናትነት የሚያምኑ ምእመናንን በሰይፍ የሚያስጠፋው ሐሳዌ መሲሕ ከመምጣቱ በፊት ዛሬ የርሱ መንገድ ጠራጊዎች የኾኑ መናፍቃን የልጇን የባሕርይ አምላክነትና ፈራጅነት፤ የርሷን ወላዲተ አምላክነትና አማላጅነት በመንቀፍ የስድብ አፋቸውን እንደ አባታቸው እንደ አውሬው ሐሳዌ መሲሕ የሚያላቅቁ ኾነዋል (ማቴ ፯፥፲፭-፲፯፤ ፳፬፥፳፬፤ ሮሜ ፲፮፥፲፯-፲፱፤ ፪ጢሞ ፫፥፩-፱፤ ፪ጴጥ ፫፥፪-፲፰፤ ይሁ ፲፯-፲፱)።

ይኽቺ የሐሰት ሰው ኤልዛቤል ታማኙ ናቡቴ እንዲገደል ስታደርግ የእግዚአብሔር ነቢይ ኤልያስ ደግሞ ከአምላክ ተገልጾለት በኢይዝራኤል ቅጥር አጠገብ ኤልዛቤልን ውሾች ይበሏታል ከአክዓብም ወገን በከተማዩቱ



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ የሞተውን ውሾች ይበሉታል በሜዳውም የሞተውን የሰማይ ወፎች ይበሉታል በማለት ትንቢትን ተናግሮ እንደ ትንቢቱ ቃል አስከፊ አሟሟትን ሞተዋል።

ዛሬም ሰውን ወደተሳሳተ ክሕደት የሚመሩ የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት በኑፋቄ የሚመርዙ የዘላለም ሕይወትን እንዳይወርስ እንቅፋት የኾኑ ኹሉ እንደ ኤልዛቤል ጊዜያዊ ያይደለ የዘላለም ሞት እንደሚሞቱ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ ምክንያቱም በሥጋ የሞተ ሰው በነፍሱ የመዳን ዕድል ሲኖረው ሲችል የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት ክዶ የሞተ ሰው ግን የሚጠብቀው የዘላለም ሞት ነውና፤ ሰውን ከማስካድ የበለጠ ታላቅ ኀጢአት የለም፤ ለዚኽ ነው ፈጣሪያችን ክርስቶስ በዮሐ ፲፥፲ ላይ "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም" በማለት መናፍቃን ሰውን ወደ ዘላለማዊ ሞት እንዲወርዱ የሚያደርጉ የነፍስ ሌቦች መኾናቸውን አስተምሯል።

ቅዱስ ጳውሎስም ስለነዚኽ የጥፋት ልጆች በመልእክቱ ላይ "ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ኾነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለነርሱ አልኋችኁ፤ አኹንም እንኳ እያለቀስኹ እላለኊ፤ መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ኾዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ ዐሳባቸው ምድራዊ ነው" በማለት ሲያስተምር፤ ዮሐንስም በራእዩ ላይ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና ማደሪያውን ቅድስት ድንግል ማርያምን ይሳደብ የነበረ በአውሬ የተመሰለው ሐሳዊ መሲሕና የርሱ መንገድ ጠራጊዎች መናፍቃን በገሃነመ እሳት ስለሚቀበሉት መከራ ሲናገር "ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ" ብሏል (ፊልጵ ፫፥፲፰፤ ራእ ፳፥፲)።

ምእመናን ሆይ እኛም እንደ ናቡቴ በታማኝነት አባቶቻችን በብዙ ተጋድሎ ባቆዩልን ወልድ ዋሕድ በምትለው በተቀደሰው እምነታችን እስከ ሞት ድረስ በመጽናት ሃይማኖታችንን መጠበቅ ይገባናል፤ ምናልባትም በጊዜያዊ ጥቅም የመስቀል ሥር ስጦታችኊ ርስታችኊ ቅድስት ድንግልን የተዋቻኊ ካላችኊ፤ እግዚአብሔርንና ማደሪያው ቅድስት ድንግል ማርያምን ለመሳደብ አፉን ከፍቶ የርሱን ሥራ እንዲሠሩ የሚያደረጋቸው የዲያብሎስ ማደሪያ ሐሳዊ መሲሕ ከተከታዮቹ ጋር ከሚገባበት ከዘላለም





እሳት ለመዳን ቶሎ ንስሓ በመግባት የእውነት ተባባሪዎች መኾን ይገባችኊል።

ሊቃውንት አባቶቻችንም የቅድስት ድንግል ማርያምን ቃል ኪዳን በተናገሩበት ድርሳን ላይ ይኽነን ምስጢር እንደ ወርቅ አንከብለው እንደ ሸማ ጠቅልለው

*"ዛቲ ይእቲ ማርያም ወይነ ናቡቴ ዘዐፀደ ግፍዕ"* (በግፍ የሞተ የናቡቴ የተክል ቦታ ማርያም ይኽቺ ናት)[1] በማለት አስተምረዋል።

## ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ጦቢት
## የጦቢት የዐይኑ ብርሃን

ጦቢት ዐሥሩ ነገድ በ፯፻፳ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲማረኩ ዐብሮ የተማረከ ጻድቅ ሰው ነው፤ ይኽ ሰውን በመርዳት በደግነቱ የታወቀው ጦቢት ከመንገድ ወድቆ የተገኘ በድን ቀብሮ፤ በዚያው ሌሊት ከቅጥሩ አጠገብ ፊቱን ተገልጦ ተኝቶ ሳለ አዕዋፍ ትኩስ ፋንድያ ዐይኑ ላይ ጥለውበት እንደ ብልዝ ያለ ወጥቶበት ዐይኑ ጠፋ፤ ሚስቱም ባለማስተዋል "አይቴ ውእቱ ምጽዋትከ ወጽድቅከ" (በጐነትኽ ምጽዋትኽ ያዳነኽ ወዴት ነው?) በማለት በተናገረችው ጊዜ ዐዝኖ ሞትን ተመኘ (ጦቢ ፪፥፲፬)።

ያን ጊዜ መልአኩ ሩፋኤል ርሱንና ባሎቿ ስለሞቱባት ቤተሰቦቿ ያንቋሸሿት የነበረችውን የራጉኤል ልጅ ሳራን ለማዳን ተልኮ በመምጣት አስቀድሞ በርሷ ላይ ዐድሮ ባሎቿን ይገድልባት የነበረውን ጋኔን አስወጥቶ የጦቢት ልጅ ጦብያ እንዲያገባት ካደረገ በኋላ ወደ ጦቢት በመኼድ ረኀርም በመን የታወረ ዐይኑን አብርቶለት "አነ ውእቱ ሩፋኤል መልአክ አሐዱ እምነ ሰብዐቱ ቅዱሳን መላእክት" (ከሰብዐቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ሩፋኤል እኔ ነኝ) ብሏቸው ተሰወረ (ጦቢ ፲፪፥፲፭)።

ርሱም በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዘመነ ሐዲስ የኢየሩሳሌም አምሳያ የምትኾን ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሚመሠርት ተገልጾለት

*"እስመ ትትሐነጽ ኢየሩሳሌም በእብነ ሰንፔር ወበመረግድ ወበዕንቍ ክቡር"* (ኢየሩሳሌም በሰንፔር፣ በመረግድ፣ በክበረ ዕንቍ ትሠራለች) በማለት በምስጢር የከበረች ቤተ ክርስትያን በሦስቱ ስም የምትጸና መኾኑን ከገለጸ በኋላ፤ *"አረፋቲሃ ወማሕፈዲሃ ወአናቅጺሃ*

[1] ድርሳነ ኪዳነ ምሕረት ዘሠሉስ፤ ገጽ ፲፰



www.ethiopianorthodox.org

*በወርቅ ንጹሕ*"(ድልድሷ፣ ግንቧ፣ በሯ በጠራ ወርቅ ይሠራል) ማለት ውስጧ በወርቅ በተመሰለ በሕገ ወንጌል የሚጸና መኾኑን ከተናገረ በኋላ "*ወመርሕባኒ በቢረሌ ወበዕንቈ ሶፎር አትራኮስ ወበዕንቈ ሶፎር ይትገበር*" (ዐደባባይዋ በ.ረሌ በሚባል ዕንቍ፣ ኢትራኮስ በሚባል ዕንቍ፣ ሶፎር በሚባል ዕንቍ ይሠራል) ሲል የሦስቱን የዕንቍ ስሞች በማንሣት ውስጧ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ በሦስቱ ስም የሚጸና መኾኑን ከገለጠ በኋላ

"*ወይብሉ በኵሉ ፍናዊሃ ሃሌ ሉያ ይሴብሑ ወይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር ለዓለም ወበኵሉ ዓለም*" (በጐዳናዋ ኹሉ ሃሌ ሉያ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል፤ እግዚአብሔር ለዘላለሙ ይመስገን እያሉ በዓለሙ ኹሉ ያመሰግናሉ) (ጦቢ. ፲፫፥፲፮-፲፯)፤ በማለት በዓለሙ ኹሉ ያሉ ምእመናን በወርቀ ደሙ በተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ፈጣሪያቸውን እንደሚያመሰግኑ የተናገረውን ትንቢት አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ፈጽሞታልና፤ ኢትዮጵያዊዉ ቁርሎስ የተባለው የነገረ ማርያም ሊቅ በኖኅተ ብርሃን መጽሐፉ ላይ "*ወፈዋሲተ አዕይንቲሁ ለጦቢት በእደ ሩፋኤል*" (በሩፋኤል መልአክ እጅ የጦቢት የዐይኖቹ ፈዋሽ አንቺ ነሽ)[2] በማለት ሲያመሰግናት፤ ኢትዮጵያውያን ቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም

"*ዛቲ ይእቲ ማርያም ወዘጦቢት ብርሃነ አዕይንቲ*" (የጦቢት የዐይኖቹ ብርሃን ይኽቺ ማርያም ናት)[3] በማለት ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንከብለው እንደ ሸማ ጠቅልለው አስተምረዋል፡፡

ጌታችንም ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ሐዋርያትን "እንግዲኽ ኺዱና አሕዛብን ኹሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችኹንም ኹሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ኹል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ ፳፰፥፲፱)፤ በማለት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ምእመናን በሦስቱ ስም ማለት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እየተጠመቁ ቤተሰቦቹ እንደሚኾኑ ሲያስተምር፤ ቅዱስ ጳውሎስም "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ" በማለት አስቀድሞ ጦቢት እንደተናገረው፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አምላክ ደሙን አፍስሶ በወርቀ ደሙ የዋጃት መኾኗን አስተምሯል (የሐዋ ፳፰፥፳፰)፡፡

[2] አባ ጊዮርጊስ፤ ኖኅተ ብርሃን፤ ገጽ 97

[3] ድርሳነ ኪዳነ ምሕረት፤ ገጽ ፻፳





# ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ዮዲት፣ አስቴር፣ ኢዮብ

## የዮዲት የጥበብ ቃል

ቀደምት የነገረ ማርያም ሊቃውንት እመቤታችንን የዮዲት የቃሏ ጥበብ በማለት አመስግነዋታል፡፡

ይኸውም በጊዜው ፍሕዮስ ቁሮስ የሚባል የፋርስ ንጉሥ ነበረ፤ ከገናንነቱም የተነሣ ናቡከደነጾር በሉኝ በማለት ሲናገር፤ ሆሎሆርኒስ የሚባል ቢትወደድ ነበረውና ዐሥር እልፍ ከኹለት ሺሕ እግረኛ፣ ዐሥር እልፍ ከኹለት ሺሕ ፈረሰኛ፣ ዐሥር እልፍ ከኹለት ሺሕ ቀስተኛ ይዘኽ እየዞርኽ አሳምን በማለት መመሪያን ሰጠው (ዮዲ ፪፥፩-፳፰)፡፡

ርሱም ሰራዊቱን ይዞ እየዞረ ከተማዎችን ኹሉ እያቃጠለ፣ ጎልማሶችን እየገደለ አዝመራውን እያጠፋ ሲመጣ እስራኤላውያን በመላ ማቅ ለብሰው ዐመድ ነስንሰው ብዙ ቀን በመጾም እግዚአብሔር ከዚኽ ጥፋት እንዲጠብቃቸው በመለመን የኮረብታቸውን በር በመዝጋት አምባውን ኹሉ ዐጠሩ፡፡

ሆሎሆርኒስም ይኽነን ሰምቶ በእጅጉ በመቆጣት የዐሞንን አለቃ አክዮርንና ሌሎችን ሹማምንት በመጥራት ስለ እስራኤላውያን ማንነት ጠየቃቸው፤ አክዮርም ጥንት አባታቸውን አብርሃምን ከወገኑ ለይቶ እንዴት ወደ ከነዓን እንዳገባው ፤ ወደ ግብጽ ከተሰደዱም በኋላ ጠላታቸው ፈርዖንን አስጥሞ ለአርባ ዘመን በምድረ በዳ መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከጭንጫ አፍልቆ በመመገብ ጠላቶቻቸውን ድል ነሥተው ምድረ ርስትን እንዴት እንዳወረሳቸው ከነገረው በኋላ ፈጣሪያቸውን ከበደሉ ድል እንደሚነሣቸው በደል ከሌለባቸው ግን ፈጣሪያቸው እንደሚረዳቸው ነግሮ እንዳይወጋቸው መከረው፡፡

ሆሎሆርኒስም ተበሳጭቶ የነዚያን ጥፋት ሳላሳይኽ አንተን አልገድልኽም ብሎ አክዮርን አሥረው በቈላተ ቤጤልዋ እንዲጥሉት አዘዘ፤ እስራኤልም አግኝተው እግር ብረቱን በመፍታት ይዘውት ገቡ፤ ርሱም ሆሎሆርኒስ በነርሱ ላይ በጠላትነት እንደ ተነሣባቸው በነገራቸው ጊዜ በግምባራቸው ወድቀው እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው ማደሪያው ቤተ መቅደስን እንዲጠብቅ ለዐምስት ቀናት ተማፀኑ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ይኸ የመጣውን መከራ "*ወሰምዐት በከ.ያሆን መዋዕል ዮዲት ወለተ ሚራሪ*" ይላል የሚራሪ ልጅ ዮዲት ሰማችው፤ ይኸቺ ዮዳት ባሏ ምናሴ ከሞተ በኋላ ከወንድ ተለይታ በቤቷ ሰገነት ላይ የብሕትውና በታ አበጅታ በወገቧ ማቅ ታጥቃ ቅዳሜ፣ የሠርቀ ወርኀ ዋዜማ፣ የሠርቀ ወርኀ ዕለት፣ በበዓለ ሠዊት፣ በበዓለ መጸለት፣ በበዓለ ፋሲካ ነው እንጂ ምሳ ቀምሳ አታውቅም ነበር፤ ርሷም እስከ ዐምስት ቀን ድረስ ፈጣሪያቸው ቢሰማቸው ሊሰማቸው፤ ባይሰማቸው ሊክዱት አይደለም ብላ ቀኖና ገብታ እስራኤላውያንን "ስሙኝ ለልጅ ልጅ ዘመን የሚነገር ሥራን እሠራለኍ፤ እኔ የምሠራው ሥራ እስኪፈጸም ድረስ አልነግራችኹም" አለቻቸው፤ እነርሱም መርቀው ሰደዷት (ዮዲ ፰፥፩-፴፮)።

ከዚያም እግዚአብሔርን ለምና የለበሰችውን የማቅ ልብስ አውልቃ፣ ሰውነቷን ታጥባ፣ ሽቱ ተቀብታ፣ ራሷን ተቀብታ፣ አጊጣ አገልጋይን አስከትላ ሆሎሆርኒስ ወዳለበት ኼደች፤ ዘበኞችም ይዘው በውበቷ በመደነቅ ለንጉሥ ትገባለች በማለት ወደ ሆሎሆርኒስ አስገቧት፤ ርሱም በውበቷ በመደነቅ ለምን እንደመጣች ጠየቃት፤ ርሷም በጥበብ ኾና እስራኤል የአምላካቸውን ሕግ ስለጣሱ ለጥፋት እንደተቃረቡና በዚኽም ምክንያት ከነርሱ ኰብልላ ወደርሱ እንደመጣች ከነገረችው በኋላ ሌሊት ወደ ምድረ በዳ እየኼደች እንድትጸልይ እንዲፈቅድላት በዚኽም ጸሎቷ መቼ መዝመት እንዳለበት እንደሚገለጽላት በጥበብ ነገረችው፤ ርሱም ባግዋ የሚባል ባልደረባ ሰጣት።

ዮዲትም እየወጣች ስትጸልይ ሰነበተች እግዚአብሔርም መንገዷን ኹሉ ያቃናላት ነበር፤ ሆሎሆርኒስም በአራተኛው ቀን ምሳ አድርጎ ዮዲትን አስጠራት፤ ርሷም ልብሷን ለብሳ አጊጣ ገባች፤ ርሱም መልኳን እያየ በደስታ በመኾን ሳይታወቀው እጅግ ብዙ ወይን ጠጣ፤ አገልጋዮቹም ሥጋዊ ፈቃዱ የተነሣ መስሏቸው ዮዲትን ብቻ አድርገው ኹሉም ከድንኳኑ ወጡ፤ ሆሎሆርኒስ ግን አብዝቶ ስለጠጣ ሰክሮ ወዲያውኑ እንቅልፉን ተኛ።

ርሷም ተነሥታ ትጸልይ ገባመር፤ "የፍጹም ኀይል ፈጣሪ ሆይ አቤቱ ይኸነን የኾነውን እይ፤ ኢየሩሳሌም ከፍ ከፍ ትል ዘንድ በዚኽች ጊዜ በኔ እጅ ኀይልኽን አድርግ፤ ማደሪያኽ እስራኤልን በምታነሣ ገንዘብ ጊዜው ደርሷልና፤ በኛ የተነሡ ጠላቶች በሚጠፉ ገንዘብ ዐሳቤን ፈጽምልኝ" ካለች በኋላ የራሱን ሰይፍ ከራስጌው አንሥታ የራሱን ጠጕር ይዛ፤ "የእስራኤል ፈጣሪ ዛሬ አጽናኝ" በማለት አንገቱን አለችው፤ ሴት





ደካማ ናትና ሳይቈረጥ ቀረ ደገመችው ተቈረጠ፤ ከዙፋኑ ወርውራ ጥላ አገልጋይዋን ጠርታ አንገቱን አኸል በሚይዙበት ራምት ከታ ወጣች።

ከዚያም በሩቅ ኾና ድምፅዋን ለእስራኤል ጠባቂዎች አሰማታ ተጣራች፤ እነርሱም በሩን ከፈቱላት፤ ርሷም ጠላታችኹን ገድዬላችኍ መጣኍ በማለት የሆሎሆርኒስን አንገት አውጥታ አሳየቻቸው፤ እነርሱም ፈጣሪያቸውን በማመስገን "የረዳሽ እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው ስምሽን ለዘላለሙ እንዲጠራ ያድርግልሽ" አሏት፤ ርሷም ሲነጋ አንገቱን በተራዳ ላይ ሰቅላችኍ ተዋጉ አለቻቸው።

እነርሱም እንደ መከረቻቸው አንገቱን በተራዳ አድርገው ይዋጉቸው ገመር፤ የንጉሡም አሽከሮች ሹሙን "ጌታችንን ቀስቅስልን" አሉት፤ ርሱም ቢገባ ራሱ ተቈርጦ ሬሳው በምድር ላይ ወድቆ አገኘው፤ "ዛቲ ዕብራዊት ገበረት ኀሣረ ላዕለ ቤተ ናቡከደነጾር" ያቺ ዕብራዊት ሴት በናቡከደነጾር ወገን ላይ ኀፍረትን አድርጋለች አላቸው፤ ወታደሮቹም ደንግጠው ሸሹ፤ እያሳደዱ አጥፍተዋቸዋል፤ ከዚያም በመደሰት ሊቀ ካህናቱ ኢዮአቄምና ታላላቅ ሰዎች "በኢየሩሳሌም ላይ አንቺ እመቤት ነሽ፤ የእስራኤል ክብራቸው አንቺ ነሽ፤ የወገኖቻችንም መመኪያ አንቺ ነሽ" በማለት ሲያመሰግኗት ሕዝቡም ዘንባባ ይዘው አመስግነዋታል።

ይኸ በእስራኤል ዘሥጋ ላይ በጠላትነት የተነሣ ዐሥር እልፍ ከኹለት ሺሕ እግረኛ፣ ዐሥር እልፍ ከኹለት ሺሕ ፈረሰኛ፣ ዐሥር እልፍ ከኹለት ሺሕ ቀስተኛ የነበሩት ሆሎሆርኒስ የወገኖቻችን መመኪያ ብለው እስራኤላውያን ባመሰገኗት በጥበበኛዪቱ በዮዲት እጅ አንገቱ በሰይፍ ተቈርጦ እንደ ሞተ ኹሉ፤ ዛሬም እስራኤል ዘነፍስ በተባልን ምእመናን ላይ ጽኑ ፍዳና መከራ ሊያመጣብን የሚወድ ጠላታችን ዲያብሎስን ከሰራዊቱ ከአጋንንት ጋር አክሲስ ምክሕነ (የመመኪያችን ዘውድ) በምንላት በመስቀል ሥር ስጦታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳንና ጸሎት በምልጃዋ ከልጇ በምታሰጠን መንፈሳዊ ጥበብና ኀይል ድል የምንነሣው ነውና ሊቃውንት የቃል ኪዳኗን ክብር በጻፉበት ድርሳን ላይ

"*ዛቲ ይእቲ ማርያም ወዘዮዲት ጥበበ ነገር እንተ አውደቀቶ ለሆሎሆርኒስ ፀር*" (ጠላት ሆለሆርኒስን ድል ለነሣች ለዮዲት ጥበብ የምትኾን ማርያም ይኽቺ ናት)[4] በማለት ሲያመሰግኗት፤

የመልክአ ማርያም ደራሲም የእመቤታችን የመላዎቿን ሕዋሳት ክብር በሚናገረው መጽሐፉ ላይ

[4] ድርሳነ ኪዳን ምሕረት ዘሰኑይ፥ ገጽ ፻፴



www.ethiopianorthodox.org

"ማርያም ድንግል ለዮዲት ኀበበ ቃላ" ( ድንግል ማርያም ለዮዲት የቃሏ ጥበብ አንቺ ነሽ)[5] በማለት ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ አስቀምጦታል።

ምስጋናዋ ከሰማይ ከዋክብት ከባሕር አሸዋ ይልቅ የበዛ እመቤታችንን ቀደምት መምህራን በዮዲት የቃል ጥበብ ብቻ ሳይኾን የአስቴር ጸሎቷን የምታሳርግላት ብለው አመስግነዋታል።

መጽሐፈ አስቴር በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት ከ ፬፻፹፮-፬፻፷፭ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የተፈጸመውን የእስራኤልን ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ሲኾን፤ የዕብራውያኑ መጽሐፈ አስቴር ዐጭር ከመኾኑ የተነሣ አንድ ጊዜ እንኳን ስመ እግዚአብሔር አልተጠቀሰበትም፤ ሙሉ በኾነው ከጽርኡ ጋር አንድ በኾነው በኢትዮጵያው መጽሐፈ አስቴር ግን ከ፷፩ ጊዜ በላይ የእግዚአብሔር ስም ተጠቅሷል፤ ሙሉ ታሪኩን ከመጽሐፈ አስቴር እንመልከት።

መቶ ኻያ ሰባት አህጉርን ይገዛ የነበረው የአርጤክስስ ሚስት የነበረችው እስራኤላዊቷ አስቴር፤ በመቶ ኻያ ሰባት አህጉር ያሉትን ወገኖቿን በተንኰል ሊያጠፋ ከነበረው ከሐማ የክፋት ሥራ ሕዝቡን ለመታደግ ሦስት ቀን እንዲጾሙ ለመርዶክዮስ ነግራው፤ ሕዝቡም ጾመው እግዚአብሔርም ልመናቸውን ተቀብሎ እስራኤላውያን ኹሉ ሐማ ካወጀባቸው ጥፋት ድነው፤ መርዶክዮስ እንዲሾም ሲኾን ሐማም ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ግንድ ላይ እንደተሰቀለ ኹሉ፤ እኛም እስራኤል ዘነፍስ ምእመናንም ዲያብሎስን በመስቀል ሥር አጋኘ፣ ረዳት፣ እናት ትኾነን ዘንድ ከፈጣሪያችን በተቀበልናት በእናታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎትና ቃል ኪዳን ድል የምንነሣው ኾነናልና፤ ሊቃውንት የማይሻር ከልጇ የተሰጣትን ቃል ኪዳን በተናገሩበት መጽሐፍ ላይ

"ዛቲ ይእቲ ማርያም ወምዕራገ ጸሎታ ለአስቴር" (የአስቴር የጸሎቷ መሰላል ማርያም ይኽቺ ናት)[6] በማለት አስቴርን በምእመን በመመሰል ሲያስተምሩ፤ ዳግመኛም በፍቅሯ፣ በጣዕመ ፍቅሯ፣ በቃል ኪዳኗ ከቍስለ ሥጋ፣ ከቍስለ ነፍስ፣ ከዘላለም ሞት የምንድንባት ነንና

"ዛቲ ይእቲ ማርያም ዘኢዮብ ጸወነ መስዕ" (የኢዮብ የሰሜናዊ ምሥራቅ አምባ መጠጊያው ማርያም ይኽቺ ናት)[7] በማለት ሲያመሰጥሩ፤ የተፈሥሐ ማርያም ደራሲም በመጽሐፉ ላይ

[5] መልክአ ማርያም፤ ለእመታትኪ
[6] ድርሳነ ኪዳን ምሕረት ዘሰኑይ፤ ገጽ ፻፲፱
[7] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ ፻፳





"ሙካፈ ስእለቱ ለኢዮብ አመ በቍስሉ ይደዊ" (በቍስለ ሥጋ በታመመ ጊዜ የኢዮብ የልመናው መቀበያ አንቺ ነሽ)[8] በማለት ደዌ ነፍሳችንን በመስቀል ተሰቅሎ ያራቀልን፤ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክን በድንግልና የወለደችልን የቅድስት ድንግል ማርያምን የምልጃዋን ታላቅነት አስተምረዋል።

በተጨማሪም እግዚአብሔር አምላክ ደዌ የጸናበት ኢዮብን ከደዌ ሥጋው ሊያድነው፤ ምሕረትን ሊሰጠው ሲል በደመና ተገልጦ ድኅነትን እንደሰጠው ኹሉ በዘመነ ሐዲስም ልዑል አምላክ ደዌ ነፍስ ጸንቶባቸው የነበሩትን የሰው ልጆች ለማዳን ሲል ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተወልዶ ምሕረትን ለዓለም ሰጥቷልና ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ "ንዒ ማርያም ለኢዮብ ደመናሁ" (የኢዮብ ደመና ማርያም ሆይ በረድኤት ነይ)[9] በማለት በመዐዛ ቅዳሴው ላይ አመስግኗታል (ኢዮ ፵፥፩)።

# ምዕራፍ ኹለት

# ነገረ ማርያም ከመዝሙረ ዳዊት እስከ ማሕልየ መሓልይ

## ክፍል አንድ

## ነገረ ማርያም በመዝሙረ ዳዊት

ንጉሥ ዳዊት ከወንድሞቹ መኻከል በፈቃደ እግዚአብሔር የተመረጠ ሲኾን በነቢዩ ሳሙኤል እጅ ቅብዐ መንግሥትን በተቀባ ጊዜ ሰባት ሀብታት ዐድረውበታል፤ እነዚኽም ጸጋዎቹ ሀብተ ኀይል፣ ሀብተ መዊእ፣ ሀብተ ክህነት፣ ሀብተ መንግሥት፣ ሀብተ በገና፣ ሀብተ ፈውስ፣ ሀብተ ትንቢት ናቸው።

ሀብተ ኀይል የሚለው ታግሎ መጣል፣ ሩጦ መቅደም ሲኾን፤ ሀብተ መዊእ የሚለው ሰንደቅ በተተከለበት ዐላማ በተዘረጋበት፣ነጋሪት በተደረደረበት ገብቶ ድል የመንሣት ስጦታ ሲሰጠው፤ በሀብተ ክህነቱም መሥዋዕት ይሠዋ ነበር (፪ ሳሙ ፳፬፥፲፰-፳፭)፤ በሀብተ መንግሥቱም ከወንድሞቹ መኻከል ተመርጦ ሲነግሥ (፩ ሳሙ ፲፮፥፲፫)፤ ሀብተ በገናና ሀብተ ፈውስ ስለተሰጠው በዚኽ ስጦታው አሳምሮ በገናውን ሲደረድር ሳኦል ከሕመሙ ይፈወስ ነበር (፩ ሳሙ ፲፮፥፳፫)።

[8] መጽሐፈ ሰዓታት፤ ገጽ ፹፱
[9] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መዐዛ ቅዳሴ፤ ቍ ፳፮



www.ethiopianorthodox.org

በተሰጠውም የትንቢት ሀብት በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት ስለ አምላክ ሰው መኾን፣ ስለ ጥምቀቱ፣ ስለ ሕማማቱና ስቅለቱ፣ ስለ ትንሣኤው፣ ስለ ዕርገቱና ስለ ዳግም ምጽአቱ ሲናገር በተጨማሪም ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕናዋና ቅድስናዋ፣ ስለ አምላክ እናትነቷ፣ ስለ ተሰጣት ታላቅና ፍጹም ክብር፣ ስለ ቃል ኪዳኗና አማላጅነቷ በመዝሙሩ ላይ በስፋት ተናግሯል።

ይኸ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በርካታ የነገረ ማርያም ምስጢር ሲናገር ከእነዚኽ መኻከል በመዝሙሩ ላይ

*"እንስ ተሠየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ በጽዮን በደብረ መቅደሱ"* (እኔ ግን በእነርሱ ላይ ንጉሥ ኾኜ ተሾምኹ፤ በተቀደሰ ተራራው በጽዮን ላይ) መዝ ፪፥፮ በማለት ቃል ኪዳኗ ጸወነ ሥጋ፣ ጸወነ ነፍስ በመኾኗ ምክንያት ጽዮን የተባለችና፤ ማሕፀኗን እንደ ዙፋን አድርጎ ፱ ወር ከ፭ ቀን በመላእክት የተመሰገነባት በመኾኗ፣ ምክንያት ደብረ መቅደስ ከተባለች ከቅድስት ድንግል ማርያም የባሕርይ ገዢ ንጉሥ ክርስቶስ እንደሚወለድ ሲናገር፤ ዳግመኛም *"ውእቱሰ ከመ መርዓዊ ዘይወፅእ እምጽርሑ"* (ርሱም እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል) በማለት መርዓዊ ሰማያዊ የተባለ ክርስቶስ፤ ንጽሕት እልፍኝ (አዳራሽ) ከተባለች ከቅድስት ድንግል መወለዱን በመዝሙሩ ተናግሯል (መዝ ፲፰፥፭)።

በታቦተ ጽዮን ፊት በታላቅ ደስታ የዘመረ የእግዚአብሔር አገልጋይ ዳዊት ስለ አማናዊቷ የእግዚአብሔር ታቦት (ማደሪያ) ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ተገልጾለት የተናገራቸው ትንቢቶች ብዙ ሲኾኑ፤ እኔም ከትንቢቱ መኻከል የንግሥትነቷን ክብር በማስቀደም የተናገረውን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ እገምራለኹ።

## ንግሥት

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር፣ ቅድስና፣ ንግሥትነት፣ አማላጅነትና በንጉሡ ሰማይና ወምድር በኩል ስለመመረጧ *"አዋልደ ንግሥት ለክብርከ"* (የእቴጌ (የንግሥት) ሴት ልጆች ለክብርኽ ናቸው) በማለት ሰማያዊ ንጉሥን የወለደች የንጉሣችን የክርስቶስ እናቱ የንግሥተ ሰማይ ወምድር የቅድስት ድንግል ማርያም የአደራ፣ የቃል ኪዳን ልጆች ለጌትነቱ እንደሚገዙና ለክብሩ ለመንግሥተ ሰማያት የመመረጣቸው ነገር ተገልጾለት አስቀድሞ በመዝሙሩ አመስግኗል (መዝ ፵፬፥፱-፲፫)።





በእውነት ቅድስት ድንግል ማርያም ንግሥት መኾኗን ንግሥት መባሏን ነቢዩ ዳዊት ብቻ ሳይኾን ነቢያት ሐዋርያት ባንድ መንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ሲጽፉ፤ ከዐበይት ነቢያት አንዱ ኢሳይያስ በትንቢቱ ላይ "ነገሥታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይኾናሉ፤ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይኾናሉ፤ ግምባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል፤ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ" በማለት የእቴጌዎች እመቤት፣ የንግሥታት ንግሥት መኾኗን ተናግሮላታል (ኢሳ ፵፱፥፳፫)።

ዳግመኛም ሰማያዊ ንጉሥን በመውለዷ ምክንያት ፍጥረት ኹሉ ንግሥት እመቤታችንን እንደሚያመሰግናት ጠቢቡ ሰሎሞንም በመሓልዩ ላይ "ርግቤ መደምደሚያዬ አንዲት ናት፤ ለእናትዋ አንዲት ናት፤ ለወለደቻትም የተመረጠች ናት፤ ቆነጃጅትም አይተው አሞገሱአት፤ ንግሥታትና ቁባቶችም አመሰገኑአት፤ ይኽቺ እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጎበኝ፤ እንደ ጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሓይም የጠራች፤ ዐላማ ይዞ እንደተሰለፈ ሰራዊት የምታስፈራ ማን ናት?" በማለት በትንቢት መነጽርነት የተገለጸለትን የንግሥትነቷን ክብር ጽፏል (መሓ ፮፥፱-፲)።

ይኽነን የንግሥትነት ክብሯን በዐይኑ የተመለከተ ከሐዋርያት አንዱ ዮሐንስም፤ በዚኽ ዓለም ያሉ ምድራውያን ንግሥታት የወርቅ ካባ ሲለብሱ፤ የወርቅ ጫማ ሲጫሙ፤ የወርቅ የዕንቍ አክሊል ሲደፉ፤ የምድርና የሰማይ ንግሥት አማናዊ ፀሓይ ክርስቶስን የወለደች ቅድስት ድንግል ግን የቀን ጌጥ ፀሓይን ተጐናጽፋ የሌሊት ጌጦች የኾኑትን ጨረቃን ተጫምታ፤ ከዋክብትን በራሷ ደፍታ እንደምትገኝ በራእዩ ላይ "ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ፤ ፀሓይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት፣ በራስዋም ላይ የዐሥራ ኹለት ከዋክብት አክሊል የኾነላት" በማለት ልክ እንደ ዳዊት የንግሥትነቷ አስደናቂ ክብርን በጉልህ አስተምሯል (ራእ ፲፪፥፩)።

ለንግሥት እመቤታችን የአደራ ልጆቿ እንደኾንን ኹሉ ርሷም የአደራ እናታችን እንደኾነች ራሱ ባለቤቱ በዕለተ ዐርብ በእግረ መስቀሉ ሥር ለተገኘ ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ ለዮሐንስ እጅግ የሚወዳትና ከኹሉ መርጦ እናቱ ያደረጋት እናቱ ቅድስት ድንግልን "እናትኽ እነኋት" ብሎ ሲሰጠው፤ የሚወደው ዮሐንስን የአደራ ልጇ ታደርገው ዘንድ የሚወዳት እናቱን "እነሆ ልጅሽ" በማለት አደራ ሰጥቷታል (ዮሐ ፲፱፥፳፮-፳፯)፤ ይኽም የአምላካዊ የአደራ ትእዛዝ ለሚወደው ለዮሐንስ ብቻ ሳይኾን በሃይማኖት፣ በምግባር ርሱን ለምንመስል ለኹላችን የአደራ እናታችን



www.ethiopianorthodox.org

የአደራ ልጆቿ ነንና፤ ይኽ በዮሐንስ በኩል ለኹላችን የተሰጠ የእናትነት ጸጋዋ አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ለክቡር ዳዊት ተገልጾለት "*አዋልደ ንግሥት ለክብርከ*" (የንግሥት ሴቶች ልጆች ለክብርኽ ናቸው) ሲል ትንቢትን መናገሩ በእጅጉ ያስደንቃል፡፡

በመቀጠልም "*ወትቀውም ንግሥት በየማንከ፤ በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወሑብርት*" (በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝኽ ትቆማለች) በማለት ንግሥት እመቤታችን ልጇ በሰጣት የአምላክ እናት የመኾን ክብር ጸንታ፤ በወርቅ የተመሰሉ ንጽሐ ሥጋን፣ ንጽሐ ነፍስን፣ ንጽሐ ልቡናን አስተባብራ ይዛ፤ ለምልጃ በልጇ በንጉሠ ሰማይ ወምድር በክርስቶስ ቀኝ መቆሟ ለዳዊት አስቀድሞ ተገልጾለት ተናግሯል፡፡

ይኸውም እንኳን የሰማይና የምድር ንጉሥ የአካላዊ ቃል የክርስቶስ እናት ይቅርና የምድራውያን ነገሥታት እናቶች በልጆቻቸው የነበራቸው ቦታ፣ ክብርና ተሰሚነት እጅግ ታላቅ እንደነበረ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል፡፡

ለምሳሌ ያኽል የንጉሥ ሰሎሞን እናት ቤርሳቤሕ በልጇ ዘንድ የነበራትን ክብርና ተሰሚነት መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ "ቤርሳቤሕም የአዶንያስን ነገር ትነግረው ዘንድ ወደ ንጉሡ ወደ ሰሎሞን ገባች፤ ንጉሡም ሊቀበላት ተነሣ፤ ሳማትም በዙፋኑም ተቀመጠ፤ ለንጉሡም እናት ወንበር አስመጣላት በቀኙም ተቀመጠች፤ ርስዋም አንዲት ታናሽ ልመና እለምንኻለኍ አታሳፍረኝ አለች፤ ንጉሡም እናቴ ሆይ አላሳፍርሽምና ለምኚ አላት" ሲል የእናት ተሰሚነት በልጅ ዘንድ ምን ያኽል ታላቅ እንደኾነ ይነግረናል (፩ ነገ ፪፥፲፱-፳)፡፡

ዳዊትም በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያምም በልጇ በንጉሠ ሰማይ ወምድር በክርስቶስ ቀኝ ቆማ የምታማልደን መኾኗንና ልመናዋም በልጇ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና መወደድ ተገልጾለት አመስግኗል፤ ሊቃውንቱም ይኽነን የቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢር በጥልቀት በመረዳት ከዚኽ የተነሣ "የናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ" በማለት የእናት ልመና በልጅ ዘንድ ያለውን ተሰሚነት በምሳሌ ሲያስተምሩ ኑረዋል፡፡

የሶርያ ፀሓይ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በውዳሴ ማርያም፡-

"*ወበእንተዝ ንስእል ንቤሃ ኵሎ ጊዜ ከመ ታስተስሪ በእንቲአነ ኀበ ፍቁር ወልዳ ኄርት ይእቲ በኀበ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሊቃነ ጳጳሳት እስመ አምጽአት ለነ ዘኪያሁ ይጸንሑ ወለነቢያትኒ አምጽአት ለሙ*





*ለዘበእንቲአሁ ተነበዩ ወለሐዋርያትኒ ወለደት ሎሙ ዘሰበኩ በስሙ ውስተ ኵሉ አፅናፈ ዓለም ለሰማዕት ወለመሃይምናን ወፅአ እምኔሃ ዘተጋደሉ በእንቲአሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዕለ ጸጋሁ ዘኢይትዐወቅ*"

(ስለዚኽ ኹል ጊዜ ርስዋን እንለምን ከተወደደ ልጅዋ ታማልደን ዘንድ በቅዱሳንና በሊቃነ ጳጳሳት ኹሉ ዘንድ ቸር ናት፤ ደጅ የሚጠኑትን ወልዳላቸዋለችና፤ ሐዋርያትም እስከ ዓለም ዳርቻ በስሙ ያስተማሩለትን ወልዳላቸዋለችና፤ ሰማዕታትና ምእመናንም የተጋደሉለት የጥበቡ ጸጋ ብዛት የማይታወቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከርሷ ተወልዷልና)[10] በማለት ዘወትር ከልጇ ታማልደን ዘንድ በልጇ ቀኝ ለምልጃ የቆመች የአምላካችንን እናት እንድንማፀናት አስተምሯል፡፡

ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ፳ሺ፬ከ፳፪ ዘመን ሲፈጸም ያለ ዘርዐ ብእሲ አካላዊ ቃል ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና የፀነሰች፤ ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፣ በኅቱም ድንግልና የወለደች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ በገርርባዋ ያዘለች ርሷ ብቻ ናትና፤ በርሷ አማላጅነት የምናቀርበው ጸሎት ምን ያኽል ታላቅ እንደኾነ በሰዓታት መጽሐፉ ላይ

"*ወፈድፋደሰ በእንተ ማርያም እምከ እንተ ይእቲ ትምክህተ ዘመድነ በእንተ ማሕፀና ዘጾረከ ወበእንተ ድንግልናሃ ዘኢረስሐ በፀኒሶትከ ወኢማሰነ በወሊዶትከ፤ በእንተ አዕዳዊሃ እለ ገሰሳከ ወበእንተ አብራኪሃ እለ ሐቀፉከ፤ በእንተ አጥባቲሃ እለ ሐፀናከ ወበእንተ ከናፍሪሃ እለ ሰዐማከ፤ በእንተ ዘባና ዘሐዘለከ ወበእንተ እኢጋሪሃ እለ አንሶሰዋ ምስሌከ፤ በእንተ አዕይንቲሃ ብሩሃት፤ ወእእዛኒሃ ስሙዓት፤ ወአእናፊሃ ምዑዛት፤ ወአስናኒሃ ጽዕድዋት እለ ተበሥራ በቃለ ገብርኤል መልአክ፤ በእንተ ሥጋ ወነፍስ ዐዕም ወደም ጸጕር ወአሥራው ዘነሣእከ እምኔሃ፤ ወረሰይኮ አሐደ ምስለ መለኮትከ ዘእንበለ ፍልጠት ኢውላጤ ዘእንበለ ቱስሕት ወኢቡዓዴ በከመ መሐሩነ አበው*"

(ይልቁንም የወገናችን መመኪያ ስለምትኾን ስለ እናትኽ ስለ ማርያም አንተን በመፅነስና አንተን በመውለድ እድፍ ጉድፍ ስላላገኘው ስለ አልተለወጠ ድንግናዋና ስለ ተሸከመኽ ማሕፀኗ፤ ስለ ታቀፉኽ ስለ ክንዶቿና፣ ስለ ዳሰሰኽ ስለ እጆቿ፤ ስለ ሳሙኽ ስለ ከንፈሮቿ ስለ አሳደጉኽ ስለ ጡቶቿ፤ ከአንተ ጋር ስለ ተመላለሱ ስለ እግሮቿና፤ ስለ አዘለኽ ስለ ገርርባዋ፤ ብሩሃት ስለሚኾኑ ስለ ዐይኖቿ በጎ መዐዛ ስላላቸው

[10] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘኀሙስ



www.ethiopianorthodox.org

አፍንጮቿ፤ ጸዐዳ ስለሚኾኑ ጥርሶቿ፤ በመልአኩ በገብርኤል ቃል ስለ ተበሠሩ (ብሥራትን ስለ ሰሙ) ስለ ጆሮ፦ቿ፤ ክርሷ ስለነሣኸው ሥርኅና ጸጉር፣ ደምና ዐፅም ስለ ነፍስና ሥጋ አባቶቻችን እንደ አስተማሩን ፈጽሞ ያለመለየትና ያለመለወጥ ከመለኮትነትኽ ጋራ አንድ ያደረግኸው)[11] በማለት እናትና ልጅ ያላቸው ግንኙነት ቃላት ከቶ ሊገልጸው የማይችል ጥልቅ መኾኑን እንዳስተማረ፤ በአምላካችን ቀኝ ዘወትር ለምልጃ የምትቆም ንግሥታችን ቅድስት ድንግልን ዘወትር በአባታችን በዳዊት መዝሙር ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታመሰግናታለች፡፡

ነቢዩ ዳዊት በመቀጠል *"ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምኢ እዝነኪ"* (ልጄ ሆይ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዩ) በማለት በባሕርዩ በአብራኩ ያለች በመኾኗ ቅድስት ድንግልን በትንቢቱ "ልጄ" እያለ ጌታ በቅዱስ ገብርኤል ዐድሮ የሚነግራትን ታላቅ የብሥራት ቃልን እንድትሰማ በትንቢቱ አስቀድሞ ነግሯታል፤ ይኽነንም ይዘው ሊቃውንት በምስጢር እመቤታችንን ወለተ ዳዊት (የዳዊት ሴት ልጅ) እያሉ ስያሜ ሰጥተዋቷል፡፡

ነቢዩ በመቀጠል *"ርስዒ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ"* (ወገንሽን ያባትሽንም ቤት ርሺ) በማለት እንደ ወገኖቿ ሴቶች ልጆች ልማድ በዘር በሩካቤ መውለድ የሌለባት ፍጹም በቅታ የተገኘች መኾኗን ከገለጸ በኋላ፤ *"እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ እስመ ውእቱ እግዚእኪ"* (ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፤ርሱ ጌታሽ ነውና) በማለት ንጉሠ ሰማይ ወምድር የኹሉ ጌታ ፈጣሪዋ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ ድንግልናዋን ወዶ ሥጋዋን ለመዋሐድ የመምረጡን ድንቅ ምስጢር መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ገልጾለት ይኽነን ትንቢት ሲናገር ሊቃውንትም ከዳዊት ቃል በመነሣት ብዙ ምስጢር አስተምረዋል፡፡

ከሊቃውንት አንዱ አባ ሕርያቆስም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት በተናገረው ቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ

*"በአማን ነጸረ እግዚአብሔር አብ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ ወውስተ ኵሉ አጽናፍ አስተንፈሰ ወአጼነወ ወኢረከበ ዘከማኪ ወሠምረ መዐዛ ዚአኪ ወአፍቀረ ሥነኪ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘየፈቅር"*

(እግዚአብሔር አብ በሰማይ ኾኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችን ኹሉ በእውነት ተመለከተ፤ ተነፈሰ አሻተተም፤ እንደ

[11]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መጽሐፈ ሰዓታት ገጽ ፰





አንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺ መዐዛ ወደደ፤ የሚወደውን ልጁንም ወደ አንቺ ላከ)[12] በማለት መዐዛ ንጽሕናዋ መዐዛ ቅድስናዋ በአምላክ ዘንድ የተወደደ መኾኑን ሲገልጽ፤

አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ክቡር ዳዊት የተናገረውን ኃይለ ቃል ምስጢሩን በመጠቅለል ሲያሖስጥሩ

*"እግዚአብሔር ነጸረ ኵሎ ዓለመ*
*ወኢረከበ ማርያም ዘከማኪ እመ*
*ኪያሁሰ ጽጌ ዘእምከርሥኪ ተቀሥመ*
*ዳዊት አመረኪ እንዘ ይብል ቅድመ*
*ስምዒ ወለትየ ወርእዩ ዳግመ*
*እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ አዳመ"*

(እግዚአብሔር ዓለምን ኹሉ ተመለከተ፤ ማርያም እንዳንቺ ያለች እናትን አላገኘም፤ ርሱስ ከማሕፀንሽ የተገኘ አበባ ነው፤ ዳዊትም ልጄ ሆይ ስሚ ዳግመኛም እዩ፤ ያማረ ደም ግባትሽን ንጉሥ ወዷልና ሲል አመለከተሽ)[13] በማለት በድንቅ ሃይማኖታዊ አገላለጽ አስቀምጠውታል፡፡

ክቡር ዳዊትም በመቀጠል *"ወየሰግዱ ለኪ አዋልደ ጢሮስ በአምኃ ወለገጽኪ ይትመሐለሉ ኵሎሙ አሕዛብ ብዑላነ ምድር"* (የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው ይሰግዱለታል፤ የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ) በማለት የልጇ የዐማኑኤልን የባሕርይ አምላክነት ምእመናን አምነው ሃይማኖታቸውን ምግባራቸውን እንደ እጅ መንሻ ይዘው የአምልኮት ስግደት እንደሚሰግዱለትና፤ ቅድስት ድንግል እናቱም ፈጣሪዋን የወለደች በመኾኗ ከልጇ እንድታማልዳቸው ትውልደ ሴም፤ ትውልደ ካም፤ ትውልደ ያፌት በፊቷ ዘወትር የሚማለሉ መኾናቸውን አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

እመቤታችንም በታላቅ አክብሮት እጅ እየነሣ "ጸጋን የተመላሽ ደስተኛዪቱ ሆይ ደኅ ይበልሽ፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው ከሴቶች መኻከል የተባረክሽ ነሽ" በማለት ባበሠራት በቅዱስ ገብርኤልና፤ መንፈስ ቅዱስ መልቶባት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ "አንቺ ከሴቶች መኻከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ

[12] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፳፴

[13] አባ ጽ.ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቍ [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

እንዴት ይኾንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማሕፀኔ በደስታ ዘሎአልና፤ ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት" በማለት በፊቷ እየተማለለች ባመሰገነቻት በኤልሳቤጥ ብቻ ተመስግና እንደማትቀር፤ ቀድሞ አባቷ ዳዊት በተናገረው ትንቢት መሠረት ትውልድ ኹሉ በፊቷ እንደሚማለል፤ "እነሆም ከዛሬ ዠምሮ ትውልድ ኹሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የኾነ ርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና" በማለት እንደተናገረች፤ ይኽነን የወንጌል ቃል በማክበር ዳዊት በተናገረው ትንቢታዊ ቃል እንደ ቅዱሳን አባቶቻችን እኛም ንጽሕት ነሽ ክብርት ነሽ እያልን በፊቷ እየተማለልን በሥዕሏ ፊት ቆመን እንማፀናታለን (ሉቃ ፩፥፴፱፤ ፵፩-፵፫፤ ፵፱)።

ለምሳሌም ያኽል በፊቷ ሲማለሉ ከነበሩ ቅዱሳን አበው መኻከል የነበረው አባ ይስሐቅ እመቤታችንን በፍጹም ልቡናው ከመውደዱ የተነሣ ከሠርክ ጸሎት በኋላ ሌሎች መነኮሳት ለመኝታ ወደ የበአታቸው ሲኼዱ ርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመኼድ በቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ፊት ቆሞ በፊቷ እየተማለለ ሦስት መቶ ስግደት እየሰገደ፤ በእያንዳንዱ ስግደቱ ላይ *"ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አርእየኒ እመከ አሐተ ሰዓተ"* (ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለአንዲት ሰዓት እናትኽን አሳየኝ)[14] እያለ በመጸለይ ለሰባት ዓመት ከቆየ በኋላ፤ በሰባተኛው ዓመት በታላቅ ግርማ ተገልጻለት እመ አምላክን ለማየት በቅቷል፤ ርሷም ምን እንደሚሻ ብትጠይቀው በታላቅ መንፈሳዊ ደስታ በመኾን የንግሥተ ሰማይ ወምድር የርሷን ገጽ ያዩ ዐይኖቹ ሌላ ማየት እንደማይፈልጉና ከልጇ እንድታማልደው ብቻ እንደሚፈልግ ነግሯት፤ ርሷም ከሦስት ቀን በኋላ እንደሚያርፍ ክፍሉም ከርሷ ጋር መኾኑን ገልጻላት ባርካው ዐርጋ፤ በሦስተኛው ቀን ይኽ ቅዱስ አባት አርፏል።

በመኾኑም እያንዳንዱ የተዋሕዶ ምእመን በፍቅሯ በጣዕመ ፍቅሯ ጸንቶ በፍጹም ተመስጦ *"እዌድሰኪ ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ መጠነ ይክል አፉየ አስተበፅዐ እበየኪ፤ ልሳነ ኪሩቤል ኢይክል አብጽሖ ውዳሴኪ ወአፈ ሱራፌል ኢይፈጽም ነገረ ዕበየኪ ማርያም"*

(ክብር ምስጋናን የተመላሽ ድንግል ሆይ አንደበቴ የሚችለውን ያኽል አንቺን እየመሰገንኹ ገናንነትሽን እደነቃለኍ፤ እመቤታችን ሆይ የኪሩቤል አንደበት ምስጋናሽን ማድረስ አይቻለውም የሱራፌልም አንደበት ገናንነትሽን ተናግሮ አይፈጽመውም)[15] እያለ በፊቷ ዘወትር

[14] ተአምረ ማርያም ገጽ ፻፷፩

[15] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ መጽሐፈ ሰዓታት ገጽ ፲፱





በጸሎት ይማለላል።

ክቡር ዳዊት በመቀጠል *"ኵሉ ክብራ ለወለተ ንጉሥ ሀሴቦን"* (ለሀሴቦን ንጉሥ ሴት ልጅ ኹሉ ክብርዋ ነው) በማለት የንጉሥ ዳዊት የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ የኾነች የእመቤታችን ክብሯ አፍአዊ፣ ምድራዊ ሳይኾን መንፈሳዊና ዘላለማዊ መኾኑን ካስረዳ በኋላ *"በዘአዝፋረ ወርቅ ዑጽፍት ወኁብርት"* (በወርቅ ዘቦ ልብስ የተጐናጸፈችና የተሸፋፈነች ናት) በማለት በወርቅ የተመሰለ ንጽሐ ሥጋ፤ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡናን አስተባብራ የተገኘች እንደኾነች ገልጦ

*"ወይወስዱ ለንጉሥ ደናግለ ድኅሬሃ ወቢጻሂ ይወስዱ ለከ"* (በኋላዋ ደናግሉን ለንጉሡ ይወስዳሉ፤ ባልንጀሮችዋንም ወደ አንተ ያቀርባሉ) ሲል ባልንጀሮቿ በማለት በስም ደናግል የተባሉ ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ለንጉሥ ክርስቶስ ማደራቸው ተገልጾለት አስተምሯል።

ይኽ ብቻም ሳይኾን *"ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ"* (በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ) በማለት ንጽሕናዋን ቅድስናዋን ዘላለማዊ ድንግልናዋን በትንቢት ስለተናገሩ ስለ ዐበይት ነቢያት ፈንታ ደቂቅ ነቢያት፤ ስለ ደቂቅ ነቢያት ፈንታ ክብሯን ወላዲተ አምላክነቷን በስብከት የሚያስተምሩ ሐዋርያት፤ ስለ ሐዋርያት ፈንታም ሰብዓ አርድእት፤ ስለ ሰብዓ አርድእት ፈንታ ሊቃውንት ተተክተው እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ አማላጅነቷን፣ የአምላክ እናትነቷን ሲመሰክሩላት የሚኖሩ መኾናቸውን ከገለጸ በኋላ

*"ወትሠይሚዮሙ መሳእክተ ለኵሉ ምድር"* (በምድርም ኹሉ ላይ ገዢዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ) በማለት የሠያሚ ነገሥት፣ የሠያሚ ካህናት የክርስቶስ እናት መኾኗንና፤ ይኽነንም የአምላክ እናትነቷን ለመሰከሩ ለነ ደቅስዮስ ወንበር፤ ለነ ኒቆላዎስ ዐጽፍ፣ ለነ ቅዱስ ኤፍሬም "አንገዘ እግዚአ መዋግደ ጸጋከ" (አቤቱ የጸጋኽን ማዕበል ግታው፤ ወስነው) እስኪሉ ድረስ በቃል ኪዳኗና በአማላጅነቷ ከልጇ ያሰጠቻቸው ታላቅ በረከት መንፈሳዊ ሹመትና ብቃት መኾኑን ያሳያል።

*"ወይዘከሩ ስመኪ በኵሉ ትውልደ ትውልድ"* (ለልጅ ልጅ ኹሉ ስምሽን ያሳስባሉ) በማለት በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በርሷ ወላዲተ



www.ethiopianorthodox.org

አምላክነት በማመን የጸና ያለፈው የሚመጣው ትውልድ ኹሉ "ሰአሊ ለነ ቅድስት" (ቅድስት ሆይ ለምኝልን) እያለ የተቀደሰ ስሟን ሳይጠራ የሚውል ማንም እንደማይኖር ቅዱስ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ገላጭነት ተናግሯል። (መዝ ፵፬፥፲-፲፯)

ይኸነን በትውልድ ኹሉ የሚደረገውን ታላቅ ምስጋናዋን ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ ሲገልጽ

*"ወኵሎሙ ማኅበረ መላእክት ይዌድሱኪ እስመ ተመሰልኪ በሥርዐተ ንጽሕኪ ምስሌሆሙ፤ ወኵሎሙ ማኅበረ ነቢያት ይዌድሱኪ እስመ ብኪ ተሠልጠ ትንቢቶሙ፤ ወኵሎሙ ማኅበረ ሐዋርያት ይዌድሱኪ እስመ ወልድኪ ተኣነዎሙ ወመዋርስተ መንግሥቱ ረሰዮሙ፤ ሰማዕት ሠናያን መዊዕ ይዌድሱኪ እስመ ሱታፌ ሕማሙ ለወልድኪ ጸሩ በሥጋሆሙ፤ ደናግል ወመነኮሳት ይዌድሱኪ እስመ በአርአያ ንጽሕኪ በዕፀ ሕይወቶሙ፤ ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት ይዌድሱኪ እስመ ሥልጣነ አፉሁ ለወልድኪ ተሰውጠ ውስተ አፉሆሙ፤ ቀሲሳን ሥዩማን ይዌድሱኪ እስመ ሊቀ ኮነ ወልድኪ ለሥርዌ ክህነቶሙ፤ ዲያቆናት ሠናያን ሩጸት ይዌድሱኪ እስመ ኮኑ ላእካነ ለምስጢረ መለኮተ ወልድኪ፤ አናጕንስጢስ ወመዘምራን ይዌድሱኪ እስመ ለስብሐተ ወልድኪ ከመ ጸናጽላት ይደምፁ በውስተ ቤተ መቅደስ፤ ወኵሎሙ ማኅበረ ክርስትያን ይዌድሱኪ እስመ ለብሱ ሰንዱነ ጥምቀት ዘእማየ ገቦ ወልድኪ"*

(የመላእክት አንድነት ኹሉ ያመሰግኑሻል፤ በንጽሕና ሥርዐት እነርሱን ትመስያለሽና፤ የነቢያት አንድነት ኹላቸው ያመሰግኑሻል ተስፋ ትንቢታቸው እውን ኾኖ በአንቺ ተፈጽሟልና፤ የሐዋርያት አንድነት ኹላቸው ያመሰግኑሻል የተወደደ ልጅሽ ወንድሞችን አድርጓቸዋልና፤ ድሰ መልካሞች ሰማዕታት ያመሰግኑሻል የልጅሽ መከራ አንድነት በሥጋቸው ተሸክመዋልና፤ ደናግልና መነኮሳት ያመሰግኑሻል ሕይወታቸውን ለንጽሕናሽ ምሳሌ ብዕዐት አድርገዋልና፤ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት ያመሰግኑሻል የልጅሽ አንደበት ሥልጣን በአንደበታቸው ተዋሕዷልና፤





ሹማምንት ቀሳውስት ያመሰግኑሻል ለማዕርገ ክህነታቸው ልጅሽ አለቃ ኾነዋልና፤ አንባቢዎችና መዘምራን ያመሰግኑሻል ልጅሽን ለማመስገን እንደ ወርቅ ጸናጽሎች ይጮኻሉ፤ የክርስቲያን አንድነት ኹላቸው ያመሰግኑሻል ከልጅሽ ጐን ከፈሰሰው ውሃ የጥምቀት መጐናጸፊያን ለብሰዋልና)[16] በማለት ዳዊት አስቀድሞ በትንቢቱ እንደተናገረ ፍጥረት ኹሉ የፈጣሪውን እናት ብፅዕት እያለ የሚያመሰግናት መኾኑን አስተምሯል።

## የእግዚአብሔር ከተማ

ነቢዩ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንደሚያበሥርና ርሷም የአምላክ ማደሪያ እንደምትኾን ተገልጾለት

*"ፈለግ ዘይውሕዝ ያሠተፌስሕ ሀገረ እግዚአብሔር"* (የሚፈስስ ወንዝ የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኛል) በማለት ወንዝ ከላይ ወደታች እንዲፈስ ኹሉ ከሰማይ ወደ ምድር የወረደ ቅዱስ ገብርኤልም የእግዚአብሔር ሀገር እመቤታችንን "ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ" ብሎ ልዩ ብሥራትን ነግሮ ደስ የሚያሰኛት መኾኑን ተናግሯል (መዝ ፵፭፥፬-፮)።

የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ፤ መልአኩ ከላይ እንዴት እንደመጣ ቅድስት እመቤታችንንም እንዴት ደስ እንዳሰኘ ሲጽፍ

*"What reason has summoned the watcher for His descent..."*

(መልአኩን በፊቱ መላክ ለምን አስፈለገው? ቢሉ ብላቴና እናቱ የመውረዱን ነገር፤ ያለጋብቻ በማሕፀኗ መፀነሷን ሳትሰማ እንዳትቀር ነዋ፤ በዚኽም ምክንያት በድንግልና ስለምትወልደው፣ ስለምታዝለው፣ ስለምትሸከመው ልጅ ለእመቤታችን ያሳውቃት ዘንድ መልአኩን ላከ፤ ከመላእክቱ መኻከል አንዱ ትእዛዙን ተናገረ፤ ርሱም በመንገዱ እንዳይዘገይ በፈጣን ክንፎቹ ቸኰለ፤ ገብርኤል የተናገራቸው ቃላት የተሰወሩ ናቸው፤ በልዑል ጌታ በምስጢር ተነግረዋልና፤ መላኩ ብቻ

[16] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ፤ ምዕ ፲፱፥፳፮-፴፩

www.ethiopianorthodox.org

በመጽሐፍ ተጻፈልን፤ ግን እንዴት ባለኹኔታ እንደተናገረ አልተጻፈልንም፤ መልአኩ የሚያውቀውን ኹሉ ለምታምነው ሴት አስተማረ፤ የሰማውንም ለተባረከችው ሴት ነገረ፤ ይኽም መልአክ በንጉሡ የታወጅውን ይዞ ኼደ፤ ከሰማያት ኃይላት በላይ ፈጥኖ ኼደ፤ ከመሰብሰባቸው በላይም ተነጠቀ ግን አልተከለከለም፤ ፈጥኖ ከመላእክቱ ኅብረት ተለይቶ ተነሣ አልዘገየም፤ ፈጣን ነፋስ ላይ ወጣ፤ በነበልባል መንገዶች ውስጥም ዐለፈ፤ የመላእክትን ኅብረት ባሉበት ትቶ ወደ ምድር ወረደ፤ ከልዑል ቦታ ወርዶ ወደ እመቤታችን ማርያም ቀርቦ ራሱንም ዝቅ አደረገ፤ መልአኩ የንጉሡን እናት ሲመለከት ራሱን ዝቅ አደረገ፤ መልእክቱን ተናገረ በጸጥታም መልሱን ጠበቀ፤ ሰላም የመላበት መልእክቱን አስተላለፈ፤ በምስጢር ምስጢር ኾኖ የተጻፈውን ከፍቶ በርቱዕ አንደበቱ በፊቷ አነበበ፤ ከሴቶች ኹሉ የተባረክሽ ለኾንሽ ላንቺ ሰላም ይኹን፤ እነሆ ጌታዬ ካንቺ ጋር ነው አላት... እመቤታችን ከመልአኩ ገብርኤል ጋር እንዲኽ እየተነጋገረች የቆመችበት ያ ጊዜ በድንቅ የተመላ ነው፤ አንዲት ከድኻ ቤት የወጣች ትሕት ልጅ እና አንድ መልአክ የምድርና የሰማይን ሰራዊት ስለሚያስታርቅ ጉዳይ በመደነቅ ተነጋገሩ)[17] በማለት አስደናቂውን የምሥራች ቃልን በማብሠር ደስ እንዳሰኛት አስተምሯል፡፡

ነቢዩ ዳዊትም በዚኽ ትንቢቱ ቅድስት ድንግል "የእግዚአብሔር ከተማ" በማለት የተናገረበት ምክንያት፤ ንጉሥ በከተማው እንዲኖር ኹሉ ጌታም ማሕፀኗን ከተማ አድርጎ ፱ ወር ከ፭ ቀን ሲመሰገንበት የሚኖር ነውና ነው፤ ከዚኽም የተነሣ ሊቃውንት በተለያዩ ድርሳናት ላይ ቅድስት ድንግል ማርያምን *ሀገረ እግዚአብሔር፤ ማኅደረ መለኮት፤ ጽርሐ ቅድሳቱ ለወልድ* (የወልድ የመመስገኛው አዳራሽ)[18] በማለት አመስግነዋታል፡፡

ክቡር ዳዊትም በመቀጠል "ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል" (ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ) በማለት ልዑል እግዚአብሔር ማደሪያው ቅድስት ድንግል ማርያምን የቀደሰ ማለት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ያጸና፣

[17] Jacob of Serugh on Nativity p48, On the Mother of God p 29

[18] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መጽሐፈ ሰዓታት፤ ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ድጓ ገጽ ፫፻፷፬





ያከበረ፣ የለየ መኾኑን በመንፈስ እግዚአብሔር በመታኘት ከተናገረ በኋላ "*እግዚአብሔር ውስተ ማእከላ ኢትትሀወክ ወይረድኣ እግዚአብሔር ፍጽመ*" (እንዳትታወክም እግዚአብሔር በመኻከልዋ ነው፤ እግዚአብሔርም ፈጥኖ ይረዳታል) በማለት እመቤታችን በዘመዷችዋ ፍዳ እንዳትያዝ እግዚአብሔር በማሕፀኗ ዐድሮ የሚረዳት የሚጠብቃት መኾኑን አስተምሯል፡፡

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በዘመዶቿ ፍዳ እንዳትያዝ ጌታ እንዴት እናቱን እንደጠበቀ ሲያስተምር

*"Our Lord descending to earth beheld all women..."* (አምላካችን ወደ ምድር ያሉትን ኹሉንም ሴቶች ተመለከተ፤ ከነርሱም መኻከል መልካም የነበረችውን ርሷን ርሱ ለራሱ መረጣት፤ መረመራት፣ ትሕትናን እና ቅድስናንም በርሷ ውስጥ አየ፤ ንጹሐ ልብ ያላትና አምላክዋን አጥብቃ የምትሻ ነፍስ ነበረች፤ የተቀደሰ ልብና የጥጹምነት ባሕርይ በሙሉ ነበራት፤ ስለዚኽም ርሱ ከኹሉ ይልቅ ንጽሕትና ቅን የኾነቺውን ርሷን ለራሱ መረጣት፤ ከስፍራው ወርዶ ከሴቶች ኹሉ መኻከል ብፅዕት በኾነችው በርሷ ዐደረ፤ ምክንያቱም ከርሷ ጋር የሚተካከል አንድ ስንኳ በምድር ላይ አልተገኘምና፤ ርሷ ብቻዋን ትሕት፣ ንጽሕት፣ ጽድልት እና መርገም (ኵነኔ) የሌለባት ናት፤ ስለዚኽም ሌላ ማንም ሳትኾን ርሷ ብቻ እናቱ ልትኾን የተገባች ኾነች፤ ከክፋት የራቀችና ከዐመፃ የጸዳች መኾኗን ርሱ ተመለከተ፤ በውስጧም አንድስ ስንኳ የረከሰ መሻት አለመኖሩን አየ፤ ምንም አይነት የቅንጦት ሐሳብ የላትም፤ በጭካኔ የሚጐዳ ዓለማዊ ምክርም የለባትም፤ የምድራዊ ኵራት መሻትም በርሷ ውስጥ አይነድም፤ ልቧም በተራና በርካሽ ነገሮች አልተያዘም፤ ርሷን የሚመስል ከርሷም ጋር አቻ የሚኾን በምድር ኹሉ አለመኖሩን ዐይቶ፤ እናት ትኾነው ዘንድ እና መልካም ወተት ይጠባ ዘንድ ርሷን መርጦ ወሰዳት፤ ርሷ በእግዚአብሔር ፍቅር የተመላች እና አስተዋይ ነበረች፤ ምክንያቱም አምላካችን ፍቅር በሌለበት ስፍራ አያድርምና፤ ታላቁ ንጉሥ ወደኛ ይመጣ ዘንድ በወደደ ጊዜ፤ ከምድሪቱ ኹሉ ንጹሕ በኾነውና ርሱን ደስ ባሰኘው ማደሪያ ዐደረ፤ በድንግልና ባጌጠውና አንዳች እንከን ባልነበረው ማሕፀን ዐደረ፤ ቅድስናን የሚያጐድል አንዳች ሐሳብም በዚኽ ማሕፀን አልነበረም፤ በተፈጥሮ (በባሕሪዋም) በፊታድዋም ከኹሉ ይልቅ መልካም ነበረች፤ ምክንያቱም ደስ በማያሰኙ ፍላጎቶች ክፉ ያልረከሰች ነበረችና፤ ከሕፃንነቷ ገርምራ ኵነኔ በሌለበት እውነተኛ ታማኝነት ጸንታ ቆማለች፤ ከሕገጋቱ ሳትተላለፍም በዚኹ መንገድ ተጓዘች፤ ቀድሞውኑ የነበረው



www.ethiopianorthodox.org

ተፈጥሮዋ መልካም የኾነውን ብቻ በማሻ ፈቃድ ተጠብቆ ኖረ፤ ምክንያቱም በአካሏ ውስጥ የድንግልና ማረጋገጫዎች (መገለጫዎች)፤ በነፍሷም ውስጥ የተቀደሱ ነገሮች ኹል ጊዜ ነበሩና)[19] በማለት በንጽሕና በቅድስና የተጌጠች፤ አስቀድሞ ዳዊት እንደተናገረው ባለቤቱ እግዚአብሔር በዘመዶችዋ ፍዳ እንዳትያዝ የጠበቃት መኾኑን ሊቁ በማራቀቅ አመስጥሮታል።

በተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለዳዊት የራቀውን አቅርቦለት የረቀቀውን አጕልቶለት ጊዜው ሳይደርስ እንደደረሰ ጊዜው ሳይቀርብ እንደቀረበ ኹኖ የአምላክ ሥጋዌ ተገልጾለት *"በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ"* (እንደ ሰማን እንዲኹ ዐየን) በማለት ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ሲሉ እንደሰማን ከእመቤታችን ተወልዶ ዐየነው፤ *"በሀገረ እግዚአ ኃያላን በሀገረ አምላክነ እግዚአብሔር ሣረራ ለዓለም"* (በሰራዊት ጌታ ከተማ፣ በአምላካችን ከተማ፣ እግዚአብሔር ለዘላለም ያጸናታል) ሲል በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ለዘላለም ከጸናች ከሀገረ እግዚአብሔር ከድንግል የመወለዱን ደረቅ ሐዲስ የኾነ ትንቢታዊ ኀይለ ቃልን ተናግሯል (መዝ ፵፯፥፰)።

## ክንፈ ርግብ

ሰባት ሀብታት የተሰጡት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በምድረ ርስት በኢየሩሳሌም ላይ የተገኘች በየዋህነቷ በርግብ የምትመሰል ቅድስት ድንግልን ክንፎቿ በብር በተሠሩ ጕኖቿም በወርቅ በተሸለሙ በርግብ አምሳል በመንፈስ እግዚአብሔር ተመልክቶ በመዝ ፷፯፥፲፫ ላይ

*"እመኒ ቤትክሙ ማዕከለ መዋርስት"* (በርስቶች መኻከል ብታድሩ) በማለት ቀድሞ ኖኅ ለልጁ ለሴም ባወረሰው ኋላም ለአብርሃም ወደ ተሰጠው ወደ ሴም ዕፃ ብትደርሱ *"ክንፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር"* (ከብር እንደተሠሩ እንደ ርግብ ክንፎች) በማለት በዚያች የሴም ርስት ውስጥ በየዋህነቷ በርግብ የተመሰለችው ቅድስት ድንግል ማርያምን ክንፎቿ በብር በተሠሩ ርግብ አምሳል ማለት የሥጋዋን የነፍሷንና የሕሊናዋ ንጽሕናን በብር በተሠሩ ክንፎች አምሳል ማየቱን ከገለጸ በኋላ ፡-

*"ወገበዋቲሃኒ በሐመልማለ ወርቅ"* (ወገቦቿም በወርቅ ቅጠል የተሠሩ) በማለት በወርቅ የተመሰለ ወገበ ልቡናዋ "እንደ ቃልኽ

[19] Jacob of Serugh, on the mother of God pp. 23-25





ይኹንልኝ" በማለ የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት በማመን የጸና መኾኑን በምስጢር ከገለጸ በኋላ እናቱን እንዲያበሥር ባዘዘው በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ሰማያዊ ንጉሥ ጌታ በየዋህነቷ በርግብ ከተመሰለችው ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ድኅነትን እንደሚያደርግ *"አመ አዘዘ ሰማያዊ ንጉሥ ላዕሌሃ"* (ሰማያዊ ንጉሥ በላይዋ ባዘዘ ጊዜ) በማለት የተናገረው ትንቢታዊ ኀይለ ቃል በእጅጉ አስደናቂ ነው።

ሊቃውንትም ይኽነን ምስጢር በመረዳት ቅድስት ድንግልን "ርግበ ዳዊት" እያሉ ሲያመሰግኗት፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም የዳዊትን ዝማሬ መሠረት በማድረግ *"ክንፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ሰላም ለኪ፤ ወገበዋቲሃኒ በሐመልማለ ወርቅ ሰላም ለኪ"* (በብር የተሠራሽ የርግብ ክንፍ ሰላምታ ይገባሻል፤ ወገቦቿም በወርቅ ቅጠል የተሠሩ ሰላምታ ይገባሻል)[20] በማለት እመቤታችንን እስከ ዕለተ ምጽአት ታመሰግንበታለች።

እንዲኽ ብላም ምስጋናን ከምታቀርብ በልጇ ደም ከተመሠረተ ችውና የሲኦል ደጆች ከማያነዋውጿት ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ ወላዲተ አምላክነቷን ከምትመሰክር ቤተ ክርስቲያን "ርግበ ዳዊት" የተሰኘች ቅድስት ድንግል ማርያም እንደማትርቅ፤ አባ ጽጌ ድንግልንና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ

*"ተንሥኢ ወንዒ ያሬ ገነት እምአድባር ከርቤ ወዐልው*
*ወሐውጺ ቤተ ክርስቲያን እንተ መሳክው*
*ርግበ ተኀብዮ ማርያም ዘተአምርኪ ፍትው*
*ክንፍኪ ርሱይ በጽጌ ብሩር ጽዕድው*
*ወበጽጌ ወርቅ ሐመልሚል ገቦኪ ሥርግው"*

(የገነት ፆፍ ድንግል ሆይ፤ ከሽቱዎች ኹሉ ከሚበልጡ ከርቤና ዐልው ከአሉባቸው ተራራዎች ተነሥተሽ ነዪ፤ ታምርሽም ያማረ የተወደደ የትንቢት ርግብ ማርያም የብርሃን መስኮት ያለባት ቤተ ክርስቲያንን ጎብኚ፤ ክንፍሽ ነጭ መልክ ባለው ብሩማ አበባ ያጌጠ ነው፤ ጕንሽም ቢጫና አረንጓዴ በመሰለ ወርቅ አበባ የተሸለመ ነው)[21] በማለት ምስጢሩን

[20] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መጽሐፈ ሰዓታት ገጽ ፹፮

[21] አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቊ ፲፫



www.ethiopianorthodox.org

በማራቀቅ ተርጕመውታል።

የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ከዳዊት መዝሙር በመነሣት በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*"ዖሬ ትንቢት አንቲ በብሩር ዘግቡር አክናፊሃ*
*ወበሐመልማለ ወርቅ ጽሩይ ወግሉፍ ገበዋቲሃ*
*ዘሐለዩ ላቲ ደቂቀ ቆሬ ለጽዮን በአናቅጺሃ"*

(የቆሬ ልጆች ጽዮንን በደጃፎችዋ ያመሰገኗት፣ ጕኖቿ በጠራ የወርቅ ሐመልማል የተቀረጹና ክንፎቿም በብር የተሠሩ የትንቢት ዖፍ አንቺ ነሽ)[22] በማለት ሲያስተምር፣ ይኸቺ በዳዊት መዝሙር በርግብ አምሳል የተገለጸች የቅድስት ድንግል ማርያምን በረከቷን በመፈለግ በመጽሐፈ ሰዓታቱ ላይ በድጋሚ፦ *"ንዒ ኀቤየ ኦ ድንግል ምስለ ዳዊት አቡኪ መዘምር ዘሐለየኪ እንዘ ይብል ክንፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር"*

(ድንግል ሆይ በብር የተሠራ የርግብ ክንፍ ነሽ ብሎ ካመሰገነሽ ካባትሽ ከዳዊት ጋር ወደኔ ነዪ) በማለት ሲያመሰግናት፣ ይኸው ሊቅ በዚኽ ሳያበቃ በአርጋኖን መጽሐፉ ላይም፦ *"ተፈሥሒ ኦ ርግብ ጸዐዳ ክንፊሃ በብሩር ዘግቡር ወገበዋቲሃኒ በሐመልማለ ወርቅ ዕጽፍት ወሐብርት"*

(ጕኖቿ በወርቅ ዐመልማሎ ተሸልመው የተጕናጸፉላት፣ ክንፎቿም በብር የተሠሩላት ነጭ ርግብ ሆይ ደስ ይበልሽ)[23] ሲል በየዋህነቷ በርግብ የተመሰለችው የቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ ድንግልናዋን እነ ዳዊት እነ ሰሎሞን በወርቅ መስለው የተናገሩላት መኾኗን መስክሯል።

እመቤታችን በርግብ፣ በክንፍ መስለው የተናገሩ ነቢያት ብቻ ሳይኾኑ፣ ከሐዋርያት መኻከል ዮሐንስ በራእዩ ላይ "ዘንዶውም ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት፤ ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፣ ዘመናትም፤ የዘመንም እኩሌታ ወደምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሓ እንድትበር ለሴቲቱ ኹለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት" በማለት በዘንዶ የተመሰለ ዲያብሎስ በእባብ በተመሰለ በሄሮድስ ዐድሮ አምላክን የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምን ወደ ግብጽ በረሓ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር እንድትሰደድ ሲያደርግ ማሕደረ መንፈስ ቅዱስ ለኾነቿው ለእመቤታችን በኹለት የንስር ክንፎች የተመሰሉ ንጽሐ ሥጋና ንጽሐ ነፍስ የተሰጣት መኾኑን አስተምሯል (ራእ ፲፪፥፲፫-፲፬)።

[22] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 3፤ መጽሐፈ ሰዓታት ገጽ ፲፱
[23] አርጋኖን ዘንሙስ፤ ምዕ ፴፲፫





## ዐዲሲቱ እንቦሳ

በክቡር ደሙ ፈሳሽነት ዓለምን ያዳነ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሚሸልቱት ፊት ዝም እንደሚል በግ አፉን ያልከፈተ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስን ስለምትወልድ ስለቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጾለት

*"አሠምሮ ለእግዚአብሔር እምላሕም ጣዕዋ ዘኢያብቈለ ቀርነ ወጽፍረ"* በማለት ቅድስት ድንግል በእምቦሳ፤ መሥዋዕት ኾኖ የቀረበ ልጇን ቀንድና ጥፍር ባለበቀለ በላሕም መስሎ ተናግሯል (መዝ ፷፰፥፴፩)።

ይኽነን የዳዊትን ቃል ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በአርጋኖን መጽሐፍ ላይ በጥልቀት ሲተረጕም

*"ወኢረከበ ሰይጣን ወኢምንተኒ ምክንያተ በላዕሌሁ ወበእንተዝ ይቤ ዳዊት አሠምሮ ለእግዚአብሔር አምላሕም ጣዕዋ ዘኢያብቈለ ቀርነ ወጽፍረ፤ ላሕመ እንከ ሰመዮ ለወልደ እግዚአብሔር ወጣዕዋኒ ሰመያ ለቅድስት ድንግል ወዘይቤሰ ዘኢያብቈለ ቀርነ ወጽፍረ በእንተ ዘአልቦቱ ትዕግልተ ውስተ እዴሁ ወኢክበደ ኀጢአት ዲበ ርእሱ አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ኢየሱስ ናዝራዊ ወልደ ቅድስት ጣዕዋ አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ወላሕም መግዝእ ዘኢይትዌዳእ ጕብሉ አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ዘይቄድሶሙ ለእለ በልዕዎ ወይሬስዮሙ ብሁዓነ ለእለ ነሥዕዎ፤ አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ዘተሠውዐ በእደ ዕብራውያን፤ አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ዘተሠውዐ በእደ አይሁዳዊ አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ዘኢይትኄየል በቀርኑ በቅድመ እለ ይረግዝዎ ወበግዕ ነባቢ ዘኢየውሥዐ ቃለ በቅድመ እለ ይቀርጽዎ (ኢሳ ፶፫፥፯) አማንኬ መሥዋዕት ንጹሕ ዘኒ በልዐ እምሥጋሁ ኢይመውት ወዘኒ ሰትየ እምደሙ ኢይማስን"*

(ሰይጣን በርሱ ላይ ምንም ምክንያት አላገኘም፤ ስለዚኽም ዳዊት እንዲኽ አለ ከባለቀንድና ሰኰናው ከተሰነጠቀ በሬ ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘዋለኊ (መዝ ፷፰፥፴፩)፤ የእግዚአብሔርን ልጅ ላም (ወይፈን) ብሎ ጠራው፤ ቅድስት ድንግልንም እምቦሳ ብሎ ጠራት፤ ቀንድና ጥፍር ያላበቀለ ብሎ የተናገረው ንጥቂያ በእጁ በራሱም ላይ ኀጢአት ስለሌለበት ነው ፤ የንጽሕት እምቦሳ ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ በእውነት ንጹሕ የተወደደ መሥዋዕት ነው፤ መሥዋዕትነቱ የማያቋርጥ ፍሪዳነቱ የማያልቅ ንጹሕ ላም እውነተኛ መሥዋዕት ነው፤ የበሉትንም የሚቀድሳቸው የተቀበሉትንም ኀይላን ክቡራን የሚያደርጋቸው ርሱ በእውነት ንጹሕ መሥዋዕት ነው፤ በሚወጉት ፊት በቀንዱ የማይበረታታ የንጹሕ መሥዋዕት ላም በሚሸልቱት በአይሁድ ፊት ምላሽ ያልሰጠ ነባቢ በግዕ



www.ethiopianorthodox.org

እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው (ኢሳ ፶፫፥፯) ከሥጋው የበላ አይሞትም ከደሙም የጠጣ ጥፋት አያገኘውም እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነውና)[24] በማለት ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን ምግበ ርትባን ስቴ ጽሙኣን ላሕም ወልደ እግዚአብሔርን ያስገኘችልን ዐዲሲቱ ዕንቦሳ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን በጥልቀት አስተምሯል፡፡

ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በመጽሐፈ ድጓው ላይ ምስጢሩን በመጠቅለል "ይዌድስዋ መላእክት ለማርያም በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ፦ (ድንግል ማርያምን መላእክት በመጋረጃ ውስጥ ኾነው ያመሰግኗታል፤ ዐዲሲቱ እንቦሳ ማርያም እያሉም ሰላም ይሏታል)[25] በማለት ማኅበረ መላእክት በመላ የፈጣሪያቸውን እናት በዚኽ ቃል እንደሚያመሰግኗት አስተምሯል፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በመጽሐፈ ሰዓታቱ ላይ በዳዊት ቃል ሲያመሰግናት

"ኵሎን አዋልዲሃ ለሔዋ
በምግባረ ሠናይ እለ ተሰርገዋ
እምንዋመ ሀኬት እለ ጽሕዋ
ዕበያተኪ ዜነዋ
ተፈሥሒ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ"

(ከስንፍና እንቅልፍ የነቁ በመልካም ምግባር ያጌጡ የሔዋን ልጆች በመላ፤ ዐዲሲቱ እንቦሳ ማርያም ደስ ይበልሽ እያሉ ገናንነትሽን ተናገሩ)[26] በማለት ምእመናን ኹሉ መድኀኒታቸው ክርስቶስን የወለደችላቸው ቅድስት ድንግል ማርያምን የሚያመሰግኑአት መኾኗን አስተምሯል፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በእንቦሳ መስሎ የገለጸ ክቡር ዳዊት ብቻ ሳይኾን ነቢዩ ኢሳይያስም በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በትንቢቱ በምዕ ፯፥፳፩-፳፪ ላይ፡- "በዚያም ቀን እንዲኽ ይኾናል ሰው ከላሞቹ አንዲት ጊደርንና ኹለት በጎችን ያሳድጋል የአንዲት በግ ወተትም ኹለት ሰዎችን ያጠግባል ወተትም ይበዛል በሀገሪቱም መኻከል የቀረ ኹሉ ቅቤና ማር ይበላል" በማለት እመቤታችንን በእንቦሳ መስሎ የተናገረውን ሊቃውንትም የነቢያትን ትንቢቶች በተረጐሙበት መጽሐፈ ፀሓይ በሚለው መተርጕመ መጻሕፍት የኢሳይያስን ትንቢት ሲተነትኑ

[24] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ አርጋኖን ዘሰኑይ ምዕ ፲፥፴፮-፵፫
[25] ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ ገጽ ፻፶፹፪፣ መዋሥዕት ዘእግዝእትነ ማርያም ገጽ ፶፬
[26] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ መጽሐፈ ሰዓታት ገጽ ፷፫





"ኢሳይያስኒ ይቤ ይእተ አሚረ ያመገዝዕ ሰብእ ዕጐልተ እምውስተ አልሕምት ወክልኤ እምውስተ አባግዕ ወይበዝኀ እንከ ሐሊብ ዘውስተ ምድር ወይሴሰዩ መዐረ ወቅብዐ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር፤ ሰብእሰ ክርስትያን አሙንቱ ወዕጐልትኒ ማርያም ይእቲ ወአልሕምትኒ አበው ቀደምት እሙንቱ ወክልኤ አባግዕሰ ሐዲስ ወብሉይ ሀሊብሰ ትምህርተ ወንጌል ወመዐርኒ ትምህርተ ኦሪት ወቅብዕኒ ማየ ጥምቀት ወምድርኒ ቤተ ክርስትያን ይእቲ ወእለኒ ይነብሩ ውስቴታ ክርስትያን እሙንቱ"

(ኢሳይያስ እንዲኽ ይላል ያን ጊዜ ሰው ከላሞች መኻከል እምቦሳን ያደልባል፤ ከበጎች መኻከልም ኹለቱን፤ እንግዲኽ በምድር ውስጥ ወተት ይበዛል፤ በምድር የሚኖሩ መዐርንና ቅቤን ይመገባሉ፤ ሰዎች የተባሉት ክርስቲያኖች ናቸው፤እምቦሳም የተባለች ማርያም ናት፤ በአልሕምት የተመሰሉት ቀደምት አበው ናቸው፤ በኹለት አባግዕ የተመሰሉትም ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ናቸው፤ በወተት የተመሰለ ትምህርተ ወንጌል ነው፤ በማር የተመሰለ ትምህርተ ኦሪት ነው፤ ቅብዕ የተባለው የጥምቀት ውሃ፤ ምድርም የተባለች ቤተ ክርስቲያን ናት፤ በውስጧም የሚኖሩ ክርስቲያን ናቸው)[27] በማለት ሲያስተምሩ፤ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በድጓው ላይ "ኢሳይያስ ይቤ ሐዳስዩ ጣዕዋ" (ኢሳይያስም ዐዲሲቱ እንቦሳ አንቺ ነሽ አለ)[28] በማለት አስተምሯል፡፡

ይኽነንም የምስጢር አንድነት ስናይ ለኹሉም ቅዱሳን አበው የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር የገለጠ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እናመሰግናለን፡፡

## ፀምረ ዳዊት

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ለጊዜው ለልጁ ለንጉሥ ሰሎሞን፤ ፍጻሜው ግን ለሰማይና ለምድር ንጉሥ ለክርስቶስ የኾነ ታላቅ የሥጋዌ ምስጢር ተገልጾለት በመዝ ፸፩፥፮ ላይ

"ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር" (እንደ ጠል (ዝናም) በባዘቶ ላይ ይወርዳል) በማለት ጠል ምሳሌው የኾነ የሕይወት ውሃ፣ የሕይወት ዝናም የተባለ አካላዊ ቃል ክርስቶስ፤ ፀምር ምሳሌዋ በኾነች በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን የሚያድር መኾኑን ከገለጠ በኋላ፡ ይኽነኑ በማጉላት "ወከመ ነጠብጣብ ዘያንጠበጥብ ዲበ ምድር" (በምድርም ላይ

[27] መጽሐፈ ፀሓይ፣ ገጽ ፲፮
[28] ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል) በማለት ለስ ብሎ የሚንጠባጠብ ጠብታ ዝናም ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ አማናዊ ንጹሕ ዝናም የሚባል ጌታ፤ የተጠማች ምድር ምሳሌዋ በሚኾን በድንግል ማሕፀን ፱ ወር ከ፭ ቀን ማደሩን በምሳሌያዊ አገላለጽ አስተምሯል።

እመቤታችንን በፀምር፤ አካላዊ ቃል ክርስቶስን ቤጠል መስሎ በምሳሌ ማስተማር መግለጥ ቀደም ያለ እንደኾነ "ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል አንድ" ብዬ በጻፍኹት መጽሐፍ ላይ "ንጽሕት መሰክ" በሚለው የዘዳግም ፴፪፥፩-፪ ትንታኔና፤ የጌዴዎንን ፀምር (ብዝት ግምጃ) በሚለው ክፍል በሰፋት የተነተንኩት ሲኾን፤[29] ዳግመኛም ጌታን በጠብታ፤ ድንግልን በተጠማች ምድር መስሎ መግለጽን በዚኸኛው የነገረ ማርያም መጽሐፍ ላይ በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ ፵፩፥፲፰ ትንታኔ ላይ በሰፊው የምናየው ሲኾን፤ የነዚኽ ኹሉ ቅዱሳን አበው የቃላቸው የምሳሌያቸውን ሕብረት ስናይ ያናገራቸው አንድ መንፈስ ቅዱስ መኾኑን እንረዳለን።

ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ይኽነን የዳዊትን ቃል በመጽሐፈ ምስጢር ላይ ሲተረጕመው፡- *"ዳዊትኒ ይቤ በእንተ ርደተ መለኮት ኀበ ማርያም ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር ወከመ ነጠብጣብ ዲበ ምድር ወይሠርጽ ጽድቅ በመዋዕሊሁ ወብዙኀ ሰላም እስከ የኀልፍ ወርኅ ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር ወእም አፍላግ እስከ አጽናፈ ዓለም ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሑ ነገሥተ ተርሴስ ወደስያት አምኃ ያበውኡ ነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያመጽኡ ናሁኬ አግሀደ ቃለ መዝሙር ርደተ ወልደ እግዚአብሔር ኀበ ማርያም ሶበ ይብል ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር ወከመ ነጠብጣብ ዘያንጠበጥብ ዲበ ምድር"*፡- (ዳዊት ስለ መለኮት ወደ ማርያም መውረድ፤ እንደ ጠል በፀምር ላይ ይወርዳል በምድርም ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ፤ በዘመኑም ጽድቅ ይበቅላል፤ ጨረቃ እስኪያልፍ ብዙ ሰላም ይኾናል፤ ከባሕር እስከ ባሕር ከወንዞችም እስከ ዓለም ዳርቻ ይገዛል፤ ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይገዛሉ ጠላቶቹም ዐመድ ይቅማሉ፤ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ አለ፤ እነሆ የዚኽ መዝሙር ቃል እንደ ጠል በፀምር ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታም በምድር ላይ ይወርዳል ባለ ጊዜ የእግዚአብሔር ወልድን ወደ ማርያም መውረድ ገለጠ)[30] በማለት

[29] መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፤ ነገር ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል አንድ፤ገጽ 143፤161

[30] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መጽሐፈ ምስጢር፤ ገጽ ፶፩





የዳዊት ትንቢት የተፈጸመባት የጠለ ሕይወት የክርስቶስ ማደሪያ ንጽሕት ፀምር መኾኗን መስክሯል።

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ስለዚኽ ምስጢር በመጽሐፈ ድጓው ላይ *"ዳዊትኒ ይቤ ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር፤ ፀምርሰ ይእቲ ማርያም"* (ዳዊትም እንደ ጠል በግምጃ ላይ ይወርዳል አለ፤ ፀምርም የተባለች ማርያም ናት)[31] በማለት ሲተረጕመው ዳግመኛም በመጽሐፈ ዝማሬው ላይ፡- *"ናስተበፅዖ እንዘ ንብል ግርምት ድንግል ሐዳስ ሐመር ዘኢቀርባ ማዕበል አማን ዘዳዊት ፀምር፤ ጽዋዐ መድኀኒት ተውህበ ላቲ በእደ መላእክት"*፡- (ማዕበል የማይቀርባት ዐዲሲቱ መርከብ ግርምት ድንግል እያልን እናመሰግናታለን፤ በእውነት የዳዊት ፀምር ናት፤ መድኀኒትነት ያለው ጽዋን ከመላእክት እጅ ለርሷ ተሰጣት) በማለት በዳዊት ፀምር የመመሰሏን ምስጢር በጥልቀት አስተምሯል።

## ደብረ ጽዮን

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ልዑል እግዚአብሔር ከሌሎች ሴቶች ይልቅ ከነገደ ይሁዳ የተወለደችውን የቅድስተ ቅዱሳን የድንግል ማርያምን ሥጋ ለመዋሐድ መምረጡን በመዝሙሩ ላይ

*"ወኀደጋ ለደብተራ ዮሴፍ ወኢኀረዮ ለሕዝበ ኤፍሬም"* (የዮሴፍን ድንኳን ተዋት፤ የኤፍሬምንም ወገን አልመረጠውም) በማለት ባሕርየ ዮሴፍን ከመዋሐድ እንደተለየትና ባሕርየ ኤፍሬምን ለመዋሐድ እንዳልመረጠው ከገለጸ በኋላ፤ ከዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል ውስጥ ከቤተ ይሁዳ የተወለደችው፤ ቃል ኪዳኗ አምባ መጠጊያ በመኾኑ በጽዮን ተራራ የተመሰለችው የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ ለመዋሐድ ወዶ እንደመረጠ ሲገልጽ *"ወኀረዮ ለሕዝበ ይሁዳ ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ"* (የይሁዳን ወገን ግን መረጠ፤ የወደደውን የጽዮንን ተራራ) በማለት ትንቢት ተናግሯል (መዝ ፸፯፥፷፯-፷፱)።

ከዚያም *"ሐነጸ መቅደሶ በአርያም ወሣረረ ውስተ ምድር ዘለዓለም"* (መቅደሱን በአርያም ሠራ፤ ለዘለዓለምም በምድር ውስጥ መሠረታት) በማለት ማደሪያው በመኾኗ በመቅደስ የተመሰለችው የወደዳት ቅድስት ድንግል ማርያምን ልክ እንደ አርያም በልዕልና ከፍ ከፍ ያደረጋትና፤ በዚኽ ምድር ካሉት በንጽሕና በቅድስና በጽናቷ ማሕፀን የፈጠራት መኾኗን ክቡር ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ

[31] ቅዱስ ያሬድ፤መጽሐፈ ድጓ፤ ገጽ ፻፺፯፤ ዝማሬ ዘማርያም፤ ገጽ ፻፳፬



www.ethiopianorthodox.org

ምስክርነቱን ሰጥቷል።

ይኽነን የዳዊት ቃል ትንቢት ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ከብሉያትና ከሐዲሳት መጻሕፍት ጋር እያስማማ፤ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከያዕቆብ ልጅ ከይሁዳ ነገድ ከተገኘች ከቅድስት ድንግል ተወልዶ የፈጸመው መኾኑን እያራቀቀ ሲገልጽ

*"ነጸረ እግዚአብሔር እምሥራቅ እስከ ዐረብ ወእምአዜብ እስከ መስዕ ወእምአጽናፍ እስከ አጽናፈ ዓለም ወርእየ ኅዕለ ኵሎሙ እለ ኅዱራን ዲበ ምድር ወኢረከበ ዘከመ ያዕቆብ ፤ወአዕረፈ ኀሊናሁ ላዕለ እስራኤል በከመ ጽሑፍ ዘይብል እስመ ለያዕቆብ ኀረዮ እግዚብሔር፤ ወካዕበ ጽሑፍ ዘይብል ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር፤ ወነጸረ ካዕበ እግዚአብሔር ላዕለ ተዓይነ ያዕቆብ እምነገደ ሮቤል እስከ ነገደ ብንያም ወአዕረፈ ኀሊናሁ ላዕለ ነገደ ይሁዳ፤ ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ ሐነጸ መቅደሶ በአርያም ወሣረራ ውስተ ምድር ዘለዓለም፤ ወኀረዮ ለዳዊት ገብሩ ወነጸሮ እንከ ላዕለ ቤተ ዳዊት ረከባ ለቅድስት ድንግል አፍቀረ ሥነ ዚአሃ ወፈተወ ላሕያ ወሠምረ መዐዛሃ ወአደመቶ እምኵሎሙ ዘመደ ዕጓለ እመሕያው በከመ ይቤ ዳዊት ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ እዝንኪ ርስዒ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ እስመ ውእቱ እግዚአብሔር እስመ ኢፈቀደ እግዚአብሔር ይትኣኀዎሙ ለኪሩቤል ወይትመሰሎሙ ለሱራፌል ወይኩኖሙ አርአያ ለትጉሃነ ሰማይ ኢፈቀደ ይሳተፎሙ ለእሳታውያን አላ ፈቀደ ይትማሰሎሙ ለመሬታውያን በከመ ይቤ ጳውሎስ ዘአኮ መላእክተ ተወክፈ አላ ዘርዐ አብርሃም አልዐለ ወፈቀደ ይትማሰሎሙ ለአኀዊሁ"*

(እግዚአብሔር ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከአዜብም እስከ መስዕ ከዓለም ዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ አየ፤ በምድር ላይ ወደሚያድሩት ኹሉ አየና እንደ ያዕቆብ ያለ አላገኘም (መዝ ፴፪፥፲፫)፤ ልቡናውም በእስራኤል ላይ ዐረፈ፤ የተጻፈው እንደተናገረ "እግዚአብሔር ያዕቆብን መርጦታልና" (መዝ ፻፴፬፥፪)፤ ዳግመኛም እንዲኽ የሚል ጽሑፍ አለ" ያዕቆብ የእግዚአብሔር ወገኖች እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ ኾነ" (ዘዳ ፴፪፥፬)፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር ወደ ያዕቆብ ከተማ ተመለከተ፤ ከሮቤል ነገድ ገርምሮ እስከ ብንያም ነገድ ደረሰ፤ ልቡናው በይሁዳ ነገድ ላይ ዐረፈ፤ ፈቃዱም በዳዊት ቤት ላይ ኾነ እንዲኽ የሚል እንደተጻፈ "የኤፍሬምን ወገን አልመረጠውም የይሁዳን ወገን መረጠው እንጂ፤ የጽዮንን ተራ ራ የወደደ መቅደሱን በአርያም ሠራ፤ አገልጋዩ ዳዊትን መረጠው"





(መዝ ፸፯፥፷፯-፷፱)፤ እንሆ ወደ ዳዊት ቤት ተመልክቶ ቅድስት ድንግልን አገኛት መልኳን አፈቀረ፤ ደም ግባቷን ወደደ፤ መዐዛዋን ፈቀደ ከሰው ልጆች ኹሉ ይልቅ አማረችው፤ ዳዊት በመዝሙር እንዲኽ ብሎ እንደተናገረ "ልጄ ሆይ ስሚ ተመልከቺም በጆሮሽም አድምጪ፤ ወገኖችሽንና የአባትሽን ቤት ርሺ ንጉሥ ደም ግባትሽን ወዷልና፤ ጌታሽ ፈጣሪሽ ርሱ ነውና" (መዝ ፵፬፥፲-፲፩)፤ የኹሉ ጌታ (ፈጣሪ) ኪሩቤልን ወንድማማች ይኾናቸው ዘንድ ሱራፌልንም ይመስላቸው ዘንድ አልወደደምና፤ ትጉሃን የሰማይ መላእክትን በመልክ ይመስላቸው፤ እሳታውያን መላእክትንም ይሳተፉቸው ዘንድ አልወደደም፤ መሬታውያንን ይመስላቸው ዘንድ ወደደ እንጂ ጳውሎስ እንደተናገረ እንዲኽ ሲል "መላእክትን የተቀበለ አይደለም የአብርሃምን ዘር ከፍ ከፍ አደረገ እንጂ ወንድሞቹን ሊመስላቸው ወደደ" (ዕብ ፪፥፲፩)[32] በማለት ይኽ የነገረ ማርያም ሊቅ አስፋፍቶ ተርጕሞታል።

## እውነትና ሰላም

ይኽ ነቢይ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በመዝ ፹፬፥፲-፲፫ ላይ "ምሕረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ፤ እውነት ከምድር በቀለች ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተ፤ እግዚአብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል፤ ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች" በማለት ሣሕል ጽድቅ የተባለች ኤልሳቤጥ፤ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ የሰላም አባት ክርስቶስን በመውለዷ ምክንያት "እውነት ሰላም" ከተባለቺው ከእመቤታችን ጋር በቤተ ዘካርያስ የመገናኘታቸውን ነገር ተገልጦለት ተናግሯል።

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ይኽ የኤልሳቤጥና የእመቤታችንን በቤተ ዘካርያስ የመገናኘታቸውን ነገር በድርሳኑ ሲገልጽ *"She diligently made straight for Elizabeth..."* (እመቤታችን ማልዳ ተነሥታ ቀጥታ ወደ ኤልሳቤጥ ኼደች፤ በዚያም አስደናቂ የኾነውን ዐዲስ ፅንስ ልታይ ወጣች፤ በእውነተኛው መልአክ የተነገራትን ኹሉ እመቤታችን ማርያም አጥብቃ አምናለችና፤ እናም በእርግጥ በሚደንቅ ኹኔታ ፀንሳለች፤ ያቺን በዕድሜ ያረጀችና የደከመች ነገር ግን ፀንሳ የነበረችውን ሴት ልታይ ኼደች፣ ምክንያቱም ከመልአኩ የሰማችውን ቃል ኹሉ አምናለችና፤ ይኽቺ ብላቴና እና ያቺ ያረጀች ሴት ተገናኙ፤ ንጋት እና ምሽት ተገናኝተው እንደተሳሳሙ አድርጎ መናገር ይቻላል፤ እመቤታችን ማርያም ንጋት ናት፤ እናም የጽድቅ ፀሓይን

[32] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘቀዳሚት፤ ምዕ ፫፥፲፭-፲፱



www.ethiopianorthodox.org

ተሸክማለች ኤልሳቤጥ ግን የብርሃን ኮከብን የምትሸከም ምሽት ናት፤ ንጋት መጥታ ወዳጅዋ ለኾነቺው ለምሽት ሰላም ሰጠቻት ምሽትም ንጋት ስትስማት በማየቷ እጅግ ተደሰተች ብላቴናዪቱ ድንግል ጠቢብ እና ትሕት ነበረች በዕድሜ ያረጀችው ሴትም እንደ እናት አድርጋ በአክብሮት ተቀበለቻት ኮከቡ (ዮሐንስ) ፀሓይን (ጌታን) ለመቀበል ባለመቻሉ ምክንያት በርሱ መገለጥ (መታየት) በደስታ መላወስና መዝለል ጀመረ፤ የንጋት ብርሃን የምሽት ጨለማን አገኘው (ተገናኘው) እናም ቀሰቀሰው፤ ነገር ግን የብርሃንን ጨረር ሲቋቋመው አልቻለም)[33] በማለት የኤልሳቤጥና የእመቤታችንን መገናኘት የዮሐንስን በማሕፀን መስገድ በጥልቀት ገልጾታል።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም ርቱዐ ሃይማኖት በሚለው የሃይማኖት መጽሐፍ ላይ ይኽነን ምስጢር ሲያስረዱ፦ "ከዚኽ በኋላ ሦስት ወር ሲኾን ፀሓይ እመቤታችን ጌታን ፀንሳ ወደ ምሥራቅ ኼደች፤ የቀን መንገድን የሚጠርግ ጎሕን የሚሰብክ የንጋት ነግኅ ኮከብ እናቱ ምዕራብ ኤልሳቤጥ በሰማች ጊዜ የሌዊ ወገን እናቱ የጌታዬ እናቱ ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድነኝ እያለች አሰምታ ተናገረች ...ያን ጊዜም እመቤታችን ከኤልሳቤጥ ጋራ ተገናኘች፤ ይቅርታና እውነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ፍቅርም ተስማሙ ብሎ ዳዊት የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ"[34] በማለት የትንቢቱ ፍጻሜን አስተምረዋል።

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም በመቀጠል *"ርትዕሰ እምድር ሠረፀት"* (ቅንነት ከምድር በቀለች) በማለት በምድር ከተመሰለች ከቅድስት ድንግል ማርያም አካላዊ ቃል ነፍስን ሥጋን መንሣቱን ደኃራዊ ልደቱን ሲገልጽ *"ወጽድቅኒ አምሰማይ ሐወጸ"* (ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተ) ብሎ አካላዊ ቃል ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የመወለዱን ቀዳማዊ ልደቱን ገልጦታል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ

*"ብኪ ሣህል ወርትዕ ተራከባ*
*ወበእንቲኣኪ ጽድቅ ወአሚን ሰላመ ተዋህባ"*

(ባንቺ ይቅርታ ተገናኙ፤ ስለ አንቺም እውነትና ሃይማኖት ሰላምታን ተሰጣጡ)[35] በማለት ምስጢሩን ገልጾታል።

[33] Jacob of Serugh, on the mother of God P 49
[34] ርቱዐ ሃይማኖት ገጽ ፶፬-፶፭
[35] አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 39





ይኽውም ትሰብእትና መለኮት በማሕፀነ ማርያም ቢገናኙ እግዚአብሔር ልጁን ለኵነት መስጠቱን *"ወእግዚአብሔርኒ ይሁብ ምሕረቶ"* (እግዚአብሔር ምሕረቱን ይሰጣል) በማለት ከአስረዳ በኋላ፤ እመቤታችንም ሥጋዋን ነፍሷን በቅድስና በንጽሕና አጽንታ ፍሬ ሕይወት ጌታን ለመውለድ ለተዋሕዶ በቅታ የምትገኝ መኾኗን *"ምድርኒ ትውህብ ፍሬሃ"* (ምድርም ፍሬዋን ትሰጣለች) ሲል ክቡር ዳዊት አስተምሯል።

## እናታችን ጽዮን

የዝማሬና የትንቢት ጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጡት ክቡር ዳዊት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር በተለይም ስለ ሥርወ ልደቷ፤ አምላክን ስለ መውለዷ፤ በርሷ አማላጅነት ስለሚማጸኑት ምእመናን ተገልጦለት ከተናገራቸው ትንቢቶች መኻከል በመዝ ፹፮፥፩-፯ ላይ

*"መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን"* (መሠረቶችዋ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው) በማለት የእመቤታችን ሥርወ ልደት ከቤተ መንግሥት ከቤተ ክህነት ከኾኑት ከተቀደሱት ከቅዱስ ኢያቄምና ከቅድስቲቱ ሐና የመኾኑን ነገር በምሳሌ ገልጾታል።

ይኽነን የሥርወ ልደቷን ነገር በመቅድመ ተአምር ላይ *"ወሥርወ ልደታ ለእግዝእትነ ማርያም እምቤተ ዳዊት ንጉሥ መንገለ አቡሃ ወእምቤተ አሮን መንገለ እማ፤ ስመ አቡሃ ኢያቄም ወስመ ወላዲታ ሐና"*

(የእመቤታችን ማርያም ትውልዷ ባባቷ በኩል ከንጉሡ ከዳዊት ወገን ነው፤ በናቷም በኩል ከካህኑ ከአሮን ወገን ነው፤ የአባቷ ስም ኢያቄም ነው፤ የእናቷም ስም ሐና ነው)[36] ሲል የዘር ሐረግዋ ከቤተ መንግሥት ከቤተ ክህነት ወገን እንደኾነ ሊቃውንት አስተምረዋል።

በመቀጠልም *"ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን እምኵሉ ተዓይኒሁ ለያዕቆብ"* (ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወዳቸዋል) በማለት ከሌሎች ደናግል ይልቅ ጽዮን የተባለች የድንግል ማርያምን ሕዋሳት ለተዋሕዶ ጌታ ወዶ የመረጠው መኾኑን ከገለጠ በኋላ *"ነኪር ነገሩ በእንቲኣኪ ሀገረ እግዚአብሔር"* (የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ ስላንቺ የተነገረው ነገር ድንቅ ነው) ብሏታል።

ይኸውም ነቢዩ ዳዊት ድንግል ማርያምን "የእግዚአብሔር ከተማ" ያለበት ምክንያት ንጉሥ በከተማው እንዲኖር ኹሉ ንጉሠ ሰማይ ወምድር አምላክም ማሕፀኗን እንደ ከተማ አድርጎ ፱ ወር ከ፭ ቀን እንደሚኖር ተገልጾለት የተናገረው ሲኾን፤ ያለዘር ያለሩካቤ አካላዊ ቃልን መፅነሷ፣

[36] መቅድመ ተአምር ቊ ፲፭-፲፮



www.ethiopianorthodox.org

በኅቱም ድንግልና መውለዷ፤ የድንግልና ጡቶቿን ማጥባቷ ለኹሉ ድንቅ ነውና *"ነኪር ነገሩ በእንቲኣሃ"* (ስላንቺ የተደረገ ነገር ድንቅ ነው) በማለት አድንቋል። ከዚያም *"እዜክሮን ለረዓብ ወለባቢሎን እለ የአምራኒ ወናሁ ኢሎፍሊ ወጢሮስ ወሕዝብ ኢትዮጵያ እለ ተወልዱ በህየ"* (የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለኹ እነሆ ፍልስጥኤማውያን ጢሮስም የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚኽ በዚያ ተወለዱ) በማለት በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው በቤተ ክርስቲያን የተወለዱ አስቀድሞ የሚያውቁት ምእመናን አሕዛብን እንደሚያውቃቸውና እንደሚሰበስባቸው ከተናገረ በኋላ፤ እኒኽ የተሰበሰቡት የእግዚአብሔር ልጆች ኹሉ ጸሎቷ ጸወነ *ሥጋ* ጸወነ ነፍስ በመኾኑ ጽዮን የምትባል ቅድስት ድንግል ማርያምን እናታችን የሚሏት መኾኑን *"እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ"* (ሰው እናታችን ጽዮን ይላል) በማለት ትንቢት ሲናገር፤ ቅድመ ዓለም የነበረ የባሕርይ አምላክ አካላዊ ቃል ከ*ሥጋዋ ሥጋን* ከነፍሷ ነፍስን *ነሥቶ* በ*ሥጋ* ከርሷ እንደሚወለድ ተገልጾለት *"ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ"* (በውስጥዋም ሰው ተወለደ) ሲል አስተምሯል (ገላ ፬፥፬)።

ይኸ ክቡር ዳዊት በመቀጠል *"ወውእቱ ልዑል ሣረራ"* (ርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት) በማለት ራሱ ባለቤቱ ወልደ እግዚአብሔር በድንግልና የወለደችው እናቱን በንጽሕና፣ በቅድስና፣ በዘላለማዊ ድንግልና ያጸናት ያስጌጣት መኾኑን ካስረዳ በኋላ *"እግዚአብሔር ይነግሮሙ ለሕዝቡ በመጽሐፍ ወመላእክቲሁኒ እለ ተወልዱ በውስቴታ ከመ ፍሡሓን ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴትኪ"* (እግዚአብሔር ለሕዝቡ በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል በአንቺ የሚኖሩ ኹሉ ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል) ብሎ ከቤተክርስቲያን በልጅነት ተወልደው የሚኖሩ ምእመናንና አለቆች ወይም መምህራን የኾኑት ሊቃውንት ኹሉ በአባታቸው በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በእናታቸው በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ዘላለማዊ ድንግልናና ወላዲተ አምላክነት በማመን ደስ ብሏቸው የሚኖሩ መኾኑን በመንፈሰ እግዚአብሔር በመቃኘት አማናዊ ትንቢት ተናግሯል።

## ጽዮን

ይኸ ቅዱስ ዳዊት በመንፈሰ እግዚአብሔር በመቃኘት ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ትኾን ዘንድ ስለመመረጧ ተገልጾለት በመዝ ፻፴፩፥፲፫-፲፬ *"እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን"* (እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና) በማለት ጸወነ ጻድቃን ጸወነ ኅጥኣን በመኾኗ





ጽዮን የተባለችው ቅድስት ድንግል ማርያምን ወልደ እግዚአብሔር ለእናትነት የመረጣት መኾኑን ተናግሯል።

ይኸ ለአምላክ እናትነት የመመረጧን ምስጢር በርካቶች ሊቃውንት በየድርሳናቸው ላይ በስፋትና በጥልቀት አስተምረዋል፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው ላይ *"በአማን ነጸረ እግዚአብሔር አብ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ ወውስተ ኵሉ አጽናፍ አስተንፈሰ ወአጼነወ ወኢረከበ ዘከማኪ ወሠምረ መዐዛ ዚኣኪ ወአፍቀረ ሥነኪ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር"*፦ (እግዚአብሔር አብ በሰማይ ኾኖ ምሥራቁንና ምዕራቡን ሰሜኑንና ደቡቡን ዳርቻዎችን ኹሉ በእውነት ተመለከተ፤ ተነፈሰ አሸተተም እንደአንቺ ያለ አላገኘም የአንቺን መዐዛ ወደደ የሚወደው ልጁን ወደ አንቺ ሰደደ)[37] በማለት ልዩ የኾነ ምርጫዋን ተናግሯል። ክቡር ዳዊት በዚኽ መዝሙሩ መመረጧን ከተናገረ በኋላ *"ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ"* (ማደሪያውም ትኾነው ዘንድ ወድዶአታልና) በማለት ቅድስት ድንግል ማርያምን እናቱ ትኾን ዘንድ መርጦ ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ ያድር ዘንድ መውደዱን ገልጦታል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በውዳሴ ማርያም ላይ ለአምላክ እናትነት የመመረጧን ምስጢር ሲያስረዳ *"ዕበያ ለድንግል ኢይትከሀል ለተነግሮ እስመ እግዚእ ኀረያ መጽአ ወኀደረ ላዕሌሃ ዘዮኀድር ውስተ ብርሃን ኀበ አልቦ ዘይቀርቦ ተጸውረ በከርሣ ፱ተ አውራኀ ዘኢይትረአይ ወዘኢይትዐወቅ ወለደቶ ማርያም እንዘ ድንግል ይእቲ"* (የድንግል ገናንነቷን ሊናገሩት አይቻልም፣ ጌታ መርጧታልና፤ የሚቀርበው በሌለ ብርሃን ውስጥ የሚኖር ርሱ መጥቶ ዐደረባት፤ ዘጠኝ ወር በማሕፀንዋ ዐደረ፤ የማይታይና የማይመረመር (ታይቶ የማይታወቅ) ርሱን በድንግልና ወለደችው)[38] በማለት አስተምሯል።

የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በመጽሐፉ ላይ ቅድስት ድንግል ማርያም ለአምላክ እናትነት ስለመመረጧና፤ አካላዊ ቃል ፱ወር ከ፭ቀን በማሕፀኗ ያድር ዘንድ መውደዱን በድርሳኑ ላይ ሲገልጽ *"This deed which took place in her gave me power..."* (ይኸ በርሷ ውስጥ የተከናወነው ሥራ ብርታት ስለሰጠኝ፤ ስለማይሻር ውበቷ እነዚኽን ነገሮች ልናገር ችያለኹ፤ ርሷ የእግዚአብሔርን ልጅ እናት በመኾኗ ምክንያት፤ በዚኽ ምድር ፍጹም

[37]አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቊ ፳፬

[38]ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ



www.ethiopianorthodox.org

ንጽሕት የኾነች ብቸኛዋ ሴት ርሷ እንደኾነች አይቼ ጠንቅቄ አምኛለኊ፤ መልካሙን ከክፉው መለየት ካወቀችበት ጊዜ ገምሮ፤ ርሷ በልብ ንጽሕና እና በሀሳብ እውነተኛነት ጸንታ ቆማለች፤ በሕጉ ውስጥ ካለው ጽድቅ ፊቷን አላዞረችም፤ ምድራዊና ሥጋዊ መሻትም አላሰናከላትም፤ ከሕፃንነቷ ገምሮ የቅድስና ባሕርያት በውስጧ ነበሩ፤ ከፍ ባለችም ጊዜ እነዚኽን አጥብቃ በጥንቃቄ አብዝታለች፤ አምላኳ ኹልጊዜ በፊቷ (ከዐይኖቿ ፊት) ነበር፤ በርሱ ይበራላት ዘንድ በርሱም ደስ ይላት ዘንድ ዐይኖቿን ከርሱ አላነሣችም፤ ርሱም ንጽሕናዋን እና የነፍሷን ንጽሕና ስላየ፤ አንዳች ክፋትም (ክፉ ነገርም) ስላልነበራት በርሷ ያድር ዘንድ ወደደ፤ እንደርሷ ያለች አንድም ሴት ታይታ ስለማይታወቅ፤ ከሥራዎች ኹሉ በላይ ታላቅና ድንቅ የኾነ ሥራ በርሷ ውስጥ ተሠራ፤ ከሴቶች ኹሉ መኻከል አንድ ሴት ልጅ ተፈለገች፤ ከኹሉም በላይ መልካም የኾነችውም ተመረጠች፤ ቅዱስ አብ ለልጁ እናት የምትኾን ሊያዘጋጅለት ፈለገ፤ ነገር ግን ርሱ ስለመረጣት ብቻ እናቱ እንድትኾን አልፈቀደም፤ በውስጧና በዙሪያዋ በተሰወረ ውበት የተመላች ብላቴና ልጅ፤ እንዲኹም በርሷ ውስጥ የተከሠቱትን ምስጢራት ልታይ ያስቻላት የልብ ንጽሕና የነበራት፤ አንዲት ሴት ወዳና ፈቅዳ ውበት ሲኖራት፤ ያ ነው እውነተኛው ውበት ፍጹምነቷ በፈቃዷ ሲኾን፤ የአንድ ከእግዚአብሔር የኾነ ነገር ውበት ምንም ያኽል እንኳ ታላቅ ቢኾን፤ ነጻ የኾነ የግል ፈቃድ በውስጡ ከሌለ ምስጉንነት የለውም፤ ፀሓይ ውብ ብትኾንም የሚመለከቷት ግን አያመስግኑዋትም፤ ምክንያቱም ብርሃኗን የምትሰጠው ወዳና ፈቅዳ እንዳልኾነ ስለሚታወቅ ነው፤ በገዛ ፈቃዱና በውዴታ ውብ የኾነና ውበት ያለው ኹሉ፤ በእውነት ውብ እስከኾነ ድረስ ከዚኽ የተነሣ ብቻ ርሱ እውነትም ምስጉን ነው፤ እግዚአብሔርም የሚወደው ውበት ከራስ ፈቃድ የኾነውን ነው፤ ርሱን ደስ የሚያሰኝ ሲኾን አንድን መልካም ፈቃድ ርሱ ያከብራል፤ እነሆ ታሪኳን እየተናገርን ያለነው ይኽቺ ድንግል፤ መልካም ፈቃድ ስለነበራት ደስ የምታሰኝና የተመረጠች ኾናለች፤ ሰው በኾነች ሴት ልጅ በኩል ርሱ ሰው ሆኖ መጣ፤ ደስ የምታሰኝ ስለነበረች ከርሷ ይመጣ ዘንድ ርሷን መረጣት፤ የርሱ ግርማ ከሰው ከሚወለዱት ኹሉ ግርማ ይልቅ ታላቅ ስለኾነ፤ እናቱ የኾነችው የማርያም ውበት እጅግ የላቀ (የተወደሰ) ይኾናል፤ ደስ የምታሰኝና ለርሱ ምርጥ የኾነችው፤ ከትሕትናዋ፣ ከንጽሕናዋ፣ ከቀናነትዋ፣ እና መልካም ከኾነው ፈቃድዋ የተነሣ ነው፤ ከርሷ በላይ ደስ ያሰኘችው





ሌላ ብትኾን ኖሮ ሌላኛዪቱን ይመርጣት ነበር፤ ርሱ ቅን ፈታሒ እና ትክክለኛ ስለሆነ አምላክ ግለሰቦችን (ለይቶ) አያከብርም (፪ ዜና ፲፱፥፯፤ የሐዋ ፲፥፴፬)፤ አንድስ ስንኳ እንከን ወይም ጉድለት በነፍሷ ተገኝቶ ቢኾን ኖሮ፤ ሌላ እንከን የማይገኝባት እናት ለራሱ በፈለገ ነበር፤ ከውበት ኹሉ በላይ እጅግ የላቀው ይኽ ውበት፤ በመልካም ፈቃዷ ባገኘችው ብቻ ውስጥ የሚኖር ነው፤ ከዚኽ የተነሣ ኹሉም ክብርት (ግርምት) በኾነችው በርሷ መደነቁ ትክክለኛ ነው፤ አምላክ እንኳ እናቱ አድርጎ እንዲመርጣት ያደረገው እጅግ ደስ የምታሰኝ መኾንዋ ነበረና፤ ለተፈጥሮ በተሰጠው ውበት መጠን ልክ ርሷ ደስ የምታሰኝ ነበረች፤ ነገር ግን ለዚኽ ደረጃ የበቃችው በርሷ ፈቃድ ብቻ አልነበረም፤ ርሷ ለሰው የሚቻለውን ያኽል ጥረት አደረገች፤ አምላክ ከርሷ መውጣቱ (መወለዱ) ግን የርሷ ሥራ አልነበረም፤ ርሷ በቅንነቷ ወደ አምላክ በተጠጋች መጠን፤ ከነፍሷ መሻት የተነሣ ርሱም በቸርነቱ ወደርሷ ተጠጋ፤ ነገር ግን አምላክ ሥጋ ለብሶ ከርሷ መምጣቱ ያ የርሱ ጸጋ (ቸርነት) ነው፤ እንዲኽ ለበዛው ምሕረቱ ምስጋና ይድረሰው! የእመቤታችን ማርያም ውበት ከስፍር (ከመጠን) ያለፈ (በላይ) ነው፤ (ምክንያቱም) ከርሷ የምትበልጥ ሌላ ፀዓሰም ኹሉ አልተገኘችምና፤ ከዚኽ በኋላ ለርሱ የሚገባውን ለአምላክ እንስጥ፤ ጸጋውን ያለልክ በፍጥረታት ላይ አዝንቧልና፤ ዘመናት ኹሉ ለርሱ የማይበቁትን ብሉየ መዋዕል ወልድን ያመጣውን ርሱን እንወቀው፤ ከእናቶች ኹሉ መኻል አቻ ያልተገኘላትን እመቤታችን ማርያምን ያበጃትንም (እንረዳው)፤ ርሷ እንደተመሰገኑት እንደ ዮሐንስ፣ እና እንደ ኤልሳዕ፣ እንደ ኤልያስ፣ እና እንደ መልከ ጼዴቅ ንጽሕት ተደርጋለች፤ ርሷ በውበት ወደ እነዚኽ ከፍታዎች (ማዕርጎች) ከፍ ስለተደረገች፤ የቅዱሱ የአብ የባሕርይ ልጅ እናት ለመኾን ተመረጠች፤ ርሷ በነፍሷ ወደ ፍጹም ምላት ስለተጠጋች፤ ያለ ገደብ የኾነው ጸጋ ወደርሷ ተጠጋና በርሷ ዐደረ፤ የቅድስና ውበት የመላባት ርሷ ወደ አምላክ ተመለከተች፤ ርሱም ንጹሕ በኾነው ማሕፀኗ ለማደር ወደደ)[39] ሲል የንጽሕናዋን ታላቅነትና በአምላክ የመመረጧን ነገር በስፋት ገልጾታል፡፡

[39] Jacob of serugh, on the mother of God pp. 24-28



www.ethiopianorthodox.org

ክብር ይግባውና ልዑል አምላክ በዳዊት ዐድሮ "ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም" (ይቺቱ ለዘላለም ማረፊያዬ ናት) ብሎ ለዘላለም እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ እየተባለች ስትመሰገን መኖሯንና ርሱም ከርሷ የነሣው ሥጋ ከመለኮቱ ጋር ለዘላለም ተውሕዶ የሚኖር መኾኑን ከተናገረ በኋላ "ዝየ አኀድር እስመ ኀረይክዋ" (መርጫታለኹና በዚኽች ዐድራለኍ) በማለት እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ከተመረጡት የተመረጠች፤ ከተለዩት የተለየች፣ ከነጹት የነጻች፣ ከተቀደሱት የተቀደሰች አቻ ወደር የማይገኝላት ማደሪያው፣ ዙፋኑ፣ እናቱ መኾኗን አናግሯል።

ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ይኽነን የዳዊት መዝሙርን ከሌሎች ኹለት መዝሙራት ጋር በማቀናጀት በድጓው ላይ

"ይቤ ዳዊት በመዝሙር መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን ወካዕበ ይቤ ቀደሰ ማኀደሮ ልዑል ወይቤ ዝየ አኀድር እስመ ኀረይክዋ እግዚእ ለሰንበት በከርሣ ተጸውረ ሰማየ ወምድረ ዘውእቱ ፈጠረ" (ዳዊት በመዝሙር እንዲኽ ብሎ ተናገረ፤ መሠረቶቿ የተቀደሱ ተራሮች ናቸው፤ ዳግመኛም ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ ሲል ተናገረ፤ መርጫታለኹና በርሷ ዐድራለኍ አለ፤ ለማደሪያው የመረጣት ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የሰንበት ጌታዋ በማሕፀኗ ዐደረ)[40] በማለት የዳዊት መዝሙር የተካበተ የነገረ ማርያም ትምህርትን የያዘ መኾኑን ገልጧል።

ኢትዮጵያዊዉ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ልክ እንደ ቅዱስ ያሬድ ክቡር ዳዊት ስለ እመቤታችን የተናገራቸውን ሦስት መዝሙሮችን በአንድ ላይ በማቀናጀት በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ፡- "ወፈድፋደሰ እጽሕቅ ከመ ትምጽኢ ኀቤየ ምስለ ዝንቱ ማሕሌታይ ዳዊት አቡኪ፤ እስመ ይኬልሕ በእንቲኣኪ በውዑይ ፍቅር እንዘ ይብል ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘየኀድር ውስተ ጽዮን ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ (መዝ ፱፥፲፩) ወካዕበ ይቤ ዳዊት ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል እግዚአብሔር ውስተ ማእከላ ኢትትሀወክ (መዝ ፵፭፥፬-፭) ወካዕበ ይቤ ዳዊት ዕግትዋ ለጽዮን ወሕቀፍዋ ወተናገሩ በውስተ ማኅፈዲሃ፤ደዩ ልበክሙ ውስተ ኀይላ ወትትካፈልዎ ለክበዲሃ ከመ ትንግሩ ለካልእ ትውልድ (መዝ ፵፯፥፲፪-፲፫) ሚ መጠን ክቡር ሥርዐት ተውህባ ለቅድስት ድንግል በዲበ ቅድስት ኦሪት ወንጌል ቅዱስ፤ ወዲበ ቅዳሳን ነቢያት ቅዱሳን ሐዋርያት፤ ወዲበ ብሉይ ኪዳን ሐዲስ፤ በዲበ ፍትሕ ዘተውህበ ለእስራኤል ፍትሐ

[40] ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ድጓ ገጽ ፫፻፹፱





ቀኖና ዘአርድእት ዋሕድ ወበእንተዝ ይቤ ትትካፈልዎ ለክበዲሃ፤ ሶበ ይብል እንከ ከመ ትንግሩ ለካልዕ ትውልድ በእንተ ውሉደ ጥምቀት ይዜኑ እለ ኢኮኑ ዘይትሜክሑ በልደት ዘሥጋ፤ ወእለ ወሀቦሙ ሥልጣነ ውሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ ወእለ ኢኮኑ እምነ ዘደም ወኢእምፍትወተ ሥጋ ወኢእምሥመረተ ብእሲ አላ እምእግዚአብሔር ተወልዱ (ዮሐ ፩፥፲፪-፲፫)"

(ይልቁንም ማሕሌታይ ከሚኾን ከዚኽ ከአባትሽ ከዳዊት ጋራ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እተጋለኍ፤በተቃጠለ ፍቅር ስለ አንቺ ይጮኻልና እንዲኽ እያለ በጽዮን ላይ ዐድሮ ለሚኖር ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡ፤ ሥራውንም ለአሕዛብ ንገሯቸው (መዝ ፱፥፲፩) ዳግመኛም እንዲኽ አለ፣ ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ እንዳትነዋወጥም እግዚአብሔር በመኻከሏ ነው (መዝ ፵፭፥፬-፭) ዳግመኛ እንዲኽ አለ ጽዮንን ከባችኍ ዕቀፏት በአዳራሾቿም ውስጥ ተነጋገሩ፤ በኀይሏም ልባችኹን ጨምሩ፤ ሽክሟን ትካፈሉታላችኍ ለተተኪው ትውልድ ትነግሩ ዘንድ (መዝ ፵፯፥፲፪-፲፫)፤ ምን ያኽል የበዛ የክብር ሥርዐት ተሰጣት በተመረጠች በኦሪት ላይ የተመረጠ ወንጌል በቅዱሳን ነቢያት ላይ ቅዱሳን ሐዋርያት፤ በቀደመው ኪዳን ላይ ዐዲሱ ኪዳን፤ ለእስራኤል በተሰጠ የፍርድ መጽሐፍ ላይ ከኹለት አካል አንድ አካል ከኹለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሚኾን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የቀኖና መጽሐፍ፤ ስለዚኽም ሽክሟን ትካፈላላችኍ አለ፤ ለተተኪው ትውልድ ታስተምሩ ትነግሩ ዘንድ ባለ ጊዜ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ ስለአልኾኑ የእግዚአብሔር ልጆች ይኾኑ ዘንድ ስልጣን ስለተሰጣቸውና በሥጋዊ ልደት ስለማይመኩ ስለ ጥምቀት ልጆች ይናገራል (ዮሐ ፩፥፲፪-፲፫)[41] በማለት ይኽ የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ሊቅ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ይኽነን የዳዊትን መዝሙር ተርጒሞታል።

## ክፍል ኹለት

## ነገረ ማርያም በማሕልየ መሓልይ

ጠቢቡ ሰሎሞን የንጉሥ ዳዊት ልጅ ሲኾን፤ ከአባቱ በመቀጠል በ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል ላይ የነገሠና ጥበብና ማስተዋል ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቤተ መቅደስን ለታቦተ ጽዮን የሠራ ንጉሥ ነው። ይኽ ሰሎሞን ርሱም እንደ አባቱ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በማሕልየ

[41] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ፤ ምዕ ፩፥፮-፲፩



www.ethiopianorthodox.org

ማሕልዩ ስለ እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና፣ ወላዲተ አምላክነት፣ ስለ ምትወለድበት ቦታ፣ ስለ መልኳ ደም ግቡት፣ ስለተሰጣት ታላቅ ክብር በተለያየ አስደናቂ ሕብረ አምሳል ሲገልጽ፤ በማሕልዩ የተናገራቸው እነዚኽን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌዎችን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከዚኽ በታች አስቀምጫቸዋለኊ።

## የሱፍ አበባ

ጠቢቡ ሰሎሞን በማሕ ፪፥፩-፪ ላይ ርሱም እንደ አባቱ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት የቅድስት ድንግል ማርያምን ንጽሕና በሱፍ አበባ መስሎ ሲያስተምር *"አነ ጽጌ ገዳም ጽጌ ደንጐላት ዘውስተ ቈላት፤ ወከመ ጽጌ ደንጐላት በማእከለ አሥዋክ ከማሁ አንቲኒ እንተ ኀቤየ በማእከለ አዋልድ"* (እኔ የዱር ጽጌረዳ፤ የቈላም የሱፍ አበባ ነኝ፤ በእሾኽ መኻከል እንዳለ የሱፍ አበባ እንዲኹ ወዳጄ በቈነጆኞች መኻከል ነሽ) በማለት የተናገረውን ምሳሌያዊ ኀይለ ቃል ሊቁ በድርሰቱ ላይ፡- *"ወከመ ጽጌ ደንጐላት በማእከለ አሥዋክ ከማሃ አንቲኒ ኦ ወላዲተ አምላክ"* (በእሾኽ መኻከል እንዳለ የሱፍ አበባ አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ አንቺም እንደ ርሷ ነሽ) ሲል ያቺ ሰሎሞን የተናገረላት የሱፍ አበባ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ተርጕሞታል።

ይኸውም ይቺ የሱፍ አበባ እሾኽ ዙሪያዋን ከቧት ሳለ በሾኽ መኻከል እንደምታብብ እንደምታፈራ ቅድስት ድንግል ማርያምም ኀጢአት እንደ እሾኽ በከበባቸው በአይሁድ መኻከል ሳለች ብቻዋን ከኀልዮ (ከማሰብ)፣ ከነቢብ (ከመናገር)፣ ከገቢር (ከመሥራት) ኀጢአት ተጠብቃ በሃይማኖት፣ በምግባር፣ በንጽሕና፣ በቅድስና፣ በድንግልና ጸንታ የሕይወት ፍሬ ክርስቶስን አብባ አፍርታ ተገኝታለችና ነው።

ኢትዮጵያዊዉ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን የሰሎሞንን ቃል በአርጋኖን መጽሐፉ ሲተረጕመው፡- *"ጽጌ ደንጐላት እንከ እሰምየኪ እስመ ጽጌ ደንጐላት ዕዉድ በአሥዋክ ወከመ አንቲ ነበርኪ ሠርጸ ጽጌ ንጽሕ ዘእምጕንደ ዳዊት ማእከለ አዋልደ ዕብራውያን ግዙፋነ ክሣድ ዘበእንቲኣሆን ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ያኀስሮን እግዚአብሔር ለልሂቃተ አዋልደ ጽዮን እለ ይትሜክሓ በኀሳሮን ወያገዝፋ ክሣዶን ወይትቃጸባ በአዕይንቲሆን ወያጽሕሳ በእገሪሆን፤ ወይስሕባ አዝፋረ አልባሲሆን ወይዘፍና (ኢሳ ፫፥፲፮-፲፯)"* (በሱፍ ዕንጨት እመስልሻለኊ፤ የሱፍ አበባ በእሾኽ የተከበበ ነውና፤ አንቺም ከዳዊት ግንድ (ባሕርይ) የተገኘች የንጽሕት አበባ ቅንጣት ኾነሽ ሳለ፤ በጕስቁልናቸው የሚመኩ





አንገታቸውን የሚያደነድኑ በሀይኖቻቸው የሚጠቃቀሱ በእግሮቻቸው የሚያሽበሽቡ የልብሶቻቸውን ዘርፎች የሚጐትቱ የሚዘፍኑትን የቈነጆኞች አለቆች የሚኾኑ የጽዮንን ልጆች እግዚአብሔር ያዋርዳቸዋል ያጐሳቍላቸዋል ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት እንደተናገረባቸው (ኢሳ ፫፥፲፮-፲፯)፤ አንቺም አንገተ ደንዳኖች በሚኾኑ በዕብራውያን ቈነጆኞች መኻከል እንደተቀመጥሽ)[42] በማለት ግዙፋነ ክሣድ በኾኑ ኀጢአት እንደ እሾኽ በከበባቸው በአይሁድ ልጆች መኻከል ሳለች ርሷ ብቻ በንጽሕና በቅድስና ጸንታ የመገኘቷን ምስጢር ከሰሎሞንና ከኢሳይያስ ቃል በመጥቀስ ተንትኖታል።

ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስም ከዚኽ ምስጢር በመነሣት በቅዳሴው *"ኦ ድንግል አኮ በተላህዮ ዘልህቂ ከመ አዋልደ ዕብራውያን እለ ያገዝፉ ክሣዶን አላ በቅድስና ወበንጽሕ ውስተ ቤተ መቅደስ ነበርኪ"* (ድንግል ሆይ ክሣዶን አላ በቅድስና ወበንጽሕ እንደሚያገዝፉ እንደ ዕብራውያን ሴቶች ልጆች በዋዛ ያደግሽ አይደለሽም፤ በንጽሕና በቅድስና በቤተ መቅደስ ኖርሽ እንጂ)[43] በማለት ግዙፋነ ክሣድ በኾኑ በዘፈን፣ በቧልት፣ በጨዋታ፣ ኀጢአትን በመሥራት ይኖሩ ከነበሩ ከዕብራውያት ሴቶች ልጆች ተለይታ በቤተ መቅደስ ማደጓን አስተምሯል።

አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ይኽነን የሰሎሞንን ቃል ሲያብራሩ

*"ጽጌ ደንጐላ ዘቈላ ወአኮ ዘደደክ*
*ዘጸገይኪ ጽጌ በማእከለ አይሁድ አሥዋክ*
*ተአምረ ድኂን ማርያም ዘልማድኪ ምሂክ*
*መሀክኒ ለምእመንኪ እምጻዕረ ኵነኔ ድሩክ*
*ተአምኖትየ ኢይኩን በበክ"*

(በእሾኾች አይሁድ መኻከል የደጋ ያይደለ የቈላ የሱፍ አበባን ያበብሽና ልማድሽ መራራት የኾነ የመዳን ምልክት ማርያም፤ ብርቱ ከኾነ ከጭንቅ የቅጣት ፍርድ ታማኝሽን አድኚኝ፤ በአንቺ መታመኔ ከንቱ ኾኖ እንዳይቀር)[44] በማለት በሱፍ አበባ መመሰሏን አጕልተው ተርጕመዋል።

### መሸከሚያ (ዙፋን)

ይኽ ጥበብና ማስተዋል ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሰሎሞን በማሕ ፫፥፱ ላይ *"መጸረ ገብረ ለርእሱ ንጉሥ ሰሎሞን እምዕፀወ ሊባኖስ*

[42] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ፤ ምዕ ፰፥፲፮-፲፯
[43] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም፤
[44] አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቁ ፲፲



www.ethiopianorthodox.org

አዕማዲሁ ገብረ ዘብሩር ምስማኩ ዘወርቅ መንበሩ ዘሜላት ውስጡ ንጡፍ በእብነ ሰንፔር" (ንጉሥ ሰሎሞን መሸከሚያን ከሊባኖስ ዕንጨት ለራሱ አሠራ፤ ምሰሶቹን የብር፤ መደገፊያውንም የወርቅ፣ መቀመጫውንም ሐምራዊ ግምጃ አደረገ) በማለት ልዩ የነገረ ማርያም ምሳሌ በተለይም የአምላክ እናትነቷን ንጽሕናዋን ቅድስናዋን የሚያጐሉ ምስጢራውያት ነገሮችን አስተምሯል።

ይኸነንም ሰሎሞን ጠቅልሎ የተናገረውን የነገረ ማርያም ምስጢር ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እየተነተነ በኖኅተ ብርሃን መጽሐፉ ላይ ሲተረጉም "ንግባእኬ ከመ ንሰብሓ ለምልዕተ ውዳሴ እንዘ ንብል መጸርር አንቲ ለንጉሠ ነገሥት ወለእግዚአ አጋእዝት በከመ ይቤ ሰሎሞን መጸረ ገብረ ለርእሱ ንጉሥ እምዕፀወ ሊባኖስ አዕማዲሁ ገብረ ዘብሩር ምስማኮ ዘወርቅ ወመንበሮ ዘሜላት፤ መሃረ ገብረ እምዕፀው ሊባኖስ አንተ ይእቲ ትስብእተ ዋሕድ ዘነሥአ እምኔኪ፤ አዕማድሰ ዘይቤ እሉ እሙንቱ አዝማድኪ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ አበዊሆሙ ለሕዝብ ወለአሕዛብ እለ ይፈርዩ አፈዋተ ወእለ ያውሕዙ ዕፍረተ፤ ወምስማኮ ገብረ ዘወርቅ ንጹሕ አንተ ይእቲ ንጽሕ ድንግልናኪ ዘሕሩም እምርኩስ ወንጹሕ እምደነስ፤ ወመንበሮ ገብረ ዘሜላት እስመ ዘከመ ሜላት ፍቱል ሥጋ ዚኣኪ ከለሎ"፦ (ምስጋና የተመላች እመቤታችንን የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታን የወሰንሽ የተሸከምሽ ዙፋን አንቺ ነሽ እያልን እናመሰግናት ዘንድ እንመለስ፤ ንጉሥ ለራሱ ከሊባኖስ ዕንጨቶች ዙፋን ሠራ፤ ምሰሶዎቹን የብር፣ መከዳውንም የወርቅ፣ ዙፋኑን የሐር አደረገ ብሎ ሰሎሞን እንደተናገረ፤ ከሊባኖስ እንጨቶች ዙፋንን አደረገ ያለውም ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ከአንቺ የነሣት ሥጋ ናት፤ ምሰሶች ያላቸው እሊኽ ግን ሽቱን የሚያፈሩ ሽቱን የሚያፈሱ የሕዝብና የአሕዛብ አባቶች ዘመዶችሽ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ናቸው፤ መከዳውንም የንጹሕ ወርቅ አደረገ ያለው ከርኩሰት የተለየና ከኀጢአትም የነጻ የድንግልናሽ ንጽሕና ናት፤ ዙፋኑን ከሐር አደረገ ያለው እንደተፈተለ ሐር ያንቺ ሥጋ ስለጋረደው ነው)[45] በማለት ሊቁ የሰሎሞን ቃል በጥልቀት ተርጉሞታል።

ሊቃውንት የቅድስት ድንግል ማርያምን ቃል ኪዳን በተናገሩበት ድርሳን ላይ በመሓልዩ የተናገረውን ይኸነን የሰሎሞንን ቃል በመጽሐፈ ምሳሌ ከተናገረው ኀይለ ቃል ጋር በማገናኘት ሲተረጉሙ፦ "ይእቲኬ መጸረ መቅደስ ቤተ ንጉሥ ዘአዕማዲሃ ዕፀወ ሊባኖስ እለ ግቡራት በብሩር

[45] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ ኖኅተ ብርሃን ገጽ 104-105





ወመንበሩ ዘሜላት ምስማኩ ዘወርቅ ወንጡፍ ውስጡ በእብነ ሰንፔር በከመ ይቤ ሰሎሞን ጥበብ ሐነጸት ላቲ ቤተ ወአቀመት ውስቴታ ሰብዐተ አዕማደ ዛቲ ይእቲ ጥበቡ ለአብ ወሃቤ ኪዳን ምሕረት ዘይቤ ዕዝራ ተቀስመት ጥበብ እምሥረዊሃ ነየ ቤት ማኅደረ መለኮት ማርያም ወለተ ዳዊት መርዓት ሥርጉት ዘወፅአት እምግበበ አናብስት ወነዮሙ አበዊሃ አብርሃም ቀዳማይ ወይስሐቅ ዳግማይ ወያዕቆብ ሣልሳይ ወይሁዳ ራብዓይ ወሌዊ ሐምሳይ ወዳዊት ሳድሳይ ወሰሎሞን ሳብዓይ"(ምሰሶዎቿ በብር የተሠሩ የደጋ ዛፎች የኾኑላት፤ የንጉሥ ማደሪያ መቅደስ መሸከሚያ ማርያም ይኸቺ ናት፤ ዙፋኗ የሐር፣ መጨጊያው የወርቅ፣ ውስጡ በሰንፔር ድንጊያ የተነጠፈች መቅደስ ይኸቺ ናት፤ ሰሎሞን ጥበብ ቤቷን ሠራች፤ በውስጧም ሰባቱን ምሰሶዎችን አቆመች እንዳለ (ምሳ ፱፥፩) የምሕረት ቃል ኪዳንን የሚሰጥ የአብ ጥበቡ ይኸቺ ናት፤[46] በዕዝራ ጥበብ ከሥሮቿ ተለቀመች በማለት እንደተነገረ፤ ከአናብስት ጉድጓድ የወጣች (ከነገሥታቱና ከካህናቱ ወገን የተወለደች) የተሸለመች ሙሽራ፣ የዳዊት ልጅ ማርያም እነኋት፤ ሰባት ምሰሶዎች የተባሉ አባቶቿም አንደኛ አብርሃም፣ ኹለተኛ ይስሐቅ ሦስተኛ ያዕቆብ፣ አራተኛ ይሁዳ፣ አምስተኛ ሌዊ፣ ስድስተኛ ዳዊት ሰባተኛ ሰሎሞን ናቸው)[47] በማለት አስተምረዋል።

## የሊባኖስ ሙሽራ

ይኸ ሰሎሞን በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ የምትወለድበት ቦታ ተገልጾለት በማሕ ፬፥፯-፲ ላይ "ኵለንታኪ ሠናይት አንተ ኀቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ" (ወዳጄ ሆይ ኹለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም) በማለት ምንም ነውር ነቀፋ የሌለባት፣ የማሰብ፣ የመናገር፣ የመሥራት ኀጢአት ፈጽሞ ያላገኛት፣ በሥጋ፣በነፍስ፣በልቡና ንጽሕና ያጌጠች መኾኗን ተናግሮላታል።

በሰሎሞን ውብ ተብሎ የተነገረለት የእመቤታችን የሥጋ፣ የነፍስ፣ የልቡና ንጽሕና በእጅጉ ያስደንቃል፤ ሊቃውንትም በመቅድመ ተአምር ላይ "እግዝእትነ ማርያም ትነጽሕ እመላእክት" (እመቤታችን ማርያም ከመላእክት ይልቅ ንጽሕት ናት)[48] በማለት የንጽሕናዋን ነገር በስፋት አስተምረዋል። ይኸውም ልዑል እግዚብሔር በዕለተ እሑድ

[46] ሊቃውንት የአብ ጥበቡ ወልድ መኾኑን ሲያስተምሩ በዚኽ መጽሐፍም በተዘዋዋሪ የአብ ጥበብ የተባለ የወልድ እናት የመኾኗን ነገር አመላክተዋል።

[47] ድርሳነ ኪዳነ ምሕረት ዘሠሉስ፤ ገጽ ፻፳፩

መላእክትን በሦስቱ ሰማያት በዐሥር ከተማ በነገድ መቶ አድርጎ ፈጥሮ በተሰወራቸው ጊዜ ከመላእክተ ብርሃን ወገን የነበረውና ማዕርጉ ከፍ ያለው ሳጥናኤል በዚያ ምንም ኀጢአት በሌለበት በብሩህ ሰማይ ውስጥ ሐሰትና ክሕደትን ከልቡናው አመንጭቶና አስቦ መቶ ነገደ መላእክትን እኔ ፈጠርኋችሁ ባለ ጊዜ በርሱ ነገድ ውስጥ ያሉ መላእክት በመከፋፈል እኩሌቶቹ አዎን ፈጠርኸን በማለት የሐሰት ቃሉን ሲቀበሉ እኩሌቶቹ በመፍዘዝና በመጠራጠር የነበራቸውን ክብር በማጣት ጨለማን ለብሰው ወደ እንጦርጦስ ሲወርዱ ሌሎቹ ነገደ መላእክት ግን ይኽነን ሐሰት በመቃወም በእምነታቸው ጸንተው በክብር ላይ ክብርን አግኝተዋል (ኢሳ ፲፬፥፲፪-፲፯፤ ራእ ፲፪፥፯-፱)።

ሊቃውንቱም የእመቤታችንን ንጽሕና በተናገሩበት ክፍል ላይ *"ለመላእክትሂ ኢተክህሎሙ ድንጋሌ ኅሊና እስመ አቡሁ በፍትወት ወወረዱ ምድረ በመዋዕል ዘቀዳሚ"* (ኀጢአትን ከማሰብ መቆጠብ ለመላእክትስ (ለሳጥናኤልና ለሠራዊቱ) አልተቻላቸውም በቀደመው ዘመን (በመዠመሪያው ዕለት እሑድ) ያልተሰጣቸውም አምላክነትን ሽተው በድለው ከሰማይ ወደ ምድር ወርደዋልና)[49] በማለት እንዳስተማሩ እነዚኽ መላእክት ምንም ኀጢአት ባልተሰማበት ዓለም ሳሉ በማሰብ፣ በመናገር፣ በመሥራት ሲበድሉ ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ኀጢአት እንደ ጉም እንደ እሾኽ በከበበው በዚኽ ዓለም እያለች ከማሰብ፣ ከመናገር፣ ከምሥራት ኀጢአት ተቆጥባ በሃይማኖት፣ በምግባር፣ በንጽሕና፣ በቅድስና፣ በድንግልና ጸንታ ተገኝታለችና *"ድንግል በሥጋኪ ወድንግል በኅሊናኪ"* (በሃሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ) እያልን እንደ ሰሎሞን ነውር የሌለበት ውብ ቅድስናዋን እንመሰክራለን።

ይኽነኑ ንጽሕናዋን ቅዱሳን አበው በጥልቀት በማመስጠር ሲያስተምሩ *"ኢበዝ ዓለም ወበዘይመጽእኒ ዓለም ዘኢተውህበ ለመላእክት ተውህበ ድንግልና ለማርያም ቅድስት እስመ ለመላእክት ቦ እለ ወድቁ በትዕቢተ ኅሊናሆሙ ረኪቦሙ ድንግልና ኅሊና ማርያምሰ ዘተደንገለት በክልኤ ፍና በድንግልና ሥጋ ወበድንግልና ኅሊና በከመ አስተርአየት በክልኤ ፍና በሰርጐ መዓልት ወበሰርጐ ሌሊት ለቢሳ ፀሓየ ወወርኀ ታሕተ እገሪሃ ወከዋክብተ ዲበ ርእሳ" ወከማሁ አስተርአየት በክልኤ ፍና በድንግልና ሥጋሃ ወበድንግልና ኅሊናሃ እንበለ ሙስና እስመ ንጽሕት ይእቲ እምኵሉ ትሕዝብት ወእምኵሉ ርስሐተ ኀጢአት"*

[49] ዝኒ ከማሁ ቍ ፲፰





(በዚኽኛው ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ቢኾን ለክብርት እመቤታችን የተሰጣት ድንግልና ለመላእክት ስንኳ አልተሰጣቸውም፤ መላእክትስ (ሳጥናኤልና ሠራዊቱ) ድንግልና ከተሰጣቸው በኋላ ስለበደሉ ድቀት አግኝቷቸዋልና፤ ማርያምስ በኹለት ፊት ማለት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ኅሊና የጸናች ነች፤ በኹለት ፊት ማለት በቀን የሚያበራ ፀሓይን ተጐናጽፋ በሌሊት የሰለጠነ ጨረቃን ተጫምታ በራስዋም ላይ ከዋክብትን ተቀዳጅታ እንደተገለጸች (ራእ ፲፪፥፩)፤ እንደዚኹ ኹሉ ያለመለወጥ በኹለት ፊት ማለት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ኅሊና ፀንታ ተገኘች ርሷ ከርስሐተ ኀጢአትና ከመጠራጠርም ኹሉ ንጽሕት ናትና)[50] በማለት የአምላክን እናት ንጽሕና አስተምረዋል።

ጠቢቡ ሰሎሞን ይኽቺ ንጽሕት እናት በሊባኖስ ተራራ እንደምትወለድ መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት፦ *"ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ ንዒ ወተወፅኢ እምቅድመ ሃይማኖት እምርእሰ ሳኔር ወኤርሞን እምግበበ አናብስት ወእምአድባረ አናምርት"* (ሙሽራዬ ሆይ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነዪ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነዪ ከአማና ራስ ከሳኔር ከኤርሞን ራስ ከአንበሶች መኖሪያ ከነብሮችም ተራራ ተመልከች) በማለት ትንቢት እንደተናገረ ንጽሕት ሙሽራ ቅድስት ድንግል ማርያም ግንቦት አንድ ቀን በሊባኖስ ተራራ ተወልዳ ትንቢቱ ፍጻሜውን አግኝቷል።

ታላቁ ኢትዮጵያዊዉ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ይኽነን የሰሎሞንን ቃል ሲተረጉም *"ወካዕበ እሰምየኪ ወለተ አናብስት እስመ ከመ ጣሕረ አንበሳ ወንቃወ አንበሳዊት ይደምፅ ዜና ልደትኪ እስመ ለይሁዳ ይቤሎ አቡሁ ያዕቆብ ዕጓለ አንበሳ ወበእንተዝ ለመይኩኪ ወለተ አናብስት በከመ ይቤ ሰሎሞን ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ ወትወፅኢ እምግበበ አናብስት ጥቀ ግሩም ዜና ልደትኪ እምሕዝብ ዘይትሜካሕ ወእምነገድ ኀሩይ"* (ዳግመኛም የአንበሶች ልጅ ነሽ እልሻለኊ፤ የልደትሽ ዜና እንደ አንበሳ ጩኸት እንደ ሴት አንበሳ ድምፅ ነውና፤ ይሁዳን አባቱ ያዕቆብ የአንበሳ ግልገል ብሎታልና (ዘፍ ፵፱፥፱)፤ ስለዚኽም የአናብስት ልጅ አልኹሽ ሰሎሞን እንዲኽ ሲል እንደተናገረ ሙሽራዬት ሆይ ከሊባኖስ ተራራ ነዪ ከአንበሶች ጕድጓድ ወጥተሽ ነዪ (ማሕ ፬፥፲)፤ ከምርጥ ነገድነት የተነሣ ከሚመካ ወገን የመወለድሽ ዜና እጅግ ግሩም ነው)[51] በማለት አመስጥሮታል።

[50] ተአምረ ማርያም ገጽ ፳፻፮-፫፻፯፤ ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ፤ ነገረ ማርያም

[51] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሠሉስ ምዕ ፲፪፥፲፭-፲፫



www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ የነገረ ማርያም መጽሐፋቸው ላይ ይኽነን የሰሎሞንን ቃል ሲተረጉሙ

*"ለንጉሠ ነገሥት ሰሎሞን ከመ ተፈሥሐ ልቡ*
*በዕለተ ወፃእኪ መርዓት ለአንበሳ ትንቢት እምግቡ*
*ማእከለ ማኅበር ፍሱሓን ተአምረኪ እንዘ እነቡ*
*እዜምር ለኪ ጽጌ ሐና ወፍኖተ ነፈርዐጽ እሌቡ*
*ከመ ጣዕዋ ሐሊበ ዘይጠቡ"*

(ትንቢት ከተነገረለት ከአንበሳ ጉድጓድ፤ ድንግል ሙሽራ በተገኘሽ ጊዜ የንጉሦች ንጉሥ የሰሎሞን ልቡ እንደተደሰተ፤ ደስ ባላቸው በመላእክት አንድነት ፊት ታምርሽን እየተናገርኹ የሐና አበባ ማርያም እዘምርሻለኹ፤ ወተትን ጠብቶ እንደሚዘል እንቦሳም ዝለል ዝለል ይለኛል)[52] በማለት ሰሎሞን ስለቅድስት ድንግል ማርያም ልደት የተናገረው ትንቢት ፍጻሜውን አግኝቶ ደስታን ለኹላችን እንደሰጠን አብራርተው ገልጠዋል፡፡

## የተቈለፈች ገነት፣ የታተመች የውሃ ጒድጓድ

ጠቢቡ ሰሎሞን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልና፣ ከኀጣውእ ከፍትወታት ተጠብቃ የሕይወት ተክል፣ የሕይወት ውሃ ክርስቶስን የምትወልድ መኾኗ ተገልጾለት በማሕ ፬፥፲፪-፲፫ ላይ *"ገነት ዕጹት እኅትየ መርዓት ገነት ዕጹት ዐዘቅት ኅትምት"* (እኅቴ ሙሽሪት የተቈለፈች ገነት የተዘጋች ገነት የታተመች ጒድጓድ ናት) በማለት በምሳሌ ተናግሯል፡፡ ይኸውም በሀገራቸው ይኽነን ተክል ሌባ እንዳይደርስበት አሪያ እንዳይኮሳበት፣ ቀበሮ እንዳይተነፍስበት በውጭ በውስጥ ዐጥረው ሲያኖሩት፤ የውሃ ጒድጓድዱን ደግሞ ጠላት መርዝ እንዳይበጠብጥበት ንስናሽ እንዳይጥልበት ፍንጃል የሚባል ቀለም ለብጠው ለ፲ ለ፳ የማይነሣ መግጠሚያ አድርገው ያኖሩታል፡፡

ይኽቺን ተክል በውስጧ የያዘችውን ገነት (የተክል ቦታ) ሌባ እንዳይደርስባት አውሬ እንዳይተነፍስባት በውስጥ በአፍአ ታጥራ እንድትጠበቅ ኹሉ አማናዊ የሕይወት ተክል ጌታን በማሕፀኗ የተሸከመች ገነት ነባቢት የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያምም ከእናቷ ማሕፀን ገሮምራ በረድኤተ እግዚአብሔር ተጠብቃ ኖራለች፤ የሐሳብ ኀጢአት ክፉ የለባትምና ገነት በርሷ፣ ተክል በጌታ፣ አጥር በረድኤተ እግዚአብሔር ተመስሏል፡፡

[52] አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ፤ ቍ ፵፯



ዳግመኛም ይኽቺን ውሃ የያዘች ጒድጓድን ጠላት መርዝ ንስናሽ እንዳይጥልባት ደንጊያ እንዲገጥሟት የሕይወት ውሃ ክርስቶስን የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምም ልማደ አንስት ዘርዐ ወራዙት ፈጽሞ የለባትም፤ ቅድመ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ፀኒስ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ፀኒስ ድኅረ ወሊድ ዘላለማዊት ድንግል ናት፡፡

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ሰሎሞን በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የተናገረላት የቅድስት ድንግል ማርያምን በረከት በመሻት በመዐዛ ቅዳሴው ላይ *"ንዒ ማርያም ዳዊት ዘወደሰኪ ወሰሎሞን ዘሐለየኪ እንዘ ይብል ገነት ዕጹት ወዐዘቅት ፍትምት ፍናወ ዚኣኪ ርግብየ ሠናይት"*

(ዳዊት ያመሰገነሽ መንገድሽ የታጠረች ተክል የታተመችም ጒድጓድ ነች፤ እንዲኽ እያለ ሰሎሞን የዘመረልሽ መልካማ ርግብ ማርያም ሆይ በረድኤት ነዪ)[53] በማለት አመስግኗታል፡፡

ኢትዮጵያውያን የነገረ ማርያም ሊቃውንትም ይኽነን የሰሎሞንን ቃል በጥልቀት ሲተረጉሙት *"ማርያምሰ ድንግል ይእቲ በክልኤ ፍና እምኵሉ ፍትወት ዘሀሎ ውስተ ዝንቱ ዓለም፤ ወኢቦአ ኀሊና ስሕተት ውስተ ልባ ወኢቀርባ ወኢምንተኒ ርስሐተ ዓለም እስመ መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ ወነተማ ከመ ኢይባእ ምንተኒ ርስሐት ውስተ ኀሊናሃ፤ ወኅትምት ይእቲ በከመ ይቤ ሰሎሞን በእንቲአሃ በማሕልየ መሓልይ ገነት ዕጹት ወዐዘቅት ኅትምት፤ ወአልቦ አመ ተርኅወ ማዕፆ ማኅተመ ድንግልናሃ ዘኀሊናሃ ወአልቦ አመ ማሰነ ማዕጾ ማኅተመ ድንግልና ሥጋሃ ኢበፀኒሶታ ወኢበወሊዶታ፤ ወእምድኅረ ወሊዶታ ድንግል ይእቲ በሥጋሃ ወድንግል ይእቲ በኀሊናሃ ዘኢይፀራዕ ስብሐተ ድንግልናሃ በአፈ ሰብእ ወመላእክት"*

(ማርያም ግን በዚኽ ዓለም ካለ ሥጋዊ ፈቃድ ኹሉ በኹለት ወገን ማለት በነፍሷም በሥጋዋም ድንግል ናት፤ የስሕተት አስተሳሰብ በአእምሮዋ (በልቧ) ውስጥ አልገባም፤ በዚኽ ዓለም የኀጢአት መሠረት የሚኾን ሥጋዊ ፈቃድ ወደርሷ አልቀረበም በአእምሮዋ ውስጥ ሠርጎ እንዳይገባ መንፈስ ቅዱስ ጠብቋታልና፤ ሰሎሞን በማሕልዩ ስለርሷ የታጠረች የተክል ቦታ የተቈለፈች ጒድጓድ ነች ሲል ተናግሯልና፤ በእውነትም የታተመች ናት፤ በመፅነሷም ኾነ በመውለዷ ጊዜ የድንጋሌ ሥጋዋ በር የተለወጠበት ጊዜ የለም፤ የድንጋሌ ኅሊናዋም በር የተከፈተበት ጊዜ የለም ከወለደችም በኋላ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች በመኾኗ በማያቋርጥ ምስጋና በሰው አንደበትና በመላእክት ዘንድ

[53] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መዐዛ ቅዳሴ ቍ ፳፯



www.ethiopianorthodox.org

ድንግልናዋ ሲመሰገን ይኖራል)[54] በማለት በጥልቀት አስተምረዋል፡፡

ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በመጽሐፈ ምስጢር ላይ ይኽንን ሲተረጕም *"ሕዝቅኤልኒ ይቤ ርኢኩ ኆኅተ በምሥራቅ ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም አልቦ ዘቦአ ዘእንበለ እግዚአ ኃያላን ቦአ ውስቴታ ወወፅአ፤ ዝኒ ዜና ማኅተም ዘአንቀጸ ሥጋሁ፤ ሰሎሞን ይቤ ገነት ዕጹት ዐዘቅት ኅትምት ፍናወ ዚአኪ ምንት ይትረከብ በኀበ ገነት አኮኑ ፍሬ አስካል ጥዑም ወምንትኑ ፍሬ አስካል ጥዑም አኮኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍሬ ድንግልናሃ ለእሙ ወብሂለ ገነትሰ ዕጹት ይትረጐም በአንቀጸ ሥጋሃ ዘዕጹት በመናሥግተ ድንግልና፤ ምንትኑ ካዕበ ይትረከብ ኀበ ዐዘቅት ዘእንበለ ማይ ጥዑም ወምንትኑ ማይ ጥዑም ዘእንበለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይቤ በወንጌል ዘጸምአ ይምጻእ ኀቤየ ወይስተይ፤ ወብሂለ ዐዘቅትሂ ኅትምት ኀይለ ድንግልናሃ ዘንጽሕት እም፤ ኵሉ ኵሉሙ ነቢያት ሰመይዋ ኅትምተ በድንግልናሃ ወዕጹተ በእንተ አንቀጸ ሥጋሃ"*

(ሕዝቅኤልም ድንቅ በኾነ ታላቅ ማኅተም የታተመች ደጃፍ በምሥራቅ አየኍ፤ ከኃያላን ጌታ በቀር የገባበት የለም ርሱ ገባበት ወጣም እንጂ አለ (ሕዝ ፵፬፥፫)፤ ይኽም የድንጋሌ ሥጋዋ ማኅተም ዜና ነው፤ ሰሎሞንም የተዘጋች ገነት የታተመች ጕድጓድ ጕዳናዎችሽ ናቸው አለ፤ በገነት ምን ይገኛል ጣፋጭ ፍሬ አይደለምን፤ የተዘጋች ገነት ማለት በድንግልና ቊልፍ በተዘጋች በድንጋሌ ሥጋዋ ይተረጐማል፤ ኹለተኛም ከጣፋጭ ውሃ በቀር ከውሃ ጕድጓድ ምን ይገኛል ፤በወንጌል የተጠማ ወደኔ ይምጣ ብሎ ከተናገረ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ጣፋጭ ውሃ ማን ነው (ዮሐ ፯፥፴፯) ፤የታተመች የውሃ ጕድጓድ ማለት የንጽሕት እናቱ የድንግልናዋ ኀይል ነው፤ ነቢያት ኹላቸው በድንግልናዋ የታተመችን ስለ ድንጋሌ ሥጋዋም የተዘጋች ብለዋታልና)[55] በማለት ሙሉ ትርጓሜ በመስጠት የሰሎሞንን ቃል አመስጥሮታል፡፡ ዳግመኛም አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ

*"ሰመዩኪ ነቢያት እለ ርእዩ ኅቡኣተ*
*ገነተ ጽጌ ዕጹተ ወኆኅተ ምሥራቅ ኅትምተ*
*እግዚአብሔር ወሀበ ለቤተ ዳዊት ትእምርተ /ትንቢተ/*
*ከመ ትፀንሲ ድንግል ወትወልዲ ሕይወተ*
*ኢሳይያስኒ ነገረ ክሡተ"*

[54] ተአምረ ማርያም ገጽ ፫፻፮

[55] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መጽሐፈ ምስጢር ገጽ ፺፰





(የተሰወሩ ምስጢራትን ያዩ ነቢያት የተዘጋች የአበባ ገነት የታተመች የምሥራቅ በር አሉሽ (ማሕ ፬፥፲፪፤ ሕዝ ፵፬፥፩-፫)፤ ድንግል በድንግልና ሕይወትን እንደምትፀንሺ እንደምትወልጂ እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ምልክትን ሰጠ፣ ትንቢትን አናገረ፤ ኢሳይያስም በግልጽ ተናገረ (ኢሳ ፯፥፲፬))[56] በማለት ይኽ የሰሎሞን ቃል ከሌሎች ነቢያት ጋር ያለውን የምስጢር ትስስር አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ የክብር ጕድጓድነቷን ሲያመሰጥር *"ኦ ዐዘቅተ ክብር ኅትምት ወተቀድሐ ማይ እምውስቴታ ማኅተመ ዚአሃ ዘእንበለ ይትከሠት ኦ ገነት ዕጹት ወተቀስመ ፍሬሃ ዘእንበለ ይትረኀው መንሥኀ ጥንታ"* (ቊልፉ ሳይከፈት ከውስጧ የሕይወት ውሃ የተቀዳባት የተቈለፈች የክብር ጕድጓድ ሆይ፤ የደጃፉ ቊልፍ ሳይከፈት ፍሬዋ የተለቀመ የተዘጋች ቦታ ድንግል ሆይ)[57] በማለት በኅቱም ድንግልናዋ ፍሬ ሕይወት፣ ማየ ሕይወት ፈጣሪያችን ክርስቶስን ለወለደችልን ለእመቤታችን የሰሎሞን የተቈለፈች የተክል ቦታ፣ የተዘጋች የውሃ ጕድጓድ ምሳሌዋ መኾኗን ሲያብራራ፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ምስጢሩን በመጠቅለል *"ገነት ዕጹት ወዐዘቅት ኅትምት"* (የታጠረች ተክል፤ የተዘጋች የውሃ ጕድጓድ አንቺ ነሽ)[58] በማለት አመስግኗታል፡፡

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በተጨማሪም በእንዚራ ስብሐት የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ ምስጢሩን ጠቅልሎ ሲተነትነው

*"ኦ እግዝእትየ ማርያም ገነት ዕጹት እንተ አልቦ ኪያኪ ዘያርኅ*
*በውስቴትኪ መዐዛ ነፋሳት ይነፍሑ*
*አንቲ ውእቱ ለሰሎሞን ዐጸደ ቀምሑ"*

(አንቺን የሚከፍት የሌለ የተዘጋች ገነት እመቤቴ ማርያም ሆይ በውስጥሽ መዐዛ ያላቸው ነፋሳት ይነፍሳሉ፤የሰሎሞን የአዝመራው ቦታ አንቺ ነሽ)[59] በማለት የመዐዛ ንጽሕናዋ፣ የመዐዛ ቅድስናዋ ነገር በአጅጉ የሚያስደንቅ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች መኾኗን አስተምሯል፡፡

በኋላ ዘመንም ሰሎሞን የተናገረው ይኽ ልዩ ምስጢር ያልተረዳቸው የሕይወት ፍሬ፣ የሕይወት ውሃ የክርስቶስን እናት

[56] አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፳፮

[57] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ አርጋኖን ዘረቡዕ ምዕ ፫፥፲፭

[58] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፳፬

[59] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤እንዚራ ስብሐት ገጽ 49



www.ethiopianorthodox.org

የአማናዊት ገነት ፣የአማናዊት ጉድጓድ የቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት፣ ዘላለማዊ ድንግልና፤ የልጇ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚመሰክረውን እውነተኛውን የሃይማኖት አጥርን ሊያፈርሱ የሚሞክሩ በሃይማኖት በምግባር የጐደሉ ታናናሾች ቀበሮች የተባሉ መናፍቃን የመነሣታቸውን ነገር በማሕ ፪፣፲፭ ላይ *"አሥግሩ ለነ ቈናጽለ ንዑሳነ እለ ያማስኑ ዐፀደ ወይንነ፤ ዐፀደ ወይንነ ይጸጊ"* (የወይን ቦታችን ያብብ ዘንድ የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ታናናሹን ቀበሮች አጥምዳችሁ ያዙልን) በማለት ተናግሯል።

ስለኾነም ይኸነን ንጹሑን ገነት ማለትም በቅዱሳት መጻሕፍትና በቅዱሳን አበው የተመሠረተውን የነገረ ማርያም ትምህርትን ለማበላሸት እንደመጣባቸው በሚተነፍሱ እንዳገኙ በሚጠቅሱ በቀበሮ ከተመሰሉ ከመናፍቃን የስሕተት ትምህርት ሕዝበ ክርስቲያኑን ኑቅተን ተግተን እንድንጠብቅ ለቤተክርስቲያን መምህራን ጌታ በሰሎሞን ዐድሮ አደራ ሰጥቷልና ይኸነን ዐደራ ለመወጣት ራሳችንን ማዘጋጀት ይኖርብናል።

የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ በእጅጉ የበዛላቸው አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ ስለዚኽ ምስጢር ሲያብራሩ

*"አርምሞትኪ ማርያም ኀሰፈ እምአንክሮ*
*እስከ ንሬኢ ሕዝብኪ ለተአምርኪ ግብሮ*
*ገነትኪ ትጽጊ ሰላመ ወተፋቅሮ*
*እለ ያማስኑ ዐፀደ ወይንነ ወፍሮ*
*ቈናጽለ ንኡሳነ አፍጥኒ አሥግሮ"*

(ማርያም የታምርሽን ሥራ እኛ ወገኖችሽ እስከምናይ ድረስ ትዕግስትሽ ከማስደነቅ ዐለፈ፤ ገነትሽ (ቤተ ክርስቲያን) ሰላምንና ፍቅርን ታገኝ ዘንድ የወይን ቦታችንን የሚያጠፉ ታናናሽ ቀበሮዎችን ፈጥነሽ ያዥልን)[60] በማለት አስተምረዋል።

ጠቢቡ ሰሎሞን በዚኹ በመቀጠል የቅድስት ድንግል ማርያም መዐዛ ምግባሯ፤ መዐዛ ቅድስናዋ፣ መዐዛ ንጽሕናዋ፤ መዐዛ ድንግልናዋ ተገልጾለት ይኸነንም በተለያዩ ድንቅ መዐዛ ባላቸው ሽቱዎች መስሎ ሲናገር *"ገነት ምስለ ፍሬ አቅማህ ቆዕ ምሰለ ናርዶስ፣ ናርዶስ ዘምስለ መጽርይ ቀጺመታት ወቀናንሞስ ምስለ ኵሉ ዕፀወ ሊባኖስ ከርቤ ወዐልው ምስለ ኵሉ መቅድመ ዕፍረታት ነቅዐ ገነት ዐዘቅተ ማየ ሕይወት"*

[60]አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፳፮





(ቡቃያሽ ሮማንና የተመረጠ ፍሬ ቆዕ ከናርዶስ ጋር ያለበት ገነት ነው፤ ናርዶስ ከቀጋ ጋር የሽቱ ሣርና ቀረፋ ከልዩ ልዩ ዕጣን ጋር፤ ከርቤና እሬት ከክቡር ሽቱ ኹሉ ጋር አንቺ የገነት ምንጭ የሕይወት ውሃ ጉድጓድ ከሊባኖስም የሚፈስስ ወንዝ ነሽ) በማለት የሕይወት ውሃ የክርስቶስ እናቱ በሊባኖስ የተወለደቿው የቅድስት ድንግል ማርያምን ልዩና ድንቅ መዐዛ ተናግሯል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ይኸነን የሰሎሞንን ቃል በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ ሲገልጸው *"ሰሎሞን አቡኪ ተነበየ ወይቤ ጼና አንፍኪ ከመ ጼና ስኂን ገነት ዕጹት እኅትየ መርዓት ገነት ዕጹት ዐዘቅት ኅትምት ፍናወ ዚአኪ ገነት ምሰለ ፍሬ አቅማሕ ቆዕ ምሰለ ናርዶስ ናርዶስ ዘምስለ መጽርይ ቀጺመታት ወቀናንሞስ ምስለ ኵሉ ዕፀወ ሊባኖስ ከርቤ ወዐልው ምሰለ ኵሉ መቅድመ ዕፍረታት ነቅዐ ገነት ዐዘቀተ ማየ ሕይወት ዘይውኅዝ እምሊባኖስ"* (አባትሽ ሰሎሞን ያፍንጫሽ መዐዛ እንደ ነጭ ዕጣን መዐዛ ነው ብሎ ትንቢት ተናገረ፤ እቴ ሙሽራዬ ሆይ የታጠርሽ ተክል ነሽ፤ መንገድሽም የታጠረች ተክል የታተመች ጉድጓድ ናት፤ ከሽቱ ቅመም ጋራ ሽቱ አለሽ፤ ቆዕ የሚባል ሽቱ ናርዶስ ከሚባል ሽቱ ጋር አለሽ፤ ናርዶስ የሚባል ሽቱ መጽርይ ከሚባል ሽቱ ጋር አለሽ፣ ቀጺመታት ቀናንሞስ የሚባሉ ሽቶች ከደጋ ሽቶች ጋር አሉሽ፤ ከሽቶች ኹሉ የሚበልጡ ከርቤና ዐልው የሚባሉ ሽቶች ከነዚኽ ኹሉ ሽቶች ጋር አሉሽ፤ የገነት ፈሳሽ ሆይ ከደጋ የሚፈስ የሕይወት ውሃ ጉድጓድ ነሽ)[61] በማለት የመዐዛዋን ነገር አድንቋል።

የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ በእጅጉ የበዛለት ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን ምስጋናው ከሰሎሞን ቃል በመነሣት የመዐዛ ቅድስናዋን ነገር ሲያደንቅ

*"ወእጠዊ ውስተ አፉየ እምፍሬ ከርሥኪ ጥዑም ለጉርዔየ ደመ አስካልኪ ወመድምም ለአንፍየ መዐዛ ዕፍረትኪ ከመ ዘሰትየ ወይነ ከራሜ ያስተፌሥሓ ለልብየ ስብሐተ ድንግልናኪ ሚመጠን ፍሥሐየ በእንቲኣኪ ወሚመጠን ሐሤትየ በእንተ ክብርኪ አዳም ንባብኪ ወመዓርዒር ቃልኪ ሙሐዘ ፍሥሓ ከናፍርኪ ወሙሒዘ ስብሐት ልሳንኪ ጥቀ ሠናይኪ ወጥቀ አደምኪ አፈቅሮ ለፍግዐኪ ዘቆምኪ ይመስል በተቀልተ ወጼና አልባስኪ ከመ ርሑ አፈው ወጼና አንፍኪ ከመ ጼና ወይን (ማሕ ፯፥፯-፰) ወመከሥተ አፉኪ ምዑዝ ከመ ጼና ጽጌ ቀናንሞስ ዘምስለ ኵሉ ዕፀወ ሊባኖስ"*

[61][illegible] አንቀጸ ብርሃን ቍ ፲፮



www.ethiopianorthodox.org

(ከማሕፀንሽም ፍሬ ወደ አፌ እጨምራለኹ፤ የፍሬሽ ደምም ለጉሮሮዬ የጣፈጠ ነው፤ የሽቱሽ መዐዛም ለአፍንጫዬ ያማረ ነው፤ የድንግልናሽ ክብርም ልቡናዬን እንደ ከረመ ንጹሕ ወይን ደስ ያሰኘዋል፤ ስለ አንቺ ያለኝ ደስታ ምን ያኽል ነው፤ አነጋገርሽ ያማረ ነው፤ ቃልሽም የጣፈጠ ነው፤ ከንፈሮችሽም የደስታ ምንጭ ናቸው፤ አንደበትሽም የምስጋና መፍለቂያ ነው፤ እጅግ በጣም አማርሽ ቁመትሽ የሰሌን ዛፍ፤ የልብሶችሽ መዐዛም አፈው በመባል እንደሚታወቀው ሽቱ፤ የአፍንጫሽ መዐዛም እንደ ወይን አበባ ሽታ የሚኾንልሽ ድንግል ሆይ ደስታሽን አወደዋለኹ (ማሕ ፯፥፰) የአፍሽም አከፋፈት እንደ ቀናንሞስ አበባ የጣፈጠ ነው፤ ከሊባኖስ ዕንጨቶች ኹሉ ጋር (ማሕ ፬፥፲፬))[62] በማለት እንደ ሰሎሞን ርሱም የፈጣሪውን እናት አመስግኗል።

## ርግበ ሰሎሞን

ጥበብ ሥጋዊ ጥበብ መንፈሳዊ በእጅጉ የተሰጠው ይኸ ሰሎሞን በመንፈሰ እግዚአብሔር በመቃኘት በየዋህነቷ በርግብ የተመሰለች ቅድስት ድንግል ማርያምን ስፍር ቍጥር ከሌላቸው ከሌሎች ሴቶች ተለይታ ለአምላክ እናትነት ብቸኛ ተመራጭ መኾኗን በማሕ ፮፥፰-፲ ላይ "አዋልድ እለ አልቦን ኍልቍ" (ቍጥር የሌላቸው ቆነጀጅርት አሉ) በማለት ስፍር ቍጥር የሌላቸው እጅግ የበዙ ሴቶች መኖራቸው ከተናገረ በኋላ "አሐቲ ይእቲ እምኔሆን ርግብየ ፍጽምትየ" (ርግቤ መደምደሚያዬ አንዲት ናት) ብሎ ከነዚያ ኹሉ ተለይታ በየዋህነቷ በርግብ የተመሰለችው ቅድስት ድንግል ብቸኛ እናት ትኾነው ዘንድ በአምላክ የመመረጧን ነገር አስተምሯል።

ስለዚኽ ነው አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ እንደርሷ ያለች ማንም የሌለች ብቸኛ የአምላክ ማደሪያ ስለመኾኗ "ሐሰሣን ነጸረ እግዚአብሔር አብ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራብ ሰሜነ ወደቡብ ወውስተ ኵሉ አጽናፍ፤ አስተንፈሰ ወአጼነወ ወኢረከበ ዘከማኪ ወሠምረ መዐዛ ዚአኪ ወአፍቀረ ሥነኪ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር" (እግዚአብሔር አብ በሰማይ ኾኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችንም ኹሉ በእውነት ተመለከተ፣ ተነፈሰ፣ አሸተተም፤ እንደ አንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺን መዐዛ ወደደ፤ የሚወደው ልጁንም ወደ አንቺ ሰደደ)[63] በማለት የወልደ እግዚአብሔር ማደሪያ ለመኾን የመመረጧን ነገር ገልጾታል።

[62] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሠሉስ ምዕ ፲፬፥፲፮-፳





ጠቢቡ ሰሎሞን በመቀጠልም "አሐቲ ይእቲ ለእማ ወኀሪት ይእቲ ለእንተ ወለደታ" (ለእናቷ አንዲት ናት፤ ለወለደቻትም የተመረጠች ናት) በማለት 'እናቷ ቅድስት ሐና በመካንነት ከኖረች በኋላ የወለደቻት አንዲት ቅንጣት ምርጥ ልጇ መኾኗ ተገልጾለት ተናግሯል።

ይኸውም በነገረ ማርያም እንደተጻፈ ሐና አንድያ የተመረጠች ልጇን በተሳለቺው መሠረት ለቤተ መቅደስ እስክትሰጣት ድረስ ከፍቅሯ ጽናት የተነሣ ላፍታ እንኳን ተለይታት አታውቅም ነበር፤ ከዕለታት አንድ ቀን ለጥቂት ጊዜ ብቻዋን አድርጋት ወጥታ ሳለ፤ መልአኩ ሰውሮባት ፈልጋ አግኝታታለች፤ ከዚያ በኋላ ኹሌ ያው እየመሰላት ተለይታት አታውቅምና ጠቢቡ አባት ሰሎሞን በትንቢት መነጽርነት ይኸ እየታየው (ለእናቷ አንዲት ናት፤ ለወለደቻትም የተመረጠች ናት) ብሎ አስቀድሞ ገልጾታል።

ከሊቃውንት መኻከል አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ ይኸንን የሰሎሞንን ቃል በመያዝ በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ

"ሚ ቡርክት ወቅድስት ይእቲ
ሰዓተ ትፍሥሕት ሐና ዘጸገየተኪ ባቲ
ወፈረየኪ ለሕይወት ኢያቄም መዋቲ
እሴብሕ ተአምረኪ ርግብየ አሐቲ
ወድኅኒተ ኵሉ ዓለም እስመ ኮንኪ አንቲ"

(ሐና አንቺን የፀነሰችባት የደስታ ቀን ምን ያኽል የተባረከች የተቀደሰች ናት፤ ሟች ኢያቄምም ለሕይወት አንቺን ያፈራባት ቀን ምን ያኽል የተባረከች የተቀደሰች ናት፤ አንዲቱ ርግቤ ማርያም አንቺ የዓለሙ ኹሉ መድኀኒት ኾነሻልና ታምርሽን አመሰግናለኹ)[64] በማለት ዓለምን ኹሉ በደሙ ፈሳሽነት ያዳነ ንጉሣችን፣ ፈጣሪያችን ክርስቶስን በድንቅ ተአምር ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ የወለደችልን ምክንያተ ድኅን ርግበ ሰሎሞን የተባለች ቅድስት ድንግልን አመስግነዋል።

ይኸ አባት ሰሎሞን በመቀጠል "ርዕያሃ አዋልድ ወአስተብፅዓሃ፤ ንግሥታት ወዕቁባት ወደሳሃ" (ቆነጃጅት አይተው አሞገሱአት፤ ንግሥታትና ዕቁባትም አመሰገኑአት) በማለት የሰማይና የምድር ፈጣሪ ንጉሥ ክርስቶስን የወለደች ንግሥት ድንግል ማርያም በ፲፪ቱ ሐዋርያት፤ በ፸፪ቱ ክርስቶስን የወለደች ንግሥት ድንግል ማርያም በ፲፪ቱ ሐዋርያት፤ በ፸፪ቱ አርድእት፤ በ፴፮ቱ ቅዱሳት አንስት ከዚያም እስከ ዕለተ ምጽአት በሚነሡ ምእመናን ኹሉ ንእድ ክብርት እየተባለች የምትመሰገን መኾኗ

[63] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፳፬



www.ethiopianorthodox.org

ተገልጸለት ከተናገረ በኋላ *"መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ትሔውጽ ከመ ጎሕ ሠናይት ከመ ወርኅ ወብርህት ከመ ፀሓይ"* (ይኽቺ እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጐበኝ እንደ ጨረቃ የተዋበች፤ እንደ ፀሓይም የጠራች ዐላማ ይዞ እንደተሰለፈ ሰራዊት የምታስፈራ ማን ናት?) በማለት እንደ ፀሓይ የሞቀ እንደ ጨረቃ የደመቀ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ በነቢያት ትንቢት አስቀድሞ የተጐበኘላት የእውነት ፀሓይ የክርስቶስ እናት የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር ተናግሯል።

ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በአርጋኖን የነገረ ማርያም መጽሐፍ ላይ የሰሎሞንን ቃል በመጥቀስ *"ወእንሰ እትፌሣሕ በእንቲአኪ ኦ ሀገረ እግዚአብሔር ወእትሐሰይ ብኪ ኦ ኤዶም ገነት ነባቢት እንተ ርእዩኪ ነቢያት ከመ ጎሕ ድልው ለወሊደ ፀሓይ በከመ ይቤ ሰሎሞን አቡኪ አይ ይእቲ ዛቲ እንተ ታስተርኢ ከመ ጎሕ"*

(የእግዚአብሔር ሀገር ሆይ እኔም ደስ እሰኝብሻለኁ፤ ፀሐይን ለመውለድ እንደተዘጋጀ ወገግታ ነቢያት ያዩሽ የምትናገሪ ኤዶም ገነት ሆይ ደስ እሰኝብሻለኁ፤ እንደማለዳ ብርሃን የምትታይ ይኽቺ ማን ናት? በማለት አባትሽ ሰሎሞን እንደተናገረ)[65] በማለት የፀሐየ ጽድቅ የክርስቶስ እናትነቷን በማጕላት ተርጕሞታል።

## ሱላማጢስ

ይኽ ሰሎሞን መኀነ ልደቷ፣ ዘላለማዊ ድንግልና ፣ቅድስናዋ፣ የአምላክ እናትነቷ ተገልጾለት እንደተናገረ ኹሉ በተጨማሪም ፍቅር አንድነት የተሰጣት፤ ፍቅር አንድነትን በቃል ኪዳኗ የምታሰጥ ፍጽምት በመኾኗ ምክንያት ሱላማጢስ የተባለች የቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታ ጋር ወደ ግብጽ የመሰደዷ ነገር ተገልጾለት በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በማሕ ፯፥፩ ላይ

*"ተመየጢ ተመየጢ ሱላማጢስ፤ ተመየጢ ወንርአይ ብኪ ሰላመ"* (አንቺ ሱላማጢስ ሆይ ተመለሺ እናይሽ ዘንድ ተመለሺ) በማለት ሱላማጢስ (ፍቅር አንድነት የተሰጣት፤ ፍቅር አንድነት የምታሰጥ ፍጽምት) ቅድስት ድንግል ተመለሺ ተመለሺ ባንቺ የተደረገውን ተድላ ደስታ እንይ ሲል እመቤታችን ርጕም ሄሮድስ በነገሠበት ወራት ከሀገሯ ተሰዳ ከልጇ ጋር ፫ ዓመት ከ፮ ወር ብዙ ፀዋትወ መከራ ተቀብላ፤ ንጉሡ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የጭንቁ የመከራው ጊዜ ዐልፎ ወደ ሀገሯ የመመለሷ

[64] አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፵፬
[65] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሠሉስ ምዕ ፩፥፲-፲፩





ነገር ተገልጾለት በናፍቆት አንቺ ሱላማጢስ ተመለሺ ተመለሺ እያለ ትንቢቱን ተናግሮላታል። ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የኾኑት አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ የነገረ ማርያም መጽሐፋቸው ላይ በበረሓ እንደምትኖረው ዋኖስ ሱላማጢስ የተባለች እመቤታችንም ከልጇ ጋር በግብፅ በረሓ መኖሯን

*"ኦ ሰላመ ሰጣዊት እንተ ትሔውጺ እምርሑቅ*
*ወትትረአዩ ለኵሉ በደብረ ምጥማቅ*
*ተፈሥሒ ድንግል ዘገዳመ ጽጌ ማዕነቅ*
*እስመ ተሰምዐ በምድርነ ቃለ ተአምርኪ ጽድቅ*
*ለአድኅኖ ዓለም ዘይበቍዕ እምብሩር ወወርቅ"*

(ፍቅር አንድነት የተሰጠሽ ፍቅር አንድነት የምታሰጪ ፍጽምት (ሱላማጢስ) ድንግል ከሩቅ የምትጐበኚ ነሽ፤ በደብረ ምጥማቅ ለኹሉ የምትታዪ የበረሓ አበባ ዋኖስ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ ፤ከብርና ከወርቅ ይልቅ በደለኛን ለማዳን እውነት ያለበት የታምርሽ ቃል በምድራችን ተሰምቷልና ደስ ይበልሽ)[66] በማለት የሰሎሞንን ማሕልይ መነሻ በማድረግ ተርጕመውታል።

ቅድስት ቤተክርስቲያናችንም ይኽነን የሰሎሞንን ቃል መነሻ በማረግ የጌታን ከእናቱ ጋር ወደ ግብጽ መሰደዱን በምታስብበት ከመስከረም ፳፮- ኅዳር ፭ ባሉት ጊዜያት ከጸሎተ ኪዳን መግቢያ ላይ እንደመርገፍ አድርጋ በዜማ ታመሰግንበታለች።

ጠቢቡ ሰሎሞን በመቀጠል በቍጥር ፫ ላይ *"ከርሥኪ ሥዉጠ ሥርናይ ወሕጹር በጽጌ"* (ኾድሽ እንደ ስንዴ ክምር በአበባም የታጠረ ነው) በማለት የእመቤታችን ማሕፀኗ ሥጋውን በአምሳለ ኅብስት የሰጠን የወልደ እግዚአብሔር ማደሪያና፤ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የታጠረ የተከበበ መኾኑን ተናግሮላታል።

. ከሊቃውንት መኻከልም አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ ይኽነን የሰሎሞን ቃል ሲተረጕሙ

*"ከመ ፍሕሶ ቀይሕ ከናፍርኪ ጽጌ*
*ሥዉጠ ሥርናይ ከርሥኪ ወሕጹር በጽጌ*
*ትእምርተ ሕይወትየ ድንግል ወዘጕንደ መንግሥት ጽጌ*
*በማሕሌተ ጽጌ እዌድሰኪ ለጽጌ*
*ተቀጺልየ ዘንጽሕኪ ጽጌ"*

[66] አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ፤ ቍ ፲፭



www.ethiopianorthodox.org

(ከንፈሮችሽ ፍሕሶ እንደሚባል ቀይ ልም ሐር ናቸው (ማሕ ፬፥፫) ኸድሽ ስንዴን የተመላ በአበባ የተከበበ ድንግል ሆይ፤ የድንኅቴ ምልክትና የመንግሥት ሥር መሠረት አንቺ ነሽና፤ የንጽሕናሽን ክብር ዘውድ ተቀዳጅቼ፤ አበባ (አንቺን) በማሕሌተ ጽጌ አመሰግንሻለሁ)[67] በማለት የመንግሥት ሥር መሠረት የኾኑ እነ ዳዊት እነ ሰሎሞን ባመስገኑበት ቃል እነርሱም የሚያመሰግኑ መኾናቸውን ገልጸዋል።

ሰሎሞን በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በዚኹ ምዕራፍ ከቍጥር ፯-፲ ላይ በስፋት የተናገረውን የመልኳን ደም ግባትና በሌሎች ምዕራፎች ላይ ሰሰርሷ የተናገራቸውን የምስጋና ቃላት ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በአንድ ላይ ሲተነትን "ኦ እግዝእትየ መርዓት እምግበበ አናብስት ዘወፃእኪ ወእምአድባረ አናምርት ወእምታዕካ ዘነገሥት፤ ዘቆምኪ ይመስል በቀልተ ወክሣድኪ ከመ አርማስቆስ ግብረ እደ ኬንያ አዕይንትኪ ከመ ኮከበ ጽባሕ (ማሕ ፬፥፱፤፯-፲) ወመላትሕኪ ቀይሕ ከመ ጽጌረዳ ዘሐይቀ ኢያሪኮ ወአስናንኪ ጸዐድዒድ ኀሡባት በሐሊብ ወጣዕመ ቃልኪ እምአስካለ ወይን፤ መዐዛ አፉኪ ከመ ርሔ አፈው፤ ወጼና አልባስኪ ከመ ሠርጸ ጢስ ዘስኂን (ማሕ ፫፥፮) ኵለንታኪ ሠናይት ኦ መርዓት አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ወመዐድም ሥንኪ ወአጥባትኪ ከመ ሐሳ፤ ወይውሕዝ እምኔሆን ሐሊብ ድንግልናዊ በዘቦቱ ተሐፅነ መሴስየ ኵሉ ዘሥጋ (ማሕ ፬፥፯፤፯፥፯-፲)"

(ከነገሥታት እልፍኝ ከእናምርት ተራሮችና ከአናብስት ጕድጓድ የወጣሽ፤ ቁመናሽ የሰሌን ዛፍ የሚመስል ሙሽራዪቱ እመቤት ሆይ፤ አንገትሽ ብልኽ አንጥረኛ እንደሠራው የወርቅ ዘንግ ነው፤ ዐይኖችሽም እንደ አጥቢያ ኮከብ ናቸው (ማሕ ፬፥፱፤፯-፲)፤ ጕንጮችሽ በኢያሪኮ ባሕር ወደብ እንዳለ ጽጌረዳ አበባ ናቸው፤ ጥርሶችሽም በወተት የታጠቡ ነጫጮች ናቸው፤ የአነጋገርሽም ጣዕም ከወይን ፍሬ ወገን ነው፤ የአፍሽም መዐዛ እንደ አፈው ሽታ ነው፤ የልብሶሽም መዐዛ የዕጣን ወገን እንደሚኾን ቅታሬ ጢስ አበቃቀል ነው (ማሕ ፫፥፮)፤ ሙሽራዪት ሆይ ኹለንተናሽ ያማረ ነውና ምንም ምን ነውር የለብሽም፤ ደም ግባትሽ ያማረ ነው፤ ጡቶችሽ እንደ ምንጭ ናቸው፤ ከነርሱም ድንግልና ወተት ይፈሳል፤ ሥጋ የለበሰውን ኹሉ የሚመግብ ጌታ ባደገበት ገንዘብ (ማሕ ፩፥፯፤፯፥፯-፲))[68] በማለት ይኽ ማሕልየ መሓልይ መጽሐፍ በርካቶች የነገረ ማርያም ትምህርቶችን እንደያዘ መስክሯል።

[67] ዝኒ ከማሁ ቍ ፯

[68] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘቀዳሚት ምዕ ፫፥፩-፬





# ምዕራፍ ሦስት

## ነገረ ማርያም በዐበይት ነቢያት

ከነቢያት መኻከል ዐበይት ነቢያት በመባል የሚጠሩት ነቢዩ ኢሳይያስ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ነቢዩ ሕዝቅኤል፣ ነቢዩ ዳንኤል ሲኾኑ፤ እነዚኽ ታላላቅ ነቢያት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው እጅግ በርካታ የዘመነ ሐዲስ ምስጢር ተገልጾላቸው ትንቢትን ተናግረዋል። የተናገሩትም ትንቢት ብዙና ታላላቅ የሥጋዌ ምስጢርን ያካተተ ስለኾነ በሊቃውንት ዘንድ ዐበይት ነቢያት (Major Prophets) የሚል ስያሜን አሰጥቷቸዋል። ታላቁ ሊቅ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ "ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት ዘነቢያት" (ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢትና ምሳሌ አንቺ ነሽ) በማለት እንዳስተማረ እነዚኽ ዐበይት ነቢያት በመላ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናትነት፣ ዘላለማዊ ድንግልና፣ ንጽሕናና ቅድስና፣ ስለ ክብሯና አማላጅነቷ በብዙ ሕብረ ትንቢትና በብዙ ሕብረ አምሳል ተናግረዋል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በአራቱ ዐበይት ነቢያት ኹሉ ክብሯ የተነገረ መኾኑን በመዐዛ ቅዳሴው ላይ "ንዒ ማርያም ለኢሳይያስ ቀርነ ትንቢቱ ወለኤርምያስ ጽርሐ ቅድሳቱ ወለሕዝቅኤል ዋካ ኆኅቱ ዘሠረቀ እምኔኪ ፀሐየ አርያም ዘየኀቱ ዘአብርሀ ለደቂቀ አዳም ሥነ መለኮቱ ወዘቦአ ኀበ አርዳኢሁ እንዘ ኆቱም ማዕጾ ቤቱ ወተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኀይል ወሥልጣን እንዘ ዕጹው መቃብረ ሥጋሁ በዓቢይ ማኅተም ወዐርገ በሥልጣነ መለኮቱ ዘከመ ተወልደ እምኔኪ በትስብእቱ በኪነ ጥበቡ እስመ እግዚአ ኵሉ ፍጥረት ወአምላክነ ውእቱ" (ማርያም ሆይ የኢሳይያስ የትንቢቱ መለከት፤ የኤርምያስም የቅድሳቱ አዳራሽ፤ የሕዝቅኤል የብርሃን ደጃፍ፤ የመለኮቱ ጸዳለ ብርሃን ለአዳም ልጆች ያበራ የአርያም ፀሓይ ከአንቺ የወጣ፤ የቤቱ መዝጊያ ሳይከፈት ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ገብቶ ያጽናናቸው የከበረ ሥጋው መቃብር በቍልፍ እንደተዘጋ በድንጋይ እንደተገጠመ በታላቅ ኀይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፤ በማይመረመር ጥበቡ በሰውነቱ ከአንቺ እንደ መወለዱ መጠን በመለኮቱ ሥልጣን ወደ ሰማይ ያረገ የፍጥረቱ ኹሉ ጌታ የሚኾን ርሱ አምላካችን ነውና በረድኤት ነዪ)[69] በማለት አመስግኗታል። እኔም አራቱ ዐበይት ነቢያት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው ስለ አምላክ እናት የተናገሩትን ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳል አስቀምጪያቸዋለኍ።

[69] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መዐዛ ቅዳሴ ቍ ፴፮



www.ethiopianorthodox.org

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ኢሳይያስ

## ክፍል አንድ

ኢሳይያስ ማለት የስሙ ትርጓሜ መድኀኒት ማለት ሲኾን በነቢይነት መነሣቱ ፯፻፵-፯፻ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው፤ ይኽ ታላቅ ነቢይ ከሌሎች ነቢያት ይልቅ በርካቶች የሐዲስ ኪዳን ምስጢራት አስቀድመው ተገልጸውለት በትንቢቱ ውስጥ ስለተናገራቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ትንቢቱን ከይዘቱ አንጻር "ደረቅ ሐዲስ" በማለት ጠርተውታል።

ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት የአምላክን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና መወለዱን ስሙም ዐማኑኤል መባሉን፤ የርሱን የባሕርይ አምላክነትን የርሷን ወላዲተ አምላክነት በስፋት የተናገረ ሲኾን ከዚኹም ጋር ስለንጽሕናዋ፣ ስለቅድስናዋ፣ ስለአማላጅነቷ፣ የአክብሮት ስግደት የሚገባት መኾኑን በስፋት የተናገረ ነቢይ ሲኾን እኛም በዚኽ የነገረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ዐሥራ አንዱን የነገረ ማርያም ትንቢቱን በዝርዝር አስፍሬያቸዋለኹ።

### ንጽሕት ዘር

ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስና አማላጅነት በትንቢቱ በምዕ ፩፥፱ ላይ *"እግዚአብሔር ጸባኦት እመ ኢያትረፈ ለነ ዘርዐ ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ"* (አሸናፊ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በኾንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር) በማለት እመቤታችን በአምላካዊ ጥበብ ከእናቷ ማሕፀን ዠምራ በአዳም በደል ከመጣው ከመርገመ ሥጋና ከመርገመ ነፍስ ተጠብቃ ያለች ንጽሕት ዘር የመኾኗንና በተጨማሪም ልዩ ስለኾነው አማላጅነቷ በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት ትንቢት ተናግሮላታል።

ይኸውም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ንጽሕት ዘር የተባለችው ቅድስት ድንግል ማርያምን ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ጠብቆ ከሴቶች ኹሉ መርጦ፤ ለርሱ እናት እንድትኾን ለእኛ ደግሞ አማላጅ እንድትኾነን የሰጠን ስለመኾኑ "ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ" በማለት ነቢዩ ገልጾታል። ኢሳይያስ መርገም የሌለባት ስለመኾኑ የተናገረውን ትንቢታዊ ኃይለ ቃልን፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ የመጣው ቅዱስ ገብርኤልም በፊቷ ቆሞ የአዳምና የሔዋን በደል በሰዎች ኹሉ ላይ ካመጣው የጸጋ መራቆትና ከእግዚአብሔር አንድነት የመለየት ጉዳትና ሐዘን ፈጽሞ





ያላገኛት፤ የእግዚአብሔር ጸጋ በምላት ያለባት፤ ከሴቶች ኹሉ ተለይታ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት፤ ስለመኾኗ በብሥራቱ ላይ *"ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት"* (ጸጋን የተመላሽ ደስተኛዪቱ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መኻከል የተባረክሽ ነሽ) በማለት መልአኩ ምስክርነቱን ሰጥቷል (ሉቃ ፩፥፳፰)።

ይኽነን የነቢዩ የኢሳይያስንና የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ምስክርነትን በመያዝ በርካቶች ቅዱሳን አባቶችም ቅድስት ድንግል ማርያም በአምላካዊ ጥበብ ከመርገመ ሥጋና ከመርገመ ነፍስ ተጠብቃ የኖረች ንጽሕት ዘር ስለመኾኗ በስፋት አስተምረዋል።

ከሊቃውንቱ መኻከል ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድጓው፡-

*"ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ጸዐዳ"* (ማርያምስ ከጥንት ዠምሮ በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች)[70] በማለት ዕንቁ ባሕርይ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች፤ ዐዲስ መዝገብ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም አዳም አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስን በመብላቱ ምክንያት ከመጣበት የሥጋና የነፍስ መርገም በጌታ ጥበብ ተጠብቃ የኖረች መኾኑን ሲገልጥ እንደ ነጭ ዕንቍ ታበራለች ብሏል። ምስጢሩም ይኽቹን ነጭ ዕንቍ ከደፈረሰ ባሕር ውስጥ ቢጥሏት እንኳን የደፈረሰው ባሕር የርሷን ጥራት ሳይለውጥ በደፈረሰው ባሕር ውስጥ ሳለች አብርታ እንድታይ ኹሉ፤ ልክ እንደ ዕንቁዋ ቅድስት ድንግል ማርያምም በአዳም ትእዛዝ መተላለፍ ከመጣ መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ በአምላካዊ ጥበብ ተጠብቃ፤ በንጽሕናና በቅድስና ጸንታ የተገኘች መኾኗን ሊቁ በጕልህ ገልጾታል።

ስለ ንጽሕናዋ በስፋት የተነተኑትን የሊቃውንቱን ትምህርት "ነገረ ማርያም በሊቃውንት" ብዬ ወደፊት በምጽፈው መጽሐፍ ላይ በጥልቀት የምተነትነው ቢኾንም ፍጹም ስለኾነው ንጽሕናዋ ካስተማሩ ሊቃውንት ውስጥ ለምስክርነት ጥቂቶቹን ከዚኽ በታች አቅርቤአቸዋለኍ።

"የማርያም ሰውነት የምድር ላይ መቅደስ ነው፤ በርሱም በኀጢአት በሞት በምድር ርግማን ፈንታ የበረከት ዘር የተዘራበት የእግዚአብሔር መልእክተኛ በሰላምታው ይኽነን ዘር ሲዘራ የኤልሳቤጥም ሰላምታ ይኽነን አረጋገጠ"[71] ቅዱስ ኤፍሬም

[70] ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፍ ድጓ ገጽ ፫፻፸፱

[71] Saint Ephrem's commentary on Tatian Diatessaron, IV, ET by C.Mecarthy 1993 pp 91-92



www.ethiopianorthodox.org

"He searched her and found humility..." (መረመራት፤ ትሕትናንና ቅድስናንም በርሷ ውስጥ አየ ንጹሕ ልብ ያላትና አምላኳንም አጥብቃ የምትሻ ነበረች፤ የተቀደሰ ልብና የፍጹምነት ጠባይዓት ኹሉ ነበሯት ስለዚኽም ርሱ ከኹሉ ይልቅ ንጽሕትና ቅን በኾነቺው በርሷ ዐደረ፤ ምክንያቱም ከርሷ ጋር የሚስተካከል አንድ ስንኳ በምድር ላይ አልተገኘምና፤ ርሷ ብቻዋን ትሕት፣ ንጽሕት፣ ጽዕዱት እና መርገም (ኵነኔ) የሌለባት ናት፤ ስለዚኽም ሌላ ማንም ሳትኾን ርሷ ብቻ እናቱ መኾን የተገባች ኾነች...ታላቁ ንጉሥ ወደ እኛ ቦታ ለመምጣት ባሰበ ጊዜ በምድር ላይ ካሉት ኹሉ በእጅጉ ንጽሕት ወደኾነቺው ዐደረ፤ ምክንያቱም ርሱን ደስ አሰኝቶታልና፤ በድንግልናና በቅድስና ክብር አጊተሳሰብ በተጌጠ በንጹሕ ማሕፀን ርሱ ዐደረ)[72] ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ

*"ከመ ገባሪ ጠቢብ ሶበ ይረክብ ግብሮ ዘይትጌበር ይገብር እምኔሁ ንዋየ ሠናየ ከመዝ እግዚእነ ሶበ ረከበ ሥጋሃ ቅዱሰ ለዛቲ ድንግል ወነፍሳ ቅድስት ፈጠረ ሎቱ መቅደሰ ዘቦቱ ነፍስ...ተፈሥሒ ኦ ማርያም እንተ ብኪ ተበትከ ማእሰረ ሐዊን ማሕመሚ አንተ ገደፋ እግዚአብሔር ውስተ ደይን"* (ብልኅ ሸክላ ሠሪ የሚሠራውን የለዘበ ጭቃ ባገኘ ጊዜ ከርሱ መልካም ዕቃ እንዲሠራ፤ እንደዚኽ ጌታችን የዚኽቺን ድንግል ንጹሕ ሥጋዋን ንጽሕት ነፍሷን ባገኘ ጊዜ ነፍስ ያለችውን ሥጋ ሲዋሐደው ፈጠረ...እግዚአብሔር በሲኦል የጣላት የሔዋን ጽኑ ፍዳ ባንቺ የጠፋ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ)[73] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

*"እመቦ ዘኢየአምን ከመ ዐማኑኤል አምላክ ዘበአማን ወድንግልኒ ንጽሕት ከመ ወላዲተ አምላክ ይእቲ ወወለደት ቃለ እግዚአብሔር ዘተሠገወ ውጉዘ ለይኩን"* (ዐማኑኤል የባሕርይ አምላክ እንደኾነ ንጽሕት ድንግልም አምላክን የወለደች እንደኾነች ሰው የኾነ የእግዚአብሔርንም ቃል እንደወለደች የማያምን ሰው ቢኖር ውጉዝ ይኹን)[74] ቅዱስ ቄርሎስ

*"ወእንተ ዝንቱ ተግህደ ቃለ ሐዋርያት ንጹሓን ወአበው መዋእያን ዘይብሉ እስመ አምላክ ቃል ነሥአ ሎቱ ሥጋ እምዘርዐ አብርሃም ወአስተርአየ እምሥርወ ዕሴይ በሥጋ ወኮነ ከማነ ወተሳተፈነ በሥጋ ወደም ወዝንቱ ኮነ እምንጽሕት ወጽሪት ወኅሪት ወቡርክት ወቅድስት*

[72]Jacob of Serugh, On the Mother of God, p.23, On the Virgin, p 924

[73]ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕ ፰፮፥፲፬፤ ፰፰፥፴፰፤ ገጽ ፪፻፲፱፤፪፻፴፬

[74]ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ፤ ምዕ ፸፯ ክፍል ፰፥፭፤ ገጽ ፪፻፶፱





*ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ ወነሥአ እምኔሃ ሥጋ ዘይትዔረየነ በህላዌ ወሕማም ዘቦቱ ነፍስ ነባቢት ወለባዊት ወተዋሐደ ቦቱ በአሐዱ አካል።"*

(ስለዚኽም አምላክ ቃል የነሣውን ሥጋ ከአብርሃም ባሕርይ ነሣ፤ ከዕሴይም ወገን ተወልዶ በሥጋ ተገለጠ እንደ እኛ ያለ ሰውም ኾነ፤ በነፍስ በሥጋም መሰለን ብለው ያስተማሩት የንጹሓን ሐዋርያት የመዋእያን (ተከራክረው የሚረቱ) የሊቃውንት ትምህርት ተገለጠ፤ ይኽም ኹል ጊዜ ድንግል ከምትኾን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ከሌለባት፤ ከከበረች ከተመረጠች፣ ከጠራች ከንጽሕት ማርያም ኾነ፤ የምትናገር፣ የምታውቅ ነፍስ ያለችው በባሕርይ፣ በሕማም እኛን የሚመስል ሥጋንም ከርሷ ነሥቶ አንድ አካል በመኾን ርሱን ተዋሐደ)[75] ቅዱስ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ

"አልቦ ዘይትዔረያ በንጽሕ ወበቅድስና በክብር ወበልዕልና እምከርሠ እማ አንጽሓ ወቀደሳ ለሐኪ አዳም ፈጣሪሃ ከመ ይልበስ ሥጋሃ ወነፍሳ ወኅሊናሃ ድልው ከመ ይልበሶሙ ወልደ እግዚአብሔር እስከ ረሰዮሙ አሐደ ምስለ መለኮቱ" (በንጽሕናና በቅድስና በክብርና በልዕልናም የሚተካከላት ማንም የለም፤ አዳምን የፈጠረ ፈጣሪዋ ከእናቷ ማሕፀን ዠምሮ ፈጽሞ አነጻት፤ ሥጋዋን ይለብስ (ይዋሐድ) ዘንድ ሥጋዋ ነፍሷን ኅሊናዋ የተገቡ ናቸውና፤ ወልደ እግዚአብሔር ይዋሐዳቸው ዘንድ ከመለኮቱ ጋር አንድ እስኪያደርጋቸው ድረስ የማርያም ሥጋዋ ከነፍሷና ከኅሊናዋ ጋር ንጹሕ ነው)[76] **ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ**

"እግዚአብሔር አብ በሰማይ ኾኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችንም ኹሉ በእውነት ተመለከተ፤ ተነፈሰ፣ አሻተተም እንደ አንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺን መዐዛ ወደደ፤ የሚወደውን ልጁንም ወደ አንቺ ሰደደ"[77] አባ ሕርያቆስ

"አኮ እምብዙኃን መናፍስት ዘይትቀድሓ ብዙኃት ሀብታተ እግዚአብሔር ወመክፈልተ ሠናያት አላ እምአሐዱ መንፈስ ውእቱኬ ጰራቅሊጦስ ዘዐቀባ ለድንግል እምከርሠ እማ ከመ ኢትጌጊ ለዓለም፤ አንጽሓ ከመ ኢትርሳሕ፤ ቀደሳ ከመ ኢትርኩስ፤ ወረሰያ ታቦተ ለወልድ ዋሕድ፤ አብ ሠምራ ወልድ ተሠገወ እምኔሃ ወመንፈስ ቅዱስ ከለላ" (ብዙዎች የሚኾኑ የእግዚአብሔር ሀብቶች በጎ ዕድልም የሚቀዱ ከብዙዎች መናፍስት አይደለም፤ ከአንድ ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ፤ ያውም

[75]ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ፤ ምዕ ፪፫ ክፍል ፪፥፲፭፤ገጽ፬፻፵፰

[76]ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ፣ መጽሐፈ ብርሃን፤ ገጽ ፸-፸፪

[77]አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም፤ ቍ፹፬



www.ethiopianorthodox.org

እስከ ዘላለሙ ድረስ እንዳትበድል ከሽኖቷ ማሕፀን ገርምሮ ድንግል ማርያምን የጠበቃት ጰራቅሊጦስ ነው፤ እንዳትተጸደፍ አነጻት፤ እንዳትረክስም ቀደሳት ለአንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ማደሪያን አደረጋት፤ አብ ወደዳት ወልድም ከርሷ ነፍስንና ሥጋን ነሣ፤ መንፈስ ቅዱስም ጋረዳት)[78] (አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ)

ይኽነን ኹሉ አስደናቂ የነገረ ማርያም ትምህርትን ስንመረምር ፍጹም የኾነው የንጽሕናዋ የቅድስናዋ አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱሳን አበው ትክክለኛ አስተምህሮ የተመሠረተ እንደኾነና ዘመን በወለደው ከንቱና የስሕተት ፍልስፍናዊ ትምህርት ፈጽሞ ሲነዋወጽ እንደማይችል በእውነት እንረዳለን፡፡

ኢሳይያስ በዚኽ ትንቢቱ ላይ መርገመ ሥጋ ምርገመ ነፍስ የሌለባት፤ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጠን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለአማላጅነትና ለእናትነት እሱ ባወቀ ባይሰጠን ኖሮ፤ እድላችን ማራቸው የሚል አማላጅ አጥተው በኀጢአታቸው እንደተቀጡና እንደጠፉ የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ይኾን እንደነበረ ተናግሯል፡፡

አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው የነቢዩ የኢሳይያስን ትንቢታዊ ኀይለ ቃል ሲተረጕሙ

*“ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ*
*እግዚአብሔር ኪያኪ እመ ኢያትረፈ ለነ*
*በትረ ተአምር ማርያም አንተ ጸገይኪ መድኅነ*
*ዘይቤ ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ*
*አላ ለንስሐ ኃጥአነ”*

(ጻድቃንን እጠራ ዘንድ አልመጣኹም ኃጥአንን ወደ ንስሓ ልመልስ እንጂ ብሎ የተናገረ መድኀን ክርስቶስን የወለድሽልን የተአምር በትር ማርያም ሆይ፤ እግዚአብሔር አንቺን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በኾንን እንደ ገሞራ በመሰልን ነበር)[79] በማለት ምልጃዋን አስተምረዋል፡፡

ፍሕመ ምሥዋዕ፣ ረኀርም ዘፋን

እሳተ መለኮት የባሕርይ አምላክን በማሕፀኗ ፱ወር ከ፭ ቀን የተሸከመች፣ በክንዷ የታቀፈች ቅድስት ድንግል ማርያም የነቢዩ ኢሳይያስ ሀብተ ትንቢቱ በተመለሰባት፣ ከለምጹ በነጻባት በፍሕመ ምሥዋዕና፣ እምላክ ተቀምጦባት በተመለከታት ረኀርም ዙፋን ትመሰላለች (ኢሳ ፮፥፩-፯) ፡፡

[78]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘእሑድ፤ ምዕራፍ ፩፥፲፯-፲፰
[79]አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ፤ ቍ ፶፩





ይኸውም በኢሳይያስ ዘመን የነበረው ንጉሡ ዖዝያን በሊቀ ካህናቱ በአዛርያስ ላይ ቅናት አድሮበት፤ ያልተሰጠውን የክህነት ሀብት በመሻት ልብሰ ተክህኖ በመልበስ የወርቅ ማዕጠንቱን በመያዝ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሲያጥን፤ ጢስ ቀታሬው ቢነካው ከግንባሩ ላይ ለምጽ ወጣባት፤ ያን ጊዜ ዐፍሮ በሻሽ ቢሸፍነው በሻሹ ላይ ወጥቶበታል፤ እነዚያም አይተው ከቤተ መቅደስ አስወጥተው አስረው እግዘውት ልጁ ኢዮአታምን በርሱ ምትክ አንግሠውታል (፪ ነገ ፲፭፥፭)፡፡

ያን ጊዜ የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ ነበር፤ ዖዝያንን ይቀርበው ነበርና ቢመክረው ቢያስተምረው ይመስለ ነበር፤ ርሱ ግን ፈርቶት ሳይመክረው፣ ሳይገሥጸው ቢቀር ነቢዩ ኢሳይያስ ሀብተ ትንቢት ተነሥቶት ለምጽ ወጥቶበት ቆይቷል፡፡ ንጉሡ ዖዝያን በሞተ ጊዜ የነገሥታት ንጉሥ ልዑል እግዚአብሔር ለኢሳይያስ ያ የፈራው ንጉሥ ማለፉን መሞቱን፤ ርሱ ግን በባሕርዩ ሞት፣ በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት እንደኾነ ለማጠየቅ በረኀርምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፤ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን መልቶት፤ ሱራፌልም በኹለት ክንፋቸው ፊታቸውን፣ በኹለት ክንፋቸው እግራቸውን ሸፍነው፤ ኹለት ክንፋቸውን ወዲያና ወዲኽ ዘርግተው፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ኹሉ ከክብሩ ተመልታለች እያሉ ሲያመሰግኑት አይቷል (ኢሳ ፮፥፩-፬)፡፡

ወዲያው በአምላክ ፈቃድ ከሱራፌል አንዱ እየበረረ ወደ ኢሳይያስ በመምጣት ከፍሕመ ምሥዋዑ በጉጠት ወስዶ ከንፈሩን ቢያስነካው ከደዌው ተፈውሷል፤ ሀብተ ትንቢቱ ተመልሶለታል (ኢሳ ፮፥፯) ፡፡

ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ኢሳይያስ የአዳም፤ መልአኩ የቀሳውስት፤ ጉጠት የሥልጣነ ቀሳውስት፤ ምሥዋዕ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ፍሕም የሥጋው የደሙ ምሳሌ፤ ይኸውም የኢሳይያስ ሀብተ ትንቢቱ በፍሕመ ምሥዋዕ እንደተመለሰለት ኹሉ በአዳም ምክንያት የኼደ ልጅነትም አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል በነሣው መለኮት በተዋሐደው በሥጋው በደሙ ለመመለሱ ምሳሌ እንደኾነ መተርጕማን ያብራራሉ (ማቴ ፳፮፥፳፮-፳፱፤ ማር ፲፬፥፳፪-፳፭፤ ሉቃ ፳፪፥፲፱-፳)፡፡

ኢትዮጵያውያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በእንዚራ ስብሐት የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ *“አ ቅድስት ለፍሕመ መለኮት ጉጠ”* (ቅድስት ሆይ የመለኮት ፍም ጉጠቱ አንቺ ነሽ)[80] በማለት ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንክብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ ሲያስተምር፤ ዳግመኛም ስለዚኽ ታላቅ ምስጢር ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በመዐዛ ቅዳሴው ላይ፡- *“አንቲ ተዐብዩ*

[80]አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 79



www.ethiopianorthodox.org

*እምኪሩቤል ወትትሌዓሊ እምሱራፌል ማሕፀንኪ ጾሮ ለነደ እሳት ግሩም ከርሥኪ አግመሮ ለፍሕመ መለኮት ፍጹም አብራክኪ ሐቀፋሁ ለዘኢይትሜጠን ኑኁ ወስፍሑ አእዳውኪ ገሰሳሁ ለዘኢይትገሰስ መብረቀ ስብሐቲሁ አጻብዕኪ ተመሰላ በጕጠተ እሳት ውዑይ በዘቦቱ ተመጠወ ነቢይ ፍሕመ ቍርባን"* (አንቺ ከኪሩቤል ትበልጫለሽ፤ ከሱራፌልም ከፍ ከፍ ትያለሽ፤ ማሕፀንሽ ግሩም የኾነ ነደ እሳትን ተሸከመ፤ ፍጹም የኾነ የመለኮትንም ፍሕም ቻለ፤ ርዝመቱ ስፋቱ የማይመጠን በመጠን ሕፃን ታቀፍሺው የማይዳሰስ የጌትነቱ ባሕርይ መብረቅ የኾነ ርሱን እጆችሽ ዳሰሱት፤ ጣቶችሽ ነቢዩ ከምሥዋዐ እሳት ፍሕመ ቍርባንን በርሱ የተቀበለበትን የምታቃጥል የእሳት ጕጠትን መሰሉ)[81] በማለት ምስጢሩን ተንትኖ አስተምሯል።

ዳግመኛም ኢሳይያስን ከደዌው ፈውሶ ሀብተ ትንቢቱን መልሶ ለመምህርነት ወደ እስራኤል የላከው አምላክ የተገለጠባት፤ ሱራፌል ክንፋቸውን ጋርደው በዙርያዋ ያሉ ይኽቺ ኢሳይያስ ያያት ረዥምና ከፍ ያለችው ዙፋን፤ በኋላ ዘመን ድዉያነ ሥጋን በተአምራት፡ ድዉያነ ነፍስን በትምህርት ያዳነ፤ ለሐዋርያት ሀብተ ስብከትን ሰጥቶ በመምሕርነት ወደ ዓለም የላከ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ ማሕፀኗን እንደ ዙፋን አድርጎ ፱ወር ከ፭ ቀን የተቀመጠባት፤ ኪሩቤል ሱራፌል በፍርሀት በመንቀጥቀጥ ኾነው፤ እሳተ መለኮቱ እንዳያቃጥላቸው ክንፋቸውን የሚጋርዱለት፤ ርሱን በክንዷ የታቀፈች፣ በገርባዋ ያዘለች፣ ሰማይ ምድር ከፊቱ የሚሸሹለትን አምላክ በክንፈሮቿ የሳመች ክብሯ ከፍ ከፍ ያለ የአማናዊት ዙፋን የቅድስት የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*"ኦ እግዝእትየ ማርያም መንበር ነዋኅ ዘኢሳይያስ ወልደ አሞጽ ዘነጸረኪ ቅድመ በዓመተ ሞተ ዖዝያን ዘለምጽ"*

(እመቤቴ ማርያም ሆይ ለምጻሙ ዖዝያን በሞተበት ዓመት፤ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ያየሽ ረዥም ዙፋን ነሽ)[82] በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ አስቀምጦታል።

የቅድስት ድንግል ማርያምን ነገር ስናስብ በእጅጉ የሚደንቀን፤ ኢሳይያስ ያያቸው ሱራፌልና ኪሩቤል ዙፋኑን በፍርሀት ኾነው

[81]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መዐዛ ቅዳሴ ቍ ፺፫

[82]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 84





የሚሸከሙት ቀዳማዊ አምላክን ርሷ ግን በማሕፀኗ መሸከሟ፤ በገርባዋ ማዘሏ፣ በክንዷ መታቀፏ ሲኾን በዚኽም ክብሯ በነገረ ማርያም ሊቃውንት ዘንድ "ሰማያዊት ሠረገላ" (Celestial Chariot) በመባል ተጠርታበታለች። ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም የተሰጣትን ይኽነን ታላቅ ክብር መነሻ በማድረግ በአንቀጸ ብርሃን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ *"ለኪ ይደሉ ለአግብርትኪ ወለአእማትኪ ትስአሊ ለነ ኀበ ወልድኪ ለእለ አመነ በስመ ወልድኪ ኦ ሙኀዘ ፍሥሐ ፊድፉደ ብኪ ግርማ ራእይ ዘየዓቢ እምኪሩቤል እለ ብዙኃት አዕይንቲሆሙ ወሱራፌል እለ ስድስቱ ክነፊሆሙ እልክቱ ይከድኑ ገጸሙ ወእገሪሆሙ በአርአያ ትእምርተ መስቀል ከመ ይድኅኑ እምእሳት ዘይወፅእ እመለኮተ ወልድኪ አንቲሰ ኮንኪ ማኅፈደ ለመለኮት ወኢያውዐየኪ እሳት መለኮት ጾርኪ ነበልባለ እሳት ወኢያውዐየኪ ነበልባለ መለኮት"* (ጸጋን የተመላሽና የደስታ መገኛ ሆይ፤ በልጅሽ ስም ላመንን ለእኛ ለወንዶችና ለሴቶች አገልጋዮችሽ ትለምኝልን ዘንድ ይገባሻል፤ ይልቁንም ዐይኖቻቸው ብዙዎች ከኾኑ ከኪሩቤልና፤ ክንፎቻቸው ስድስት ከኾኑ ከሱራፌል ግርማ የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ፤ እነዚያ ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤ እግሮቻቸውም የትእምርተ መስቀል አምሳያዎች ናቸው፤ ከልጅሽ መለኮት ከሚወጣው እሳት ይድኑ ዘንድ፤ አንቺ ግን ለመለኮት ማደሪያ ኾንሽ፤ የመለኮት ባሕርይም አላቀጠለሽም፤ የእሳት ነበልባልን ተሸከምሽ፤ የመለኮት ባሕርይም አላቃጠለሽም)[83] በማለት የአማናዊ ዙፋን የእመቤታችን ክብሯን በእጅጉ አድንቋል።

ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ኢሳይያስ ያያቸው ኪሩቤልና ሱራፌል እሳተ መለኮቱ እንዳያቃጥላቸው ክንፋቸውን ሸፍነው በፍርሀት ኾነው ዙፋኑን የሚሸከሙትን አምላክን፤ ርሷ ግን ፱ ወር ከ፭ቀን ስለመሸከሟ *"ድንግል ሆይ እሳተ መለኮት ጌታ በማሕፀንሽ ባደረ ጊዜ፤ ቀሚሱ እሳት ነው እንደምን አላቃጠለሽ? ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በማሕፀንሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተጋረደ? ክኅንሽ በቀኝ ነውን? ወይስ ክንድሽ በግራ ነውን? ትንሽ አካል ስትኾኚ፤ የሚያንጸበርቅ ነደ እሳት የሚከበው ኪሩቤል የተሸከሙት ዙፋን በማሕፀንሽ ውስጥ በወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተተከለ? ታናሽ ሙሽራ ስትኾኚ"*[84] በማለት እውነተኛዪቱ መንበር ርሷ መኾኗን መስክሯል።

[83]ቅዱስ ያሬድ፤ አንቀጸ ብርሃን ቍ ፲፪

[84]አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ.፹-፹፬



www.ethiopianorthodox.org

## ድንግልም እናትም

ይኸነን የኢሳይያስ የትንቢት መጽሐፍ ደረቅ ሐዲስ ካሰኙት መኻከል በምዕ ፯፥፲፬ ላይ የተናገረው የአምላክ ከድንግል በድንግልና የመወለድ ታላቅ ትንቢታዊ ኀይለ ቃል ነው።

ይኸውም ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ "ናሁኬ በእንተ ዝንቱ ይውህበክሙ እግዚአብሔር ትእምርተ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ ዐማኑኤል" (ስለዚኽ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እንሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች) በማለት ከሥጋና ከነፍስ መቅሠፍት የዳንበት ታላቅ ምልክት ይኸውም የሰው ልጆች ኹሉ በታላቅ ተስፋ ሲጠባበቁት የኖሩትን የአምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና የመወለድ ምስጢር መንፈስ ቅዱስ ለዚኽ ነቢይ ገልጾለት፤ ከጌታ ልደት ፯፻ ዓመት ቀደም ብሎ አስደናቂ ትንቢትን ተናግሯል።

በመኾኑም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይኸነን የኢሳይያስን ቃል ምስክር አድርጋ ቅድስት ድንግል ማርያም አምላካችን ዐማኑኤልን ከመውለዷ በፊት ድንግል፣ በወለደችውም ጊዜ ድንግል፣ ከወለደችውም በኋላ ዘላለማዊት ድንግል ናት ብላ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ እውነተኛውን ትምህርት ታስተምራለች።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ንእድ ክብርት የኾነች ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና በግብረ መንፈስ ቅዱስ የመፅነሷ ምስጢር ለረቀቀበት ለአረጋዊዉ ዮሴፍም በሕልሙ ተገልጾለት "ልጅም ትወልዳለች ርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና፤ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለኽ፤ በነቢይ ከጌታ ዘንድ እንሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይኽ ኹሉ ኾኗል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው" በማለት የኢሳይያስ ትንቢት ፍጻሜ ያገኘ መኾኑን መስክሮለታል (ማቴ ፩፥፳፩-፳፫)።

ክብር ይግባውና ፈጣሪያችን ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተወልዶ ትንቢተ ነቢያትን ፈጽሟልና፤ በርካቶች የቤተ ክርስቲያን መምሕራን በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ሰፊ ትንታኔ ሰጥተዋል።

ታላቁ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይኸነን የኢሳይያስን



www.ethiopianorthodox.org



ትንቢት በማራቀቅ በሰፊው ሲያብራራ "ኢሳይያስ ልዑለ ቃል ኮነ እምኵሎሙ ነቢያተ እስራኤል ወርእሶሙ ለነቢያተ ይሁዳ ወአዕመቀ ኀሊናሁ እስከ ቀላይ ወአልዐለ እስከ ኑኁ ሰማይ ነጸረ ወርእየ ሥጋዌ አምላክ እምድንግል እምቅድመ ኀምስቱ ምእት ዓመት ከመ ዘይእዜ ይኔጽር ከልሐ ወይቤ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ሰላ ርእየ እንከ በመንፈሰ ትንቢት ወኢርእየ በዐይነ ሥጋ ወባሕቱ በልደተ ቃልሰ እምኔሁ ከመዝ ኮነ ሕይወት ለኵሉ ዓለም" (ኢሳይያስም ከእስራኤል ነቢያት ኹሉ ይልቅ ድምፀ ታላቅ ኾነ፤ ለይሁዳም ነቢያት አለቃቸውን ኾነ፤ ዐሳቡንም እስከ ቀላይ (ወንዝ) ድረስ ጠልቆ እንዲገባ አደረገ፤ እስከ ሰማይም ከፍ ከፍ አደረገ፤ ከድንግል የአምላክንም ሥጋ መልበስ ከ፭፻ ዓመት በፊት አኹን እንደሚያይ በፍጹም አይቶ ጮኸ፤ እንዲኽም አለ ድንግል በድንግልና ፀንሳ ወንድ ልጅን ትወልዳለች አለ፣ እንግዲኽ በትንቢት መንፈስ አየ እንጂ በዐይነ ሥጋ አላየም፤ ነገር ግን ከአንቺ በኾነ የአካላዊ ቃል ልደት ለዓለም ኹሉ ሕይወት ተደረገ)[85] በማለት የኢሳይያስ ትንቢት የተፈጸመባት መኾኑን አስተምሯል።

አባ ሕርያቆስም ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ በቅዳሴው ላይ "ዕንስ ምስለ ድንግልና ዘኢሳይያስ" (ኢሳይያስ ፅንስ ከድንግልና ጋር የተናገረልሽ አንቺ ነሽ)[86] በማለት ሲያመስግናት፤ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በበኩሉ አምላክን በድንግልና ፀንሳ በመውለዷ ምክንያት የኢሳይያስ ትንቢት ስለመፈጸሙና፤ ኢሳይያስ በጊዜው ለሰው ኹሉ ተስፋ የኾነውን ይኸነን አስደናቂ ትንቢት ሲናገር በጊዜው የነበሩ የዕብራውያን ሴቶች በደስታ መሞላታቸውና፤ ዛሬ መፈጸሙን የተረዱ ሴቶች ኹሉ ፍጹም ምስጋና እንዲሚያመሰግኑ ሲገልጽ፡-"Make ready, you band of virgins ..." (እናንተ የደናግል ጉባኤ ዝግጁ ኹኑ፤ እጆቻችኹን በማጨብጨብ የምስጋና መዝሙርን ዘምሩ፤ ድንግል ታላቁን ድንቅ ጌታ ወልዳዋለችና፤ እናም ራሷ ለሀገሯ ሰዎች ድንቅ ኾናለች፤ ኢሳይያስ ኹሉንም ወጣቶች ሴቶችን በመጥራት ለደናግል ምስጢርን ገለጠላቸው፤ "አንዲት ድንግል ያለምንም ወንድ ትፀንሳለች፤ ድንቁን በቅድስና ትወልደዋለች" ሲል ኢሳይያስ በራእይ አማካይነት ተናገረ፤ እናም ወጣቶች ሴቶቹን ደስታ ተናነቃቸው፤ ማን ናት? እናም የትና መቼ? ብለው ጠየቁ፤ ይኽ አስደናቂ ነገር እውነት ይኾናል ሲሉ፤ የነቢዩ ቃላት

[85] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘኀሙስ ፤ምዕ ፰፥ ፶፰-፶

[86] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም፤ ቍ ፴፰

መሠጧቸው፤ ከዚኽ በፊት ሰምተው የማያውቁትን ነገር ለዕብራውያት ሴቶች ዘምሮላቸዋልና፤ ደናግል ሴቶችም በትንቢቱ አማካይነት ድንግል ትፀንሳለች ብሎ በተናገረው ነገር በመደነቅ ተንቀጠቀጡ፤ "ድንግል ትፀንሳለች" ብሎ ኢሳይያስ ዘመረ፤ በእመቤታችን ማርያምም ትንቢቱ ተከናወነለት፤ ስለዚኽም አስደናቂ ድንግል ተደርጋ ዕውቅና ተሰጣት፤ ኹሉም ነቢያት በመጽሐፋቸው ውስጥ ስላንቺ የጻፉልሽ ማርያም አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ ኢሳይያስ በትንቢቱ ውስጥ "ዕወቁ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙም ዐማኑኤል ይባላል" ብሎ ያወጀልሽ ማርያም አንቺ የተባረክሽ ነሽ)[87] በማለት የኢሳይያስ ትንቢት የተፈጸመባት ሰማይና ምድርን የፈጠረ ጌታን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች ድንግልም እናትም መኾኗን አስተምሯል።

## ነቢይት

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ በመንፈሰ እግዚአብሔር በመቃኘት በምዕ ፰፥፲፬ ላይ የተናገረውን የአምላክን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና የመወለድ ምስጢር በመድገም በምዕ ፰፥፫ ላይ "ወደ ነቢይቱም ቀረብኊ፤ ርሷም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች" በማለት ተናግሯል።

ኢሳይያስ በዚኽ ትንቢቱ አምላክን በኅቱም ድንግልና የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምን "ነቢይት" ያለበት ምክንያት የአምላክ እናት በመኾኗ ምክንያት በሊቀ መላእክት በቅዱስ ገብርኤልና በቅድስት ኤልሳቤጥ ብቻ ሳይኾን በነገደ ሴም፣ በነገደ ካም፣ በነገደ ያፌት የምትመሰገን መኾኗን "እነሆም ከዛሬ ገርምሮ ትውልድ ኹሉ ብፅዕት ይሉኛል" በማለት ትንቢት የምትናገር ናትና፤ ይኽ ለነቢዩ አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት በትንቢቱ ላይ "ነቢይት" ብሏታል (ሉቃ ፩፥፵፱) ። ከርሷም ጌታ የመወለዱን ነገር *"ፀንሰት ወወለደት ወልደ"* (ርሷም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች) በማለት አጉልቶ ተናግሯል።

በተጨማሪም ነቢዩ ኢሳይያስ በዚኽ ሳያበቃ ልጇ ዐማኑኤል በእውነት የባሕርይ አምላክ ሲኾን እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም የአምላክ እናት ስለመኾኗ በምዕ ፱፥፮ ላይ *"ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ፤አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይኾናል፤ ስሙም ድንቅ፣ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል"* በማለት በጉልህ አስተምሯል።

[87] T.J Lamy, Sancti Ephraem Syri Hymn et sermones, II (Malines 1886) 519-590, Bride of light pp 42-43





በመኾኑም ድንቅ አምላክን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ሳለች "እነሆም ከዛሬ ገርምሮ ትውልድ ኹሉ ብፅዕት ይሉኛል ብርቱ የኾነ ርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና ስሙም ቅዱስ ነው" (ሉቃ ፩፥፵፱) በማለት በትውልድ ኹሉ እንደምትመሰገን ትንቢት በመናገሯ ነቢይትነቷ በኢሳይያስ አስቀድሞ የተመሰከረላት ቅድስት ድንግል ማርያምን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ በማለት፤ ድንቅ፣መካር፣ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ የተባለ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስን በእውነት የባሕርይ አምላክ ብላ ሐዋርያዊት የኾነችው ቤተ ክርስቲያናችን ትመሰክራለች ።

የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ በአጅጉ የበዛለት ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም፤ ነቢዩ ኢሳይያስ ለምን ልጇን "ድንቅ" ብሎ እንደጠራውና በርሷም ስለተፈጸሙ ድንቃ ድንቅ ነገሮች በጥልቀት ሲገልጽ፡- *"The virgin daughter of David..."* (የዳዊት ድንግል ሴት ልጅ በተሰበሰቡት መኻከል ቆማለች፤ ሕፃኑን እንደተሸከመች ባለሙያዎች ከበዋታል፤ አንዱ መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቃት ሌላኛው ደግሞ ይመረምራታል፤ ርሷ ግን እንደታተመች ድንግልናዋ እንደተጠበቀ ነበር፤ ሕፃን ተሸክማለች ግን ድንግልናዋ እንዳለ ነው፤ ድንግል እንዳለች ብትቆይም ኹሉም እናቶች ለልጆቻቸው የሚሰጡትን ወተት ለልጇ ትሰጣለች፤ ማነው ብቁ የኾነና ይኽነን ለመመርመር የሚደፍር? በደረቷ ሕፃን ልጅ ተሸክማለች ግን ማኅተመ ድንግልናዋ እንደተጠበቀ ነው፤ ማንም ሰው ርሷን ቢመለከታት "ይኽ በጣም ድንቅ ነው" ከማለት ውጪ ምን ሊል ይችላል፤ ኢሳይያስ ቀድሞ እንደተናገረው ኹሉ፤ የከበረ ኢሳይያስም "ኀያል አምላክ" በማለት ሲጠራው፤ ዳግመኛም "ድንቅ ነኽ" አለው፤ ምክንያቱም የርሱ ልደት አስደናቂ ነውና፤ በዚኽም ነገር ማንኛውም "ድንቅ" ከማለት ውጪ ምን ብሎ ሊጠራው ይችላል፤ በገሮዋ ገብቶ (በብሥራት ቃል) በማሕፀኗ ውስጥ በስዉር አኳኋን ኖረ፤ ቀጥሎም ማኅተመ ድንግልናዋን ሳይለውጥ ከማሕፀኗ ወጣ፤ በተመሳሳይም ከመቃብር ሲወጣ ማኅተሙን ሳይከፍት ወጥቷል (ማቴ ፳፯፥፷፮)፤ እመቤታችን ማርያም በማሕፀኗ ውስጥ ለዘጠኝ ወራት በክብር ተሸክማዋለች፤ እናም ከርሷ ወተትን ሲጠባ የገዢናብ ጠብታዎችን ሰጥቶን ነበር፤ ርሱ በጣም አስደናቂ ነው...የእመቤታችን ማርያም ጡቶች እንደማንኞቹም እናቶች ጡቶች ናቸው፤ የሕይወት ፍሬ ርሱን ስትሸከም ግን ምንም ዐይነት ተዋሕዶተ ሰብሳብ (የጋብቻ ውሕደት) አይታ አታውቅም፤ እናንት ደፋሮች የኾናችኊ ባለሙያዎች በመደነቅ



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ ገዛም በሱ፤ ይኸ፡ ብላቴና አስደናቂ ናትና)[88] በማለት ድንቅ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስን በድንግልና የወለደች፤ እናትነት ከድንግልና፤ ድንግልናን ከእናትነት ጋር ያስተባበረች፤ ድንግል ስትኾን ከጡቶቿ ወተት ተገኝተው ዓለምን የሚመግበው ጌታ የተመገበው በመኾኑ መጋቢዋን የመገበች፤ ኢሳይያስ የተናገረው ድንቅ ምስጢር የተፈጸመባት መኾኗን መስክሯል።

የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ ተብሎ የተጠራው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ነቢዩ ኢሳይያስ ጌታን ለምን "ድንቅ" ብሎ እንደጠራው በልደት ድርሳኑ ላይ ሲያብራራ፡-"*The offspring that shone forth...*" (ያበራው ሕፃን ልጅ (ብላቴና) በግልጽ ይነገር ዘንድ አይቻልም፤ አብራርቼ እናገረዋለኍ የሚል ካለ እስኪ ይናገር? ትችል እንደኾነ እስኪ እንመልከት፤ አንተ የተማርኽ ጸሓፊ ሆይ እስኪ ጥበብኽን በሙሉ ግለጥ፤ ይቻልኽም እንደኾነ እስኪ ስለ ሕፃኑ ንግግር አሰማ፤ አንተ ጥላ ሆይ እስኪ ና ይፈቅድልኽም እንደኍ ፀሓይን ተመልከተው፤ እስኪ ውበቱን ግለጽልን፤ ስለ ደም ግባቱም ደግሞ ንገረን፤ ድንግል እናትንና ልጅን ከቶ የት አይተኽ ታውቃለኽ? እስኪ ሳትመራመር "ድንቅ" ሲል የጠራውን ኢሳይያስን አስታውስ፤ ከእመቤታችን ማርያም በቀር ወተትን የምትሰጥ ድንግል ማን ናት? የምታስተውል ሆይ "ድንቅ" ነው በል፤ ከዚያም በላይ አልፈኽ አትኺድ፤ አንተ ከዕብራውያኑ ልጅ ከኢሳይያስ በላይ ጥበበኛ አይደለኽም፤ ርሱ ሲተነብይ ዐማኑኤልን ድንቅ ሲል ጠርቶታልና፤ ርሱ ድንግሊቱ ከወላድ እናቶች ተስተካክላ ቆማ አይቷታል፤ ስለ ልጇም በመደነቅና በጨዋነት "ድንቅ" ሲል ጠራው፤ ያለ ጋብቻ ሩካቤ ልጅ መውለድ አስገራሚ ድንቅ ነው፤ አምላክ ሰው መኾኑም እንዲኹ ተአምር ነው፤ ከትውልዶች ከሃሊ የሚኾንም ርሱ ተወልዶ ማደጉም እንዲኹ ፤የዐማኑኤል ነገር አንዳች ዐይነት ማብራሪያ አያሻውም፤ መብራራት የሚችል ቢኾንማ ኖሮ እንደተባለው ድንቅ ባልኾነ ነበር፤ የርሱ ነገር በሙሉ መደነቅ እና መገረም የተገባው ነው፤ ነቢዩም ራሱ ስለርሱ እየተደነቀ "ድንቅ" ሲል ጠርቶታልና፤ ከድንግል በድንግልናዋ የተወለደን ልጅ ትፈልግ እንደኾነ አንተም እንደ ኢሳይያስ "ድንቅ" ስትል ጥራው፤ ከዚያም ባሻገር አትለፍ፤ የሰው ባሕርይ እጅግ ደካማ ነው፤ ምክንያቱም የወልደ

[88]T.J lamy, sancti Ephraem Syri Hymni et sermons, II (malines, 1886) 519-590, Bride of light pp 56-57)





እግዚአብሔር አሠራር እጅግ የላቀ ነውና በሰው ተፈጥሮ የማይገለጽ ለአንዳችም ማብራርያ የማይቻል ነው፤ ኢሳይያስ ቀድሞውኑ "ድንቅ" ሲል ጠርቶት አልነበረምን፤ የርሱ አሠራር ከጠቢባን ሰዎች ቃላት ኹሉ በላይ የሰፋ ነው፤ የርሱ መገለጽ ከጸሐፊዎች ኹሉ ሕዋሳት በላይ የላቀ ነው፤ የርሱ ልደት ከአእምሮዎች ኹሉ ስፍር በላይ የኾነ ነው፤ የርሱ ነገሩ በሙሉ ከማስተዋል በላይ ነው፤ ጠቢብ ሰው ሆይ ና በመጠቅለያ የተጠቀለለውን ሕፃን ተመልከት፤ መላው ፍጥረት በርሱ ፈቃድ ላይ እንዴት እንደሚጠገንም በርሱ ውስጥ አስተውል፤ በርሱ ተደነቅም፤ በኤፍሬታ ገና በግርግም ሳለ ርሱ ከአባቱ ጋር በመኾን ባሕርና የብስን ሲገዛ (ሲያስተዳድር) ነበር፤ልክ እንደ ሕፃን አንዲት ብላቴና ወተት የምትሰጠው ሳለ ርሱ ጤዛንና ዝናምን ለምድር አዝርዕት ይሰጣቸው ነበር፤ እምነትን የተመላች ነፍስ ያለችኽ ከኾንኽ አእምሮኽን አስጉዘውና ርሱ ፍጹም በላይም በታችም መኾኑን ተረዳ፤ ሰማያውያን በሚኾኑ ሕያዋን ሠረገላ ላይ የሚቀመጥ ርሱን ተመልከተው፤ አንዲት ብላቴና ልጅም በክንዶቿ ዕቅፍ ስትሸከመው ርሱ ግን ያው አንድ ርሱ ነው፤ እንሆ የገብርኤል ነገድ ፊታቸውን ወደ ምድር ደፍተው በርሱ ፊት ያደገድጋሉ፤ የዮሴፍ ቤት ወገኖች ግን በክንዶቻቸው ዕቅፍ ይሸከሙታል፤ ሱራፌል ከአንደበታቸው "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ" እያሉ ዝማሬን በፊቱ ያፈሳሉ (ኢሳ ፮፥፫፤ ሉቃ፪፥፴፤ራእ ፬፥፰)፤የሰው ልጆች ግን ይሸከሙታል፤ በምላሳቸው ያንጐራጕሩለታል፤ ሰማይ ለርሱ እጅግ ያንሳልና፤ ርሱ ቢያድርበት ሊይዘው አይችልም፤ የእመቤታችን ማርያም ዕቅፍ ግን በውስጡ ኾኖ ይመላለስ ዘንድ ለርሱ በቂ ስፋት አለው።)[89] በማለት ድንቅ የባሕርይ አምላክን በአስደናቂ ምስጢር የወለደች በእውነት የኢሳይያስ ትንቢት የተፈጸመባት መኾኑን በጥልቀት ገልጿታል።

## የዕሴይ በትር

ቊጥሩ ከዐበይት ነቢያት መኻከል የኾነው ነቢዩ ኢሳይያስ ጥበብን በሚገልጽ ትንቢትን በሚያናግር በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ከነገደ ዕሴይ መወለዷንና ከርሷም ጽጌ (አበባ) የተባለ አካላዊ ቃል ክርስቶስ እንደሚወለድ ተገልጾለት በምዕ ፲፩፥፩ ላይ "ትወፅእ

[89]Jacob of Serugh, On Nativity pp 121-123



www.ethiopianorthodox.org

*በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምኔሃ"* (ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣለች፤ አበባም ከርሷ ይወጣል) በማለት አስደናቂ ትንቢትን ተናግሯል።

ይኸ ኢሳይያስ የተናገረውን ትንቢታዊ ኀይለ ቃል፤ ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ድጓው ላይ ሲተረጉም *"ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ፤ ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወጽጌ ዘወፅአ እምኔሃ አምሳሉ ለወልድ ኅደረ ላዕሌሃ ቃል ሥጋ ኮነ ወተወልደ እምኔሃ"* (ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣለች፤ አበባም ከርሷ ይወጣል፤ ይኸቺውም በትር ቅድስት የኾነች የማርያም አምሳያ ናት፤ ከርሷ የወጣው አበባም የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው፤ የአብ አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ከርሷ ተወለደ)[90] በማለት ስዉሩን የትንቢት ቃል አጉልቶ ገልጾታል።

በሀገራችን ከነበሩ የነገረ ማርያም ምሁራን መኻከል አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *"ኦ ሐረገ ወይን ዘእምሥርወ ዕሴይ ወበትር ዘሠረጸት ዘእምጕንደ ዳዊት ወጽጌ ዘዐርገ እምኔሃ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ መዐዛ ቅዱሳን"*

(ከዕሴይ ሥር የወይን ሐረግ ከዳዊት ግንድ (ዘር) የበቀለች በትር፤ ከርሷም አበባ የወጣ፤ ያውም የቅዱሳን መዐዛ የሚኾን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው)[91] በማለት የኢሳይያስን ቃል እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ ከገለጸ በኋላ፤ በድጋሚ ስለዚኸ ምስጢር በመተንተን፦ *"ኢሳይያስኒ ይቤ ትወፅእ በትር ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ ወየዐርፍ ዲቤሁ መንፈሰ እግዚአብሔር መንፈሰ ልቡና ወምክር መንፈሰ ኀይል ወአእምሮ ከመ ይትፈጸም ትንቢት ዘበጽዮን ተየድዐ ወበኢየሩሳሌም ተሰብከ ዘበአፈ ነቢያት ተከልሐ ዘበዕብራይስጢ ተጽሕፈ በእደዊሆሙ ለሌዋውያን ሠረጸት ለነ በትረ ክህነት ወመንግሥት፤ በትረ ጽድቅ ወመድኅኒት፤ በትረ አሚን ወሃይማኖት፤ በትረ ቅድስና ወንጽሕ በትረ ኀይል ወመዊእ"* (ኢሳይያስ እንዲኸ አለ፤ ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዱም አበባ ይወጣል፤ በላዩም የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፋል፤ የማስተዋልና የምክር መንፈስ፤ የኀይልና የዕውቀት መንፈስ በላዩ ያርፋል፤ በጽዮን የተነገረው ትንቢት በኢየሩሳሌም የተሰበከው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ በነቢያት አንደበት ተነግሮ ተጮኸ፤ በሌዋውያን እጅ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈውን የክህነትና የመንግሥት በትር በቀለችልን፤ የጽድቅና የመድኀኒት በትር፤ የፍጹም ሃይማኖት በትር፤ የፍጹም ቅድስና በትር፤ የኀይል የድል አድራጊነት በትር በቀለችልን)[92] በማለት አማናዊት በትር ብሎ ኢሳይያስ በትንቢቱ ከተናገረላት ከርሷ፤ መዐዛ ቅዱሳን የተባለው አማናዊዉ ጽጌ ክርስቶስ የመወለዱን ነገር ተንትኖ ተርጕሞታል።



[90] ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ድጓ፤ ገጽ ፻፶፱

[91] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ መጽሐፈ አርጋኖን ዘረቡዕ ምዕ ፫፥፲፫



ይኸ በምስጢር የተራቀቀና ከፍተኛ የነገረ ማርያም ዕውቀት የነበረው አባ ጊዮርጊስ በዚኸ ሳያበቃ፤ በተጨማሪ በመጽሐፈ ምስጢር ላይ *"በከመ ፈቀደ ወአልቦ ዘይክልኦ ገቢረ ዘኀለየ በከመ ጽሑፍ ዘይብል ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ፤ምንት ውእቱ ፀአተ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ፤ ምንት ውእቱ ፀአተ በትር እምሥርው ዘእንበለ ዘርዐ ሙላድ ዘቅድስት ድንግል እንተ ኮነት እምኀበ ኢያቄም ውስተ ማሕፀነ ሐና፤ እስመ ዘርዐ ዕሴይ ውእቱ ኢያቄም አቡሃ ለማርያም ወምንትኑመ ካዕበ ዕርገተ ጽጌ እምጕንደ ዘእንበለ ሥጋዌ መለኮት እምወለቱ"* (ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣለች፤ ከግንዱም አበባ ይወጣል የሚል እንደተጻፈ፤ ያሰበውን ለማድረግ የሚከለክለው የለም፤ ከኢያቄም ተከፍላ በሐና ማሕፀን ከተፀነሰች ከቅድስት ድንግል የትውልድ ዘር በቀር የበትር ከሥሩ መውጣት ምንድን ነው? የእመቤታችን የማርያም አባቷ ኢያቄም ከዕሴይ ዘር ነውና፤ ዳግመኛም ከኢያቄም ሴት ልጁ የመለኮት ሰው መኾን በቀር የአበባ ከግንዱ መውጣት ምንድን ነው)[93] በማለት ተርጕሞታል።

በተመሳሳይ መልኩ ሊቁ የሚላኑ አምብሮስ (፫፻፴፯-፫፻፺፯ዓ.ም) ይኸነን የኢሳይያስን ትንቢታዊ ኀይለ ቃል በምስጢር ተራቅቆ ሲተረጕም *"Isaiah says, "There shall come forth..."* (ኢሳይያስም ይኸነን ይላል፤ "ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዱም አበባ ይወጣል" ይኸ ማለቱም ሥሩ የአይሁድ ቤት ሲኾን፤ በትር ድንግል ማርያም ናት ፤ የድንግል ማርያም አበባ ክርስቶስ ነው፤ በትር መባሏም ተገቢ ነው ከነገሥታቱ ቤት ከዳዊት ቤት ናትና፤ አበባዋም የዓለምን ብክለት መጥፎ ሽታ አስወግዶ የዘለዓለም ሕይወትን ሽታ ያሰፈነው ክርስቶስ ነው)[94] በማለት የትንቢተ ኢሳይያስ ፍጻሜን አስተምሯል።

[92] ገዘ. ከማሁ፤ ዘኀሙስ ምዕ ፮፥፲፯-፲፰

[93] ገዘ. ከማሁ፤መጽሐፈ ምስጢር ፤ገጽ ፻፸፬

[94] Ambrose of Milan, The Patriarch 4:18-19



www.ethiopianorthodox.org

## ፈጣን ደመና

ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ ቅድስት ድንግል ማርያም የባሕርይ አምላክ ዐማኑኤልን ይዛ ወደ ግብጽ የመሰደዷን ነገር አስቀድሞ ተገልጾለት በምዕ ፲፱፥፲፩ ላይ "*እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብጽ ይመጣል፤ የግብጽም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ*" በማለት ከገነት የተሰደድነውን እኛን ወደ ቀደመ ርስታችን ሊመልሰን እንደመጣ ለማጠየቅና፤ ጠላታችን ዲያብሎስን ከሰዎች ልብ አውጥቶ ለመስደድ፤ ክብር ይግባውና ወልደ እግዚአብሔር ልመናዋ ፈጥኖ በሚሰማላት "ደመና መፍጠኒት" በተባለች በእናቱ ብቅድስት ድንግል ማርያም ገርባ ታዝሎ ወደ ግብጽ የመሰደዱን ነገር አስቀድሞ ገልጾታል።

ይኸውም በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈ ንጉሡ ሄሮድስ ክርስቶስን ለመግደል በፈለገ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ለአረጋዊዉ ለዮሴፍ በሕልሙ ተገልጾለት "*ተንሥእ ወንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወጉየይ ውስተ ብሔረ ግብጽ*" (ሕፃኑንና እናቱን ይዘኽ ወደ ግብጽ ሽሽ) ባለው ጊዜ ይኽ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት ሲፈጸም ምልጃዋ ፈጥኖ በሚደርስ "ደመና መፍጠኒት" በተባለች በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ገርባ ታዝሎ ወደ ግብጽ በኼደ ጊዜ የግብጽ ጣዖታት ኹሉ እየተሰባበሩ ሲወድቁ፤ በነርሱ ዐድረው ያስቱ የነበሩ አጋንንት ኹሉ ሸሽተዋል፤ በመኾኑም በዚኽ የነገረ ማርያም አስተምህሮ እመቤታችን "ደመና መፍጠኒት" ወይም "ደመና ኢሳይያስ" ተብላ ተጠርታለች።

ኢትዮጵያዊዉ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን የኢሳይያስን ትንቢት በጥልቀት ሲተረጉም "*ሄሮድስ ኀሠሠ ዘኢይትረከብ ወእግዚእ ተግሕሠ ውስተ ምድረ ግብጽ ተጽዒኖ ዲበ ደመና ቀሊል፤በከመ ይቤ ኢሳይያስ ናሁ እግዚአብሔር ይወርድ ውስተ ምድረ ግብጽ ተጽዒኖ ዲበ ደመና ቀሊል ደመናሰ ቀሊል አንቲ ከመ አ ቅድስት ድንግል ሄሮድስ ፈተወ ይዕዱ ነፋሰ ውስተ ጽርሑ በአይቴ ይትከሀል ዐዲወ ነፋስ፤ ሄሮድስ ፈተወ ይጽብጥ ብርሃነ ፀሓይ በእዴሁ በአይቴ ይትከሀል ጸቢጠ ብርሃነ ፀሓይ እግዚአብሔር ተአንገደ ውስተ ምድረ ግብጽ ተሐዚሎ በዘባንኪ*" (ሄሮድስ የማያገኘውን ፈለገ፤ ጌታም በፈጣን ደመና ተጭኖ ወደ ግብጽ ምድር ኼደ፤ ነቢዩ ኢሳይያስ እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ተጭኖ ወደ ግብጽ ምድር ይወርዳል ብሎ እንደተናገረ፤ ቅድስት ድንግል





ሆይ ፈጣን ደመና መቹም መች ቢኾን አንቺ ነሽ፤ ሄሮድስ በአዳራሹ ውስጥ ነፋስን ሊዘጋ ወደደ፤ ነፋስን መዝጋት በወዴት ይቻላል፤ ሄሮድስ የፀሓይ ብርሃንን በእጁ ሊጨብጥ ወደደ፤ የፀሓይ ብርሃንን መጨበጥ በወዴት ይቻላል፤ እግዚአብሔር በገርባሽ ታዝሎ በግብጽ ምድር እንግዳ ኾነ)[95] በማለት ምስጢሩን አምልቶ አጕልቶ አብዝቶ አስፍቶ ተንትኖታል።

ማሕሌታዊዉ ቅዱስ ያሬድም በመዋሥዕት መጽሐፉ ላይ ይኽነን ምስጢር ሲተረጉም "*ወነቂሆ ዮሴፍ እምንዋሙ ገብረ በከመ አዘዞ መልአከ እግዚአብሔር ነሥአ ሕፃነ ወእሞ ወሖረ ብሔረ ግብጽ*" (ዮሴፍ ከእንቅልፉ ነቅቶ(በነቃ ጊዜ) የእግዚአብሔር መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ ሀገር ኼደ)፤ "*ኢሳይያስ ነቢዩ ልዑለ ቃል እም ነቢያት ከልሐ ወይቤ እግዚአብሔር ጸባኦት ይወርድ ብሔረ ግብጽ*" (ከነቢያት ይልቅ ድምፀ ታላቅ የሚኾን ነቢዩ ኢሳይያስ አሸናፊ እግዚአብሔር ወደ ግብጽ ምድር ይወርዳል ብሎ አሰምቶ ተናገረ)፤ "*ደመና ቀሊል ዘይቤ ኢሳይያስ ይእቲኬ ማርያም ድንግል እንተ ጾረቶ በከርሣ ለወልደ እግዚአብሔር*" (ኢሳይያስ ቀላል ደመና ብሎ የተናገረላት የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጁን በማሕፀኗ የወሰነችው ድንግል ማርያም ናት።)[96] በማለት ሙሉ ትርጓሜን ሰጥቶታል።

### የታተመች መጽሐፍ (The sealed letter)

ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ በትንቢቱ ላይ ለዘላለሙ የማይለወጥ ኅቱም ማኅተመ ድንግልናዋን በታተመች መጽሐፍ ደብዳቤ አምሳል በመግለጹ ቅድስት ድንግል ማርያም በሲቃውንት ዘንድ "መጽሐፉ ለኢሳይያስ" ተብላ ትጠራለች (ኢሳ ፳፱፥፲፩-፲፪)።

በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የታተመ መጽሐፍ (ደብዳቤ) በርካቶች ምሳሌዎችን ያመላክት ነበር፤ ከዚኽ መኻከል የንግሥና ክብርን (አስ ፫፥፯)፤ አምላካዊ ምስጢርን (ኢሳ ፳፱፥፲፩-፲፪፤ ራእ ፭፥፩-፭) የሚያሳይ ሲኾን ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በምዕ ፳፱፥፲፩-፲፪ ላይ፡- "*ራእዩም ኹሉ እንደታተመ መጽሐፍ ቃል ኾነባችኋልና ማንበብንም ለሚያውቅ ይኽነን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ ርሱ ታትሞአልና ማንበብ አልችልም ይላቸዋል፤ ደግሞም መጽሐፉን ማንበብ*

[95]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ
[96]ቅዱስ ያሬድ፤ መዋሥዕት ዘዐስተ ግብጽ፤ ገጽ ፶፫



www.ethiopianorthodox.org

*ለማያውቅ ይኸን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ፤ ርሱ ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል"* በማለት የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስለኾነቿው ለዐዋቂውም ኾነ ላላዋቂው ለማንበብ ጭንቅ የኾነችውን የታተመች የምስጢራዊት መጽሐፍን ነገር ተናግሯል።

ይኸውም ይኸቺ ኢሳይያስ የተናገረላት ቃል የተጻፈባት መጽሐፍ (ደብዳቤ) ማንም የማይከፍታትና ገልጦ ሊያነባት የሚችል ፈጽሞ የሌለ የታተመች እንደኾነች ኹሉ አካላዊ ቃል ክርስቶስንም በማሕፀንዋ የተሸከመች ቅድስት ድንግል ማርያምም ማንም ሊደርስባት የማይችል "ቅድመ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ፀኒስ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ፀኒስ ድኅረ ወሊድ" ማኅተመ ድንግልናዋ የታተመ፤ ዘላለማዊት ድንግል ናት።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስለዚኽ ምስጢር በአርጋኖን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ *"አ መጽሐፍ ኅትምት ዘአልቦ ዘክህለ ከሢቶታ አንብቦታ ወኢአንብቦታ"* (ገልጦ ሊያነባት ሊያጥፋትም የሚችል ማንም የሌለ የታተመች መጽሐፍ ሆይ)[97] በማለት ጠቅልሎ ሲናገር፤ በመጽሐፈ ምስጢር ደግሞ ይኸንን የኢሳይያስን ትንቢት በማራቀቅ ሲተረጉም፦

*"ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ዜና ዘንጽሕት ድንግል ወዘእጐሃ አረጋዊ፤ ቦአት ወለተ ዳዊት ኀበ ወልደ ዳዊት፤ ቦአት ርግብ ንጽሕት ኀበ በግዐ የዋህ፤ ቦአት መጽሐፍ ኅትምት ኀበ ብእሲ ዘኢይክል አንብቦታ በከመ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ወወሀቡ ለብእሲ ዘኢይክል መጽሐፈ ወይቤ ኢይክል አንብቦታ መጽሐፍሰ ኅትምት ይተረጐም በቅድስት ድንግል፤ ወሀብትሂ እንተ ተውህበት ይተረጐም በተወፍዮታ እምቤተ መቅደስ ውስተ ቤተ ዮሴፍ፤ ወብሂለ ኢይክል አንብቦታ በኢቀሪበ ሥጋሃ ወበ ኢያእምሮ ፅንሳ በከመ ይቤ ወንጌላዊ ወኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደቶ ወዘእንበለ ይቅረባ ተረክበት እንዘ ፅንስት እመንፈስ ቅዱስ"*

(ወንድሟ ሽማግሌ ወደሚኾን ወደ ንጽሕት ድንግል ዜና እንመለስ፤ የዳዊት ሴት ልጅ ወደ ዳዊት ልጅ ገባች፤ የዋህ ርግብ ወደ የዋህ በግ ቤት ገባች፤ የተዘጋች መጽሐፍ ማንበቧን ወደማያውቅ ሰው ገባች፤ ነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ለማያውቅ ሰው መጽሐፍ ሰጡት፤ ርሱም "ማንበቧን አልችልም" አለ ብሎ እንደተናገረ፤ ይኸውም የታተመች መጽሐፍ ግን በቅድስት ድንግል ይተረጐማል፤ የተሰጠችው ስጦታ ከቤተ መቅደስ ወደ ዮሴፍ ቤት በመስጠቷ ይተረጐማል፤

[97]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ፤ ምዕ ፩፥፲





"ማንበብንስ አይቻለኝም" ማለት በሥጋዋ አለመቀራረብ ፅንሷንም ባለማወቅ ይተረጐማል፤ ወንጌላዊ እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ሳይቀርባት (በግብር ሳያውቃት) በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች እንዳለ (ማቴ ፩፥፲፰))[98] በማለት ሊቁ ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ከመፅነሷ አስቀድሞ፣ በፀነሰችው ጊዜና፣ ከፀነሰችው በኋላ ማሕፀና በተፈትሖ የማይመረመር አስቀድሞ በነኢሳይያስ የተነገረላት መኾኑን እያብራራ ኅትምት መጽሐፍነቷን አስረድቷል።

ነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ለማያውቅ ሰው መጽሐፍ ሰጡት፤ ርሱም "ማንበቧን አልችልም" አለ ብሎ እንደተናገረ፤ ይኸውም የታተመች መጽሐፍ ግን በቅድስት ድንግል ይተረጐማል፤ የተሰጠችው ስጦታ ከቤተ መቅደስ ወደ ዮሴፍ ቤት በመስጠቷ ይተረጐማል፤ "ማንበብንስ አይቻለኝም" ማለት በሥጋዋ አለመቀራረብ ፅንሷንም ባለማወቅ ይተረጐማል፤ ወንጌላዊ እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ሳይቀርባት (በግብር ሳያውቃት) በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች እንዳለ (ማቴ ፩፥፲፰))[98] በማለት ሊቁ ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ከመፅነሷ አስቀድሞ፣ በፀነሰችው ጊዜና፣ ከፀነሰችው በኋላ ማሕፀና በተፈትሖ የማይመረመር አስቀድሞ በነኢሳይያስ የተነገረላት መኾኑን እያብራራ ኅትምት መጽሐፍነቷን አስረድቷል።

ታላቅ የነገረ ማርያም ዕውቀት የነበረው ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም ከነቢዩ ከኢሳይያስ ትንቢት በመነሣት፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በታተመችው መጽሐፍ (ደብዳቤ)፤ አካላዊ ቃል ክርስቶስን በውስጧ በተጻፈው ቃል በመመሰል ከዮሐንስ ወንጌል ምዕ ፩፥፲፬ ጋር በማያያዝ በጥልቀት ተርጕሞታል።

ይኸውም አስቀድሞ በትንቢት የታጠረው ማኅተመ ድንግልናዋን ሳይለውጥ አካላዊ ቃል ክርስቶስ በማሕፀኗ የማደሩንና፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር አብ ማንም ገልጦ ሊያነባት የሚችል የሌለ መጽሐፍ በተባለችው በርሷ ድንቅ ምስጢር መግለጡንና፤ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ልጁ ማኅተመ ድንግልናዋን ሳይከፍት እንደታተመች በማሕፀኗ ማደሩን በማራቀቅ ሲተረጕም *"Mary appeared to us a sealed letter..."* (እመቤታችን ማርያም ለእኛ የተገለጠችው የወልድና የልደቱ ምስጢራት በውስጧ እንደተሰወሩ እንደታተመ ደብዳቤ ኾና ነው፤ አካሏን እንደ ንጹሕ ወረቀት (ብራና) አቀረበችው፤ አካላዊ ቃልም

[98]መጽሐፈ ምስጢር፤ገጽ ፲፮-፲፰



www.ethiopianorthodox.org

ስለራሱ እውነተኛ ማንነት ባሕርዩን በሥጋ ጻፈ፤ እናም እንዳልነው ወልድ ያ ቃል ሲኾን፤ ርሷም ምሕረት (ይቅርታ) ለዓለም ኹሉ የተላከባት ደብዳቤ ናት፤ ርሷ ይኽ ደብዳቤ የኾነችው ከተጻፈች በኋላ ስለታሸገች ሳይኾን፤ መለኮት አተማትና ከዚያም ጻፈባት፤ የተነበበችውም ሳትከፈት ነው፤ ምክንያቱም አብ ዐዲስና እጅግ ግሩም የኾነን ምስጢር በርሷ ውስጥ ገልጧልና ነው፤ ታትማ ተዘግታ ተጠብቃ ወደኖረችው በመግባት ቃል በርሷ ዐደረ፤ የድንግልናዋ ማኅተም (ማስረገጫ) በአካሏ ነበረ፤ ግን ደግሞ እንዲኹ አስደናቂ የኾነ ፅንስም ነበረባት፤ አብ በርሷ የመልካም ነገሮች ዜና ላከልን፤ ከኀጢአታቸው እስራት የተነሣ ለተፈረደባቸውም ኹሉ ይቅርታን በርሷ በኵል አደረገ)[99] በማለት የታተመች መጽሐፍ በተባለችው በቅድስት ድንግል ማርያም የተደረገውን የአካላዊ ቃልን ምስጢር በአድናቆት ገልጦታል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ የሰላምና የይቅርታ መልእክትን የያዙ የታተሙ ደብዳቤዎች ብቻ ሳይኾኑ የክፋት መልእክትንም የያዙ የታተሙ መጽሐፎች (ደብዳቤዎችን) እናገኛለን፡፡ ይኸውም በ፪ሳሙ ፲፩፥፲፭ ላይ ንጉሥ ዳዊት የኦርዮንን ሚስት ቤርሳቤሕን ተመኝቶ ኀጢአትን ከሠራ በኋላ፤ ባሏ ኦርዮ እንዳያውቅ ለኢዮአብ ኦርዮ የሚሞትበትን ደብዳቤ በመጻፍ በማኅተም ዐትሞ፤ ኦርዮን በግፍ በማስገደል ሚስቱ ቤርሳቤሕን ወስዷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ንጉሡ አክዓብና ንግሥቲቷ ኤልዛቤል የናቡቴን የወይን ቦታ በተንኰል ለራሳቸው በመመኘት፤ ንግሥቲቱ ኤልዛቤል በንጉሡ ስም ናቡቴ የሚገደልበትን የክፋት ደብዳቤ በመጻፍ በማኅተም ዐትማ በግፍ ናቡቴ እንዲገደል አድርጋለች (፩ነገ ፳፩፥፯-፲፮)፡፡

እነዚኽ ያየናቸውን ኹለት የታተሙ መጽሐፎች (ደብዳቤዎች)፤ የክፋትና የተንኰል መልእክት በውስጣቸው የተጻፉባቸው፤ ንጹሓን ሰዎች በግፍ የሞቱባቸው ሲኾኑ፤ በተቃራኒው ግን ኢሳይያስ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የመሰከረላት የታተመች ደብዳቤ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም ግን፤ የወልድ ጥልቅ ምስጢሮች በውስጧ የተገለጹባት የሰላምን መልእክት ብቻ የያዘች፣ በመንጸፈ ደይን በሲኦል ወድቀው በጽኑ ስቃይ የነበሩ የሰው ልጆችን ነጻ ያወጣ፤ ወሃቤ ሰላም ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደችልን የታተመች የኢሳይያስ መጽሐፍ ናት፡፡[100]

[99]Jacob of Serugh, On the Mother of God, pp 38-39

[100]James p198





ይኽነንም ልዩና ድንቅ ምስጢር ቅዱስ ያዕቆብ ሲያስተምር "ማርያም ሆይ አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፤ ምስጋናንም (በረከትንም) የተመላሽ ነሽ፤ ቃሎቼ ምስጢራዊዉን ድንቅነትሽን ሊያሟኑትና ሊገድቡት አይገባም፤ ከጋብቻ በላይ (ውጪ) የኾንሽ አንቺ ንጽሕት፣ ድንግልም እናትም፤ አእላፍ የኾኑ አንደበቶች እንኳ የማይበቁት (የማይገልጹት) ጸጋን ተመልተሻል፤ ፅንስ በማሕፀንሽ አለ፤ ድንግልና ግን በአካሎችሽ ኹሉ ነው፤ በጡቶችሽ ወተት አለ፤ ማሕፀንሽ ግን ለጋብቻ ሩካቤ ዝግ ነው፤ ባገቡ ሴቶች ላይ ያለው የሩካቤ ጭንቅ ካንቺ ላይ ተወግዷል (ፈጽሞ የለም)፤ ግን በማሕፀንሽ ውስጥ እናቶችን ኹሉ ደስ የሚያሰኝ ፍሬ አለ፤ አካልሽ ከሥርዓተ ሩካቤ ነጻ ነው፤ ግን አንቺ ከወላዶች ኹሉ የተወደድሽዩቱ ሆይ ማሕፀንሽን ልጅ መልቶበታል፤ ወንድ ፈጽሞ የለም ግን ያለ ጋብቻ እንበለ ዘርዕ መውለድ አለ፤ ከዚኽም የተነሣ ዐዋቂ ነን ባዮች ተረቱ ሊረዱሽ አይቻላቸውምና ... የአብ ምስጢር የተጻፈባት ደብዳቤ ርሷ ናት፤ ዓለምም በርሱ ዐዲስ ይኾን ዘንድ (ወልድ) ከርሷ በነሣው ሥጋ የተገለጠባት፤ አንቺ ደብዳቤ ሆይ መገርመሪያ ተጽፋ ከዚያ የታሸገች (የታተመች) አይደለችም፤ መገርመሪያውኑ ታሽጋ (ታትማ) ከዚያም ተጻፈባት፤ ይኽ እጅግ ድንቅ ነው፤ በታተመች ጊዜ በምስጢር ደግሞ ተጻፈ፤ ሳይከፈትም በግልጥ ይነበባል፤ ርሷ ደብዳቤን ኾነች በርሷ የተጻፈውም አካላዊ ቃል ነው፤ በተነበበ ጊዜም ከምሥራቹ የተነሣ ምድር በራች ፈካች"[101] በማለት ከነቢዩ ከኢሳይያስ ትንቢት በመነሣት የታተመች የሰላም መጽሐፍነቷን ገልጦታል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን ያገኘች የቅድስት ድንግል ማርያምን ቃል ኪዳን በተናገሩበት ድርሳን ላይ ይኽነን የኢሳይያስን ትንቢት ሲተረጕሙ "*አሜሃ ተፈጸመ ቃለ ኢሳይያስ ዘይቤ በእንቲአሃ ዘይውህብዎ መጽሐፈ ለብእሲ ዘየአምር መጽሐፈ ወይብልዎ አንብብ ዘንተ ወይብል ኢይክል አንብቦቶ እስመ ኅቱም ውእቱ ወካዕበ ይውሁብዎ መጽሐፈ ለብእሲ ዘኢየአምር መጽሐፈ ወይብልዎ አንብብ ዘንተ ወይብል ኢየአምር መጽሐፈ፤ ወሶበ ይብል ይውሁብዎ ለብእሲ መጽሐፈ ኅቱመ መኑ ይእቲ ዛቲ መጽሐፍ ኅትምት እግዝእትነ ማርያም ይእቲ፤ ኅትምት ዘይቤ ድንግልና ኅሊና ወሥጋ ውእቱ ዘፈኀርዋ ሎቱ ካህናት ለዮሴፍ በከመ ሕግ ወኢይክል አንብቦቶ እስመ ኅቱም ውእቱ ሶበ ይብል በእንተ ዘኢቀርበ ኀቤሃ*

[101]Jacob of Serugh, On the Visitation pp 69-70



www.ethiopianorthodox.org

ወኢያአምራ በከመ የአምሩ ዕደው አንስትያሆሙ እስመ እግዚአብሔር የዐቅባ ወለውእቱኒ ኢያበውሀ ይቅረባ እስመ የአምር ውእቱ ዘይከውን በላዕሌሃ" (መጽሐፍ ለሚያውቅ ሰው አጥፌው ሰጥተው ይኽንን አንብብ እንዲሉት ታጥፏልና ማንበብ አልችልም እንዲል፤ ዳግመኛም መጽሐፍ ለማያውቅ ሰው ዘርግተው ሰጥተው ይኽነን አንብብ እንዲሉት ርሱም መጽሐፉን ማንበብ አላውቅም ይላል ብሎ ኢሳይያስ ስለርሷ የተናገረው ያን ጊዜ ደረሰ ተፈጸመ፤ የታተመች መጽሐፍ የተባለች ማን ናት? እመቤታችን ማርያም ናት፤ የታተመች ማለት በድንግልና ኅሊና በድንግልና ሥጋ ነው፤ የታተመ መጽሐፍ ለሰውዬው ሰጡት ማለት ካህናት እመቤታችንን ለዮሴፍ መስጠታቸውን ነው፤ የታጠፈ ነውና ማንበብ አላውቅም ማለት ወንዶች ሴቶቻቸውን በግብር እንዲያውቋቸው ርሱ ርሷን በግብር አለማወቁን ነው፤ እግዚአብሔር ይጠብቃታልና፤ ርሷን ይቀርባት ዘንድ አያሳሳበውም ከርሷ ጌታ እንዲወለድ ያውቃልና)[102] በማለት የረቀቀውን ምስጢር አስተምረዋል፡፡

## ጽምዕት ምድር (የተጠማች ምድር) Thirsty Land

ቊጥሩ ከዐበይት ነቢያት አንዱ የኾነው ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በምዕ ፵፬፥፫ ላይ የሕይወት ፍሬ፣ የሕይወት ውሃ ክርስቶስን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ የተገኘችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን፤ በተጠማች ምድር በመመሰል ልዩና አስደናቂ ትንቢትን ተናግሯል፡፡

ስለተጠማች ምድር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ምሳሌያዊ አገላለጽ ተገልጾ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ያኽል ክቡር ዳዊት በመዝሙሩ ላይ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርና ናፍቆት ሲገልጸው "ዋልያ ወደ ውሃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፤ አቤቱ እንዲኹ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች፤ ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች...አምላኬ አምላኬ ወደ አንተ እገሠግሣለኍ፤ ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች፤ ዕንጨትና ውሃ በሌለበት በምድረ በዳ" (መዝ ፵፩፥፩፤ ፷፪፥፲፩) በማለት ለፈጣሪው ያለውን ልዩ ፍቅር በዚኹ አገላለጽ ተናግሮታል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስም አስቀድሞ ተገልጾለት በምዕ ፵፬፥፫ ላይ "በተጠማ ላይ ውሃን፤ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለኹና፤ መንፈሴን በዘርኽ ላይ በረከቴንም በልጆችኽ ላይ አፈስሳለኹና" በማለት ውሃን ስለምታስገኘው ነገር ግን ደረቅና የተጠማች ስለኾነቺው ምድር በትንቢቱ ላይ ተናግሯል፡፡

[102] ድርሳነ ኪዳነ ምሕረት ዘየካቲት፤ ገጽ ፲፮





በቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት በእጅጉ የተራቀቁ ሊቃውንትም በመንፈስ ቅዱስ ምስጢር ገላጭነት ዘርዐ ብእሲ ሳይወድቅባት፤ ሩካቤ ብእሲ ሳይደርስባት፤ በግብረ መንፈስ ቅዱስ የሕይወት ውሃ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምን በኢሳይያስ የተጠማች ምድር በመመሰል በስፋት አስተምረዋል፡፡

ከእነዚኽ ሊቃውንት መኻከል ቅዱስ ኤፍሬም ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ይገኙበታል፡፡ የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ ከበዛላቸው ከነዚኽ አበው አንዱ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕ ፯፥፲፬ ላይ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ትለዋለች" በማለት በድንግልና እንደምትወልድ የተናገረውንና በምዕ ፵፬፥፫ ላይ "በተጠማ ላይ ውሃን፤ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለኹና" ሲል ያለ ወንድ ዘር የሕይወት ውሃ ክርስቶስን በኋላም ድንግልና እንደምትወልድ የተናገረውን ትንቢታዊ ኀይለ ቃልን በማስተባበር፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር መንፈሱን እንደሚልክ ቃል መግባቱን -(ኢሳ ፵፬፥፫) ፍጻሜው በሉቃ ፩፥፴፭ ላይ "መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል" ተብሎ የተነገረው ቃል የተፈጸመባት መኾኗን በልደት ድርሳኑ ሲገልጽ፡-

"Come, Isaiah, see the Immanuel in the cave..." (ኢሳይያስ ሆይ ና ፤ ዐማኑኤልንም በዋሻው ውስጥ ተመልከት፤ እውነት በትንቢትኽ ውስጥ ጸንቷልና ነገሩን አትመው፤ ከዚያች ከተጠማችው ምድር ከድንግል ማርያም ተክል በቀለ፤ አንተ በትንቢትኽ እንዳሳወቅኸው ርሷ አልተዘራባትም አልተተከለባትም፤ እንሆ ድንቁ፤ ተነሥ እና ከብዙ ሕዝቦች ጋር ተደነቅ፤ ምክንያቱም በድንቅ የተመላችው የርሷ ማኅተመ ድንግልናና ወተት በአንድ አካሏ ተስተባብረው አሉና፤ ድንግል እናቱ ናት፤ ከዚኽ የተነሣም ርሱ ስሙ "ድንቅ" ነው፤ በፊቱ የሰው ፍጥረት እና የሰው ልጆች ኹሉ ንግግር ኀይል የሌላቸው ናቸው፤ በድንግልናዋ የወለደቺው ብላቴናዩቱ ልጅ ጸሐፊውን አፉን አስያዘቺው፤ ቃሎቹም ደግሞ ለአንዳች ትርጉምም ይኹን ለአንዳች ገለጻ ዐቅም አልነበረውም፤ ጠቢቡ እና የረዘሙ ንግግሮቹ (ጉሩቂዎቹ) ተረትተዋል፤ ምክንያቱም ድንግልናና ወሊድ ተስተባብረው ለተመለከተ ኹሉ መናገር እጅግ የሚከብድ ነውና፤ ታላቁ የጽድቅ ፀሐይ ነጸብራቁ ወደ ውስጥ አሰባሰበ፤ አንዲት ብላቴና ልጅም ብቻዋን በቅድስና በማሕፀኗ ተሸከመቺው፤ ርሷ ብርሃናት የሚኾኑ ኹሉ የሚፈሩትን አማናዊ



www.ethiopianorthodox.org

ብርሃን ወለደቺው፤ ምክንያቱም በልደቱ አማካይነት ርሱ ጨለማን ከኹሉም ስፍራዎች ላይ አንሥቷልና)[103] በማለት ያለ ዜር ያለ ሩካቤ የሕይወት ተክል፣ የሕይወት ፍሬ፣ የሕይወት ውሃ ጌታን የፀነሰች፤ ድንግል ስትኾን ከጡቶቿ ወተት የተገኙባት በመኾኗ ነቢዩ ኢሳይያስ "በተጠማ ላይ ውሃን፤ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈሳለኹና" በማለት የተናገረው ትንቢት ፍጻሜውን ማግኘቱንና፤ ይኽም አዋቂዎች ነን ከሚሉ ኹሉ የረቀቀ ሰማያዊ ምስጢር መኾኑን አስተምሯል።

ከእመቤታችን በረከትን የተቀበለው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም፤ ነቢዩ ኢሳይያስ በተጠማች ምድር መስሎ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የተናገረውን ትንቢት እያራቀቀ ስለ ክርስቶስ ልደት በጻፈው ድርሳኑ ላይ ሲገልጽ *"Mary acquired by you..."* (ድንግል ማርያም ባንተ ያገቡ ሴቶችን መሰያን የራሷ አደረገች፤ ያለ ተራክቦ ጽንስ በርሷ አለ፤ ከተለመደው ኹናቴ ውጪ ወተት በጡቶቿ አለ፤ አንተ ሳይታሰብ (በድንገት) የተጠማቿውን መሬት የወተት ምንጭ አደረግኻት)[104] በማለት ድንግልናና ወተትን አስተባብራ በመገኘቷ የኢሳይያስ የትንቢት ቃል የተፈጸመባት መኾኑን ገልጾታል።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ በዚኹ በልደት ድርሳኑ ላይ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከኾዱ ይፈልቃል" (ዮሐ ፯፥፴፯-፴፰) በማለት ካስተማረ ከጌታ ዘንድ የሕይወት ውሃን ስለለመነች ስለ ሳምራዊቷ ሴት ሲገልጽ፡-*"Mary the thirsty land in Nazareth..."* (በናዝሬት የተጠማችዋ መሬት ማርያም በገሮዋ (ብሥራትን ሰምታ) ጌታችንን ፀነሰችው፤ አንቺም ውሃን የተጠማሽ ሴት ሆይ በመስማትሽ ወልድን (አመንሽበት) ገሮዎችሽ የተባረኩ ናቸው፤ ምንጩን ይኸውም ለዓለም የሚጠጣን የሰጠ ርሱን የጠጡ)[105] በማለት ገልጾታል፤ ኾኖም ግን ይኽቺ ሳምራዊቷ ሴት "ጌታ ሆይ እንዳልጠማ ይኽነን ውሃ ስጠኝ" በማለት ለራሷ ብቻ ይኽነን የሕይወት ውሃ ስትጠይቅ፤ የኹላችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የሕይወት ውሃ ክርስቶስን ለኹላችን በኀቱም ድንግልና ወልዳልናለችና *"ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዐብየኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበአማን"* (ድንግል ሆይ ስለዚኽ እንወድሻለን፣ ከፍ ከፍ እናደርግሻለን፤ እውነተኛውን መብልና እውነተኛውን መጠጥ ወልደሽልናልና)[106] እያልን ክብሯን እንመሰክራላታለን።

ሊቁ ኤፍሬምም ይኽነን ሲያጕላ *"From the thirsty earth..."* (የተጠማችው ምድር ምንጭን በማፍለቃ መጠን አመነጨች የመሬትንም ጥም ስትቈርጥ ዘንድ (ልትቈርጥ)[107] በማለት የተጠማች ምድር ከተባለች ከቅድስት ድንግል ማርያም፤ የሕይወት ውሃ ዐማኑኤል ተወልዶ፤ ከመሬታውያን ከእኛ የነፍሳችን ጥም የቈረጠልን መኾኑን በስፋት አስተምሯል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ካፈራቻቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ከተራቀቁት ሊቃውንት መኻከል ሊቁ ማሕሌታይ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ላይ *"ጽምዕት ምድር ዘኢሳይያስ"* (የኢሳይያስ የተጠማች ምድር)[108] በማለት ሲገልጻት፤ ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ "ተፈሥሒ ኦ ምድር ጽምዕት ዘኢሳይያስ ዘኢሰቀያ ዝናመ ደመናት" (ከደመናት ቆሚገኝ ዝናብ ያላጠጣት (የኢሳይያስ የተጠማች ምድር ሆይ ደስ ይበልሽ)[109] በማለት የትንቢተ ኢሳይያስ አማናዊ ትርጓሜን እንደ ወርቅ አንክብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ ገልጾታል።

## ንግሥተ ነገሥታት

ነቢዩ ኢሳይያስ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ለንጉሠ ሰማይ ወምድር ለክርስቶስ እናት ለንግሥተ ነገሥታት ለቅድስት ድንግል ማርያም በእውነት የአክብሮት ስግደት እንደሚገባት በምዕ ፵፱፥፳፫ ላይ "ነገሥት አማሁትኪ ወነጋሥያት ሐፃንያትኪ ወይሰግዱ ለኪ ውስተ ገጸ ምድር ወይልሕሱ ጸበለ እግርኪ" (ነገሥታትም አሳዳጊዎች አባቶችሽ ይኾናሉ፤ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይኾናሉ፤ ግምባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል፤ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ) በማለት አያቶቿ አባቶቿ ቀድሞ ከነገሥታት ወገን የኾኑ እነዳዊት እነሰሎሞን እንደነበሩና፤ እቴጌ የነበሩ እነ ቤርሳቤሕና፤ ኋላም ንጉሥ ዳዊት በመዝ ፵፬፥፲፮ ላይ "በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ" ብሎ በተናገረው ትንቢት መሠረት በመስቀል ሥር እናት ትኾነን ዘንድ በአደራ

[103] Jacob of Serugh, On the Nativity of Our Lord, pp 120-121

[104] St. Ephrem, Hymns on the Nativity 11:4, p132

[105] ibid p362

[106] አባ ሕርያቆስ፣ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፱

[107] St. Ephrem, Hymns on the Nativity p 96

[108] ቅዱስ ያሬድ ፣ መጽሐፍ ድጓ ፣ ገጽ ፫፻፺፰




www.ethiopianorthodox.org

የተቀበልናት የአደራ ልጆቿ ምእመናን ኹላችን የፍቅር ሞግዚቶቿ እንደምንኾን አስረድቷል።

ዳግመኛም ትውልድ ኹሉ "ብፅዕት" ለሚላት የነገሥታት ንጉሥን በኀቱም ድንግልና ለወለደች ለርሷ የአክብሮት ስግደት የሚገባት ናትና "ግምባራቸውን ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል፤ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ" በማለት የተናገረውን ትንቢት በመያዝ ለንግሥታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የአክብሮት ስግደትን እናቀርባለን ።

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ለአማልክት አምላክ፣ ለጌቶች ጌታ፣ ለነገሥታት ንጉሥ ለክርስቶስ እናት ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናና የአክብሮት ስግደት የሚገባት መኾኑን ኢሳይያስ የተናገረውን ቃል መነሻ በማድረግ ቅድስት ድንግልን ሲያመሰግን "ማኅበረ ቅዱሳን የዐውዱኪ ሐዋርያት ወነቢያት ይዌድሱኪ ወየኮቱኪ እስመ ኪያኪ ኀርየ ለታዕካሁ ከመ ትኩኒዮ ማኅደረ፤ መላእክት ይኬልሉኪ ጻድቃን ይባርኩኪ አበው ይገንዩ ለኪ ነገሥት ይትቀነዩ ለኪ ወይሰግዱ ለንግሥኪ እንዘ ይልሕሱ ሀበለ አግርኪ" (የቅዱሳን አንድነት ይከቡሻል፤ ሐዋርያትና ነቢያት ፈጽመው ያመሰግኑሻል፤ ማደሪያው ትኾኚው ዘንድ አንቺን ለአዳራሽነት መርጦሻልና፤ መላእክት ይጋርዱሻል፤ ጻድቃን ያመሰግኑሻል፤ አባቶች ያገለግሉሻል፤ ነገሥታት ይገዙልሻል፤ የእግርሽን ትቢያ እየላሱ ለንግሥናሽ ይሰግዳሉ)[110] በማለት ንእድ ክብርት ለኾነች ለርሷ የሚገባትን ምስጋና አስተምሯል።

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ኤርምያስ
# ክፍል ኹለት

ኤርምያስ ማለት ከእግዚአብሔር የተላከ ብርሃን ማለት ሲኾን፤ ትውልዱ ከነገደ ሌዊ በመኾኑ ክህነትን ከነቢይነት አስተባብሮ የተገኘ ነው። በነቢይነት መነሣቱም የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ በነገሠ በ፲፫ኛው ዓመተ መንግሥት ከ፮፻፳፯-፭፻፹፮ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲኾን፤ ርሱም እንደ ኢሳይያስ በበትር የምትመሰል የቅድስት ድንግል ማርያምን ምሳሌ በለውዝ በትር አምሳል ተመልክቷታል (ኤር ፩፥፲፩)።

[109] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘኀሙስ ምዕ ፱፥፲፭

[110] ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ዝማሬ ወመዋሥዕት



www.ethiopianorthodox.org



ይኽ ብቻ ሳይኾን ከኹለት ደቀ መዛሙርቱ ከባሮክና ከአቤሜሌክ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነች ዐጽቀ በለስ በንስር አንገት የተላከለት ታላቅ ነቢይ ነው።

## የአቤሜሌክ በለስ

ንጽሐ ሥጋን፣ ንጽሐ ነፍስን፣ ንጽሐ ልቡናን አስተባብራ የተገኘች የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ፤ አቤሜሌክ በሙዳይ ውስጥ ባስቀመጣት የበለስ ቅርንጫፍ ትመሰላለች (ተረ. ኤር ፱፥፩-፴)።

ይኸውም የነቢዩ ኤርምያስ ደቀ መዛሙርት የነበሩት አቤሜሌክና ባሮክ የሚናገረውን የምርኮ ትንቢት በመስማት "ኢታርእየነ ሙስናሃ ለኢየሩሳሌም" (የኢየሩሳሌም ጥፋቷን አታሳየን) እያሉ ይጸልዩ ስለነበር፤ ምርኮ ሲደርስ እግዚአብሔር ነቢዩ ኤርምያስን አቤሜሌክን ለድውያን የሚቀባ ዐጽቀ በለስ እንዲያመጣ ወደ አግሪጳስ ወይን ቦታ እንዲልከውና፤ ባሮክንም መቃብረ ነገሥትን እንዲጠብቅ እንዲያደርግ፤ በዚኽም ከምርኮ መከራ እንደሚሰወሩ ነግሮት ኤርምያስም የታዘዘውን አድርጓል።

አቤሜሌክም ዐጽቀ በለሷን በሙዳይ አድርጎ ይዞ ሲመጣ ጥቂት ያርፍ ዘንድ በጥላ ሥር ሲቀመጥ ወዲያው እንቅልፍ እንቅልፍ ብሎት በተአምር ስሳ ስድስት ዓመት ተኝቶ ነቅቷል፤ ያን ጊዜም በለስ ያለበትን ሙዳይ ሲከፍት በለሲቱ ዐዲስ ኹና ወተቷ እየፈሰሰ አገኘ፤ "ተመልሼም ብተኛ መምህሬ ኤርምያስ ይቈጣኛል" ብሎ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ሲጀምር፤ አገሩ ተፈትቶ መንገድ ጠፍቶ፤ ከተማውና ቤቱ ተሰውሮት ለመኼድ ቸገረው፤ ያን ጊዜ እንቅልፍ ባይለቀኝ ነውን ፤ ወይንስ አእምሮዬ ተለይቶኛል ብሎ ቆሞ ሲመለከት ከተራራ ላይ መልአኩ በአምሳለ አረጋዊ ታየው፤ ከዚያም ኼዶ "አይቴ ሀለዉ ኤርምያስ ወአኀውየ"(የእግዚአብሔር አገልጋዩ ኤርምያስ የት አለ? ባገር ያሉ ወገኖች ኹሉና የሌዊ ወገን ባሮክስ የታለ?) በማለት ሲጠይቀው፤ ኢየሩሳሌም ከጠፋች ስሳ ስድስት ዓመት መኾኑንና እነኤርምያስም በስደት በባቢሎን መኖራቸውን አስረዳው።

አቤማሌክም ለአረጋዊዉ "ሽማግሌ ባትኾን በነቀፍኩኽ ነበር፤ ለድዉያን የምንቀባው በለስ ቈርጠኽ አምጣ ብሎ መምህሬ ልኮኝ፤ በለሷ ዐዲስ ኾና ወተቷ እየተንጠፈጠፈና፤ ቅጠሏ ሳይጠወልግ እንዲኽ ትለኛለኽ" በማለት ሙዳዩን ከፍቶ በለሲቱ ትኩስነቷንና ወተቷ እየተንጠፈጠፈ አሳየው፤ ርሱም በማድነቅ "እግዚአብሔር ከመከራው በእንቅልፍ ሰውሮኽ ነው እንጂ ፤ ሕዝቡ ወደ ባቢሎን ተማርከው ከኼዱ

ዛሬ ስሳ ስድስት ዓመት ኾነ" በማለት፤ የበለስ ማፍሪያ ጊዜ እንዳይደለ አሳየው፤ ከዚያም አቤሜሌክን መልአኩ እየመራው ከባሮክ ጋር አገናኘው፤ እነርሱም ኩምርኮ የመመለስ ነገር እንዲገለጽላቸው ቀኖና ቢገቡ ከምርኮ ለመመለስ አራት ዐመት እንደቀረው ተገልጾለቸው ያነን በወረቀት ጽፈው ሳሉ የታዘዘ ንስር ሲመጣ የምሥራቹን መልእክትና በለሲቱን በአንገቱ አስረው ሲልኩት ያነን ይዞ ወደ ባቢሎን ወርዷል (ተረ. ኤር ፲፥፩-፴፪)፡፡

ኤርምያስም ከወገኖቹ ሰው ሙቶበት ሊቀብረው ሲዘጋጅ፤ ንስሩም ኤርምያስ በማለት በቃል ሰብኣዊ በመጥራት፤ የምሥራቹን መልእክትንና ወተቷ የሚንጠባጠበውን ትኩሷን በለስ በመስጠት፤ ወዲያውኑ "ወኬደ ለምዉት በኪደተ እግሩ" ይላል ምዉቱን ቢረግጠው ተነሥቶ የምሥራቹን ቃል መስክሮ ዐርፏል፤ ቃሉም "ከምርኮ ለመመለስ አራት ዓመት ቀርቶታልና፤ ከአሕዛብ የተጋባችኍ ተፋቱ፤ ያልተጋባችኍ ተጠበቁ" የሚል ሲኾን፤ ኤርምያስም ለሕዝቡ ይኽነን ቢነግራቸው ደጋጎቹ ሲቀበሉ ክፋዎቹ ግን "እንመለስ እንጂ ሀገራችንን ማን ነሥቶን፤ ሚስቶቻችንንስ ማን አፋትቶን" በማለት ዝም አሉ፡፡

ጊዜው ሲደርስ ኤርምያስ ደጋጎቹን ይዞ ጉዞ ሲዠምር በፊት ቃሉን ያልተቀበሉት ሲከተሉት ሲመጡ አይቶ "አትከተሉኝ ቀድሞ አይኾንም ብላችኍ የለምን" አላቸው፡፡ አሕዛብም "እንዲኽ ሲጠሏችኍ አትቀሩምን፤ የሚስት የልጅ ሀገርስ ሀገር አይደለምን" ቢሏቸው፤ ሀገራችን ሳንገባ አንቀርም በማለት ሲኼዱ፤ ኤርምያስም ከአቤሜሌክና ከባሮክ ጋራ በመኾን ድል አድርጎ መለሳቸው፤ እነርሱም ተመልሰው ወደነበሩበት ወደ ባቢሎን ሲኼዱ፤ የባቢሎን ሰዎችም "እኛን ጠልታችኍ ኼዳችኍ የለምን" አንቀበልም ብለው ቢያባርሯቸው፤ እነርሱም እግራቸው እንዳደረሳቸው በመኼድ ሀገር አቅንተው ኑረዋል፤ ሀገሪቱም ሰማርያ ተብላለች (ተረ. ኤር ፲፩፥፩-፴)፡፡

ይኸውም ለጊዜው ቢደረግ ለኋላው ግን ምሳሌ ነበር፤ ባሮክ የእግዚአብሔር አብ፤ ንስር የወልደ እግዚአብሔር፤ ባቢሎን የሲኦል ምሳሌ፤ ኤርምያስ የአዳም፤ እስራኤል የነፍሳት፤ አንወጣም ያሉት የአይሁድ፤ ንስሩ በምርኮ በባቢሎን ወደታሰሩት ወርዶ ምሥራች ከምርኮ መመለስ ኾነ እንዳለ ጌታም ፭ሺሕ ከ፭፻ ዘመን በመንጸፈ ደይን ወድቀው በሲኦል የታሰሩ ነፍሳትን በዕለተ ዐርብ ነጻ የማውጣቱ ምሳሌ ነው፤ ይኽነንም ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ ሲገልጽ "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ኾነ፤ በርሱም ደግሞ ኼዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው"





በማለት አስተምሯል (፩ ጴጥ ፫፥፲፰-፳)፡፡

በለስ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ፤ ያቺ ስሳ ስድስት ዘመን ቅጠሏ ሳይጠወልግ ዐዲስ ኾና ወተቷ እየተንጸፈጸፈ እንደተገኘች ኹሉ ከአዳም እስከ እመቤታችን ያለው ትውልድ ቢቈጠር ስሳ ስድስት ሲኾን፤ ይኸም ምሳሌነቷ በስሳ ስድስተኛው ትውልድ ከቤተ ይሁዳ የተገኘችው ቅድስት ድንግል ማርያም ቀድሞ በአዳም የነበረ ንጽሐ ጠባይዕ ሳያድፍባት ድንግልናዊ ወተትን ያስገኘች መኾኗን አስቀድሞ ያሳየ ነውና፤ ንጽሕተ ንጹሓን፣ ቅድስተ ቅዱሳን የኾነች ርሷን "የአቤሜሌክ በለስ" በማለት እናመሰግናታለን፡፡

አባ ጊዮርጊስ ስለዚኽ ምስጢር አርጋኖን በተባለው የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ ሲተነትነው፡- *"ወሀየንተ ኀጠታተ አብላስ ዘቀሰምን አቤሜሌክ ኢትዮጵያዊ ረድአ ኤርምያስ ነቢይ፤ ወወደዮን ውስተ መሶብ፤ ወሕቀ ሐዊሮ ኖመ ታሕተ ጽላሎተ ዕፅ ስሳ ወስድስተ ዓመተ፤ ወነቂሆ መሰሎ ዘዮም ኖመ ወዘዮም ነቅሀ ከሠተ ሙዳዮ ወርእየ ኀጠታተ አብላስ ወረከቦን እንዘ ያንጸፈጽፋ ሐሊቦን፤ ወበጺሖ ኀበ ባሮክ ፈነወ በክሳደ ንስር ምስለ መጽሐፈ መልእክት ኀበ ኤርምያስ ነቢይ ከመ ይኩን ፈውሰ ለድውያን ጼዋ ጽዮን ዘነበሩ ውስተ ባቢሎን ወከማሁ ደመ ፍሬ ክርሥኪ ዘተሐጽነ በሐሊበ ድንግልናኪ ዘያንጸፈጽፍ ተውህበ ከመ ይኩን ፈውሰ ለድውያነ ፄዋ ጽዮን ዘነበሩ ውስተ ሲኦል"*

(የነቢዩ ኤርምያስ ደቀመዝሙር ኢትዮጵያዊዉ አቤሜሌክ ለቅሞ በመሶብ ውስጥ በአኖራቸው የበለስ ቅንጣቶች ፈንታ ተድላ ደስታን ተከደንኍ፤ ጥቂትም ዕልፍ ብሎ በዕንጨት ጥላ ሥር ስሳ ስድስት ዘመን ተኝቶ ቢነቃም ዛሬውኑ ተኝቶ ዛሬውኑ የነቃ መሰለው፤ ሙዳዩን ከፍቶም የበለሶቹን ቅንጣቶች አየ፤ ወተታቸውን እያንጠፈጠፉ አገኛቸው፤ ባሮክም ወደ አለበት በደረሰ ጊዜ በንስር አንገት አድርጎ ከጽሑፋዊ መልእክት ጋር ወደ ነቢዩ ኤርምያስ ላከ በባቢሎን ለሚኖሩ የጽዮን ምርኮኞች ሕሙማን ፈውስ ይኾን ዘንድ እንዲኹም በሚንጸፈጸፍ ድንግልናዊ ወተትሽ ያደገው የማሕፀንሽ ፍሬ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በሲኦል ለነበሩ የጽዮን ምርኮኞች ሕሙማን ፈውስን ይኾን ዘንድ ተሰጠ)[111] በማለት ሙሉ ትርጓሜን በመስጠት የምሳሌውን መፈጸም በጉልህ አስተምሯል፡፡

ይኽ ታላቅ ሊቅ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ በድጋሚ ምስጢሩን ጠቅልሎ ሲገልጸው

[111] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ ፮፥፰-፲፩



www.ethiopianorthodox.org

*"አንቲ ውእቱ ዘበለስ ትንቢት ከረቦ*
*አቤሜሌክ ኢትዮጵያዊ ሐዲስ እንተ ረከቦ*
*፷ወ፮ተ ዓመተ በጊዜ ነቅሀ ሰኪቦ"*

(ስሳ ስድስት ዘመን ተኝቶ በነቃ ጊዜ በሐዲስነት (በትኩስነት) ኢትዮጵያዊዉ አቤሜሌክ ያገኘው የትንቢት በለስ ቅርጫት አንቺ ነሽ)[112] በማለት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት፣ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጥ የፍሬ ሕይወት የክርስቶስ እናት መኾኗን ሲገልጽ፣ በተጨማሪም በዚኹ መጽሐፍ ላይ

*"መጽሐፈ ብሥራት አንቲ በክሣደ ንስር ዖፍ ዘነገድኪ ብሔረ ፋርስ*
*እንዘ ትጸውሪ ፍሬሁ ለዕፀ ፈውስ*
*ከመ ትናዝዚ ልቦሙ ለእለ ነበሩ ሕዝብ በተጽናስ"*

(በችግር የተቀመጡ ወገኖች ልቡናን ታረጋጊ ዘንድ የፈውስ ዕፀ ፍሬን ተሸክመሽ ንስር በተባለ ዎፍ ወደ ፋርስ ምድር የኼድሽ የምሥራች መልእክት አንቺ ነሽ)[113] በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ አስቀምጦታል።

## ነገረ ማርያም በትንቢተ ሕዝቅኤል
## ክፍል ሦስት

ሕዝቅኤል ቍጥሩ ከዐበይት ነቢያት መኻከል ሲኾን ትውልዱ ከነገደ ሌዊ የኾነ ትንቢቱም በ፵፰ ምዕራፍ የተከፈለ ከ፭፻፺-፭፻፸ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረ ነው ይኸም ነቢይ በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ በትንቢቱ ላይ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናትነትና ዘላለማዊ ድንግልና የተናገራቸውን የነገረ ማርያም ምሳሌዎችን ከዚኽ በታች አስቀምጬያቸዋለኍ።

### ኪሩባዊት ሠረገላ

ይኽ ታላቅ ነቢይ ሕዝቅኤል በኮቦር ወንዝ ላይ ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀኗ የተሸከመች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ በገርርባዋ ያዘለች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ የምትኾን ሠረገላኗ ተመልክቷል (ሕዝ ፩፥፬-፳፰)።

[112] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ እንዚራ ስብሐት ገጽ 41

[113] ዝኒ ከማሁ ገጽ 27





መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሠረገላ በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ለምሳሌም ያኽል ዮሴፍ በሠረገላ ላይ ተቀምጦ በግብጽ የተሾመውን ሹመት (ዘፍ ፵፩፥፵፫)፤ ኤልያስ ያረገበት ሠረገላ (፪ነገ ፪፥፲፩)፤ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ጌትነት የጠቀሰው (መዝ ፷፫፥፫)፤ ዳዊት ለልጁ ለሰሎሞን ለቤተ መቅደስ እንዲሠራ ያዘዘው የኪሩቤል የወርቅ ሠረገላ (፩ዜና፳፰፥፲፰) ሲገኝ ነቢዩ ሕዝቅኤልም በፈለገ ከቦር ያየት ጌታ የተቀመጠባት ሠረገላን በቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢር የተራቀቁ ቅዱሳን አበው በእመቤታችን መስለው በስፋት አስተምረዋል።

እነዚኽ ሊቃውንትም ኪሩቤል ሱራፌል እሳተ መለኮቱ እንዳያቃጥላቸው በፍርሀት በረዐድ ኾነው፤ በእሳት ሠረገላ ዙፋኑን የሚሸከሙለት፤ በእሳት አዕማድም ዙፋኑን የሚይዙለት ቀዳማዊ አምላክን በማሕፀኗ የተሸከመች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ በገርርባዋ ያዘለች ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ናትና፤ ጉልበቶቿን በእሳት ሠረገላ፤ እጆቿንም በእሳት አዕማድ መስለው የተሰጣትን ክብር አስተምረዋል።

ከእነዚኽ መምህራን መኻከል ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ እና አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ሲገኙ፤ ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ የተባለው የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ስለዚኽ ምስጢር በኆኅተ ብርሃን መጽሐፉ *"አንቲ ተዐብዪ እምኪሩቤል ወትፈደፍዲ እምሱራፌል እስመ ሱራፌል ወኪሩቤል በሠረገላ እሳት ይጸውርዎ ወበምጽናዐ እሳት ይጸንዑ መንበሮ፤ ወአንቲሰ ጾርኪዮ በከርሥኪ ወሐዘልኪዮ በዘባንኪ ወሐቀፍኪዮ በአብራክኪ ህየንተ ሠረገላ እሳት አብራክኪ ኮና ወህየንተ ምጽንዐቲሁ ዘእሳት እደውኪ ኮና"*

(ከኪሩቤል ይልቅ አንቺ ትበልጫለሽ፤ ከሱራፌልም ይልቅ ትልቂያለሽ፣ ትከብሪያለሽ፤ ኪሩቤልና ሱራፌል በእሳት ሠረገላ ተሸክመውታልና፤ በእሳት አዕማድም ዙፋኑን ይደግፋሉና፤ አንቺ ግን በማሕፀንሽ ወስንሺው፣ በገርርባሽም ዐዘልሽው፣ በጉልበቶችሽም ዐቀፍሺው፤ ጉልበቶችሽ እንደ እሳት ሠረገላ ኾኑ፤ እጆችሽም እንደ እሳት አዕማድ ኾኑ)[114] በማለት የክብሯን ታላቅነት መስክሯል።

በተመሳሳይ መልኩ የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ ያተባለው ቅዱስ ኤፍሬም የኪሩቤልን ሠረገላና ቅድስት ድንግል ማርያምን ሲያነጻጽር

[114] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ ኆኅተ ብርሃን፣ ገጽ120



www.ethiopianorthodox.org

*"Blessed are you Mary..."* (በሙሉ መደነቅ በሠረገላው ላይ የሚታየው ልጅ እናት ስለኾንሽ የተባረክሽ ነሽ፤ ድምፅ ከተቸራቸው ከነዚያ መንኰራኵሮች ለርሱ ምስጋና ይቀርባል፤ ኪሩቤልም በነጐድጓድ ድምፅ በፍርሀት ምስጋናን ለርሱ ያቀርባሉ፤ የተባረክሽ አንቺ ርሱን ዐቀፍሺው እናቱ እንደመኾንሽ በፍቅር ደባበሺው እንደ መንኰራኵሮቹም ለርሱ አጐነበስሽ)[115] በማለት መላእክት ዙፋኑን ተሸክመው ያለማቋረጥ የሚያመሰግኑት ርሱን በማሕፀና መሸከሟ፣ በክንዷ መታቀፏ፣ በገርባዋ ማዘሏ ልዩ የሚያደርጋት መኾኑን በማነጻጸር አስተምሯል።

ቅዱስ ኤፍሬም በድርሰቱ በኪሩቤል በሱራፌል ላይ ዐድሮ የሚኖር ርሱ በሥጋዌው የፈጸመውን ታላቅ ትሕትናን ሲያደንቅ *"As You Michael's fiery ranks quake..."* (ሰው ለኾንኸው አምላክ ላንተ ነበልባላዊ የሚካኤል ነገድ ይርዳሉ፣ ይንቀጠቀጣሉ፤ የኤልሻዳይ ልጅ ሆይ ኪሩብና ሌሎቹ እንስሳት ተቀናጅተው ርቱዕ በኾነ መንኰራኵራቸው የሚይዙት ሠረገላ ላንተ የሚበቃ አይደለም፤ ነገር ግን የእመቤታችን ማርያም ንጹሕ ደረቷ ያዘኽ)[116] በማለት ከኪሩቤል ሠረገላ ይልቅ የቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት በጌታ ዘንድ የተወደደ መኾኑን ገልጾታል።

ከአራት መቶ በላይ መንፈሳውያት መጻሕፍትን የጻፈው የእመቤታችን ባዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ይኸ ሊቅ በዚኽ ንጽጽራዊ ትምህርቱ ላይ፤ እመቤታችን ከሰማያውያን መላእክት ክብሯ የበለጠ፤ ዙፋኑንም ከሚሸከሙ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ይልቅ የመፈራት፣ የመወደድ፣ የባለሟልነት ግርማ ከልጇ የተሰጣትና፤ መላእክትን የፈጠረ ጌታን በመውለዷ ከሰማያዊዉ ሠረገላ የበለጠች መኾኗን ሲገልጽ፦

*"The chariot of fire carries Him in awe ..."* (የእሳት ሠረገላው በፍርሀት ርሱን ይይዘዋል፤ ግን ደካማዪቷ ጉልበት መቃጠል ሳያገኛት ርሱን ያዘችው፤ የነበልባል መንኰራኵሮች በፍርሀት አጅበውታል፤ ግን ርሱ በትንሿ በዳዊት ሴት ልጅ በፍቅር ታቀፈ፤ ኪሩቤል በረዐድ ኾነው ርሱን ይሸከማሉ፤ ሱራፌልም ፊታቸውን አዙረው "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ" እያሉ ይጮኻሉ፤ ድንግል ማርያም ግን ርሱን በደረቶቿ ዐቀፈቺው)[117] በማለት የተሰጣትን ታላቅ ክብር አድንቋል።

[115] T.J. Lamy, Sancti Ephraem Syri Hymni et sermons, II (Malines, 1886, 519-590, Bride of light p48
[116] ibid pp 50-51
[117] ibid p62



www.ethiopianorthodox.org



ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግም አስቀድሞ ለነሕዝቅኤልና ለነኢሳይያስ በኪሩቤል ሠረገላ ላይ የተገለጸውና በኋላ ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ርሱ መኾኑን በልዩ ድርሰቱ ሲያስረዳ

*"Look upon Him..."* (ሰማያውያን በሚኾኑት ሠረገሎች ላይ የሚቀመጥ ርሱን ተመልከተው፤ አንዲት ብላቴና ልጅም በክንዶቿ ዕቅፍ ስትሸከመው፤ ርሱ ግን ያው አንድ ርሱ ነው)[118] በማለት አስተምሯል።

ታላቁ የነገረ ማርያም ሊቅ ኢትዮጵያዊዉ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *"ኦ ሠረገላ ኪሩባዊት ዘኮንኪ መጸረ ለዘይነግሥ ዲበ ነገሥት ወይትመለአክ ዲበ መላእክት እትጋነይ ለኪ ኦ ሠረገላ ብርሃን እንተ ርእያ ሕዝቅኤል በፈለገ ኮበር ዘባቢሎን"* (በመላእክት ላይ አለቃ ለሚኾንና በነገሥታት ላይ ለሚነግሥ መቀመጫ የምትኾኚ ኪሩባዊት ሠረገላ ሆይ...የባቢሎን ክፍል በሚኾን በኮቦር ወንዝ ሕዝቅኤል ያያት የብርሃን ሠረገላ ሆይ ለአንቺ አገለግላለኹ)[119] በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ ገልጾታል።

ይኸው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ኪሩቤል በእሳት ሠረገላ ኾነው በፍርሀት የተሸከሙትን አምላክ ርሷ ግን በጠባብ ማሕፀኗ የተሸከመች፣ ክብሯ ከፍ ከፍ ያለ መኾኑን ሲተነትን

*"ሕዝቅኤል ወልደ ቡዝ ሰብአ ዐይን ተሰምየ ለቤተ እስራኤል፤ በብሔረ ባቢሎን ወበፈለገ ኮቦር ርእየ ለእግዚአብሔር እግዚእ አዶናይ ዲበ ሠረገላ ኪሩቤል ሥርዐተ መላእክቲ ነጸረ ወምስጢረ ትጉሃን ለበወ ወጸዋትዊሆሙ አእመረ ወሰብሐቲሆሙ ዘኢይፀራዕ ሰምዐ ወመንኰራኵረ ሠረገላሆሙ ወርእየ መልክአ ገጾሙ ዘበትርብዕት ወአክናፊሆሙ ዘበበስሱ ውብዙኃ አዕይንቲሆሙ ዘኢይትኌለቍ ዘከመ ርእየ ወዘከመ ነጸረ ኢይደዐ ዘንተ ኵሎ ክብረ ርእየ እንዘ ይርዕድ ወኢክህለ ለኪሮቦ ወኢተረበቦ ለአሐዱ እምኔሆሙ በከመ ይቤ ለሊሁ ኢቀረብክዎሙ ለጠይቆ ወአንቲሰ ጾርኪዮ በከርሥኪ ለዘይርዕዱ እምኔሁ እሙንቱ ግሩማን ራእይ ወክቡራን ሕይወት ወሐቀፍክዮ በአብራክኪ ለዘኢይትኌበሉ ሱራፌል ቀሪበ ዐውደ መንበሩ ወሐዘልክዮ በዘባንኪ ለመስተጸዕነ ኪሩቤል"*

(የቡዝ ልጅ ሕዝቅኤል በባቢሎን ለእስራኤል ቤት ጉበኛ (ሰላይን) ተባለ፤ በኮቦር ወንዝም የዓለሙን ጌታ አዶናይ እግዚአብሔርን በኪሩቤል

[118] Jacob of Serugh, On the Nativity p121
[119] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ምዕ ፭፤፲፤ዘኀሙስ ምዕ ፭፥፱

ሠረገላ ላይ አየው፤ የመላእክትንም ሥርዐት ተመለከተ፤ የትጉሃን መላእክትንም ምስጢር ተገነዘበ፤ ወገኖቻቸውን ዐወቀ፤ የማይቋረጥ የማይታጐል ምስጋናቸውንም ሰማ፤ የሠረገሎቻቸውንም መንኰራኵር በአራቱ አግጣጫ[120] የሚመለከተውን የፊታቸውን መልክ ስድስት ስድስት የኾነውን ክንፋቸውን፤ የማይቈጠረውንም የዐይናቸውንም ብዛት ይኸንን ኹሉ ክብር በፍጹም እንደ አየ ተናገረ፤ እየራደ እየተንቀጠቀጠ አየ፤ ከእነርሱም አንዱን ስንኳ ቀርቦ ሊዳስሰው አልቻለም፤ ርሱ "ለመረዳት አልቀረብኋቸውም" ብሎ እንደተናገረ (ሕዝ ፩፥፳-፲፮)፤ አንቺ ግን ከግርማው የተነሣ በሕይወታቸው የከበሩ፣ በግርማ የተፈሩ እነርሱ የሚንቀጠቀጡለትን በማሕፀንሽ ተሸክምሺው፤ ሱራፌል የዙፋኑን ዙሪያ መቅረብ የማይደፍሩትን በጉልበትሽ ዐቀፍሺው፤ በኪሩቤል ዐድሮ የሚኖር ርሱን በገርርባሽ አዘልሺው)[121] በማለት ተንትኖታል፡፡

## የተቈለፈች መቅደስ

አምላክን ከመውለዷ አስቀድሞ ድንግል፣ በወለደቿው ጊዜ ድንግል፣ ከወለደቿውም በኋላ ዘላለማዊት ድንግል የኾነች የእውነት ሁሓይ የክርስቶስ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ነቢዩ ሕዝቅኤል በምሥራቅ ባየት ማንም ሰው ባልገባባት የእስራኤል አምላክ ብቻ ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት በወጣበት ተዘግታ በምትኖረው ዐዲስ መቅደስ ትመሰላለች (ሕዝ ፵፬፥፩-፪)፡፡

ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የተገለጸለትን ድንቅ ምስጢር ሲገልጽ "ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር፤ እግዚአብሔርም ይኽ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፤ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" በማለት የዘላለማዊ ድንግልናዋን ነገር ተናግራል፡፡

ይኸውም መቅደስ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ በር የድንግልናዋ፤ መቈለፊያው የማኅተመ ድንግልናዋ ምሳሌ፤ አምላክ ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት ሲወጣ ማየቱ እንበለ ዘርዕ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና መወለዱን፤ "አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" ብሎ መናገሩ ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀንዋ የተሸከመቿው እናቱ

120 አግጣጫ የተባለበት ምክንያትም በማእዙ ቋንቋችን ገጽ ስለሚል ነው፡፡

121 አርጋኖን፣ ምዕ ፌ፥፳፱-፳፫





ቅድስት ድንግል ማርያምም ማኅተመ ድንግልናዋ የማይለወጥ ዘላለማዊት ድንግል መኾኗን ሲገልጽለት ነው፡፡

ለነቢዩ ሕዝቅኤል የተገለጸለትን ይኸንን አስደናቂ ምስጢር ሊቁ ቅዱስ ጎርጎሬዎስ ዘእንዚናዙ ሲተረጕም *"ከመ ኆኅት ዘርእየ ሕዝቅኤል ነቢይ ዘኢቦአ ውስቴታ ብእሲ ዘእንበለ አምላከ እስራኤል ቦአ ውስቴታ ወወጽአ እንዘ ኢይትረኀው ኆኅት ኢታስተማስሉ ኦ አብዳን ዕንሳ ለእግዝእትነ ማርያም ወወሊዶታ ከመ ኵሉን አንስት ሐሰ ላቲ ለእግዝእትነ ማርያም አላ ሀንሰቶ ለቃለ እግዚአብሔር ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወወለደቶ ዘእንበለ ሃፀር ወሕማም ወኢያእመረት ወኢተዐውቃ ፍጹመ ሕማመ ወሊድ ወበእንተዝ ዕንሳ ይትነከር ወንይለ ዕበየ ወሊዶታ ኢይትነገር ወከመዝ ወለደት ዘኢይረክቦ መኑሂ ክዋኔሁ ወኢተነሥተ ማኅተመ ድንግልናሃ"*

(ከእስራኤል ፈጣሪ በቀር ሰው እንዳልገባበት ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዳየት ደጃፍ ማኅተመ ድንግልዋ ሳይለወጥ በኅቱም ድንግልናዋ ተፀንሶ ተወለደ፤ እናንት አላዋቆች የእመቤታችን የማርያምን ፅንሷንና መውለዷን እንደ ሌሎች ሴቶች ኹሉ አታስመስሉ፤ ለእመቤታችን ለማርያም በፅንስና በወሊድ በሌሎች ሴቶች መመሰል አይገባትም፤ የእግዚአብሔር ቃልን ያለወንድ ዘር ፀነሰቺው፤ ያለ ጭንቅና ያለምጥም ወለደቺው እንጂ፤ በመውለድ ጊዜ የሚኾን ምጥ ፈጽሞ አላገኛትም፤ ስለዚኽ መፅነሷ በጣም ይደነቃል፤ የመውለዷ ምስጢር ኀይልም አይመረመርም፤ ማንም ማን ባሕርዩን የማያውቀው ርሱን ወለደችው፤ ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም)[122] በማለት የወላዲተ አምላክ ምሳሌ ስለኾነቺው ነቢዩ ሕዝቅኤል ስላየት የተዘጋች ደጃፍ በስፋትና በጥልቀት አስተምሯል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ቅድስት ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት የውዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ

*"ሕዝቅኤል ነቢይ ኮነ ስምዐ በእንቲአሃ ወይቤ ርኢኩ ኆኅተ በምሥራቅ ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም አልቦ ዘቦአ ዘእንበለ እግዚአ ኀያላን ቦአ ውስቴታ ወወፅአ"* (ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለርሷ መሰከረ ድንቅ በኾነ ታላቅ ቍልፍ የተዘጋች ደጅ በምሥራቅ አየኊ አለ፤ ከኀያላን ጌታ በቀር ወደርሷ ገብቶ የወጣ የለም) *"ኆኅትሰ ድንግል ይእቲ እንተ ወለደት ለነ መድኅነ እምድኅረ ወለደት ኪያሁ ነበረት በድንግልና ከመ ትካት"*

122 ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ጎርጎሬዎስ ዘእንዚናዙ፣ ምዕ ፳፬ ፡፲ ፡፡ ገጽ ፻፴



www.ethiopianorthodox.org

(ደጃፍም የተባለች መድኀኒታችንን የወለደች ድንግል ናት፤ ርሱን ከወለደች በኋላ እንደቀድሞው በድንግልና ኖራለች)[123] በማለት አምላክን ከመውለዷ በፊት ድንግል፤ ከወለደችውም በኋላ ድንግል መኾኗ ነቢዩ ሕዝቅኤል ባየት ራእይ አስቀድሞ የተገለጸ መኾኑን መስክሯል።

ይኸ የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ቅዱስ ኤፍሬም በድጋሚ በድርሳኑ ላይ *"Ezekiel, born in the captivity... "* (በምርኮ የተወለደው ሕዝቅኤል የዳዊት ሴት ልጅ የኾነችውን ድንግል በትንቢት ዐይን አይቶ ነበር፤ እንዲኹም ከእግዚአብሔር በተላከው የርሱ ራእይ ውስጥ የድንግልናዋን አምሳል ገለጸ፤ በከለዳውያን ምድር ትንቢት የማርያምን አምሳል አሳየ፤ ርሷንም በነቢያት መጻሕፍት አስቀመጣት፤ በቅዱሳት መጻሕፍትም የርሷን ታሪክ አስጠበቀ፤ ስለዚኽም ማንም ሰው ይኽነን በማንበብ ሊረዳ ይችላልና፤ በሩ በጥብቅ ተዘግቶ እንደሚኖር "እግዚአብሔር ገብቶታል ተዘግቶ ይኖራል" በማለት ጌታ ለነቢዩ በካህናት ጉባኤ መኻከል ገልጾለታልና)[124] ሲል ጌታ አስቀድሞ ስለ እናቱ ዘላለማዊ ድንግልና በሕዝቅኤል ዐድሮ ማናገሩን ገልጾታል።

ይኸ የሕዝቅኤል ትንቢታዊ ኀይለ ቃል የቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልናዋን የሚጠራጠሩ ·ሰነፎች መናፍቃንን የሚወቅስና የሚያሳፍር መኾኑን ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሲያብራራ

*"Today let Ezekiel... "* (ዛሬ ሕዝቅኤል በራእዩ ድንቅ የኾነው ትንቢቱ በጉላ በተረዳ ነገር በርግጥ ፍጻሜውን አግኝቷልና ይደሰት፤ በዚያ በባቢሎን የተዘጋችውን በር ተመልክቶ "እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" በማለት ተናገረ፤ ማርያም የተዘጋው በር ናት፤ ክርስቶስ የድንግልናዋን በር ፈጽሞ ሳይከፍት ወደ ዓለም ገብቶባታልና፤ ስለዚኽ ክርክሩ ጸጥ ይበል)[125] በማለት የሕዝቅኤል ትንቢት በወላዲተ አምላክ ዘላለማዊ ድንግልና ለሚያምኑ ምእመናን ኹሉ ኀይላቸው አጋዣቸው ሲኾን ፤ በአንጻሩ ደግሞ የመናፍቃንን አንደበት የሚዘጋ የትንቢት ዐዋጅ መኾኑን መስክሯል።

በዜና አበው (patrology) ክፍለ ትምህርት ላይ ሰባት መቶ ኀምሳ ሃስት መጻሕፍትን እንደ ጻፈ የሚነገርለት፤ የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የሚባለው ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ስለ እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና

[123] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ

[124] T.J.Lamy, Sancti Ephraem Syri Hymni et sermons, II ( Malines, 1996) 519-590, Bride of Light pp 39-40

[125] ibid p63



www.ethiopianorthodox.org



ባስተማረው ትምህርት ላይ፤ ርሱም እንደ ቅዱስ ኤፍሬም የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና ለሚጠራጠሩ መናፍቃን የሕዝቅኤልን ትንቢት እየጠቀሰ መልስ ሲሰጣቸው

*"Come, Ezekiel, man who grew up..."* (በመገለጦች ተከቦ ያደገው፤ ለሚሰሙትም ኹሉ እውነትን የሚያስተምር ጸሓፊ የነበረው ሕዝቅኤል የመለኮታዊ ምስጢራት መገለጦች የበዙለትና ታላቅ ሸክም የተሸከመው ነቢይ ራሱን ከሰዎች በማግለል (በስዉር) መልካሚቷን መንገድ ተከተለ፤ አንተ መናገር የተሰጣቸውን ሠረገሎች ድምፅ የሰማኽ ባለሞገስ ሆይ (ሕዝ ፫፥፲፫) እንዲኹም የክንፎቻቸውን ድምፅ እና የዚያን ሠረገላ ታላቅ እንቅስቃሴ የሰማኽ (ሕዝ ፲፥፭)፤አንተ የኪሩቤልን መልክ መለወጥ ያየኽ የበራልኽ ነፍስ ሆይ፤ እንዲኹም እኒያ የእሳት ላንቃዎች በከፍታ ላይ የተቀመጠውን ሲያመሰግኑ የሰማኽ (ሕዝ ፩፥፬-፳፰)፤ ሕዝቅኤል ሆይ ና፤ አንተ የቡዝ ልጅ ሆይ ና (ሕዝ ፩፥፳፫)፤ የተጠቀለለውን የትንቢትኽን ቃል ብራና አምጣልን፤ አንተ ቁምና እውነትን ተናገር ሌሎቻችን ኹሉ ዝም እንበል፤ ካየኻቸው ራእዮች መኻከል ድንግል ማርያም ታይታኽ እንደኾነ፤ ፍጥረት ኹሉ ውበቷን ያይ ዘንድ መልኳን ግለጥልኝ፤ በትንቢትኽ ውስጥ የጌታኽን እናት የሚመለከት አንዳች ነገር ካለ፤ ይኸ ለሚሰሙት እጅግ ውድ ስለኾነ ተነሣና አብራራልን፤ ይኸም ያም (መናፍቅ) ከመውለዷ በኋላ ድንግል አልነበረችም በማለት ይናገራልና፤ እውነት ድንግልናዋን ዐጥታ እንደኾነ እስኪ አንተ አስረዳን፤ ሕዝቅኤል ዛሬ ያንተ ተራ ነውና እስኪ ተናገር፤ ስለ እመቤታችን ማርያም ተናገርና ከንቱ ምርምሮችን ግታልን፤ እስከ አኹን በትንቢት ተነግሮ የነበረው ምን እንደነበር እንስማ፤ የማትመረመር ስለኾነቺው ስለ ድንቅ እናታችን ይኸ ነቢይ በትንቢቱ ውስጥ እንዲኽ ተናግሮ ነበር "ጌታም የቅድስተ ቅድሳንን በር አሳየኝ፤ እነሆ የተዘጋ መኾኑን አየኹ፤ ጌታም እንደተናገረው ይኸ በር ዝግ ኾኖ ይቆያል፤ አይከፈትምም ማንም በርሱ አይገባም በርሱም አይወጣም፤ በርሱ የሚገባው ጌታ ራሱ ስለኾነ ዝግ ኾኖ ይቆያል"፤ አንተ የመንፈስ ነቢይ ሆይ ይኸ ቃል ምን ማለት እንደኾነ እስኪ ገልጠኽ አብራራልን፤ በትንቢት የተነገረው የተዘጋው በር ድንግል ማርያም ናት፤ ምክንያቱም መሲሑ ጌታ በርሱ በኩል ወደ ዓለም መጥቶ ዝግ አድርጎ ትቶታልና፤ ጌታ በዚኽ በር ሲገባ እንዳልከፈተው ዕብራዊ የኾነው ሕዝቅኤል ከእኛ ጋር ዐብሮ ይኽነኑ ይመሰክራል፤ እግዚአብሔር እንደወደደው በመወለድ በር ወደ

ዓለም ገባ፤ ያንንም በር በድንግልና ዘጋው፤ ነቢዩ በሩ ተዘግቶ ያየው ያ ቤተ መቅደስ ስለ ድንግልናና ስለማይለወጥ ድንግልናዋ የሚያሳየን ነው፤ ቅዱሱ መሲሑ ሲኾን ቤተ መቅደሱ ማርያም ናት፤ የተዘጋውም በር በርሷ የሚኖረው የማይጠፋው የድንግልናዋ ማኅተም ነው)[126] በማለት የድንግልናዋን ማኅተም ሳይከፍት በኅቱም ድንግልና የመወለዱን ድንቅ ምስጢር አስቀድሞ ለሕዝቅኤል በተዘጋች በር አማካይነት እንደገለጸለት አስተምሯል፡፡

ይኽ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ስለ እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና ያስተማረው የሃይማኖት እውነታ መኾኑን የሕዝቅኤልን ትንቢት ምስክር በማድረግ ሲተነትን "And in truth, if it were not so as I say... " (እውነት ለመናገር እኔ እንደምለው ልክ እንዲኹ ባይኾን ኖሮ፤ ነቢዩ ለምን ይኽነን በር አየ? በሩስ ለምን የተዘጋ ኾነ? ርሱ ይኽነን በር ያየው የሰው ልጅ የገባበት በር ስለኾነ ነው፤ ዝግ ኾኖ ያየውም በርሱ በወጣ ጊዜ የድንግልና ማኅተሙን ያላጠፋው በመኾኑ ነው፤ የእግዚአብሔር ልጅም የገባው ኹሉም በሚወለድበት በር ነው፤ ነገር ግን በመወለድ ወደ ዓለም በገባም ጊዜ ይኽነን በር አልከፈተውም ፤ ርሱም ድንግል እናቱን በተዘጋው በር አስቀድሞ ስለገለጻት እናም ለሕዝቅኤል (በሩ) ዝግ መኾኑን በግልጽ አሳይቶታል፤ ታሪኩም እውነት ነው፤ ልክ እንደዚያ ማንም እንዳልከፈተው በር የማርያም የድንግልናዋ ማኅተምም እንዲኹ ጸንቶ ይቆያል፤ የድንግል ማሕፀን በተዘጋ በር ለእኛ ተብራርቶልናል፤ በሩ ዝግ እንደኾነ ኹሉ የድንግልም ማሕፀን የታተመ ነው፤ ጌታ "ይኽ በር ፈጽሞ አይከፈትም" ብሏልና፤ ይኽም "ይኽነን የድንግልና ማኅተም ማንም አይለውጠውም" ማለት ነው፤ ቡርክት የኾነቺውን የርሷን ማሕፀን ያተመው የጌታ ቃል ነው፤ ርሱም ራሱ እንኳ በመወለድ በርሱ ሲወጣ የድንግልናዋን ማኅተም አለወጠውምና፤ በድንግልና በር የገባው ርሱ እግዚአብሔር ነው፤ ርሱ እግዚአብሔር ስለኾነም ነው የገባበትን በር ማኅተም እንደተዘጋ የተወው)[127] በማለት የሕዝቅኤልን ትንቢት በስፋት ተርጕሞታል፡፡

ይኽነን እግዚአብሔር ስለ እናቱ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የገለጸውን ምስጢር የማይቀበሉ ኹሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የወጡ ስለመኾናቸው ቅዱስ ያዕቆብ

[126] Jacob of Serugh, Homily on the perpetual virginity of Mary pp Vii-X

[127] ibid p.X



www.ethiopianorthodox.org



ሲገልጽ "Just as the door that the prophet saw..." (ልክ እንደዚያ ነቢዩ እንዳየው በር እንደሰማነውም ድምፅ፤ "አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" (ሕዝ ፵፬፥፪)፤ ስለዚኽ የማይሻረው እውነት ይኽ ነው፤ ርሱ አምላክ መኾኑን አምኖ የሚቀበል ማንም ቢኖር፤ ርሱን የወለደች እመቤታችን ማርያምም ድንግል እንደኾነች ደግሞ አምኖ ተቀብሏል፤ ከርሷ የተወለደው ርሱ የባሕርይ አምላክ መኾኑን የሚጠራጠርም፤ በወለደቺው ጊዜ ድንግልናዋን እንደለወጠ ያስባል (ያምናል) ማለት ነው፤ ክርክር የሌለበት ነገራችን በዚኹ መቋጫውን ያገኝ፤ ስለ ወልድ ካወቅን በርሱ ስለ እናቱ ማወቅ ይቀለናል፤ በተገለጠው ማንነቱ እግዚአብሔርን ካወቅነው፤ ያም ማሕፀን በድንግልና ጸንቶ እንደሚኖር ለመረዳት ደግሞ ቀላል ይኾንልኻል፤ ነገር ግን ስዉር ኾኖ ቀርቶ የኾነው ጥርጣሬ (አለማመን) ነፍስኽን ወርሷት ከኾነ፤ ያ ማሕፀን ድንግል ኾኖ የሚኖር መኾኑን ለማመን ያዳግትኻል፤ ለነቢዩ በመገለጥ የታየው ያ በር፤ እግዚአብሔር እንደገባበት ግን ዝግ እንደነበርም ደግሞ ልብ በል፤ የባሕርይ አምላክ በርሱ ዐልፎ ሲገባ፤ ልክ እንደ ደካማው (ፍጡር) ለመግባት የግድ መክፈት እንደማይኖርበት ግልጽ ኾኗልና፤ በዚኽ በር ሊገባ የነበረው የባሕርይ አምላክ ሳይኾን ሌላ (ፍጡር) ቢኾን ኖሮ፤ ሳይከፍት መግባት ለርሱ (ለፍጡር) የማይቻል ስለኾነ ለመግባት የግድ መክፈት ይኖርበት ነበር፤ በሩ ግን ለጌታ መግቢያ ኾኖ ስለኾነ የኖረው፤ ርሱ ራሱ ዘግቶ ዐተመውና መቼም እንደማይከፍተው ደግሞ አረጋገጠ፤ እመቤታችን ማርያምም በማይለወጥ ድንግልና ስለኾነች፤ በመውለድ ጊዜም አልጠፋባትም (አላጣችውም) ምክንያቱም የወለደቺው የባሕርይ አምላክን በድንቅ ነውና፤ እመቤታችን ማርያም የወለደቺው የባሕርይ አምላክ ያልኾነ ዕሩቅ ብእሲ ቢኾን ኖሮ፤ የድንግልናዋ ማኅተም ይጠፋ ነበር፤ ምክንያቱም ዕሩቅ ብእሲ (ፍጡር) ያን የድንግልና ማኅተም መጠበቅ (አለመለወጥ) አይቻለውምና፤ እነዚኽ ኹለቱ የተቈራኙ (የተያያዙ) ነገሮች ናቸው፤ አንዱን የማያምን (የሚጠራጠር) ሌላኛውን ማመን አይቻለውም፤ እመቤታችን ማርያም የወለደቺው እግዚአብሔርን መኾኑን ካልተቀበለ፤ ድንግልናዋ ያልተለወጠ መኾኑንስ እንዴት ይቀበላል? ከርሷ የተወለደው ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጅ የኾነው ጌታ መኾኑን ካመነ፤ የድንግልናዋ ማኅተምም ያልተለወጠ ስለመኾኑ አይጠራጠርም፡፡)[128] በማለት የቅድስት ድንግል ማርያም ጣዕመ

[128] ibid pp x-xi

ውዳሴዋ በእጅጉ የበዛለት ይኸ ቅዱስ አባት እንዳስተማረ፣ ጥንቱን ነቢዩ ሕዝቅኤልም በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ዘላለማዊ ድንግልናዋን እንደመሰከረ ኹሉ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችንም በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት፤ በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናትነት አምና ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ የእመቤታችንን ዘላለማዊ ድንግልናዋን እየመሰከረች፤ ከእውነቱ የራቁ ተጠራጣሪዎች ደግሞ ወደ እውነቱ ቃል እንዲመጡ ስትመሰክር ትኖራለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ሊቃውንት ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ አምላክ እናት ዘላለማዊ ድንግልናዋ ተገልጦለት የተናገረውን ትንቢት በጥልቅ የነገረ ማርያም ዕውቀታቸው ሲተነትኑ

*"ወበእንቲአሃ ኮነ ስምዐ ሕዝቅኤል ነቢይ ወይቤ ርኢኩ ኆኅተ በምሥራቅ ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም ወይቤለኒ እግዚአብሔር ዝንቱ ኆኅት ዕፁወ ይኩን ወኢይትረኀው ወኢይባእ ቦቱ ብእሲ እስመ ዝንቱ ኆኅት ዕፁወ ይኩን ወኢይትረኀው ወኢይባእ ቦቱ ብእሲ እስመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ቦአ ቦቱ ወይኩን ዕፁወ፤ ኆኅትሰ ዘይቤ ድንግል ይእቲ እንተ ወለደት ለነ መድኅነ ወዝንቱኒ ኮነ እምቅድመ ትለዶ ወእምድኅረ ወለደት ኪያሁ ነበረት በድንግልና ከመ ትካት፤ እስመ እግዝእትነሰ ኮነት ማኅደረ ለመንፈስ ቅዱስ ወበእንተዝ አልባቲ ፀኒስ ዕንስ ከመ ካልኣት አንስት ወኢይትከሃል ትትገሰስ በእደ ብእሲ ምድራዊ፤ ወይእቲኒ ኮነት ስምዐ ላዕለ ርእሳ ሶበ ይቤላ መልአክ ትፀንሲ በብሂል እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ፤ ወበእንተዝ ኮነት ምሳሌሁ ለአብ እስመ ኢኮነት እንከ ወላዲተ ሰብእ ዘእንበለ እሙ ለሥግው ቃል በእንተ ዘአልባቲ ካልኣት ጠባይዓት በከመ ኢኮነ ለአብ፤ ቦኑ ይትከሀሎ ነቢር ለመኮንን በመንበረ ንጉሥ ወለቀሲስኒ በመንበረ ሊቀ ጳጳስ ወከማሁ አኮ ዘይትከሃል በዘነደረ ቦቱ እሳተ መለኮት ይኅድር ብኢሲ ወበዘተሠዕለ ቦቱ ዘይትከሃል ሠዓሌ ሕፃናት አኮ ዘይትለካእ ወይትቀረጽ ዘርዐ ብእሲ በከዊነ ቀለም፤ አኮኑ ሕዑር ዐውደ ማሕፀና በትንቢት ወቅጹር በቅጽረ ብዕዓት ወኀለፈ ቃል በእንተ ድንጋሌሃ ለድንግል ከመ ይኩን ዕጽወ ለዓለም ወኢይትረኀው ወኢይባእ ቦቱ ብእሲ፤ ወበእንተዝ ተኀርየ ዮሴፍ አረጋዊ በከዊነ ሐዲስ ካህን በአምሳለ አሮን ቀዳማዊ ከመ ይትከሀን ወይትለአክ ለእሙ መቅደሰ ማእምንት ወለቅድስተ ቅዱሳን ትስብእቱ ለዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር"*

(ስለ ርሷ ነገር ነቢዩ ሕዝቅኤል በምሥራቅ በኩል በድንቅ ቍልፍ የተቈለፈች አዳራሽ አየኍ ብሎ ተናገረ፤ ጌታ www.ethiopianorthodox.org





የአዳራሽ ደጅ አፍ ተዘግቶ ይኑር እንጂ አይከፈት ሰውም አይግባበት የእስራኤል አምላክ ርሱ እግዚአብሐር እንደተዘጋ ገብቶበታልና ብሎ ተናገረ፤ ደጃፍ የተባለች መድኀኒታችንን የወለደችልን ድንግል ማርያም ናት፤ ርሱን ከመውለዷ በፊት፣ በወለደችው ጊዜ፣ ከወለደችውም በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠምና፤ እመቤታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደመኾኗ መጠን እንደ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ መፅነስ በእደ ብእሲ መዳሰስ የለባትም፤ ስለዚኽም ርሷ ስለ ራሷ መልአክ ትፀንሻለሽ ባላት ጊዜ እኔ ወንድ የማላውቅ ድንግል ስኾን እንዴት ለመውለድ ይቻለኛል ስትል መስክራለችና፤ ኹለተኛም የአብ ምሳሌ ስለኾነች ከሥግው ቃል በቀር ለዕሩቅ ብእሲ እናት መኾን በባሕርይዋ ኹለተኛ መውለድ አትችልም ለአብ እንዳይቻለው፤ በውኑ በሊቀ ጳጳስ መንበር ቀሲስ በንጉሠ ነገሥት ዙፋን መኰንን ደፍሮ ሊቀመጥ ይገባዋልን እንደዚኹም እሳተ መለኮት ባደረበት ማሕፀን ዕሩቅ ብእሲ ሊያድር አይችልም፤ ሠዓሊ ሕፃናት የተባለ ርሱ ጌታ በተሣለበት ስሌዳ በተቀረጸበት ሰሌዳ ሊቀረጽ አይቃጣም አይታሰብም፤ የእመቤታችንስ ዐውደ ማሕፀኗ አስቀድሞ በትንቢት ታጥሯል በብዕዐት ተቀጥሯል ለዘለዓለሙ ተዘግቶ ይኑር አይከፈት ሰው አይግባባት የሚል አምላካዊ አዋጅ ተነግሮበታል፤ ስለዚኽም አማናዊት መቅደስ እናቱን የዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ቅድስተ ቅዱሳን ትስብእቱን ዐዲስ ካህን ኾኖ ለማገልገል አረጋዊ ዮሴፍ እንደቀዳማዊ ካህን አሮን ተመረጠ)[129] በማለት ቅድመ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ፀኒስ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ፀኒስ ድኅረ ወሊድ የአምላክ ማደሪያ የኾነው ማሕፀኗ በተፈትሖ ፈጽሞ የማይመረመር ለዘላለሙ ተዘግቶ እንዲኖር የአምላክ ዐዋጅ የታወጀበት በንጽሕና በቅድስና የተጌጠ መኾኑን አስተምረዋል።

ይኽ ነቢዩ ሕዝቅኤል በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት የተናገረውን የቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልናዋን የሚቃወሙ፤ ዲያብሎስ ልቡናቸውን ዙፋን ሰውነታቸውን ድንኳን፤ አእምሮአቸውን ሜዳ ልቡናቸውን ስሌዳ፤ አድርጎ ከሚጫወትባቸው እውነተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን ከሚያጣምሙ ከሐሰት ልጆች ከመናፍቃን የስሕተት ትምህርት ፈጽመን እንድንጠበቅና በተቀደሰችው እምነት ራሳችንን እንድናጸና ዳግመኛ ሲመክሩን፦

*"ወይእዜኒ አኃውየ ፍቁራን ይደልወነ ንጽናዕ በአሚኖትነ ወበትምህርትነ ዘነቅዐ እምኀዕሉ ዘውእቱ ትንቢተ ነቢያት ወተሰብከ በቃለ*

129 ተአምረ ማርያም፤ ገጽ ፻፴፬-፻፴፭

ሐዋርያት ወበጽሐ ኀቤነ እንዘ ይትነገር በበመትልው እምቅዱሳን አበው ቀደምት፤ ወባሕቱ ሐዊር በዘኢሖረ ሐዋርያ ወገዱሮሙ በዘኢኮነ ድልወ እንዘ ይገፍዑ ትንቢተ ወያንኀሉ ምሳሌያተ ወሰቢረ ኖኀት በተዐድዎ ሕገ ኃት ለአቅሞ ጣዖት ውስተ ቤተ መቅደስ ነባቢት ወአንብሮ ጣዖት ምስለ ታቦተ አምላከ እስራኤል ውእቱ ግብሮሙ ለአረማውያን ውፁኣን ወርኁቃን እምሕገ ኦሪት ብሊት ወእምሕገ ወንጌል ሐዲስ ንሕትት ከመ ዘየአክዩ እምነ ተንባላት በእንተ ክሕደቶሙ፤ ወይእዜኒ ንርሐቅ ወንትየይ እምዝንቱ ግብረ ኑፋቄ ዘአረማውያን ወንትሉ አሠረ ፍኖቶሙ ለነቢያት ወለሐዋርያት አበዊነ ቀደምት በኵሉ ግብር ወንእመን ከመ ድንግልት ይእቲ በክልኤ ፍና እምቅድመ ትፅንሶ ወእምቅድመ ትለዶ ለመድኅኒነ ወእምድኅረ ወለደት ኪያሁ ነበረት በድንግልና በከመ ርእየ ሕዝቅኤል በራእዩ ወኢሳይያስኒ በከመ ተነበየ በትንቢቱ ለዓለመ ዓለም ወበእንተዝ ነአኵቶ ወንሴብሖ ለዐማኑኤል አምላክነ ዘዐቀበ ማኅተመ ድንግልናሃ እንበለ ሙስና ለዓለመ ዓለም"

(አኹንም የተወደዳችኹ ወንድሞቼ ሆይ ከላይ ከነቢያት ትንቢት የፈለቀው በሐዋርያት ቃል የጸደቀው ከጥንት ከቅዱሳን አባቶቻችን ሲያያዝ ሲነገር የመጣውን ሃይማኖታችንና ትምህርታችንን አጥብቀን አጽንተን መያዝ ይገባናል፤ ነገር ግን ወንጌላዊ ሐዋርያ ባልኾኑበት ገለሥግሦ ኺዶ ትንቢት ጥሶ አማናዊ ምሳሌ አፍርሶ ደፍሮ መዝጊያ ሰብሮ በነባቢት መቅደስ ጣዖት ማቆም፤ ታቦተ አምላከ እስራኤልን ከጣዖት ጋራ ማኖር፤ ከብሉይ ከሐዲስ ኪዳን የራቁ በሐዲስ ኪዳን የሚሳለቁ፤ ከተንባላት የሚከፉ የአረማውያን ልዩ ሥራ እንደኾነ እንወቅ እንረዳ፤ አኹንም ከአረማውያን የኑፋቄ ሥራ ፈጽመን እንራቅ፤ በቀደሙ አባቶቻችን ነቢያት ትንቢታዊ እምነትና በሐዋርያት ወንጌላዊ ትምህርት እመቤታችን ማርያም ከመፀነሷ በፊትና ከፀነሰች በኋላ ከመውለዷ በፊትና ከወለደችውም በኋላ ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዳየው ራእይ ኢሳይያስ እንደተናገረው ትንቢት ለዘላለም በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች እንደኾነች እናምናለን፤ ስለዚኽ ማኅተመ ድንግልናዋ እንዳይለወጥ አድርጎ የጠበቃት አምላካችን ዐማኑኤልን ለዘላለሙ እናመሰግነዋለን::)[130] በማለት እንዳስተማሩን ቅድስት ቤተ ክርስትያናችን እግዚአብሔር ወልድን በኅቱም ድንግልና የወለደችልንን የቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልናዋን ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ ስትመሰክር ትኖራለች፡

[130] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ ፪፻፴፱



www.ethiopianorthodox.org



# ነገረ ማርያም በትንቢተ ዳንኤል
## ክፍል አራት

ዳንኤል ማለት ፍትሐ እግዚአብሔር ማለት ሲኾን ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ የኾነ ፮፻፫-፭፻፴፯ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረ ታላቅ ነቢይ ሲኾን በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ በርካታ የሥጋዌ ምስጢርንና የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና፣ እንበለ ዘርዕ ስለኾነው ፅንሷና ስለ አምላክ እናትነቷ ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው፤ እኛም ይኽንን ትንቢታዊ ኀይለ ቃሉን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከዚኽ በታች አስቀምጨዋለኹ::

### የዳንኤል ተራራ

በነቢዩ በዳንኤል ዘመን የነበረው ንጉሡ ናቡከደነጾር በንግሥናው ኹለተኛ ዓመት ላይ ከርሱ ቀጥሎ የሚነግሠው ማን እንደኾነ ለማወቅ ሲመኝ በራእይ ራሱ የወርቅ፣ ደረቱና ክንዶቹ የብር፣ ኾዱና ወገቡ የናስ፣ ጭኖቹ የብረት፣ እግርና እግሩ የብረትና የሸክላ ቅልቅል ምስል ቆሞ ርሱን ሲመለከት፣ እጅ ሳይነካው ከረኸርም ተራራ ድንጊያ ወርዶ ያንን ምስል ሲመለከት፣ በመከርም ጊዜ በዐውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሲያደርገውና ሲፈጨው፤ በመክርም ጊዜ በዐውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሲያደርገውና ነፋስ መጥቶ ሲወስደው፣ ምስሉን የመታው ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሲኾን ምድርንም ሲመላት አይቷል (ዳን ፪፥፴፩-፴፭)::

ኹሉም ግን የተመለከተው ድንቅ ራእይ ተሰውሮበት በቤተ መንግሥቱም የነበሩ የሕልም ተርጓሚዎች ሕልሙም ትርጓሜውም ጠፍቶባቸው ሲቀጡ ሲሉ፤ ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል የንጉሡ ሕልም ከትርጓሜው ጋር ተገልጾለት ለንጉሡ ተርጒሞለታል (ዳን ፪፥፴፮-፵፬)::

በዚኽ ትርጓሜውም ድንጋዩ ከረኸርም ተራራ እጅ ሳይነካው ወርዶ ወርቁን፣ ብሩን፣ ናሱን፣ ብረቱንና ሸክላውን ፈጭቶት፤ ታላቅ ተራራ ኾኖ ምድርን ሲመላት ማየቱ በኋላ ዘመን ማለት (በዘመነ ሥጋዌ) ሲገለጽ ያለ የድኅነት ምስጢር መኾኑን ለንጉሡ አስታውቆታል (ዳን ፪፥፴፮-፵፬)::

ይኽም ድንቅ ራእይ ልዩ የኾነውን የሥጋዌ ምስጢርን ይዟል፤ ይኸውም ተራራ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ድንጋዩ የወልደ

እግዚአብሔር፣ ድንጋዩ የሰው እጅ ሳይነካው መውረዱ አካላዊ ቃል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ያለ ዘር ተፀንሶ የመወለዱን ምስጢር ሲያሳይ፤ ምስሉን ቀጥቅጦት በዓለም መምላቱ ይኸቺን ዓለም ተካፍለው ገዝተዋት የሚኖሩ ነገሥታትን አሳልፎ የሚኖረው የአብ አካላዊ ቃል ርሱ የመኾኑ፤ ተራራ አክሎ መታየቱ ፫ት ዓመት ከ፫ ወር የመንግሥቱን ወንጌል ማስተማሩ፤ በዓለም መምላቱ ዜና ልደቱ፣ ዜና ጥምቀቱ፣ ዜና ትምህርቱ፣ ዜና ስቅለቱ፣ ዜና ሞቱ፣ ዜና ትንሣኤው፣ ዜና ዕርገቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ በምድር ኹሉ የመሰማቱ አምሳል ነበር።

ይኸንንም ምስጢር ነቢዩ ዳንኤል በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በምዕ ፯፥፲፫-፲፬ ላይ በድጋሚ አብራርቶ ሲገልጸው

*"በሌሊት ራእይ አየኹ፤ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደፊቱም አቀረቡት፤ ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ኹሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው"* በማለት ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጅ ዘመኑ ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ፍጹም ሰው መኾኑና ለመንግሥቱ ፍጻሜ የሌለው አልፋና ዖሜጋ መኾኑን ተናግሯል።

ልክ እንደ ነቢዩ ዳንኤል፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለመንግሥቱ ፍጻሜ የሌለውን የአብ የባሕርይ ልጁን ያለ ዘር ፀንሳ እንደ ምትወልድ ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣው ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ሲያበሥራት *"እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም"* በማለት እንደገለጸው ቅድመ ዓለም የነበረ፣ አኹንም ያለ፣ ዓለምን አሳልፎ የሚኖረውን የአብ የባሕርይ ልጁን እንበለ ዘርዕ ፀንሳ የወለደች ርሷ በእውነት የአምላክ እናት ናት (ሉቃ ፩፥፴፩-፴፫፤ ራዕ ፳፥፲፩-፲፬)።

በርካቶች ሊቃውንትም በየድርሳናቸው ይኸንን የነቢዩ የዳንኤልን ራእይ ሲተነትኑ፤ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በማግሰኞ ውዳሴ ማርያም ላይ

*"ዘውእቱ እብን ዘርእየ ዳንኤል ነቢይ ዘተበትከ እምደብር ነዋኅ ዘእንበለ እደ ዘውእቱ ቃል ዘወፅአ እምኀበ አብ መጽአ ወተሰብአ እምድንግል ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወአድኀነነ"*





(ነቢዩ ዳንኤል ያየው ያለ እጅ ከረዥም ተራራ የተፈነቀለው ያ ድንጊያ ከአብ ዘንድ የወጣው አካላዊ ቃል ነውና፤ ያለ ወንድ ዘር ከድንግል ተወልዶ አዳነን)[131] በማለት አማናዊ ትርጓሜውን አስተምሯል።

ኢዮጵያዊዉ ዘርዐ ያዕቆብ በነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ ይኸነን የዳንኤልን ራእይ ሲተረጉም

*"ወልድኒ ተወልደ እምኔሃ ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ በከመ ተብህለ በዳንኤል ነቢይ እምደብር ወረደ እብን ዘእንበለ እደ ወሐረጸ ለምስል ወኮነ ውእቱ ምስል ከመ ጸበለ ዐውዱ፤ ወዝኩሰ እብን ዘቀጥቀጦ ኮነ ደብረ ዐቢየ ወመልአ ኵሎ ምድረ።*

*ደብርሰ ይእቲኬ ማርያም ዘተወልደ እምኔሃ ዕብነ ሕይወት ዘእንበለ ይግስሳ እደ ብእሲ በሐውዘ ፍትወተ ሥጋ፤ ወለወልድኒ እምድኅረ ተወልደ እምኔሃ ጺጋሁ ወኀይሉ ወፍቅሩ ኢተፈልጠ እምኔሃ ግርማሁ ወሞገሱ ኢሰሰለ እምኔሃ፤ ወበእንተዝ ንብል ማርያም ድንግል ይእቲ በክልኤ ፍና በድንግልና ኅሊና ወበድንግልና ሥጋ እስመ ሥምረተ ሥሉስ ቅዱስ ኀደረ ላዕሌሃ"*

(ወልድም ያለ ዘርዐ ብእሲ ከርሷ ተወለደ፤ እጅ ሳይፈነቅለው ከረዥም ተራራ ድንጊያ ተፈንቅሎ ወረደ፤ ምስሉንም ፈጨው፤ ያም ከረዥም ተራራ ድንጊያ ተፈንቅሎ ወረደ፤ ምስሉንም ፈጨው፤ ያም ምስል እንደ ዐውድማ እብቅ ኾነ፤ ያም የፈጨው ድንጊያ ታላቅ ተራራን አክሎ ምድርን ኹሉ መላ፤ ተብሎ በነቢዩ ዳንኤል እንደተነገረ።

ተራራም የተባለች በሥጋ ምኞት ጉምዥዥታ የወንድ እጅ ሳይዳስሳት፤ የሕይወት ድንጊያ ጌታ ከርሷ የተወለደ ማርያም ናት (መዝ ፻፲፯፥፳፪-፳፫፤ ማቴ ፳፩፥፵፪፤ ኤፌ ፪፥፳-፳፩፤ ፩ጴጥ ፪፥፬-፰)፤ ከርሷም ከተወለደ በኋላ የወልድ ጸጋው፣ ኀይሉ፣ ፍቅሩ ከርሷ አልተለየም፤ ግርማው ሞገሱም ከርሷ አልራቀም፤ ስለዚኽም በኹለት ወገን በድንጋሌ ኅሊና በድንጋሌ ሥጋ ማርያም ድንግል ናት እንላለን፤ የሥላሴ ፈቃድ በርሷ ላይ ዐድሯልና)[132] በማለት ስለ ሕይወት ድንጊያ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ያለ ዘር መፀነስ የተነገረውን ትንቢታዊ ኀይለ ቃል በአስደናቂ መልኩ ተርጉሞታል።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም የነቢያትን ትንቢቶች በተረጐሙበት መጽሐፈ ፀሐይ በሚለው መተርጕመ መጻሕፍት ላይ ይኸነን የዳንኤልን ትንቢት ሲተረጕሙ

[131]ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ በውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ

[132][illegible] ርያም፤ ገጽ 42-44



www.ethiopianorthodox.org

*"ደብርስ ዘይቤ ማርያም ይእቲ፤ ወእብንኒ ክርስቶስ ውእቱ፤ ተብትክሰ ዘይቤ ተወልደ ብሂል፤ ዘእንበለ እደዊ ሶበ ይብል ዘእንበለ ትድምርተ ብእሲ ብሂል፤ ወቀጥቀጦ ለልሕኩት ወለሐፂን ዝኒ ሶበ ይብለከ እስመ በመንግሥተ ሮም ተወልደ መዋዔ ነገሥት"*

(ተራራም ያላት ማርያም ናት ደንጊያውም ክርስቶስ ነው፤ ተፈነቀለ ያለውም ተወለደ ማለት ነው፤ ያለ እጅ ባለ ጊዜም ያለ ወንድ ዘር ማለት ነው፤ ሸክላውን ብረቱን አደቀቀው ይኸን በሚልኽ ጊዜ ነገሥታትን ድል የሚነሣ ጌታ በሮም ዘመነ መንግሥት ተወልዷልና)[133] በማለት ምስጢርን እንደ ወርቅ አንክብለው እንደ ሸማ ጠቅልለው አስተምረዋል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ነቢዩ ዳንኤል ክብሩን የተናገረለት ቅድመ ዓለም የነበረ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ የሚኾን እግዚአብሔር ወልድን በማሕፀኗ የተሸከመች አማናዊት ዙፋን ቅድስት ድንግል ብቻ ናትና፤ ይኽንንም ምስጢር በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*"ኦ እግዝእትየ ማርያም ወላዲተ ልዑል*
*አንቲ ተዐብዪ እምኪሩቤል*
*ወትፈደፍዲ እምሱራፌል*
*አንቲ ውእቱ መንበረ ስብሐት ጽዱል*
*ወሠረገላ እሳት ዘያንበለብል*
*እንዘ ይነብር ዲቤሁ ብሉየ መዋዕል*
*ዘነጸረኪ በሕልሙ መልአከ አጽዮድዮን ዳንኤል"*

(እመቤቱ ማርያም ሆይ አንቺ ከኪሩቤል ትበልጫለሽ፤ ከሱራፌልም ትልቂያለሽ፤ ብሉየ መዋዕል ጌታ በላዩ ሲቀመጥ የመተርጕማን ሕልም አለቃ ዳንኤል በሕልሙ ያየሽ፤ የሚያንበለብል የእሳት ሠረገላ ብሩህ የጌትነት ዙፋን አንቺ ነሽ)[134] በማለት ምስጢሩን ተርጕሞታል።

## የሠለስቱ ደቂቅ የምስጋና ጣዕም

ነቢዩ ዳንኤል ለንጉሡ ለናቡከደነጾር ሕልሙን ከተረጐመለት በኋላ ዳንኤልንና ሠለስቱ ደቂቅን በባቢሎን አውራጃ ላይ ከፍተኛ ሹመትን በየደረጃቸው ሾሟቸዋል (ዳን ፪፥፵፰-፵፱)።

[133] መጽሐፈ ሁዳይ፤ ገጽ ፳፫

[134] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 8



www.ethiopianorthodox.org



ኾኖም ግን ናቡከደነጾር ቁመቱ ስሳ ክንድ ወርዱ ስድስት ክንድ የኾነውን የወርቁን ምስል አሠርቶ በባቢሎን አውራጃ በዱራ ሜዳ ላይ በማቆም ኹሉም ላቆመው ምስል ምረቃ ተሰብስበው ሳለ፤ ዐዋጅ ነጋሪው የዘፈን ድምፅ ሕዝቡ ሲሰሙ ንጉሡ ላቆመው ምስል ተደፍተው እንዲሰግዱ ትእዛዝን የማይቀበሉ ግን በሚነድደው እሳት እቶን እንደሚጣሉ ሲናገር ሕዝቡም አሕዛቡም ለምስሉ ይሰግዱ ይረበረቡ ገርመር (ዳን ፫፥፩-፯)።

ሦስቱ ሕፃናት ግን አንሰግድም በማለታቸው "እሉ እደው ዘሤምኮሙ ለግብረ በሐውርተ ባቢሎን አበዩ ሰጊደ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርከ" በባቢሎን አውራጃ ሥራ ላይ የሾምኻቸው እነዚኽ ሰዎች ወንዶች ላቆምኸው ምስል አይሰግዱም በማለት ነገሩት፤ ናቡከደነጾርም በብስጭትና በቍጣ እንዲመጡ በማዘዙ፤ መጥተው ከፊቱ ሲቆሙ "ላቆምኹት ለወርቁ ምስል አለመስገዳችኍ እውነት ነውን? ባትሰግዱ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችኍ፤ ከእጄስ የሚያድናችኍ አምላክ ማን ነው?" በማለት ሲናገራቸው የሚያመልኩት አምላክ ከሚነድደው እሳት ሊያድናቸው እንደሚችል ገለጹለት፤ ርሱም በቍጣ የእቶኑ እሳት ከሚነደው ይልቅ ሰባት እጥፍ ማለት ፵፱ ክንድ አድርገው እንዲያነዱ በማዘዝ አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል፣ ታሥረው እንዲጣሉ በሰራዊቱ ውስጥ ላሉት ኀያላን መመሪያ ስላስተላለፈ፤ ወርዋሪዎቹም ከሰናፊላቸውና ከቀሚሳቸው ከመጐናጸፊያቸው ጋር በእሳቱ ላይ ሲጥሏቸው ከወላፈኑ ክፍተኛነት የተነሣ ወታደሮቹ ተቃጥለዋል (ዳን ፫፥፲፫-፳፫)።

*ያን ጊዜ ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጦ ለነበልባለ እሳት* ወረሰዮ ከመ ነፋስ ቆሪር ዘጊዜ ጽባሕ ይላል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወርዶ በበትረ ብርሃን ቢመታው እንዳረረ ውርጭ ኾኗል፤ ያን ጊዜ ወአንሰሰወ ማእከለ እሳት ወእኩት እግዚአብሔርሀ ወባረክዎ ይላል በእሳቱ ጕድጓድ መኻከልም በመመላለስ እግዚአብሔርንም ፈጽመው አመስግነውታል (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቍ ፩)።

ይኸም ከእሳቱ መኻከል ሳሉ የተገለጸላቸው አስደናቂ ምስጋና ልዩ የኾነ የነገረ ሥጋዌ ምስጢርን የያዘ እንደኾነ የነገረ ነቢያት ሊቃውንት አስተምረዋል፤ ይኸውም በእሳቱ መኻከል ኹነው ለስድስት ጊዜ ብቻ

*"ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም"*

(የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን፤ የተመሰገነ ነው፤ ለዘለዓለሙም የከበረ ነው) በማለት ካመሰገኑ በኋላ (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቍ ፳፯-፴፪) ለሠላሳ ሦስት ጊዜ በመደጋገም

*"ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም"*

(እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረቶች ኹሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤ ርሱ የተመሰገነ ነው፤ለዘላለሙም ከፍ ከፍ ያለ ነው) እያሉ "ያመስግኑታልን" ለ ፴፫ ጊዜ ያኽል ተናግረዋል (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቍ ፴፫-፷፭)።

በሊቃውንቱ ትንታኔ ሠለስቱ ደቂቅ ስድስት ጊዜ መላልሰው መናገራቸው ከ፶፻ ዘመናት በኋላ ምስጉን የኾነው የባሕርይ አምላክ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ማጠየቃቸው ሲኾን፤ ከዚያው ቀጥለው ደግሞ ሠላሳ ሦስት ጊዜ "ያመስግኑታል" እያሉ ቃሉን ደጋግመው ማለታቸው፤ ምስጉን የኾነው አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ሠላሳ ሦስት ዓመት በዚኽ ዓለም የሚኖር እንደኾነ ተገልጾላቸው የተናገሩ መኾኑን አስተምረዋል።

ይኽነንም ምስጢር ቀደምት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲተነትኑ

*"ወኢለከፎሙ እቶነ እሳት ግሙራ ወረሰዮ ለእቶነ እሳት ከመ ማይ ቈሪር በጊዜ ጽባሕ ወበውእቱ ሰዓት ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም፤ ወተነበዩ ስድስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ ከመ እምድኅረ ስድስቱ ምእት ዓመት ይትወለድ ክርስቶስ። ወእምድኅሬሁ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም ዘንተኒ ተነበዩ ሠላሳ ወሠለስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ ከመ እምድኅረ ተወልደ ክርስቶስ ይነብር ውስተ ዓለም ሠላሳ ወሠለስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ"*

(የሚነድደው እሳት ፈጽሞ አልነካቸውም የሚነድደውን እሳት እንደ ውሃ የቀዘቀዘ አድርጎታልና፤ በዚያን ሰዓት እግዚአብሔርን እንዲኽ እያሉ አመሰገኑት፤ የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤



www.ethiopianorthodox.org



ለዘለዓለሙ ክቡር ምስጉን ነው፤ እንዲኽ እያሉ ስድስት ጊዜ ተናገሩ፤ ከስድስት መቶ ዘመን በኋላ ክርስቶስ እንዲወለድ ለማጠየቅ፤ ከዚኽም በኋላ እንዲኽ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ እግዚአብሔርን ፍጥረቱ ኹሉ ያመሰግኑታል ክቡር ምስጉን ነውና ለዘላለሙ ይክበር ይመስገን እያሉ፤ ይኽነንም ሠላሳ ሦስት ጊዜ ተናገሩ፤ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ በዚኽ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት እንዲኖር ለማጠየቅ)[135] በማለት ልዩውን ምስጢር አስተምረውናል።

ንጉሡ ናቡከደነጾርም ባስመቃጠላቸው፤ በእሳት ውስጥ ኹነው በማመስገናቸው ተደንቆ አማካሪዎቹን "ሦስት ሰዎች አስረን በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረም? እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መኻከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለኍ፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል" በማለት፤ ስማቸውን ጠርቶ እናንተ የልዑል አምላክ ባሪያዎች ውጡ ሲላቸው ሦስቱ ሕፃናት ከእሳቱ ወጡ፤ ያን ጊዜ መሳፍንቱ ኹሉ የራሳቸው ጠጕር እንዳልተቃጠለ፤ ሰናፊላቸው እንዳልተለወጠ፤ የእሳቱ ሽታ እንኳ እንዳልደረሰባቸው አዩ።

ያን ጊዜ ንጉሡ "በርሱ የታመኑ ባሪያዎቹን ያዳነ የሲድራቅ የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ" በማለት ምስጋናውን አቀርቧል (ዳን ፫፥፳፱-፴)።

እነዚኽ ሦስቱ ሕፃናት አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል በእቶን እሳት ቢጣሉም እንኳ፣ ስለ እምነታቸው ብርታት ምስጢር ተገልጾላቸው በ፶፻ ዘመን አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፴፫ ዓመት በዚኽ ዓለም ኖሮ ነፍሳትን ከሲኦል እሳት ነጻ እንደሚያወጣ የተገለጸላቸውን ልዩ ምስጋና፣ ዛሬ ኹላችን በቃል ኪዳኗ በምልጃዋ ከገሃነመ እሳት ከምንድንባት ከምትራራልን እናት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታና፤ ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በኆኅተ ብርሃን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ

*"መሃኪቶሙ እምውስተ እቶነ እሳት ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል በእደ ቅዱስ ገብርኤል"* (በቅዱስ ገብርኤል እጅ አናንያን፣ አዛርያን፣ ሚሳኤልን በእቶን እሳት ውስጥ የራራሺላቸው አንቺ ነሽ)[136] በማለት ምስጢሩን እንደወርቅ አንክብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ ገልጾታል።

---

[135] ድርሳነ ሚካኤል ዘታኅሣሥ

[136] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ ኆኅተ ብርሃን ገጽ 97

## የዳንኤል የትንቢቱ ክንውን

ቍጥሩ ከዐበይት ነቢያት የኾነው ነቢዩ ዳንኤል በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ አካላዊ ቃል ዘመኑ ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ መርገመ ሥጋንና መርገመ ነፍስን የሚያርቅ፣ አሪታዊት ቤተ መቅደስን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚለውጥ፣ በደልን አጥፍቶ ኀጢአትን ይቅር የሚልና ጽድቅ ወንጌል እንድትነገር የሚያደርግ መኾኑ ተገልጾለት ጌታ ከእመቤታችን የሚወለድበትን የሱባዔ ቍጥር በሰንበት ቈጥሯል።

ይኸውም በምዕ ፱፥፳፬-፳፯ ላይ "ዐመፃን ይጨርስ ኀጢአትንም ይፈጽም በደልንም ያስተሰርይ የዘላለም ጽድቅ ያገባ፣ ራእይንና ትንቢትን ያትም፣ ቅዱሰ ቅዱሳኑን ይቀባ ዘንድ በሕዝብኽና በቅድስት ከተማኽ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቈጥሮአል፣ ስለዚኽ ዕወቅ አስተውልም፣ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሲሕ ድረስ" በማለት አምላክ ከእመቤታችን የሚወለድበትን የሱባዔ ቍጥር ተናግሯል።

ነቢዩ ዳንኤል ተገልጾለት "ሯ ሰንበታተ ተሰምሐ ለሕዝብከ" (ወገኖችኽን ሰባ ሱባዔ ቅጠሩቸው) ማለቱ ለጊዜው በምርኮ ያሉት እስራኤልን "በሰባ ዘመን ከፋርስ ከባቢሎን አወጣችኋለኍ ወደ ምድረ ርስታችኍ ኢየሩሳሌም አስገባችኋለኍ" ብለኽ ቍርጥ ቀጠሮ ንገራቸው ማለቱ ሲኾን ፍጻሜው ግን የነፍሳትን ነገር ሲነግረው ነው፣ ይኸም በሰባ ሱባዔ ዘመን ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከድንግል ማርያም ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ቈርሼ ደሜን አፍስሼ ከጠላታችኍ ከዲያብሎስ እጅ አድናችኋለኍ፣ በባቢሎን ከምትመሰል ከሲኦል አወጣችኋለኍ፣ወደ ሀገረ ሕይወታችኍ ወደ ገነት ኋላም ወደ መንግሥተ ሰማያት አገባችኋለኍ ብሏችኋል ጌታ ብለኽ ለነፍሳት ቍርጥ ቀጠሯቸውን ንገራቸው ሲለው ነው።

ይኸውም ሰባቱን ዘመን አንድ እያሉ እስከ ሰባ ሱባዔ ዘመን ቢራ አግብቶ ቢቈጥሩት አራት መቶ ዘጠና ይኾናል (፯×፸=፬፻፺) ፤ ይኸውም ዳንኤል ትንቢቱን ከተናገረ ከአራት መቶ ዘጠና ዘመን በኋላ መሲሕ ጌታ ከእመቤታችን የሚወለድ መኾኑን አስቀድሞ ያስረዳ ነበር።

የሠለስቱ ደቂቅ የምስጋና ጣዕም በሚለው ክፍል ላይ እንደለጽኸት አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኙ በምስጢር በስድስት መቶ ዓመት አምላክ ከሰማየ ሰማያት





መውረዱን ከቅድስት ድንግል መወለዱን ተናግረው ነበር፣ ኾኖም ግን ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅ በዘመን አንድ ኹነው ሳሉ በአቈጣጠር ተለያይተዋል፣ ይኸም በነቢያት መለየት ኑሮ ሳይኾን የአቈጣጠራቸው ስልት ነው፣ ነቢዩ ዳንኤል በሰባ ሱባዔ ማለት በአራት መቶ ዘጠና ዘመን አምላክ ከእመቤታችን ይወለዳል ማለቱ ከሚጠት (ከምርኮ መልስ) እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለውን ዘመን ቈጥሮ ሲኾን ሠለስቱ ደቂቅ በስድስት መቶ ዘመን ያሉበን ምክንያት ከጥንት ምርኮ ማለት ሴዴቅያስ ከተማረከበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕርገተ ክርስቶስ ድረስ ያለውን ቈጥረው ነው።

ይኸም የሠለስቱ ደቂቅ ስድስት መቶ ዘመን ከዳንኤል አራት መቶ ዘጠና ዘመን በቍጥር መብለጡ መቶ ዐሥር ዓመት ነው (፮፻-፬፻፺=፻፲)። ይኽ የኾነበትም ከጥንት ምርኮ ከሴዴቅያስ ጀምሮ እስከ ምርኮ መልስ ያለው ዘመን ሰባ ሰባት ዓመት ሲኾን ከልደተ ክርስቶስ ድረስ እስከ ዕርገተ ክርስቶስ ሠላሳ ሦስት ዓመት ነው፣ ሰባ ሰባትና ሠላሳ ሦስትን ቢደምሩ መቶ ዐሥር ይኾናል (፸፯+፴፫=፻፲)፣ መቶ ዐሥሩን ወስደው ዳንኤል ከተናገረው ካራት መቶ ዘጠና ዓመት ጋር ቢደምሩት ስድስት መቶ ዘመን ይኾናል፣ ይኸንንም አንድነት ስናይ ነቢያትን ኹሉ በመንፈስ እግዚአብሔር ቃኝነት ስለ ተናገሩ ምንም ዐይነት ተቃርኖና መለያየት የሌለባቸው መኾኑን እንረዳለን።

ይኽ ነቢይ ዳንኤል በዚኽ ትንቢቱ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዐመፃ በደልን አጥፍቶ "ኀጢአትኽ ተሰረየልኽ ኀጢአትሽ ተሰረየልሽ" በማለት ምሕረት መስጠቱን ጽድቅ ወንጌልን ማስተማሩና፣ ኢየሩሳሌም አምላክ ከእመቤታችን እስኪወለድ ድረስ በመፍረስ በመታነጽ ቆይታ፣ ቤተ መቅደሷም በመታነጽ ቆይቶ በዘመነ ሥጋዌ ቤተ ክርስቲያን በመኾን የምትታነጽ መኾኑን የተናገረውን ትንቢት የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ ከቅድስተ ቅዱሳን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታልና ታላቁ የቅዱሳት መጻሕፍት መምህር ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ

*ፈጻሚተ ትንቢተ ዳንኤል አንተ ነቢየ ሱሳ*

*ዘበእንቲአኪ ኮነ ምጽአተ ጽድቅ ወኀደገተ አበሳ*

(የጽድቅ መምጣትና የበደል ትድግና ስለ አንቺ የተደረገ የሱሳ ነቢይ የሚኾን የዳንኤል ራእይ (ትንቢት) ያከናወንሽ አንቺ ነሽ)[137] በማለት ምስጢሩን አስቀምጦታል።

[137] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣እንዚራ ስብሐት ገጽ 26



www.ethiopianorthodox.org

## የአናብስት ጉድጓድ

አምላክ በድንግልና የወለደችው ቅድስት ድንግል ማርያም በታተመችው በአናብስት ጉድጓድ ትመሰላለች (ተረፈ. ዳንኤል ፲፫፥፴፪-፴፱)

ይኸውም ነቢዩ ዳንኤል በሀገረ ባቢሎን በአንበሶች ጉድጓድ ተጥሎ ሳለ ዕንባቆም አዝመራውን ለሚያጭዱ ምሳ ይዞላቸው ሲኼድ፤ መልአከ ቅዱስ ሚካኤል "ስድ ዘንተ ምሳሐ ለዳንኤል እንተ ዘሀሎ ውስተ ግበ ባቢሎን" (ይኸንን የያዝኸውን ምሳ በባቢሎን በአናብስት ጉድጓድ ሳለ ለወንድምኽ ውሰድለት) አለው፤ ዕንባቆምም አቤቱ ባቢሎንን አላውቅም ሲለው ፤መልአኩ ወስዶት በባቢሎን ወዳለ ወደ አንበሶች ጉድጓድ አደረሰው።

ርሱም በአምላክ ድንቅ ጥበብ እንደተዘጋ ገብቶ ለዳንኤል ምግቡን ሰጥቶት ኼዷል፤ ዳንኤልም "*ተዘከረኒ እግዚአብሔር ዘኢኀደጎሙ ለእለ ያፈቅርዎ*" (ወዳጆቹን የማይዘነጋቸው እግዚአብሔር አሰበኝን) በማለት አድንቋል።

ይኸውም ለጊዜው ቢደረግ ለኋላው ግን ምሳሌ ነበር፤ የአናብስት ጉድጓድ የእመቤታችን፤ ምግቡ የምግበ ነፍስ፤ ዕንባቆም የጌታ ምሳሌ ሲኾን እንደተዘጋ ገብቶ እንደተዘጋ መውጣቱ ጌታ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ለመወለዱ ምሳሌ እንደኾነ መተርጉማን ይገልጻሉ።

በኢትዮጵያ ከነበሩ ከነገረ ማርያም ሊቃውንት አንዱ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ ድንቅ ስለኾነው ማኅተመ ድንግልናዋን በደጃፍ መስሎ የዳንኤልን ቃል በመጥቀስ ሲያብራራ

"*እባርክኪ ተኪንዎቶ ለወልደ አብ ዘኢያርኅወ ሠለስተ አናቅጸ፤ አንቀጸ ሥጋ ድንግልናዊ በልደቱ፤ ወአንቀጸ መቃብር በትንሣኤሁ ወዕአ እንዘ ኅቱም ውእቱ፤ ወአንቀጸ ጽርሕኒ እንዘ ዕጽው ውእቱ ቦአ ኀበ ሀለዉ አርዳኢሁ ጉቡኣን፤ ወወፅአኒ እንዘ ኢይትረኀው፤ በእንተ እሳንቱ ሠላስ አንቀጽ አንክረት ኀሊናየ በእንተ ክልኤቲሰ ረከብኩ ምክንያተ፤ በእንተ አንቀጸ መቃብር ነዋ ግብር ዘይመስሎ፤ ለዳንኤል ዘተሰምየ ብልጣሶር ወደይዎ ውስተ ግብ ምስለ አናብስት ርኁባን ወኀተምዎ ለግብ በዐቢይ ማኅተም፤ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ ይጼዐር ዳንኤል በረኀብ ፈነወ መልአኮ ኀበ ዕንባቆም ነሥኦ በሥዕርተ ድማኁ፤ ወአብኦ ውስተ ግብ ኀበ ሀሎ ዳንኤል እንዘ ኅቱም ውእቱ ግብ ወበልዐ ዳንኤል ወዕንባቆም ተብሲለ ወኀብስተ፤ ወአእኰትዎ ለእግዚአብሔር ወወፂአ*





*ውእቱ አንቀጸ ግብ፤ ወበእንተዝ አንቀጸ ጽርሕኒ ነዋ ግብር ዘይመስሎ ዘከመ ጸሐፍ ውስተ ግብረ ሐዋርያት ዘከመ ወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወአውፅኦ ለጴጥሮስ እምቤተ ሞቅሕ፤ ወእምድኅረ አውፅኦ ተረክበ አንቀጸ ቤተ ሞቅሕ ንሡግ ወቅቱረ ወዝጉሐ፤ ወሠገራት የዐቅቡ እንተ ኵለሄ (ግብ.ሐዋ ፲፪፥፯-፲፩) በእንተ እሉ ክልኤቱ አናቅጽ ረከብኩ ምክንያተ ዘገብረ ለቅዱሳን፤ ወበእንተ አንቀጸ ድንግናኪሰ ኀጣእኩ ምክንያተ እስመ አልቦ ዘሰማዕኩ ዘከመ ወለደት ድንግል፤ ወኢሂ እምድኅረ ወለደት ዘነበረት ድንግለ ኢርኢኩ፤ ኦ ኪ መንክር ዝ ግብር ወጥቀ ዕጹብ ዝ ምስጢር ዘተሠርዐ በጥበበ እግዚአብሔር ሕያው"*

(ሦስት ደጃፎችን ያልከፈተ የአብ ልጅ ጥበቡን አደንቃለኊ፤ የሥጋ ደጃፍ ድንግልናን በልደቱ፤ የመቃብር ደጃፍ ዝግ ሲኾን በትንሣኤው ወጣ፤ የአዳራሹም ደጃፍ ዝግ ሲኾን ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው ወደአሉበት ገብቶ ሳይከፍት ወጣ (ዮሐ ፳፥፲፱-፳፮)፤ ስለ እነዚኽ ሦስት ደጃፎች ልቡናዬ አደነቀች፤ ስለ ኹለቱ ግን ምክንያት አገኘኊ፤ ስለ መቃብሩ የሚመስለው ነገር አለ፤ ብልጣሶር የተባለ ዳንኤልን የተራቡ አንበሶች ወዳሉበት ጉድጓድ ጣሉት፤ ጉድጓዱንም በታላቅ መዝጊያ ዘጉት፤ ዳንኤልም በረኀብ እንደተጨነቀ እግዚአብሔር ባየ ጊዜ መልአኩን ወደ ዕንባቆም ላከ፤ በራስ ጠጕሩም ይዞ ዳንኤል ወደአለበት ጉድጓድ አስገባው፤ ጉድጓዱ ተዘግቶ ሳለ ዕንባቆምና ዳንኤልም ንፍሮውንና እንጀራውን በልተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ዕንባቆምም የጉድጓዱ ደጃፍ ተዘግቶ ሳለ ወጣ፤ ስለዚኽም አዳራሹ የሚመስለው ነገር አለ በሐዋርያት ሥራ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር መልአክ ወርዶ ከእስር ቤት እንዳወጣው ጴጥሮስንም ካወጣው በኋላ የግዞት ቤቱ ደጃፍ ተቈልፎ ተቀርቅሮ ተዘግቶ ተገኘ፤ ወታደሮቹም በየመኣዝኑ ኹሉ ይጠብቁ ነበር (የሐዋ. ሥራ ፲፪፥፯-፲፩)፤ ስለ እነዚኽ ኹለት ደጃፎች ለቅዱሳን የተደረገውን ምክንያት አገኘኊ፤ ስለ ድንግልናሽ ደጃፍ ግን ምክንያትን አጣኊ፤ ድንግል እንደ ወለደች የሰማኹት ነገር የለምና፤ ከወለደችም በኋላ በድንግልና የተቀመጠች አላየኹምና፤ ይኽ ድንቅ ነገር ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ ለዚኽ አንክሮ ይገባል በሕያው እግዚአብሔር የተሠራው ይኽ ምስጢር ዕጹብ ድንቅ ነው)[138] በማለት ይኽ የነገረ ማርያም ሊቅ በማራቀቅ ምሳሌውን አስተምሮታል።

---

[138] [illegible] ፥፯-፲፬



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት

# ነገረ ማርያም በደቂቅ ነቢያት

አራቱ ዐበይት ነቢያት ማለት ኢሳይያስ፤ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ንጽሕና፣ ቅድስና፣ ዘላለማዊ ድንግልና፣ እማላጅነት፣ ወላዲተ አምላክነቷን አምልተው አስፍተው እንደ ተናገሩ ኹሉ ዐሥራ ኹለቱ ደቂቅ ነቢያትም በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው ክብሯን መስክረውላታል። እነዚኽም ነቢዩ ሖሴዕ፣ አሞጽ፣ ሚክያስ፣ ኢዩኤል፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስ፣ ሲኾኑ በዐሥራ ኹለቱም ትንቢት ውስጥ የነገረ ማርያም ምስጢሮች ይገኛሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት የሚያውቃቸው የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እመቤታችን በደቂቀ ነቢያት ትንቢት በእንዚራ ስብሐት መጽሐፍ ላይ በአስደናቂ ኹኔታ እንዴት እንደተገለጸች ትንቢቱን በግጥም ሲተነትን

*"ኦ ድንግል አንቲ ውእቱ ለዘሩባቤል ሞገሰ ቃሉ*
*በቅድመ ንጉሥ ወዐበይቱ*
*አመ ሞአ ሎቱ ምሳሌ ወራዙት ክልኤቱ*
*አንቲ ውእቱ ርትዕት ለእግዚአብሔር ፍኖቱ*
*ዘንእደከ ዮሴዕ በፍጻሜ ትንቢቱ*
*አንቲ ውእቱ ዘነሣእኪዮ ለአሞጽ እማእከለ መርዔቱ*
*በእንተ ኀጢአት ሠላሳ ወአርባዕ ከመ ይዝልፎሙ*
*ለሕዝበ ያዕቆብ እለ ስሕቱ*
*ወለሚክያስ አንቲ ፈጻሚተ ትንቢቱ*
*ዘብኪ ኮነ ለእግዚአብሔር ተረክቦቱ*
*እምአእላፍ ሐራጊት ዘይኄይስ ተሠውዖቱ*
*ወአንቲ ካዕበ ለኢዩኤል ንቅዐ በረከቱ*
*ደብረ ጽዮን አንቲ ለአብድዩ ደብረ መድኀኒቱ*
*ዘእምኔኪ ኮነ ለእግዚአብሔር አስተርዕዮቱ*
*ዓቃቢተ ነፍሱ ለዮናስ ወእምግበ ሲኦል መጣቂቱ*
*ርጢን ቍስሉ ለናሆም ወለዕንባቆም ሰዋሰወ ጸሎቱ*
*ፈጻሚተ ራእዩ ለሶፎንያስ ወለሐጌ ትርሲተ ቤቱ*
*እብነ ርትዕ አንቲ ዘዘካርያስ ዘአዕይንቲሃ ሰብዐቱ*
*ዘተወፈያ ዮሴዕ በዕለተ አስምዑ ሎቱ*
*አንቲ ውእቱ ጸርሐ ንጽሕት ዘሚል[illegible]*





(ድንግል ሆይ የኹለቱ ጕልማሶች ክርክር ምሳሌ ባሸነፈለት ጊዜ በንጉሡና በባለሟሎቹ ፊት የዘሩባቤል የቃሉ ጣዕም አንቺ ነሽ፤ ዮሴዕ በትንቢቱ ፍጻሜ ያመሰገነሽ (ያከበረሽ) የእግዚአብሔር የቀናች ጐዳናው አንቺ ነሽ፤ ስለሦስቱና አራቱ በደሎች የእነ የያዕቆብ ወገኖችን ይዘልፋቸው ዘንድ ከመንጎቹ መኻከል አሞጽን የተቀበልሺው አንቺ ነሽ፣ ከእእላፍ ጊደሮች መሥዋዕት ይልቅ የርሱ መሥዋዕት የተሻለ የእግዚአብሔር መገኘት በአንቺ የኾነ የሚክያስ የትንቢቱ ክንውን አንቺ ነሽ፤ ዳግመኛም የኢዩኤል የበረከቱ ምንጭ አንቺ ነሽ፤ የእግዚአብሔር መገለጡ በአንቺ የኾነ የአብድዩ የመድኀኒት ተራራ የጽዮን ተራራ አንቺ ነሽ፤ የዮናስ የነፍሱ ጠባቂና ከሲኦል ጕድጓድም የምታወጪው አንቺ ነሽ፤ የናሆም የቍስሉ መድኀኒትና የዕንባቆምም የጸሎቱ መሰላል አንቺ ነሽ፤ የሶፎንያስ ራእይ ፈጻሚና የሐጌም የቤቱ ሽልማት ጌጥ አንቺ ነሽ፤ በአስመሉለት ቀን ዮሴዕ የተቀበላት ዐይኖቿ ሰባት የኾኑላት ቀጥተኛ የዘካርያስ ደንጊያ አንቺ ነሽ፤ የሚልክያስ ንጹሕ አዳራሽና የእውነተኛ ፀሐይ ደጃፍ አንቺ ነሽ)[139] በማለት ጥልቅ የኾነ የነገረ ማርያም ትምህርትን አስተምሯል።

ይኽንንም ምስጢር የእያንዳንዱን ነቢይ ትንቢት ስንመረምር በውስጡ የምናገኘው ሲኾን እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከዚኽ በታች በየቦታቸው ተንትኜአቸዋለኹ።

## ነገረ ማርያም በትንቢተ ሖሴዕ

## ክፍል አንድ

ነቢዩ ሖሴዕ በአራቱ ነገሥተ ይሁዳ ማለት በዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ጊዜ የነበረ ሲኾን ትርጓሜውም መድኀኒት ማለት ነው፤ ትንቢቱም ፲፬ ምዕራፎችና ፩፻፺፯ ቍጥሮች ሲኖሩት፤ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ስለመወለዱ፣ ወደ ግብጽ ስለ መሰደዱና ስለ መመለሱ፣ ስለ ሞቱና ትንሣኤው በሕብረ አምሳል ሲገልጽ በሐዲስ ኪዳንም በብዛት ተጠቅሷል (ሖሴ. ፮፥፩-፫፤ ፲፩፥፩-፬፤ ማቴ ፪፥፲፬-፲፭፤ ሮሜ ፱፥፳፭-፳፮)፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስተምሬዋለኹ።

139 [illegible] እንዚራ ስብሐት ገጽ 42-43

www.ethiopianorthodox.org

## ምድር

ነቢየ እግዚአብሔር ሆሴዕ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ለምእመናን ሥጋውን፣ ደሙን፣ ልጅነትን በመስጠት ለ፭ሺሕ ፭፻ ዘመን ከርሱ ተለይተው የነበሩትን ወገኖቹ ማድረጉን በምዕ ፪፥፳፫ ላይ

"በዚያን ቀን እመልሳለሁ ይላል እግዚአብሔር፣ *እሰጠዋ ለሰማይ*" (ለሰማይ እመልሳለሁ)፤ "*ወሰማይኒ ይሰጠዋ ለምድር*" (ሰማይም ለምድር ይመልሳል) በማለት ፭ ሺሕ ፭፻ ዘመን በሚፈጸምባት በዚያች ቀን ሰማይ የተባለ፣ ሰማያዊ መለኮት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፤ ምድር ከተባለች ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው የመኾኑን ምስጢር ከገለጸ በኋላ፤ "*ወምድርኒ ትሰጠዎሙ ለእክል ወለወይን ወለቅብዕ*" (ምድርም ለእኽልና ለወይን፣ ለዘይትም ትመልስላቸዋለች) በማለት ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው የኾነው ሥግው ቃል ክርስቶስ ለአዳም ልጆች ሥጋውን ደሙን፣ ልጅነቱን የሚሰጥ መኾኑን በእኽል፣ በወይን፣ በዘይት መስሎ ገልጾታል።

ከዚያም በመቀጠል "በምድርም ላይ በእኔ እዘራታለሁ" በማለት የሰላም መልእክትን የያዘቿውን የወንጌልን ቃል በምእመናን ልቡና የሚዘራ የሚያሳድር መኾኑን ከገለጸ በኋላ፤ ለ፭ሺሕ ፭፻ ዘመን በመንጸፈ ደይን በሲኦል ወድቀው ከፈጣሪያቸው ተለይተው ይቅርታን ያላገኙትን ደቂቀ አዳምን ይቅር ማለቱንና ወዳጆቹ ያልነበሩትን የሰው ልጆችን ወዳጆቹ ማድረጉን "*ወእምሕራ ለእንተ ኢኮነት ምሕልተ፤ ወአፈቅራ ለእንተ ኢኮነት ፍቅርትየ*" (ምሕረትም የሌላትን እምራለሁ፣ ወዳጄ ያልነበረችውን እወዳለሁ) ሲል ተናግሯል።

ይኽ የሆሴዕ ትንቢቱ ሲፈጸም ራሱ ባለቤቱ መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ በዮሐ ፲፭፥፲፬-፲፭ ላይ "እኔ ያዘዝኋችኹን ኹሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችኊ፤ ከእንግዲኽ ወዲኽ ባሮች አልላችኹም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለኊ" በማለት ፭ ሺሕ ፭፻ ዘመን ከርሱ ርቀን የነበርነው እኛን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ወዳጆቹ እንድንኾን የፈቀደልን መኾኑን አስተምሮናል።





ነቢዩ ሆሴዕ በመቀጠል ቀዳማዊ አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ወገኖቹ ያልነበርነውን እኛን ወገኖቹን ማድረጉንና፤ እኛም ርሱን አምነን በእውነት የባሕርይ አምላክ ብለን የምንጠራው ስለ መኾኑ "*ወእብሎሙ ሕዝብየ ለዘኢኮነ ሕዝብየ ወውእቱ ይብለኒ አግዚእየ ወአምላኪየ አንተ*" (ሕዝቤም ያልኾነውን አንተ ሕዝቤ ነኽ እለዋለኊ፤ ርሱም አንተ አምላኬ ነኽ ይለኛል) በማለት በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ ይኽ ነቢይ ታላቅ ምስጢርን ተናግሯል።

ስለዚኽ የትንቢት ፍጻሜ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ከሆሴዕ ቃል በመጥቀስ "ወደ ክብሩ የጠራን የሰበሰበን እኛ ነን፤ ከአይሁድ አይደለም ከአሕዛብም እንጂ፤ እንዲኹም ደግሞ በሆሴዕ ሕዝቤ ያልኾነውን ሕዝቤ ብዬ፤ ያልተወደደችዉንም የተወደደችው ብዬ እጠራለኊ፤ እናንተ ሕዝቤ አይደላችኹም በተባለላቸው ስፍራ በዚያ በሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ ይላል" በማለት ትንቢቱ ፍጻሜውን ያገኘ መኾኑን አስተምሯል (ሮሜ ፱፥፳፭-፳፮)።

የእመቤታችን ባዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም ቅድስት ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት የኀሙስ ውዳሴ ማርያም ላይ ከነቢዩ ሆሴዕ ቃል በመነሣት፤ ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ለ፭ሺሕ ፭፻ ዘመን ከርሱ ተለይተን በመንጸፈ ደይን የወደቅነውን የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ ሕዝቡ (ወገኑ) ያልነበርነውን እኛን ሕዝቦቹ (ወገኖቹ) ያደረገን ስለመኾኑ ሲገልጽ "*አሐዱ ዘእምቅድስት ሥላሴ ርእዮ ትሕትናነ አጽነነ ሰማየ ሰማያት መጽአ ወኀደረ ውስተ ከርሠ ድንግል ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኀጢአት ባሕቲታ ወተወልደ በቤተልሔም በከመ ሰበኩ ነቢያት አድኀነነ ወቤዘወነ ወረሰየነ ሕዝበ ዚአሁ*" (ከቅድስት ሥላሴ አንዱ አካል ወልድ መዋረዳችንን አይቶ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ መጥቶ በድንግል ማሕፀን ዐደረ፤ ከብቻዋ ከኀጢአት በቀር እንደኛ ሰው ኾነ፤ ነቢያት ትንቢት እንደተናገሩ በቤተልሔም ተወለደ፤ ፈጽሞ ተቤዠን አዳነን፤ ወገኖቹም አደረገን)[140] በማለት በስፋት ገልጾታል።

ሐዋርያዋው ቅዱስ ጴጥሮስም ከነቢዩ ሆሴዕ ትንቢት ጋር ትምህርቱን በማስተባበር አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል

[140] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ውዳሴ ማርያም ዘኀሙስ



www.ethiopianorthodox.org

ማርያም ተወልዶ የራ ሺሕ ፳፻ ዘመን ጨለማን አስወግዶ፣ ብርሃንን ሰጥቶን ወገኖቹ ያልነበርነውን እኛን ወገኖቹ ያደረገን መኾኑን በ ፩ ጴጥ ፪፥፱-፲ ላይ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችኹን የርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችኁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችኹም አኹን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችኁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችኁ አልነበራችኹም፤ አኹን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል" በማለት አስተምሮናል።

# ነገረ ማርያም በትንቢተ አሞጽ
# ክፍል ኹለት

ነቢዩ አሞጽ ከእረኛነት ከበለስ ለቃሚነት ለነቢይነት የተጠራ ፤ ዘመኑም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ፯፻፸ ሲኾን ጌታችን በሚሰቀልበት ጊዜ በዓለም ላይ ስለሚከሠተው ጨለማ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ሲናገር ዳግመኛም ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ አንድ እንደሚኾኑ መናገሩንም ሐዋርያት ጠቅሰዋል (አሞ ፰፥፰፤ ፱፥፲፩-፲፪፤ የሐዋ.ሥራ ፲፭፥፲፭-፲፰ )፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጠነዋለኊ።

## የአሞጽ ተቀባይ

ይኽ ነቢይ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ሲገልጸው

*"አንቲ ውእቱ ዘትግሕሢ ለአሞጽ እማእከለ መርዔቱ*
*በእንተ ኃጢአተ ሠለስ ወአርባዕ ኢመ ይገልፎሙ ለሕዝበ ያዕቆብ*
*እለ ስሕቱ*

(ስለ ሦስቱና አራቱ በደሎች የሳቱ የያዕቆብ ወገኖችን ያዘልፋቸው ዘንድ ከመንጋቱ መካከል አሞጽን የተቀልሺው አንቺ ነሽ)[141] በማለት ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ አስተምሯል።

[141] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንዚራ ስብሐት፣ ገጽ 42



www.ethiopianorthodox.org



ይኸውም አሞጽ ለነቢይነት የተጠራው ከ ፯፻፹፫-፯፻፵፭ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነበረው በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያንና ከ፯፻፹፮-፯፻፵፮ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነበረው የእስራኤል ንጉሥ በዳግማዊ ኢዮርብአም ዘመነ መንግሥት ሲኾን፤ የቀደመ ሥራው ላም መጠበቅና በለስ መልቀም እንጂ ከነቢያት ወገን አልነበረም፤ ይኽነንም ራሱ አሞጽ በምዕ ፯፥፲፬-፲፭ ላይ ሲገልጸው "እኔ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለኹምና፤ እግዚአብሔርም በጎቹን ከመከተል ወሰደኝ፤ እግዚአብሔርም ኺድ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢትን ተናገር አለኝ" በማለት አመራረጡን ተናግሯል።

ይኽ ነቢይ ለዚኽ አገልግሎት ከተጠራ በኋላ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በኋላ ዘመን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዚኽ ዓለም ሲያስተምር፥ እስራኤላውያን የርሱን ትእዛዝ ባለመጠበቅ በክፋት፣ በቅናትና በምቀኝነት ጻድቀ ባሕርይ ርሱን በጥንድ ጫማ ዋጋ በ፴ ብር አሳልፈው እንደሰጡትና፤ እውነትን የሚያስተምሩ በዓለም የተናቁ ሐዋርያትን ራስ ራሳቸውን እየቀጠቀጡ እያሳዳዱ፤ እውነተኛውን መንገድ በማጣመማቸው ምክንያት ስለሚመጣባቸው ስለሦስት ስለ አራት መከራ በምዕ ፪፥፮-፯ ላይ

"ጻድቁን ስለ ብር፤ ችጋረኛውንም ስለ አንድ ጥንድ ጫማ ሸጠውታልና፤ ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የእስራኤል ኀጢአት መቅሠፍቱን ከማድረግ አልመለስም፤ የድኾችን ራስ በምድር ትቢያ ላይ ይረግጣሉ፤ የትሑታንንም መንገድ ያጣምማሉ" በማለት የተናገረው ትንቢትና፤ በተጨማሪም በጌታ ስቅለት ጊዜ ዓለም ስለመጨለሟ በምዕ ፭፥፳ ላይ

"የእግዚአብሔር ቀን ብርሃን ሳይኾን ጨለማ አይደለምን? ጸዳል የሌለውም ድቅድቅ ጨለማ አይደለምን" በማለት የተናገረውን ትንቢት አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በሙሉ ፈጽሞታልና "ስለ ሦስቱና አራቱ በደሎች የሳቱ የያዕቆብ ወገኖች ይዘልፋቸው ዘንድ ከመንጋቱ መካከል አሞጽን የተቀበልሺው አንቺ ነሽ" በማለት ሊቁ አባ ጊዮርጊስ አመስግኗታል።

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ሚክያስ
## ክፍል ሦስት

ይኸ ነቢይ ሚክያስ ከ ፯፻፶፱-፮፻፺፯ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነበሩት በሦስቱ የይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፣ በአካዝና፣ በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የነበረ ሲኾን የሖሴዕና የኢሳይያስ የዘመን ጓደኛ ነው፤ ኢሳይያስ በኢየሩሳሌም ሲያስተምር ሚክያስ ደግሞ በምዕራባዊዉ ይሁዳ ያስተምርና ትንቢት ይናገር ነበር፤ ስለ ሥጋዊም የተናገሩት ትንቢት ብዙውን ጊዜ ይመሳሰላል፤ ለምሳሌም ያኽል ኢሳይያስ በምዕ ፪፥፫ ላይ "ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔር ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና" በማለት ሕግ የተባለ ሐጋጌ ሕግ (ሕግን የደነገገ) ጌታ ምልጃዋ ጸወነ ሥጋ ጸወነ ነፍስ በመኾን ጽዮን ከተባለች፤ ዳግመኛም የሰላም አለቃ ርሱን ፱ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ በመሸከሟ ኢየሩሳሌም (ሀገረ ሰላም) ከተባለች ከእመቤታችን ስለመወለዱ የተናገረው ትንቢትና ነቢዩ ሚክያስ በምዕ ፬፥፪ ላይ የተናገረው ተመሳሳይነት አላቸው[142]፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጬዋለኊ፡፡

### ቤተልሔም

ይኽ ነቢይ ሚክያስ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ ቅድመ ዓለም የነበረው ዘላለማዊዉ ንጉሥ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በቤተልሔም የመወለዱ ነገር አስቀድሞ ተገልጾለት በምዕ ፭፥፪ ላይ

"አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መኻከል ትኾኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ከዘላለም የኾነ በእስራኤል ላይ ገዢ የሚኾን ይወጣልኛል" በማለት አስደናቂ ትንቢትን ተናግሯል፡፡

[142]ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽ ኢሳይያስና ሚክያስ የተናገሩትን ሲያብራራ "እስመ ሕግ ይወጽእ እምጽዮን ዘተብሀለ በእንተ ጽላተ ሕግ ወኪዳን ዘይትሀቀብ በውስተ ከርሠ ታቦት ቅቱለ ወርቅ ዘውእቱ ዑመሪ አሪት ወቃለ እግዚአብሔር እምኢየሩሳሌም ዘተብህለ በእንተ ልደተ ቃለ እግዚአብሔር ንጹሕ እማርያም ቅድስት ድንግል ፤ እስመ ይእቲ ወለተ እስራኤላውያን እምሰብአ ኢየሩሳሌም (ሕግ ከጽዮን ይወጣልና የተባለው በወርቅ የተለበጠው የታቦት ከርሥ ውስጥ የሚጠበቅ ስለሚኾን የሕግና የኪዳን ጽላት ነው ፤ ያውም የኦሪት መጨመሪያ ነው ፤ የእግዚአብሔር ቃልም ከኢየሩሳሌም ይወጣል የተባለው ከቅድስት ድንግል ማርያም ንጹሕ የእግዚአብሔር ቃል ስለመወለዱ ነው ፤ ርሷ ከኢየሩሳሌም ሰዎች የእስራኤላውያን ብላቴና ናትና) በማለት ትንቢታቸውን አስፋፍቶ ተርጕሞታል (አርጋኖን ዘገሙስ ፮፥፳፱-፴)፡፡



www.ethiopianorthodox.org



ይኸውም መተርጕማን እንደሚገልጹት ነቢዩ ሚክያስ ሌላውን አህጉር ሲያስተምር ውሎ ወደ ማታ በቤተልሔም በኩል ሲያልፍ ተፈታ ቋያ በቅሎባት አራዊት ሰልጥነውባት አይቶ እንዲኽ እንደኾንሽ አትቀሪም፤ ንጉሥ ይነግሥብሻል፤ ድንኳን ይተከልብሻል፤ የነጋሪት ድምፅ ይሰማብሻል፤ እስራኤል ደጅ ይጠኑብሻል፤ አሕዛብ ይገብሩብሻል ሲል ይኽነን ትንቢት ተናግሮላት ነበር፡፡

ርሱም የተናገረው አልቀረም፤ ለጊዜው በቤተልሔም ዘሩባቤል ነግሦባታል፤ ድንኳን ተተክሎባታል፤ የነጋሪት ድምፅ ተሰምቶባታል፤ እስራኤል ደጅ ጠንተውባታል፤ አሕዛብ ገብረውባታልና፤ የትንቢቱ ፍጻሜ ግን የኤፍራታ ዕጣ የምትኾን ቤተልሔም በይሁዳ ሀገር ከነገሡ ነገሥታት ብትበልጥ እንጂ እንደማታንስ የተነገረው ትንቢታዊ ኀይለ ቃል፤ እስራኤል ዘነፍስን የሚጠብቅ ንጉሥ ክርስቶስ በርሷ እንደሚወለድ የሚገልጽ ነበር፡፡

ይኸውም ዘሩባቤል እንደነገሠባት፤ የነገሥታት ንጉሥ ክርስቶስ ተወልዶባታል፤ ድንኳን እንደተተከለባት በጌታ ልደት የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል፤ የነጋሪት ድምፅ እንደተሰማባት ቅዳሴ መላእክት ተሰምቶባታል፤ እስራኤል ደጅ እንደጠኑባት መቶው ነገደ መላእክት ደጅ ጠንተውባታል (ሉቃ ፪፥፲፫-፲፬)፤ አሕዛብ እንደገበሩባት ሰብአ ሰገል ስፈጣሪያቸው ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ገብረዋልና ይኽ የሚክያስ ትንቢት ፍጻሜውን አግኝቷል (ማቴ ፪፥፲፩)፡፡

የአማልክት አምላክ የነገሥታት ንጉሥ ክርስቶስ በቤተልሔም ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል ኮከቡ እየመራቸው "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና" እያሉ መጠየቃቸውን ንጉሥ ሄሮድስ ሰምቶ በመደንገጥ የካህናት አለቆችንና የሕዝቡን ጸሐፊዎች ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንደሚወለድ በጠየቃቸው ጊዜ የነቢዩ የሚክያስን ትንቢት በመግለጥ በቤተልሔም መኾኑን ነግረውታል (ማቴ ፪፥፭-፮)፡፡

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም ስለ ክርስቶስ ልደት በጻፈው መጽሐፍ ላይ አማናዊዉ ንጉሥ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ በቤተልሔም የተደረገውን የመላእክትን ምስጋና ሲገልጥ

*"The angles marveled..."* (መላእክት ተደነቁ፤ ገባኤያት በደስታ ጮኹ፤ ሥልጣናትም ጮኹ፤ ክፍላተ ሰራዊት አመሰገኑ፤ ሰልፈኞችም ተንቀጠቀጡ እናም ወደ ምድር ወረዱ፤ እሳታውያን ፍጡራን በድምቀት አበሩ፤ ረቂቃኑ እስትንፋስ አወጡ፤ መዘምራን ተሰበሰቡ፤ ሺዎች ከእልፋት ጋር በታላቅ ድምፅ አመሰገኑ፣ በረሓማዋ ምድር

(ቤተልሔም) ከሰማያውያን ኀይላት ጋር አስተጋባች፤ የመላእክት ውበትም በታላቅ ግርማው በሌሊት ወጣ፤ የእሳት ብልጭታዎች እየተጠማዘዙ ምድርን ከለሉ፤ የብርሃን ፍንጣቂዎችም አበሩ እናም ጨለማው ተገፈፈ፤ የእሳት ክንፎች ተዘረጉ ምኽቱም ጠፋ፤ ሰማያውያን ፍጡራን ወደታች ወረዱ በምድርም ላይ ተመላለሱና ሰማይ አደረጉት፤ ዳርቻዎች ለክብር ጌታ የምስጋናን ዘውድ አዘጋጁ፤ አንደኛው ከሰማይ ሌላኛውም ከምድር ስርሱ ተበረከቱ፤ የሰማይ እና የምድር ፍጡራን አንዱ ከሌላው ጋር ተደባለቁ (ሉቃ ፪፡፱)፤ እናም ብቻውን የኹሉ ጌታ ለኾነው የምስጋናን ዘውድ አበጁ (ጠለፉ)፤ ለሰዎች ያበሥሩ ዘንድ መላእክት ወረዱ፤ እንዲኽ ባበራው በወልድ አማካይነት ከምድር ወደ ሰማይ ይሸጋገራሉና፤ አንዱ ወገን ከሌላኛው ጋር ተያይዞም ምስጋናን አስተጋባ፤ መላእክት እና ሰዎች በተለያየ ድምፅ አመሰገኑ፤ ከነገደ ገብርኤል የኾኑት ከአዳም ወገን ለኾኑት ድምፅን ሰደዱ፤ በሰማያውያን ምስጋና (ውዳሴ) ይቀሰቀሱ ዘንድ፤ የሚካኤል ነገድም በጣፋጭ ዜማ ተጣሩ፤ የሰው ዘር ሰምቶ የነርሱን ዝማሬ ይማር ዘንድ፤ የኪሩቤል ድምፅም በታላቅ ኀውጽውጽታ አስተጋባ፤ የተዘጉ አንደበቶችን ለምስጋና ያነሣሣ ዘንድ፤ ሱራፌ "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ" የሚል ምስጋናን እንደ መለከት አሰማ፤ ያመሰግኑ ዘንድ ሰዎችን ለመቀስቀስ፤ ከፈጣኖቹ ሠረገላዎችም ነጐድጓድ ወጣና ምድራቱን ነቀነቃት፤ ተናውጣ እንድትነሣ፤ ጌታዋ መጥቷልና በምስጋና እንድትዘምርም፤ ሰማያውያኑ በበገናዎቻቸው የዝማሬያቸውን ዜማ አሰሙ፤ ክብር በአርያም ለምድር ሰላም ተስፋም ለአዳም፤ በላይ በሰማይ የክብር ዘውድ ለሰማያት ጌታ እና በታች በምድር ላይ ለሰዎች በጎ ፈቃድ (ሉቃ ፪፡፲፬))[143] በማለት ሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም የኤፍራታ ዕጣ በኾነቺው በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ ሚክያስ ትንቢት እንደተናገረው የብርሃን ድንኳን እንደተተከለባት፤ መላው ነገደ መላእክት ደጅ እንደጠኑባትና ቅዳሴ መላእክት እንደተሰማባት አስተምሯል።

በጥልቅ የነገረ ማርያም ዕውቀቱ የሚታወቀው ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ነቢዩ ሚክያስ "አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሺም ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ ንጉሥ ከአንቺ ይወጣልና" በማለት ስለተናገረውና ስለተፈጸመው አስደናቂ ምስጢር ሲገልጽ

[143] Jacob of Serugh, On Nativity, pp 80-81





*"ሥርዐተ ሰማይ ከማሁ ተሠርዐ በዲበ ምድር፤ ቤተልሔም ተመሰለት ከመ ሰማይ ህየንተ ፀሓይ ዘየዐርብ ሠረቀ በውስቴታ ፀሓየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኢየዐርብ ወዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን፤ ወህየንተ ወርኅ ዘያስተባሪ መሊአ እምሕጸተ ዐውደ ብርሃኑ አስተርአየት ቅድስት ድንግል ማርያም ዘበዕብራይስጢ ማሪሃም ዘምሉአ ሰብሐተ ድንግልናሃ ወዘኢየሐጽጽ ለዝሉፉ፤ ወህየንተ ኆዋክብት አስተርአዩ መላእክተ ብርሃን፤ መኑ እምክፈለኒ ከመ እኩን ህልወ ኀበ ውእቱ ማኅበር እስብሕ ምስለ መላእክት ወአንክር ምስለ መወልዲት ወእግነይ ምስለ ኖሎት ወአስምክ ምስለ ሰብአ ሰገል፤ መኑ እምክፈለኒ አእምኅ ኀለ ኀበ ሰከበ ሕይወተ ሙታን ወመንጽሔ ኃጥአን ወተስፋ ቅቡጻን ወባላሒ ፅጉባን፤ መኑ እምክፈለኒ ከመ እስዐም ምድረ ኀበ ቤደ ነሶሳወ እግረ ለወለተ ዳዊት፤ መኑ እምክፈለኒ ከመ ይልክፈኒ ጽላሎተ ክነፈሃ ለወለተ ሣሕል፤ መኑ እምክፈለኒ ከመ እጹር አሳእኒሃ ለወለተ ምሕረት፤ መኑ እምክፈለኒ ከመ እትልዋ ለወለተ ብርሃን ኀበ ሖረት"*

(የሰማይ ሥርዐት በምድር ላይ ተሠራ፤ ቤተልሔምም እንደ ሰማይ ተመሰለች፤ በሚጠልቅ ፀሐይም ፈንታ በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራ ኀልፈት ጥልቀት የሌለበት አማናዊ ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጧ ወጣ፤ ክብርሃኑ ጉድለት መምላትን የሚያፈራርቅ በጨረቃ ፈንታ የድንግልናዋ ምስጋና ዘወትር የማይጉድል በኹሉ የመላ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች የተመረጠች ድንግል ማርያም ተገለጠች፤ በከዋክብት ፈንታም የብርሃን መላእክት ታዩ፤ በዚኽ ማኅበር እኖር ዘንድ ከጥበብ ሰዎች ጋራ እጅ እነሣ ዘንድ፤ ከእረኖችም ጋራ አገለግል ዘንድ፤ ከሰሎሜም (ከአዋላጇቱ) ጋራ አደንቅ ዘንድ ከመላእክትም ጋራ አመሰግን ዘንድ፤ በዚኽ ማኅበር አንድነት እንድኖር ማን በአደለኝ? ፤የተጨነቁትን የሚያድን የተስፋ ቈረጡች ተስፋ፤ የተዳደፉትን የሚያነጻ የሙታን ሕይወት የተኛበትን በረት እጅ እነሣ ዘንድ ማን ባደለኝ? ይቅርታን የምታሰጥ ብላቴና የረድኤት ክንፎቿ ጥላ ይነካኝ ዘንድ ማን ባደለኝ? ምሕረትን የምታሰጥ ብላቴና ጫማዋን እሸከም ዘንድ ማን ባደለኝ?፤ ብርሃንን ላስገኘች ብላቴና በኼደችበት እከተላት ዘንድ ማን ባደለኝ?)[144] በማለት በቤተልሔም የተደረገውን ድንቅ ምስጢር ለማየት ምን ያኽል እንደጓጓ ገልጾታል።

ይኽ ብቻ ሳይኾን የሚክያስ ትንቢት ቤተልሔም ማለት ትርጓሜዋ

[144] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ አርጋኖን ዘሰኑይ ምዕ ፀ ፈ፡፣



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ኅብስት (የእንጀራ ቤት) ማለት ነውና፤ ነቢዩ በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት "የሕይወት እንጀራ የጌታ እናት እመቤታችን በይሁዳ ከነገሠ ነገሥታት ብትበልጪ እንጂ አታንሺም፤ ወገኖቼ እስራኤል ዘነፍስን የሚጠብቁትው ንጉሥ ክርስቶስ እምኔኪ "ካንቺ"፤ ብሂ "ባንቺ" ባሕርይ ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ ይወለዳልና" ሲል የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ (ዮሐ ፮፥፴፭) ያለ ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን አማናዊ ንጉሥ ክርስቶስን የወለደቺልን የኅብስተ ሕይወት የክርስቶስ እናቱ አማናዊት ቤተልሔም የመኾኗን ምስጢር ትንቢቱ የገለጠ ነውና፤

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ምስጢሩን በአስደናቂ መልኩ ሲያስቀምጥ

*"አንቲ ውእቱ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ*
*ንጉሠ እስራኤል ዐቢይ እንተ አስተርአየ እምውስቴታ*
*ዘያበርሃ ለጥበብ ወለተለብዎ ዘይከሥታ"*

(ጥበብን የሚያበራትና ትንቢትንም የሚገልጣት፤ ታላቁ (አማናዊው) የእስራኤል ንጉሥ በውስጧ የተገለጠ የኤፍራታ ዕጣ የኾንሽ ቤተልሔም አንቺ ነሽ)[145] በማለት አማናዊት ቤተልሔም ቅድስት ድንግል ማርያምን አመስግኗታል፡፡

በኹለተኛ ደረጃም በቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢር የተራቀቀው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ከነቢዩ ሚክያስ ትንቢት በመጥቀስ ሲያመሰግናት

*"ወለሚክያስ አንቲ ፈጻሚተ ትንቢቱ*
*ዘብኪ ኮነ ለእግዚአብሔር ተረክቦቱ*
*እምአእላፍ ሐራጊት ዘይኄይስ ተሠውዖቱ"*

(ከአእላፍ ጊደሮች መሥዋት ይልቅ የርሱ መሥዋት የተሻለ የእግዚአብሔር መገኘት በአንቺ የኾነ የሚክያስ የትንቢቱ ክንውን አንቺ ነሽ)[146] በማለት ነቢዩ ሚክያስ በትንቢቱ በምዕ ፮፥፮ ላይ

*"ምን ይዤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ልምጣና በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ? የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የአንዱን ዓመት ጥጃ ይዤ በፊቱ ልምጣን? እግዚአብሔርስ በሺሕ አውራ በጎች ወይስ በእልፍ የዘይት*

[145]እንዚራ ስብሐት ገጽ 44

[146]እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 43





*ፈሳሾች ደስ ይለዋልን? ወይስ የበኵር ልጄን ስለ በደሌ የኾዴንም ፍሬ ስለ ነፍሴ ኀጢአት እሰጣለኹን? ሰው ሆይ መልካሙን ነግሮኻል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድን ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፤ ከአምላክኽም ጋር በትሕትና ትኼድ ዘንደ አይደለምን"* በማለት እነ ዳዊት፣ ሰሎሞን ያቀረቡት ንጹሕ ጠቦት፣ እነ ኢዮስያስ የሠዉት እልፍ በግ፣ ዮፍታሔ የሠዋት በኵራዊት ብላቴና ኹሉ፤ በሐዲስ ኪዳን ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የተሰፋ አበው ፍጻሜ በኾነው በራሱ መሥዋዕትነት እንዲቃለሉ (እንዲፈጸሙ) ስላደረጋቸው፤ ይኽነን ኹሉ መሥዋዕት እንዳልወደደና ይልቁንም እግዚአብሔር የሚሻው ፍርድንና ምሕረትን እንድናደርግ መኾኑን ሊቁ ከሚክያስ ትንቢት ጠቅሶ ተናግሯል (ማቴ ፲፪፥፯፤ ፱፥፲፫)፡፡

ይኸውም በብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ይቀርብላቸው የነበሩት እስራኤል ዘሥጋ፤ መሥዋዕት አቅራቢዎች ሌዋውያን ካህናት፤ መሥዋዕቱ ከእንስሳት፣ ቍርባኑ ከእኽል ሲኾን፤ ኹሉም ግዳጅ መፈጸም ያልቻሉ ፍጹም ድኅነትን ያላስጡ፤ አቅራቢዎቹም ድካም፣ ኀጢአት፣ ሞት ይስማማቸው ስለነበር አስቀድመው ለራሳቸው መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር (ዕብ ፱፥፱)፡፡

ከዚኽም የተነሣ ሌዋውያን ካህናት፣ በሚያቀርቡት መሥዋዕት መርገመ ሥጋንና መርገመ ነፍስን መሻር ስለተሳናቸው፤ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጁ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ መርገመ ሥጋንና መርገመ ነፍስን ሽሮ ዘላለማዊ ሕይወት የሚኾነንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሰጥቶናልና

*"ወለሚክያስ አንቲ ፈጻሚተ ትንቢቱ*
*ዘብኪ ኮነ ለእግዚአብሔር ተረክቦቱ*
*እምአእላፍ ሐራጊት ዘይኄይስ ተሠውዖቱ"*

(ከአእላፍ ጊደሮች መሥዋት ይልቅ የርሱ መሥዋት የተሻለ የእግዚአብሔር መገኘት ባንቺ የኾነ የሚክያስ የትንቢቱ ክንውን አንቺ ነሽ) በማለት ሊቁ ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ አስተምሯል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ኢዩኤል
## ክፍል አራት

ኢዩኤል የኹለቱ ነገድ ነቢይ ሲኾን ከ፰፻፲-፯፻፶ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንደነበር ይገመታል፤ ይኸ ነቢይ በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በስቅለት ዕለት ስለሚፈጸመው ተአምር ለሐዋርያት በ፶ኛው ዕለት መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድ የተናገረ ሲኾን በሐዋርያት ሥራም ላይ ተጠቅሷል (ኢዮ ፪፥፳፰-፴፪)፤ የሐዋ.ሥራ ፪፥፲፯-፳፩)፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጠነዋለን፡፡

### የበረከት ምንጭ

የኹለቱ ነገድ ነቢይ የነበረው ኢዩኤል በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በዘመነ ሐዲስ ስለሚገለጠው ምስጢር በምዕ ፫፥፲፰ ላይ

*"ወይከውን ይእተ አሚረ ያንጸፈጽፍ መዓር እምአድባር ወይውሕዝ ሐሊብ እምአውግር ወይነቅዕ ማይ እምኵሉ በሐውርተ ይሁዳ ወይፈለፍል ነቅዕ እምቤተ እግዚአብሔር"*

(በዚያን ቀን እንዲኽ ይኾናል፤ ተራሮች መዓርን ያንጠባጥባሉ፤ ኮረብቶችም ወተትን ያፈሳሉ፤ በይሁዳም ያሉት ፈፋዎች ኹሉ ውሃን ያጎርፋሉ፤ ከእግዚአብሔር ቤት ምንጭ ይፈልቃል) በማለት ለ፭ሺሕ ፭፻ ዘመን በረሀበ ነፍስ በጽምአ ነፍስ ስንሰቃይ ከነበርነው ከኛ ይኽነን ፍዳ ለማራቅ፤ ምግበ ርኁባን ስቴ ጽሙኣን ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ በመዓርና በወተት የሚመሰሉ ዐሠርቱ ቃላትና ወንጌልን፤ ስለ ክብራቸው በተራራና በኮረብታ በተመሰሉት በሐዋርያትና በአርድዕት እንድትነገር እንደሚያደርግና፤ ከቤተ እግዚአብሔርም በምንጭ የተመሰለ ልጅነት፣ ሥጋው ደሙ እንዲሰጠን እንደሚያደርግ የተናገረውን ትንቢት የሕይወት ውሃ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሙሉ በሙሉ ፈጽሞታልና፤





ሊቀ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ *"ወአንቲ ነዐበ ለኢዮኤል ነቅዐ በረከቱ"* (ዳግመኛም የኢዮኤል የበረከቱ ምንጭ አንቺ ነሽ)[147] በማለት ሲያብራራ በተጨማሪም በመዐዛ ቅዳሴ መጽሐፉ ላይም

*"ወምድረ አንቅዕቱ ለኢዩኤል ነቢየ ኤልዳ ወመዓረ ጺቃውዕ ዘይሁዳ ምስለ ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነቅዐ አእምሮ ወጥበብ ፈለገ ጥዒና ወሕይወት"*

(የኤልዳ ነቢይ የኢዩኤል የምንጩ ቦታ የይሁዳ የመዓር ወለላ የዕውቀት መፍለቂያ የሕይወት የደኅንነት መገኛ ከሚኾን ልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ በረድኤት ነዩ)[148] በማለት ምስጢሩን እንደወርቅ አንክብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ ተናግሮታል፡፡

በሀገራችን ከነበሩ የነገረ ማርያም ሊቃውንት ኍልቈ መኳንንት ከሚኾኑት ሊቃውንት መካከል አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ ይኽነን የኢዮኤልን ትንቢታዊ ኀይለ ቃል ሲያመሰጥሩ

*"ማዕረረ ትንቢት ማርያም ዘዘመነ ጽጌ እንግዳ*
*ወዘመነ ፍሬ ጺጋብ ዘዓመት ረኃብ ፍዳ*
*ብኪ ተአምረ ዘይቤ ኢዮኤል ነቢየ ኤልዳ*
*ያንጸፈጽፍ እምአድባሪሁ ወእምአውግሪሁ ለይሁዳ*
*ጺቃውዐ መዓር ቅድው ወሐሊብ ጸዓዳ"*

(በዐዲሱ የአበባ ዘመን (ወራት) የረሃብ ዘመን ለውጥ በኾነው በጽጋብ የፍሬ ዘመን የተገኘሽ የትንቢት አዝመራ ማርያም ሆይ፤ የኤልዳ ነቢይ ኢዩኤል ከይሁዳ ተራራዎችና ኮረብቶች ያማረ የጣፈጠ ማርና ነጭ ወተት ያፈሳል ብሎ የተናገረው በአንቺ ታወቀ)[149] በማለት የኢዩኤል ትንቢት የታወቀባት መኾኗን አስተምረዋል፡፡

[147] ዝክ. ከማሁ ገጽ 44
[148] መዐዛ ቅዳሴ፣ ቍ ፴፱
[149] አባ ጽጌ ድንግል፣ ማሕሌት ጽጌ ቍ፳፮



www.ethiopianorthodox.org

## ነገረ ማርያም በትንቢተ አብድዩ
## ክፍል አምስት

አብድዩ ለነቢይነት የተጠራው በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ፰፻፶-፰፻፵፫ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የተጠራ ሲኾን ነገዱ ከነገደ ኤፍሬም የኾነና፤ ኤልዛቤል ነቢያትን ካህናትን ስታስፈጅ ሃምሳውን በአንድ ዋሻ ሃምሳውን በአንድ ዋሻ አድርጎ ልብስ ቀለብ እየሰጠ ይረዳቸው የነበረ ነበር (፩ነገ ፲፰፥፲፫) ከአክአብ ሞት በኋላም የአካዝያስ ቢትወደድ ኾኖ ከኖረ በኋላ ነቢዩ ኤልያስን ተከትሎ ኼዷል፤ እኔም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጬዋለኹ፡፡

### የአብድዩ ተራራ

በኢዮራም ዘመን ለነቢይነት የተጠራው ይኽ አብድዩ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በምዕ ፩፥፲፯ ላይ

*"ወይከውን መንግሥት በደብረ ጽዮን ወመድኀኒት በኢየሩሳሌም"*

(መንግሥት በጽዮን ተራራ መድኀኒት በኢየሩሳሌም ይኾናል)[150] በማለት አስቀድሞም በክቡር ዳዊት መዝሙር ላይ "የዮሴፍንም ድንኳን ተዋት፤ የኤፍሬምንም ወገን አልመረጠውም የይሁዳን ወገን ግን መረጠ ፤የወደደውን የጽዮንን ተራራ፤ መቅደሱን እንደ አርያም ሠራ፤ ለዘላለምም በምድር ውስጥ መሠረታት" (መዝ ፸፯፥፷፯-፷፱) ብሎ ከነገደ ዮሴፍና ከነገደ ኤፍሬም መወለድ እንዳልፈቀደ፤ ይልቁንም በንጽሕና በቅድስና ክብሯ እንደ አርያም ከፍ ከፍ ያለችና፤ ቃል ኪዳኗ አምባ መጠጊያ በመኾኑ ምክንያት በጽዮን ተራራ ከተመሰለች ከነገደ ይሁዳ ከተወለደች አማናዊት መቅደስ ከቅድስት ድንግል ይወለድ ዘንድ መምረጡን እንደተናገረ ኹሉ፤ አብድዩም መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት ተመሳሳይ ትንቢትን ተናግሯል፡፡

ዳግመኛም መሲሕ ጌታ የሰላም አለቃ የተባለ ርሱን በመውለዷ ምክንያት ኢየሩሳሌም (ሀገረ ሰላም) ከተባለች ከቅድስት ድንግል ተወልዶ፤ ለዓለሙ ኹሉ ድኅነትና ሰላም በቀራንዮ ተሰቅሎ አብድዩ የተናገረውን ትንቢት ፈጽሞታልና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ

[150] ሙሉ ንባቡ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲዘለል በግእዙ ላይ ግን ንባቡ ይገኛል፡፡



www.ethiopianorthodox.org



*"ደብረ ጽዮን አንቲ ለአብድዩ ደብረ መድኀኒቱ*

*ዘእምኔኪ ኮነ ለእግዚአብሔር አስተርእዮቱ"*

(የእግዚአብሔር መገለጡ በአንቺ የኾነ የአብድዩ የመድኀኒት ተራራ፤ የጽዮንን ተራራ አንቺ ነሽ)[151] በማለት አስደናቂ የነገረ ማርያምን ትምህርትን አስተምሯል፡፡

## ነገረ ማርያም በትንቢተ ዮናስ
## ክፍል ስድስት

ነቢዩ ዮናስ ከራሱ መጽሐፍ ውጪ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጠቀሰ ነቢይ ነው (፪ ነገ ፲፬፥፳) ፤ ዮናስ የእስራኤል ነቢይ ሲኾን የነበረበትም ዘመን በዳግማዊ ኢዮርብአም ዘመነ መንግሥት ፰፻፳፭-፯፻፹፬ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው፤ ከአሞጽ ጋርም በዘመን ሲገናኝ ዮናስ ያስተማረው ከምድረ እስራኤል ውጪ በነነዌ ስለኾነ ነቢየ አሕዛብ ይባላል፤ እኔም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጬዋለኹ፡፡

### የዮናስ ጠባቂ

በዮናስ ጊዜ ልዑል እግዚአብሔር "ተነሥተኽ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ኺድ፤ ክፋታቸውም ወደፊቴ ወጥቶአልና፤ በርሷም ላይ ስበክ" ብሎ ቢያዘው ርሱ ግን በእንቢተኛነት ወደ ተርሴስ ለመኼድ በመርከብ ተጭኖ ሲጓዝ እግዚአብሔር ግን ታላቅ ማዕበል አምጥቶ መርከቢቱ ልትሰበር ስትቃረብ ዮናስ ከተኛበት ነቅቶ ባሕሩንና የብሱን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን እንደሚያመልክ ለተሳፋሪዎቹ ነግሮ ከእግዚአብሔር ፊት ሊኰበልል ስላሰበ ይኽ ኹሉ እንደመጣ ነግሮአቸው አንሥተው ወደ ባሕር እንዲጥሉት ተማጸነ (ዮና ፩፥፩-፲፬)፡፡ እነርሱም ወስደው ወደ ባሕር ሲወረውሩት የታዘዘ ዓሣ ዐንበሪ ውጦት ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ኾድ አድሮ ከወጣ በኋላ ወደ ነነዌ በመኼድ አስተምሮ ሕዝቡም ንስሓ ገብተው ሊድኑ ችለዋል (ዮና ፫፥፩-፲)፡፡

ይኽ ዮናስ በዓሣ ኾድ ውስጥ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት አድሮ እንደወጣ ኹሉ አካላዊ ቃል ክርስቶስም ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተወልዶ፤ ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር

[151] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ እንዚራ ስብሐት ገጽ 43

ምድርን በኪደተ እግሩ ቀድሶ ወንጌልን አስተምሮ ለቤዛ ዓለም በመስቀል ተሰቅሎ፤ በሞቱ ሞተ ነፍስን ሽሮ፤ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በመቃብር አድሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ የመነሣቱ ምሳሌ እንደኾነ ራሱ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ ፲፪ ፡ ፵ ላይ "ዮናስ በዓሣ ዐንበሪ ኾድ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት እንደነበረ እንዲኹ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል" በማለት አስተምሯል።

በመኾኑም ቀድሞ ነቢዩ ዮናስ በምሳሌነት የገለጸውን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስተ ቅዱሳን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታልና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በአርጋኖን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ

*"ዮናስ ወልደ አማቱ ተአዘዘ ከመ ይስብክ ለሰብአ ነነዌ በእንተ ሙስናሃ ለሀገር፤ ወተኀጥአ እምገጸ እግዚአብሔር ወዐርገ ሐመረ ምስለ እለ ይነግዱ ባሕረ ከመ ይሑር ብሔረ ተርሴስ ወአንሥአ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ ማዕበለ ባሕር ግሩመ ወወረውዎ ውስተ ልበ ባሕር፤ ወአዘዘ እግዚአብሔር ለዐንበሪ ዐቢይ ከመ የኀጦ ለዮናስ ወነበረ ዮናስ ውስተ ከርሡ ዐንበሪ ሠለስ መዋዕለ ወሠለስ ለያልየ ወቲያ ዐንበሪ ውስተ ሐይቀ ባሕር ዘየወለ ነነዌ፤ ወሰበከ ሎሙ ዮናስ ለሰብአ ነነዌ ከመ ይነስሐ ወነስሐ ሰብአ ሀገር በስብከቱ ወድኀኑ እመቅሰፍት ዘምድር ወኢድኀኑ እመቅሰፍት ዘበሰማይ፤ ወወልድኪሰ ነበረ ውስተ ከርሠ ምድር ሠለስ መዋዕለ መሠለሰ ለያልየ ወሰበከ ሎሙ ግእዛነ ለፂዉዋን ወአድኀኖሙ እምእደ ሲኦል ወእሞት ባልሐሙ"*

(የአማቱ ልጅ ዮናስ ስለ ሀገሪቱ ጥፋት የነነዌን ሰዎች ያስተምር ዘንድ በታዘዘ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊት ኰብልሎ ጠፋ፤ ወደ ተርሴስ ሀገር ሲኼድ በባሕር ከሚኼዱ ጋራ ወደ መርከብ ወጣ፤ እግዚአብሔርም የሚያስፈራውን ማዕበል ስለ አስነሣ ወደ ባሕር ወረወሩት፤ እግዚአብሔርም ታላቁን ዐንበሪ አዘዘው፤ ዮናስን ይውጠው ዘንድ፤ ዮናስም በዐንበሪው ኾድ ውስጥ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት ተቀምጦ ዐንበሪው በነነዌ አውራጃ በምትገኝ የባሕር ወደብ ላይ ተፋው፤ ዮናስም የነነዌ ሰዎች ይጸጸቱ ዘንድ ሰበከላቸው የሀገሪቱ ሰዎችም በስብከቱ ተጸጽተው ከምድራዊ መቅሰፍት ዳኑ ከሰማያዊ መቅሰፍን ግን መዳን አልቻሉም፤ የአንቺ ልጅ ግን ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በመቃብር ውስጥ ኖሮ ለምርኮኞች ነጻነትን ሰበከላቸው፤ ከሲኦል እጅም ነጥቆ ከሞት አዳናቸው)[152] በማለት ፈጣሪያችን ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የፈጸመውን

[152] አርጋኖን ዘንሙስ ምዕ ፳፥፺፮-፺፱





ድኅነት ገልጾታል።

በተጨማሪም ነቢዩ ዮናስ በዚያ በጨለማ በዓሣ ዐንበሪ ኾድ ውስጥ ሳይሞት ተጠብቆ እንደወጣ ኹሉ፤ በርሷ ወላዲተ አምላክነት በልጇ የባሕርይ አምላክነት የምናምን ኹላችን እናት፤ አማላጅ ትኾነን ዘንድ በመስቀል ሥር በአደራ በተቀበልናት በእናታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነትና በልጇ ቸርነት ከሞተ ነፍስ ተጠብቀን ሲኦል ከመውረድ የምንድን ነንና፤ ታላቁ የነገረ ማርያም መምህር አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*"ዓቃቢተ ነፍሱ ለዮናስ ወእምግበ ሲኦል መጣቂቱ"* (የዮናስ የነፍሱ ጠባቂና ከሲኦል ጕድጓድም የምታወጪው አንቺ ነሽ)[153] በማለት ዮናስን በምእመን በመመሰል አስተምሯል።

## ነገረ ማርያም በትንቢተ ናሆም
## ክፍል ሰባት

ነቢዩ ናሆም እንደ ዮናስ በነነዌ ላይ ትንቢት የተናገረ ነቢይ ሲኾን በዮናስ የተነገረው የነነዌ ጥፋት ከናሆም በኋላ ፮፻፲፪ ቅደመ ልደተ ክርስቶስ ተፈጽሟል፤ ናሆም ለነቢይነት የተጠራው ፯፻፴ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነበር፤ እኔም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጬዋለኍ።

### የናሆም መድኅኒት

ከዐሥራ ኹለቱ ደቂቀ ነቢያት አንዱ ነቢዩ ናሆም በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በምዕ ፫ ፡ ፲፰-፲፱ ላይ

*"አሕዛብኽም በተራሮች ላይ ተበትኗል፤ የሚሰበስበው የለም ስብራትኽ አይፈወስም፤ ቍስልኽም ክፉ ነው፤ ወሬኽንም የሚሰሙ ኹሉ እጃቸውን በአንተ ላይ ያጨበጭባሉ፤ ክፋትኽ ኹል ጊዜ ያላለፈችበት ሰው ማን ነውና?"* በማለት ለጊዜው በነነዌና በባቢሎን ላይ የሚደርሰውን መከራ ፍጻሜው ግን ነፍሳት ለ ፭ሺ.ሕ ፭፻ ዘመን በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ሲኦል ተፈርዶባቸው በክፉው በዲያብሎስ የሚደርስባቸውን ጽኑ መከራ ያሳየ ነበር።

[153] ዝክ. ኪሚዮ ገጽ 43



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱ ላይ "ስንጠአት ሞተን በጽድቅ እንድንኖር ርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችኁ፤ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፤ አኹን ግን ወደ ነፍሳችኁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል" (፩ ጴጥ ፪፥፳፬-፳፭) በማለት እንደተናገረ፤ በዚኽ ፭ሺሕ ፭፻ ዘመን ውስጥ የሰው ልጆች ከእውነተኛ ሕይወታቸው ከፈጣሪያቸው ተለይተው ቍስለ ሕዘናቸው በስፋበት ወቅት፤ መርገመ ሥጋችንና መርገመ ነፍሳችንን ሽሮ፤ ቍስለ ሐዘናችንን አጥፍቶ ወደ ቀድሞው ደስታችን የመለሰን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በኀቱም ድንግልና ሀንሳ በኀቱም ድንግልና ወልዳልናለችና፤ ታላቁ ሊቅ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ "ወፈዋሲተ ቍስሉ ለናሆም" (የናሆምን ቍስል የምታድን)[154] በማለት አመስግኗታል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም መድኀኒታችንን ወልዳ ያስገኘችልን ምክንያተ ድኂን ርሷ ናትና በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ "ርጢነ ቍስሉ ለናሆም" (የናሆም የቍስሉ መድኀኒት አንቺ ነሽ)[155] በማለት እመ መድኀኒት ቅድስት ድንግል ማርያምን አመስግኗታል።

## ነገረ ማርያም በትንቢተ ዕንባቆም
## ክፍል ስምንት

ዕንባቆም ከ፮፻፰-፭፻፺ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በዘመነ ኢዮአቄም ያስተምርና ትንቢትም ይናገር የነበረ ነቢይ ነው፤ ዳንኤልና ሕዝቅኤል በባቢሎን ምርኮኞችን ሲያስተምሩ ኤርምያስና ዕንባቆም በኢየሩሳሌም ትሩፋንን ያስተምሩ ነበር፤ ትውልዱም ከነገደ ስምዖን ሲኾን አካላዊ ቃል ከነገደ ይሁዳ ከተገኘች ከቅድስት ድንግል ማርያም በእንስሳት መካከል በበረት ውስጥ እንደሚወለድ ተገልጾለት የተናገረ ነቢይ ነው፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጬዋለኍ።

### የፋራን ተራራ

ይኸ ነቢይ ዕንባቆም በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጁ ፭ሺሕ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ከቅድስት

[154] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፮

[155] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 43



www.ethiopianorthodox.org



ድንግል ማርያም ተወልዶ እንስሳት እስትንፋሳቸውን ሲገብሩለት አስቀድሞ ተገልጾለት በአድናቆት በጸሎቱ በትንቢቱ በምዕ ፫፥፩-፫ ላይ

"እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራህኩ" (አቤቱ ድምፅኽን ሰምቼ ፈራኍ) በማለት ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የመወለዱን ነገር ሰምቶ እንደፈራ ከገለጸ በኋላ፤ "ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ" (ሥራኽንም አይቼ አደነቅኍ) በማለት ዘመኑ ሲፈጸም የአብ የባሕርይ ልጁ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከእመቤታችን ያለ አባት ሲወለድ በራእይ አይቶ የድኅነት ሥራውን እንዳደነቀ ገልጿል።

በእውነት ነቢዩን ያስደነቀው የጌታ ምስጢረ ልደቱ ርሱን ብቻ ሳይኾን ኹሉን የሚያስደንቅ ነው፤ የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት ይኸንን የክርስቶስን ልደት በአድናቆት ሲገልጽ "አ ለዝንቱ ልደት ዘኮነ ውስተ ምድር ወመፀዐሁ ውስተ አርያም ወይሴብሕዎ በዝየ በቃል ዓቢይ"

(በዚኽ ዓለም ለተደረገው ምስጋናው ሰማያዊ ለሚኾን መላእክት ለሚያመሰግኑት ለዚኽ ልደት አድናቆት ይገባል) በማለት አስተምሯል።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግም ቅድመ ዓለም ከአብ ያለእናት የተወለደው ወልደ እግዚአብሔር በኋለኛው ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን በአድናቆት ሲገልጽ

*"He is clothed in flame, girded in swaddling clothes..."* (ርሱ እሳትን ለብሷል፤ በመጠቅለያ ጨርቅም ተጠቅልሏል፤ ግን ደግሞ ከመታወቅ በላይ ነው፤ በዙፋን ላይ ተቀምጧል እንዲኹም በግርግም ተኝቷል፤ ግን ደግሞ አይመረመርም፤ በኪሩቤል ገርባ ላይ ተቀምጧል እንዲኹም ጉልበቶች ተሸክመውታል፤ እናም በዚያ ምክንያት ርሱ ታላቅ ነው፤ የተፈጠሩ ፍጥረታትን የሚያንቀሳቅሳቸው ርሱ ሥጋን ተዋሕዷልና እነርሱ ድንቁን ይናገራሉ፤ ርሱ ወገኖችን ያኖራቸዋል፤ ርሱ እንዲኹ ወተት ይጠባል፤ ርሱን ይረዳው (ያውቀው) ዘንድ ማን ይችላል? ፤ ርሱ ዝናብን ያዘንባል ርሱ ደግሞ ጡት ይጠባል፤ እናም ድንቁን ተመልከቱ፤ ርሱ ልዑል እና ግሩም ነው የሚቀኙለት ነው እንሆ ድንቁ፤ ሰማይ ለርሱ እጅግ ያንሰዋል እናም ርሱ ማደሪያ ፈለገ፤ እነሆ እንዴት ያለ ጸጋ ነው፤ ሱራፌል ራሳቸውን ይሸፍናሉ፤ ዮሴፍ ይሰግዳል አንዳች ድንቅ በዚያ አለና፤ ሥልጣናት ተዘርግተዋል ሰዎችም ደካሞች ናቸው፤ ያስተውል ዘንድ ግን ማን ይችላል?)[156] በማለት ፈጽሞ ለመመርመር የማይቻል አድናቆት ብቻ የሚገባው መኾኑን አስተምሯል።

[156] Jacob of Serugh, on Nativity P 30

ነቢዩ ዕንባቆምም በመቀጠል "በማእከለ ክልኤ እንስሳ ርኢክዮ" (በኹለት እንስሳ መኻከል አየኹኽ) በማለት ጌታ ከእመቤታችን በቤተልሔም በእንስሳት በረት በላምና በአህያ መኻከል የመወለዱን ነገር አስቀድሞ ገልጾታል።

በጥልቅ የነገረ ማርያም ዕውቀቱ የሚታወቀው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ይኽነን የዕንባቆም ትንቢት ሲያብራራ

"ዕንባቆም ወልደ ዳኮር ሰምዐ ድምፀ ርደቱ ለወልድኪ ወፈርሀ እንዘ ይብል በልቡ አይ መካን ያገምሮ ወርእየ ግብሮ በትሕትና ዕጹብ ዘበአጽርዖት ጥብሉል ወበዲበ ጎል ስኩብ ወአንከረ በማእከለ እንስሳ ክልኤ፤ ወርእዮ ከመ ቀርበ ዓመቲሁ አእመረ ወከመ በጽሐ ጊዜሁ ለበወ ዝንቱ ነቢይ ምሉአ መንፈስ ፈርሀ በነሲናሁ ወአንከረ በመንፈሱ፤ ወአንቲሰ ጸርኪዮ በክርሥኪ"

(የዳኮር ልጅ ዕንባቆም የልጅሽን የመውረዱን ድምፅ ሰምቶ ፈራ፤ በልቡ እንዲኽ ሲል እንደምን ያለ ቦታ ይወስነዋል? በኹለት እንስሳ መኻከል በጨርቅ ተጠቅልሎ በበረት ተኝቶ በሚያስደንቅ ትሕትና ያደረገውን ሥራ አይቶ አደነቀ፤ ዘመኑም እንደቀረበ አይቶ ዐወቀ፤ ጊዜውም እንደደረሰ ተገነዘበ፤ መንፈስ ቅዱስን የተመላ ይኽ ነቢይ በሐሳቡ ፈራ፤በመንፈሱም አደነቀ፤ አንቺ ግን በዓለሙ ኹሉ የመላውን ጌታ በማሕፀንሽ ተሸከምሺው)[157] በማለት ተርጕሞታል።

በተጨማሪም ነቢዩ ዕንባቆም በመቀጠል አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከነገደ ይሁዳ ከተወለደች ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለመወለዱ

"እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእምአህጉረ ይሁዳ" (እግዚአብሔር ከቴማን ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ከይሁዳም አውራጃዎች ይመጣል) በማለት የተናገረው ትንቢት በእውነት ተፈጽሚልና፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ

"ወደብረ ፋራን ዘዕንባቆም" (ፋራን የተባለች የዕንባቆም ተራራ አንቺ ነሽ)[158] በማለት ሲያመሰግናት፤ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ "ወለዕንባቆም ሰዋስወ ጸሎቱ" (የዕንባቆምም የጸሎቱ መሰላል አንቺ ነሽ)[159] ሲል ነቢዩ ዕንባቆም በጸሎቱ ላይ የተናገረው ትንቢት የተፈጸመባት መኾኑን አስተምሯል።

[157] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ አርጋኖን ዘንሙስ ፻፹፯

[158] አባ ሕርያቆስ፣ ቅዳሴ ማርያም ቊ ፴፰

[159] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ እንዚራ ስብሐት ገጽ 43





ሊቃውንትም የነቢያትን ትንቢቶች በተረጐሙበት መጽሐፈ ፀሐይ በሚለው መተርጕመ መጻሕፍት ላይ ይኽነን የዕንባቆምን ትንቢት ሲተረጕሙ

"ወካዕበ ይቤ እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእምአህጉረ ይሁዳ ከደኑ ሰማያተ ሥኑ ወመልአ ምድረ ስብሐቲሁ ወጸዳሉኒ ከመ ብርሃን ውእቱ፤ ቴማንሰ ይተረጐም በየማነ አብ ዘወጽአኒ እምህየ ወልድ ውእቱ፤ ደብረ ፋራንኒ ትተረጐም በማርያም ድንግል ዘወለደቶ ለቃለ አብ"

(ዳግመኛም እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል፤ ቅዱሱም ከቴማን ተራራና ከይሁዳ አውራጆች፤ ደም ግባቱ ሰማያትን ሸፈነ፤ ጌትነቱም ምድርን መላ፤ጸዳለ ረድኤቱም እንደ ብርሃን ነው አለ፤ ቴማንም በአብ ቀኝ ይተረጐማል፤ ከዚያም የወጣው ወልድ ነው፤ የፋራን ተራራም የአብ አካላዊ ቃልን በወለደች በድንግል ማርያም ትተረጐማለች)[160] በማለት ገልጸውታል።

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ሶፎንያስ
## ክፍል ዘጠኝ

ነቢዩ ሶፎንያስ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ከ፮፻፴፱-፮፻፳፰ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲኾን፤ ይኸውም ከኢየሩሳሌም የጥፋት ቀን ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጠነዋለን።

### የሶፎንያስ ራእይ

በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የነበረው ነቢዩ ሶፎንያስ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በትንቢቱ በምዕ ፩፥፯ ላይ

"ናሁ አስተዳለወ እግዚአብሔር መሥዋዕቶ ወቀደሶሙ ለኅሩያኒሁ" (እነሆ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን አዘጋጀ፤ የመረጣቸውንም ቀደሳቸው) በማለት ፩ሺሕ ፭፻ ዘመን ሲፈጸም አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ለዓለም መሥዋዕትነት ቢዛ ለመኾ በቀራንዮ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን ማዳኑንና ሥጋውን ቈርሶ ደሙን

[160] [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

አፍስሶ የተጠመቀ ምእመናንን የሚቀድስ፣ የሚያከብር መኾኑን የተናገረውን ትንቢት ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ከቅድስተ ቅዱሳን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታልና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ *"ፈጻሚተ ራእዩ ለሶፎንያስ"* (የሶፎንያስ ራእይ ፈጻሚ አንቺ ነሽ)[161] በማለት አመስግኗታል።

ክብር ይግባውና ባለቤቱ ክርስቶስ ኀሙስ ማታ በአልዐዛር ቤት የመረጣቸው ሐዋርያት አብረውት ሳሉ ኅብስቱን ወይኑን ለውጦ እንደሰጣቸው በማር ፲፬፥፳፪-፳፬ ላይ እንደተጻፈ *"እንጀራውን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ሰጣቸውና እንካችሁ ይኽ ሥጋዬ ነው አለ፤ ጽዋዉንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው ኹሉም ከርሱ ጠጡ፤ ርሱም ይኽ ስለ ብዙዎች የሚፈስስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ ነው"* በማለት ሥጋውን በልተን ደሙን ጠጥተን የዘላለም ሕይወትን እናገኝ ዘንድ የሰጠንን የሕይወት ምግብ የሕይወት መጠጥ ክርስቶስን ወልዳ አስገኝታልናለችና

*"ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዐብየኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበአማን"* (ማርያም ሆይ ስለዚኽ ነገር እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን እውነተኛውን መብልን እውነተኛውን የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናልና)[162] እያልን እናመሰግናታለን።

ነቢዩ ሶፎንያስ እንደተናገረው አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተወልዶ የሚቀበሉትን ለመቀደስ አማናዊ መሥዋዕት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ሰጥቶናልና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በሥርዐተ ቅዳሴዋ ላይ በካህኑ አማካይነት

*"አአምን አአምን አአምን ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋው ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ እምእግዝእተ ኵልነ ቅድስት ድንግል በክልኤ ማርያም ወረሰዮ አሐደ ምስለ መለኮቱ ዘእንበለ ቱስሕት ወኢትድምርት ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ ወኮነ ሰማዕተ በስምዕ ሠናይ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ ወመጠዎ በእንቲኣነ ወበእንተ ሕይወተ ኵልነ"*

(አምናለኹ አምናለኹ አምናለኹ በኹለት ወገን ድንግል ከምትኾን ከኹላችን እመቤት ከቅድስት ማርያም የነሣው የጌታችንና

[161] ዝኒ ከማሁ ገጽ 43

[162] አባ ሕርያቆስ፣ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፬



www.ethiopianorthodox.org



የአምላካችን የመድኀኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይኽ እንደኾነ፤ ያለመቀላቀልና ያለትድምርት ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር አንድ ያደረገው፤ በጴንጤናዊው ጲላጦስም ዘንድ ባማረ ምስክርነት ምስክር የኾነ፤ ስለ እኛና ስለ ኹላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው)[163] በማለት እምነቷን ትገልጻለች።

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ሐጌ
## ክፍል ዐሥር

ነቢዩ ሐጌ በባቢሎን የተወለደ ሲኾን ከመገኛመሪያዎቹ ከባቢሎን ምርኮ ተመላሾች ጋር የመጣና ከምርኮ መልስ በኋላም የነበረ ነቢይ ነው፤ ሐጌና ዘካርያስ ከምርኮ መልስ በኋላ የፈረሰውን ቤተ መቅደስ እንዲታነጽ ሕዝቡን ያተጉ ነበር፤ ኹለተኛው ቤተ መቅደስ ፭፻፳-፭፻፲፮ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲሠራ ያን ጊዜ ነቢዩ ሐጌ ዋና ረዳት ነበር (ሐጌ ፩፥፲፬፤ ዕዝ ፮፥፩)፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች እስቀምጬዋለኍ።

### የሐጌ ሽልማት

እስራኤላውያን በባቢሎን በምርኮ መከራ ላይ እያሉ የፈረሰውን ቤተ መቅደስ በማሰብ፤ ለእግዚአብሔር ከባቢሎን ብታወጣን ቤተ መቅደሱን ሳንሠራ የግል ቤታችንን አንሠራም ብለው የተሳሉትን ስለት ከባቢሎን ሲወጡ በመዘንጋት ቤታቸውን እየሠሩ ቤተ መቅደስንም ለመሥራት ጊዜው አይደለም እያሉ ዝም ብለው ቢቀመጡ እግዚአብሔር በነቢዩ ሐጌ ዐድሮ ገሥጿቸዋል።

ቃሉም ይኽ ነበር፤ "በውኑ ይኽ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችኍ በተሸለሙ ቤቶቻችኍ ለመኖር ጊዜው ነውን? አኹንም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲኽ ይላል፦ ልባችኹን በመንገዳችኍ ላይ አድርጉ፤ ብዙ ዘራችኍ ጥቂትም አገባችኍ፤ በላችኍ ነገር ግን አልጠገባችኹም፤ ጠጣችኍ ነገር ግን አልረካችኹም፤ ለበሳችኍ ነገር ግን አልሞቃችኹም፤ ደመወዙን የተቀበለ ሰው በቀዳዳ ከረጢት ያደርገው ዘንድ ደመወዙን ተቀበለ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲኽ ይላል፤ ልባችኹን በመንገዳችኍ ላይ አድርጉ፤ ወደ ተራራው ውጡ፤ እንጨትንም አምጡ ቤቱንም ሥሩ እኔም በርሱ ደስ ይለኛል፤ እኔም እመሰገናለኍ ይላል

[163] [illegible]

እግዚአብሔር" (ሐጌ ፪፥፰)።

በዚኽም አምላካዊ ትእዛዝ የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል፤ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር በመኾን የአምላካቸውን የሠራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን ቤት ሠርተዋል (ሐጌ ፩፥፫-፰)።

ነቢዩ ሐጌም በመንፈስ እግዚአብሔር በመቃኘት በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተወልዶ በኋለኛዋ ቤተ መቅደስ አንጻር በወርቅ በብር ያይደለ በገዛ ደሙ ስለሚመሠርታት፤ ልጅነት፤ ሥጋው ደሙ ስለሚሰጥባት፣ የሰላም ወንጌል ስለሚነገርባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ክብር በምዕ ፪፥፰-፱ ላይ

*"ዚአየ ውእቱ ወርቅ ወብሩር ይቤ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ወይኄይስ ትርሲቱ ለዝንቱ ቤት ደኃሪ እምቀዳሚ ይቤ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ፤ ወእውህብ ሰላመ ለዝንቱ ብሔር ይቤ እግዚብሔር ዘኵሎ ይመልክ"*

(ብሩ የእኔ ነው ወርቁም የእኔ ነው ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ከፊተኛው ይልቅ የዚኽ የኋለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ በዚኽም ስፍራ ሰላምን እሰጣለኊ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር) በማለት የተናገረውን ትንቢት አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታልና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*"ወለሐጌ ትርሲተ ቤቱ"* (የሐጌም የቤቱ ሽልማት ጌጥ አንቺ ነሽ)[164] በማለት አመስግኗታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱ በ፩ጴጥ ፩፥፲፱ ላይ *"ከአባቶቻችኊ ከወረሳችኹት ኑሯችኊ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይኾን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችኊ ታውቃላችኊ፤ ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ"* በማለት ክቡር በኾነው በክርስቶስ ደም የተዋጀን እንደኾንና፤ ነቢዩ ሐጌም እንደተናገረው በወርቅ በብር ከኾነው ከበፊቱ ይልቅ በደመ ክርስቶስ የተመሠረተችው የቤተ ክርስቲያን ክብር እንደሚበልጥ መስክሯል።

ነቢዩ ሐጌ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ *"ከፊተኛው ይልቅ የዚኽ የኋለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር"* በማለት ራሱ ባለቤቱ ልዑል እግዚአብሔር ዘመኑ ሲፈጸም

[164] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 43



www.ethiopianorthodox.org



ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ፤ ቤተ ክርስቲያንን በደሙ እንደሚመሠረት የተናገረው ትንቢት በእውነት ፍጻሜውን አግኝቷልና፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ምዕ ፳፥፳፰ ላይ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ኹሉና ስለራሳችኊ ተጠንቀቁ" በማለት ታላቅ ትምህርትን አስተምሯል።

በመኾኑም ትውልድ ኹሉ ብፅዕት የሚላት ቅድስት ድንግል ማርያም፤ በክቡር ደሙ ፈሳሽነት የተወጃጀንና፤ የሲኦል ደጆች ሊያነዋውጿት የማይችሉትን ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የመሠረተልን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳ አስገኝታልናለችና፤ ክርስቲያኖች በመላ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበን የልጇን የባሕርይ አምላክነት የርሷን ዘላለማዊ ድንግልናና ወላዲተ አምላክነቷን ለዘላለም ስንመሰክርላት እንኖራለን።

ይኽነን የቤተ ክርስቲያን ልዩ ምስጋና ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በአርጋኖን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ሲገልጸው

*"ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አመተ እንተ ግዕዛት በጸዳዐተ ወልድኪ ወሕሥምት እንተ ሠናየት በሞተ በኵርኪ፤ ትዌድሰኪ ቤተ ክርስቲያን መካን እንተ ፈረየት በዕፀ መስቀሉ ለዋሕድኪ ወርስሕት እንተ ነጽሐት በደመ ፍሬ ከርሥኪ፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕዝንት እንተ ተናዘዘት በትንሣኤሁ ለፍቁርኪ ወትሕት እንተ ተለዐለት በዕርገቱ ለሠርጸ ድንግልናኪ፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በማየ ገቦ ወልድኪ ተጠሚቃ ወደመ ርግዘቱ ተንቲማ፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘተመርዐዋ ወልድኪ ዐማኑኤል በግዐ ለእግዚአብሔር፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ተሰምየት ዕምርተ አሐተ ምስለ ዘወለድኪዮ ወእንተ ኮነት አሐደ አባለ ምስለ ዘሐፀንኪዮ፤ ትዌድሰኪ ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ሰቢሓ በልሳን ወየቢባ በከናፍር፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠፊሓ በአእዳው ወአፅሒሳ በአእጋር፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወትትፌሣሕ ብኪ ወትጼውዖሙ፡ ለውሉዳ ከመ ይስግዱ ታሕተ መከየደ እግርኪ፤ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስትያን ወትሰግድ ለኪ ወለተ ኦሕዛብ ለወለተ እስራኤል እስመ በጸጋ ወልድኪ ኮነት እስራኤላዊተ፤ እስመ ውእቱ ተስሐ ዕበዮ በትሕትናሃ ወትሕትናሃ ተስሐ ውስተ ዕበዩ እስመ አዕምዚኣሃ ሞተ ነሥአ ወአምዚኣሁ ሕይወተ*

*ጸገዎ ዘበአፍቅሮታ ወረደ ታሕተ ወኢኀፈረ ከዊነ ከማነ ዘእንበለ ኀጢአት ባሕቲታ፤ ደክመ ወሐመ ወርኀበ ወጸምዐ፤ ተሰቅለ ወሐመ ወወረዶተ ምራቀ ርኩሳን ተወክፈ ወጥዕመ ሞተ በሥጋ ዘንተ ኵሎ ኮነ በእንቲኣሃ ምንትኑ ዘኢያፈቅራ ነፍሶ ጥቀ ኢምህክ እምኔሃ፤ ወበትንሣኤሁ ከፈላ ሕይወተ ዘለዓለም ወበዕርገቱ አልዐላ ወረሰያ ልጽቅተ ለመንግሤሁ ወአቅረባ መባአ ለእግዚአብሔር አቡሁ፤ ወበእንተዝ ትዌድሰኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወትሰግድ ለኪ በውዕይ ፍቅር በእንተ ፍቅረ ወልድኪ ዘተሠውጠ ውስተ ልባ ወኢይትኀደግ ለዝሉፉ ዝክረ ስሙ እምውስተ አፉሃ፤ ኦ ድንግል፣ ኦ ንጽሕት፣ ኦ ድንግል፣ ኦ ቡርክት፣ ኦ ቅድስት፣ ኦ ኅሪት፣ ስብሐተ ድንግልናኪ መልአ በኵለሄ ወውዳሴ ዚኣኪ ሰፈፈ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም፤ ባሕረ ውቅያኖስ ውሱን በድንጋጊሁ ወባሕረ ሐኖስኒ ዐቅም ቦ በአምጣኒሁ ወለስብሐተ ዘኣኪሰ አልቦቱ ዐቅም፤ ወአልቦቱ መስፈርት፣ ወአልቦቱ ወሰን፣ ወአልቦቱ ማኅለቅት ወኀሊናኒ ኢይክል አግምሮቶ ወልሳንኒ ኢይክል ፈጽሞቶ"*

(ጕስቋላ ሳለች ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው ልጅሽ ሞት ያማረች፤ በልጅሽ መከራ መቀበል ነጻ የወጣች አገልጋይ ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፤ ተዳድፋ ሳለ በማሕፀንሽ ፍሬ ደም የነጻች፤ መከን ስትኾን ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው አንድ ልጅሽ ዕፀ መስቀል ያፈራች ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፤ ያዘነች ስትኾን በልጅሽ በወዳጅሽ ትንሣኤ የተጽናናቺው፤ ወራዳ ስትኾን በድንግልናሽ ቡቃያ መውጣት (ዕርገት) ከፍ ከፍ ያለቺውም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፤ በልጅሽ ጐን ውሃ ተጠምቃ ተወግቶ በፈሰሰው ደሙ ታትማ (ተቀብታ) ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች (ዮሐ ፲፱፥፴፬፤ ኤፌ ፭፥፳፮-፳፯፤ ቲቶ ፫፥፭)፤ የልዑል እግዚአብሔር በግ የተባለ ልጅሽ ዐማኑኤል የተሞሸረባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች (ዮሐ ፩፥፳፱፤ ኢሳ ፶፫፥፯)፤ ከወለድሺው ጋራ አንድ ሰውነት ካሳደግሺውም ጋራ አንድ አካል የኾነቺው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአንደበቷ ዘምራ በከንፈሯ እልል ብላ ታመሰግንሻለች፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእጆቿ ኣጨብጭባ በእግሮቿ አሸብሽባ ታመሰግንሻለች፤ ቤተ ክርስቲያን ትወድስሻለች፤ በአንቺም ደስ ትሰኛለች፤ በእግርሺም በታች ይሰግዱ ዘንድ ልጆቿን ትጠራቸዋለች (ኢሳ ፷፥፲፫፤መዝ ፺፩፥፲፪) ፤ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፤ የአሕዛብም ልጅ ለእስራኤል ልጅ ትሰግዳለች፤ በልጅሽ ጸጋ እስራኤላዊትን ኾናለች፤ ርሱ ልዕልናውን ወደ



ትሕትናዋ፣ ትሕትናዋንም ወደ ልዕልናው ስለጨመረ (ስለ አዋሐደ) ከርሷ ዘንድ ሞትን ወሰደ፤ ከርሱ ዘንድ ሕይወትን ሰጥቷልና፤ ርሷን በመውደዱ ከልዑል ዙፋን ዝቅ ብሎ ወርዶ ከብቻዋ ከኀጢአት በቀር ሥጋን ተውሕዶ እንደኛ መኾንን አላፈረም፤ በፈቃዱ ደከሞ፣ ታመመ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ ተሰቅሎ ታመመ፣ የርኩሳን አይሁድንም ምራቅ ትፋ ተቀበለ፤ ሞትንም በሥጋ ቀመሰ፤ ይኽነን ኹሉም ስለ ርሷ አደረገ፤ ርሷን ያልወደዳት ምን ጊዜ ነው? ከፍቅሯ የተነሣ ለነፍሱ ስንኳ አልራራም፤ በትንሣኤውም የዘለዓለም ሕይወትን ዐደላት፤ በዕርገቱም አሳቃት ከፍ ከፍ አደረጋት፤ ለርሱ አካልን አድርጎ እንደ መባ ለባሕርይ አባቱ ለእግዚአብሔር አብ አቀረባት፤ ስለዚኽም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች ከልቡናዋ ስለተዋሐደው (በልቡናዋ ስለተዘራው) የልጅሽ ፍቅር በፍቅር እየተቃጠለች ትሰግድልሻለች፤ የስሙ አጠራርም ለዘወትር ከአንደበቷ አይቋረጥም፤ ድንግል ሆይ አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ንጽሕት ሆይ! ድንግል ሆይ የተመሰገንሽ ቡርክት ሆይ! ድንግል ሆይ የተመረጥሽ ቅድስት ሆይ! የድንግልናሽ ምስጋና በኹሉ መላ ውዳሴሽም በዓለም ዙሪያ ሰፈፈ፤ የውቅያኖስ ባሕር በምልአቱ ውሱን ነው፤ የሐኖስም ባሕር በመጠኑ ልክ አለው፤ ለአንቺ ምስጋና ግን ልክና መጠን፣ ወሰንና መስፈርት፣ ማለቂያም የለውም አእምሮም አይወስነውም አንደበትም ተናግሮ ሊፈጽመው አይችልም)[165] በማለት በጥንተ ተፈጥሮ በሐዲስ ተፈጥሮ የፈጠረን፤ በክበረ ደሙ ፈሳሽነት የተወጃጀን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስን በመውለዷ ምክንያት ከጐኑ በፈሰሰ ውሃ (ማየ ገቦ) ተጠምቀን ልጆቹ እንድንኾን ያደረገን ክርስቲያኖች በመላ፤ ተነግሮ የማያልቅ የርሷን የአምላክ እናትነት ክብርና የልጇን የባሕርይ አምላክነት ሐጌ ትንቢትን በተናገረላት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስንመሰክር እንደምንኖር በስፋት አስተምሯል።

[165] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ፤ምዕ ፳፥፲-፳፰



www.ethiopianorthodox.org

# ነገረ ማርያም በትንቢተ ዘካርያስ
# ክፍል ዐሥራ አንድ

ነቢዩ ዘካርያስ በምርኮ ሀገር በባቢሎን ተወልዷል፤ አባቱ በራክዩ በባቢሎን ስለሞተ ከአያቱ ሐዶ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶአል፤ እርሱ እና አያቱ በዘሩባቤል መሪነት ከመገርመሪያዎቹ ወጪዎች ጋር ከምርኮ ተመልሰዋል (ነሕ ፲፪፥፩-፲፮)፤ ዘካርያስ የገገረው ዘሩባቤል የነቢዩ ሐጌ እና የሊቀ ካህናቱ ኢያሱ (ዮሴዕ) የዘመን ጓደኛ ሲኾን ትንቢቱን የገርመረው በ፭፻፲፱ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው (ዘካ ፫፥፩-፱፤ ፮፥፲፩፤ ዕዝ ፭፥፩-፪)።

ይኸም ዘካርያስ ጌታችን በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን፤ በ ፴ ብር መሸጡን፤ በጦር መወጋቱን፤ ሕማማተ መስቀልን መቀበሉን በደብረ ዘይት የሚኾን ዳግም ምጽአቱን በግልጥ ተናግሯል (ዘካ ፱፥፱-፲፩፤ ፲፩፥፪፤ ፲፪፥፲፤ ፲፫፥፯-፲፤ ፲፬፥፬)፤ እኛም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጠነዋለን።

## የዘሩባቤል የቃሉ ጣዕምና የዮሴዕ (ኢያሱ) የልብሱ ጌጥ

በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ቅድስት ድንግል ማርያም ዘሩባቤል በንጉሡ በዳርዮስ ፊት በተናገረው ቃልና የኢዮሴዴቅ ልጅ ሊቀ ካህናቱ ዮሴዕ (ኢያሱ) ባጌጠባት ልብስ ትመሰላለች (ዕዝ. ካል ፬፥፴፫-፵፬፤ ዘካ ፫፥፩-፰፤ ፮፥፲፩-፲፪)።

ከላይ እንደተገለጸው ነቢዩ ዘካርያስ የገገረው የዘሩባቤል፣ የነቢዩ ሐጌ እና የሊቀ ካህናቱ የኢያሱ (ዮሴዕ) የዘመን ጓደኛ ሲኾን፤ በዘሩባቤል መሪነት የመገርመሪያዎቹ ምርኮኞች ሲወጡ ዐብሮ ወጥቷል፤ የወጡበትም ምክንያት አስቀድመው ተማርከው ወደ ባቢሎን ሲወርዱ ንጉሡ ናቡከደነጾር ቤተ መቅደሱን ናቡዛርዳንን ልኮ አስጠፍቶት ነበር፤ ከዚያም የናቡከደነጾር ፵፮ ዓመት፣ የሮርማሮዴቅ ፵፫፣ የብልጣሶር ፵፩ በድምሩ ፸ ዓመት ሲመላ ዳርዮስ ንጉሠ ሜዶን ነገሠ።

ለዚኽ ለዳርዮስ ሦስት ጠባቂዎች ባለሟሎች ነበሩት፤ እነርሱን "ን ኹላችን መርጠን ለንጉሥ አንድ አንድ ቃል እንናገር፤ የሚወደድ ነገር መርጠን አሻሽለን እንናገር፤ ከባልንጀራው ነገሩ በዕውቀት ለበለጠለት ሰው





ንጉሡ ዳርዮስ ብዙ ገንዘብ ይስጠው፤ ነገሩ በመወደድ ድል ለነሣ ዋጋ ድርጎ ይዳርገው፤ ነጭ ሐር ያልብሰው፤ በወርቅ ዋንጫም ይጠጣ፤ በወርቅ አልጋም ይተኛ፤ በወርቅ ሠረገላም ይቀመጥ፤ ነጭ ሐርም ይልበስ፤ በአንገቱ ዝርግፍ ወርቅ ይሰር፤ ነገሩ ስለ ተወደደለት ከንጉሡ ቀጥሎ ይቀመጥ፤ የንጉሥ ባለሟል ይኹን"፤ በማለት ተመካክረው አንዱ "ወይን ይመውእ" (ወይን ያሸንፋል) ሲል፤ አንዱ "ንጉሥ ይመውእ" (ንጉሥ ያሸንፋል) በማለት ሲናገር፤ ጥበብን የተሞላው ዘሩባቤል ግን "ብእሲት ትመውእ ወእምኵሉሰ ጽድቀ እግዚአብሔር" (ሴት ታሸንፋለች፤ ከኹሉ ግን እውነት ነገር ታሸንፋለች) ብሏል (ዕዝ ካል ፫፥፬-፲፪)።

ይኸንንም ነገራቸውን በጽሑፍ አስፍረው አስረው ከንጉሡ በራስጌው አኖረዋል፤ ንጉሡም ሦስቱንም አስጠርቶ አንዱን "ወይን ያሸንፋል ያልኸው ለምንድን ነው?" አለው፤ ርሱም "ወይን የጠጣ ሰው ደካማው ብርቱ፤ ንጉሥ ለጋስ ይኾናሉና ይኸነን ያደረገ አሸናፊ አይባልምን" አለው፤ ሊላኛውንም "አንተስ ንጉሥ ያሸንፋል ያልኸው ለምንድን ነው?" አለው፤ ርሱም "ይኸነን ዓለም ዐርሶ ቈፍሮ ውሃውን ገድቦ በባሕር ያለውን የሚገዛ ሰው ነው፤ ሰዎችን የሚገዛ ደግሞ ንጉሥ ነውና፤ ይኸነን የሚያደርግ ንጉሥ አሸናፊ አይባልምን" አለው፤ ከዚኽ በኋላ ዘሩባቤልን "አንተስ ሴት ታሸንፋለች ያልኸው ለምንድን ነው?" አለው፤ ርሱም "ንጉሥ መልከ መልካም ሴት ያገኘ እንደኾነ በገንዘቤ እዘገርበት ብሎ ያሠለጥናታል፤ ይኸውም ሲታወቅ "አርጤምስ ወለተ በጥሬቱ ትጸፍዕ ገጸከ ወትነሥእ አክሊለከ ወትወድዮ ውስተ ርእሳ" (የበጥሬቱ ልጅ ኤጲማን በቀኝኽ ተቀምጣ ፊትኽን በጥፊ ትመታለች፤ የንግሥናኽን ዘውድ አንሥታ በራሷ ላይ ትደፋዋለች አንተም ትቈጣለኽ ታኮርፋለች፤ እንደገና መልሰኽ ታቀማጥላታለኽ አፏን እያየኽ ስትሥቅ ትሥቃለኽ፤ ታዲያ እንዲኽ የምታደርግ ሴት አሸናፊ አትባልምን" አለው (ዕዝ ካል ፫፥፩-፴፩)።

ንጉሡም በእጅጉ በመደነቅ እውነት ነው ብሏል፤ በመቀጠልም "እውነት ያሸንፋል ያልኸውሳ" አለው፤ ርሱም "እውነት በያዘ ሰው ክፉ ነገር አይገኝም፤ ወይን፣ ንጉሥ፣ ሴቶች በደለኞች ናቸው፤ እነዚኽም በበደላቸው ይሞታሉ፤ ጽድቅ ግን ኹል ጊዜ ታሸንፋለች፤ ሕይወት ናትና ለዘለዓለሙ ፊጽማ ጸንታ ትኖራለችና" በማለት ስለ እውነት በስፋት አስረዳ (ዕዝ ካል ፬፥፴፬-፵)።

ያን ጊዜ ንጉሡ ዳርዮስ ዘሩባቤልን የምትወደውን ኹሉ አደርግልኻለኍ ዐዋቂ ኾነኽልና አለው፤ ያን ጊዜ ዘሩባቤል ለንጉሡ



www.ethiopianorthodox.org

"የእግዚአብሔር ሀገር ኢየሩሳሌም ልትሠራና የእስራኤል ወገን ምርኮኞች ወደ ሀገራቸው ይመለሱ" የሚል አስደናቂ መልስን ሰጠ፤ ንጉሡም ደስ ብሎት ሀገረ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምና ስሙ የተጠራባት ቤተ መቅደስ ትታነጽ ዘንድና ምርኮኞቹ እንዲመለሱ አዘዘ፤ ያን ጊዜ ሕዝቡ ሰባት ቀን በገና እየመቱ ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል (ዕዝ ካል ፴፯፥፷፫-፷፫)።

ይኸ ከጓደኞቹ ይልቅ በንጉሡ ዘንድ የተወደደ ነገርን የተናገረው ዘሩባቤል ሀገረ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሷ ታንጾ ምርኮኞች ኹሉ ወደ ቀደመ ሀገራቸው እንዲመለሱ ያቀረበው ጥያቄ ልዩ የኾነ የነገረ ማርያምን ምስጢር ይዟል።

ይኸውም ስጊዜው እስራኤል ተማርከው ወደ ባቢሎን መውረዳቸው ነፍሳት በሲኦል ለ ፭ሺ.ሕ፭፻ ዘመን የመኖራቸውን ምሳሌ ሲያሳይ፤ ዳግመኛም እንደ ዘሩባቤል ተምኔት ሀገረ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌም ተሠርታ ቤተ መቅደሷ ታንጻ የተማረኩት እስራኤል ወደ ጥንት ሀገራቸው እንዲመለሱ መናገሩ ተምኔቱን ያሳየ ቢኾንም፤ ፍጻሜው ግን የሰላም አለቃ ክርስቶስን በመውለዷ ኢየሩሳሌም (የሰላም ሀገር) ከተባለች፤ ሰማይና ምድር የማይወስኑት ርሱን ፱ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ በመሸከሟ የእግዚአብሔር ሀገር፣ የእግዚአብሔር መቅደስ ከተሰኘችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዲያብሎስ ምርኮ በሲኦል የነበሩ ነፍሳትን ወደ ጥንት ቦታቸው ወደ ጥንት ክብራቸው የሚመልስ መኾኑን ያጠይቃልና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

> *"ኦ ድንግል አንቲ ውእቱ ለዘሩባቤል ሞገስ ቃሉ በቅድመ ንጉሥ ወዐበይቱ*
>
> *አመ ሞአ ሎቱ ምሳሌ ወራዙት ክልኤቱ"*

(ድንግል ሆይ የኹለት ጕልማሶች ክርክር ምሳሌ ባሸነፈለት ጊዜ በንጉሡና በባለሟሎቹ ፊት የዘሩባቤል የቃሉ ጣዕም አንቺ ነሽ)[166] በማለት አመስግኗታል።

አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ጠቅልሎ የገለጸውን ምስጢር በአርጋኖን መጽሐፉ ሲያብራራው *"ዘሩባቤል ውእቱኒ ዘእምደቂቀ ነገሥተ ይሁዳ ዐጽቅ ቡሩክ ዘሠረጸ እምቤተ ሌዊ ቃሕወ ገብረ በምሳሌያተ ጥበቡ ምስለ ደቂቅ እለ ይነብሩ በቤተ ዳርዮስ ንጉሥ ወአንበሩ ፍትሐ ለዘሞአ በምሳሌሁ ከመ ባዝግና ወርቅ ይዕንቅ በክሣዱ፤ ወተጽላ*

[166]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 42





*ይደይ ዲበ ርእሱ፤ ወዲበ ሠረገላ ንጉሥ ይጸዐን ወበጽዋዕ ዘይሰቲ ንጉሥ ይስተይ፤ ወዲበ ዕራተ ወርቅ ይሰክብ ወወልደ ንጉሥ ይሰመይ፤ ወሶበ ነቅሐ ዳርዮስ ነገሩ ምሳሌያቲሆሙ ወአግብአ ፍትሐ ንጉሥ ዘሩባቤል፤ ወይቤሎ ንጉሥ ዘሩባቤል ምንተ ትፈቅድ እግበር ለከ ወምንተ ትፈቅድ ሀብተ እምኀቤየ፤ ወአውሥአ ወይቤሎ ዘሩባቤል ለንጉሥ እፈቅድ ከመ ትትሐነጽ ሀገረ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌም ወይትመየጡ ፄዋ እስራኤል ውስተ ብሔሮሙ፤ ወሠምረ ንጉሥ በቃለ ዚአሁ፤ ወገብረ በከመ ተነበየ ወረከበ በከመ ኀለየ፤ ወሐነጸ ቤተ እግዚአብሔር ዘአመዝበረ ናቡከደነጾር ንጉሥ ወናቡዛርዳን ሊቀ መበስላኒሁ ወተፈጸመ ሐኒጸታ ለቤተ አምላከ እስራኤል በአርብዓ ወሰብዐቱ ዓመት፤ ወአኮሰ ዘየኀድር ልዑል ውስተ ግብረ እደ ሰብእ፤ እስመ ይቤ ሰማይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ እገርየ አየኑ ቤተ ተሐንጹ ሊተ ለማኅደርየ፤ ወአየኑ መካነ ለምዕራፍየ፤ ወማኅደሩሰ ለእግዚአብሔር አንቲ፤ ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘበዐበራይስጢ ማሪሃም ዘተማረርኪ በዲበ ምድር፣ ወተቀመርኪ በዲበ አርያም ወሰፋሕኪ እምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ወእምሰሜን ወእስከ ደቡብ፣ ወእምባሕር እስከ ባሕር ወእምአፍላግ፣ እስከ አጽናፈ ዓለም"*

(ከይሁዳ ነገሥታት ልጆች ዘሩባቤል ከሌዊ ቤት የበቀለ የተባረከ ቅንጣት በንጉሥ በዳርዮስ ቤት ከሚቀመጡ ብላቴናዎች ጋር በጥበቡ ምሳሌዎች ክርክርን አደረገ፤ በምሳሌውም ለረታው ውሳኔን አስቀመጡ፤ አንገቱ ዝርግፍ ወርቅ ኒሻንን እንዲያስር በራሱም የራስ ወርቅን እንዲቀዳጅ ንጉሡም በሚቀመጥበት ሠረገላ እንዲቀመጥ በሚጠጣጠበትም የወርቅ ጽዋ እንዲጠጣ በወርቅ አልጋ ላይ እንዲተኛ የንጉሥ ልጅም ተብሎ እንዲጠራ፤ ዳርዮስም በነቃ ጊዜ ምሳሌዎቻቸውን ተናገሩ፤ ንጉሡም ፍርዱን ለዘሩባቤል መለሰ፤ ንጉሡም ዘሩባቤልን አደርግልኽ ዘንድ ምን ትሻለኽ? ከእኔስ ዘንድ የምትፈልገው ሀብት ምንድን ነው? አለው፤ ዘሩባቤልም ለንጉሡ መለሰ፤ እንዲኽ ሲል፤ የእግዚብሔር ሀገር ኢየሩሳሌም እንድትሠራ፤ የእስራኤል ምርኮኞችም ወደ ሀገራቸው ይመለሱ ዘንድ እወዳለኊ ሲል፤ ንጉሡም በዘሩባቤል አባባል ተስማምቶ እንደተናገረው አደረገለት፤ ያሰበውንም አገኘ፤ ንጉሡ ናቡከደነጾርም ከማድ ቤት ሠራተኞች አለቃ ከናቡዛርዳን ጋር ያፈረሰውን ቤተ እግዚአብሔር ሠራ፤ የእስራኤል ፈጣሪ ቤተ መቅደስ ሕንጻም በአርባ ሰባት ዓመት ተፈጸመ (ሐጌ ፩፥፩-፲፫፤፪፥፩-፱፤ዘካ ፬፥፮-፲፬፤ ዮሐ ፪፥፲፱-፳)፤ ልዑል እግዚአብሔር ግን ሰው በሠራው ሕንጻ የሚያድር አይደለም፤

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ይላልና፤ ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ እንዲህ ከሆነ ለማደሪያዬ እንደምን ያለውን ቤት ትሠሩልኛላችሁ? እንደምን ያለውንስ ቦታ ለማረፊያዬ ታዘጋጁልኛላችሁ? (ኢሳ ፷፮፥፩)፤ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ፤ በምድር ላይ የተመሠረትሽ፣ በአርያም ላይ የተዘረጋሽ፣ ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከባሕር እስከ ባሕር ከወንዞች እስከ ዓለም ዳርቻች የተዘረጋሽ የእግዚአብሔር ማደሪያው ግን አንቺ ነሽ)[167]፤ በማለት ከጽርሐ አርያም በላይ ርዝመቱ፤ ከበርባርስ በታች ጥልቀቱ፤ ከአድማስ እስከ ናጌብ ድረስ ስፋቱ ተብሎ የማይመረመረውን ምሉእ በኩለሄ የሆነውን ቀዳማዊ አምላክን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመችና ሀገረ እግዚአብሔርነቷም አስቀድሞ የተነገረላት መሆኑን በስፋት ገልጦታል።

ይህ ብቻ ሳይሆን ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን ሲፈጽም የኢዮሴዴቅ ልጅ ዮሴዕ (ኢያሱ) በለበሳት ልብስ እመቤታችን ተመስላበታለች (ዘካ ፫፥፩-፭፤፮፥፲፩-፲፪)።

ይኸውም አስቀድሞ የሰባ ዘመን ምርኮ በደረሰ ጊዜ ነቢዩ ኤርምያስ *"ምንተ እግበር በእንተ ንዋየ ቅድሳቲክ"* (ተሰውረን ስለምናገለግልበት ንዋያተ ቅድሳት ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለኸ? በላያቸውስ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለኸ? በማለት ቃለ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ *"ወዕቀቢ ንዋየኪ እስከ ምጽአቱ ለፍቁር"* (ወዳጅ እስኪመጣ ድረስ ገንዘብሽን ጠብቂ) ብሎኸ ለምድር ዐደራ ሰጣት ብሎት፤ ምድርም በተአምራት ተከፍታ ተቀብላለች (ተረ. ኤር. ፰፥፭-፯)።

ይኸቺ ምርኮ ሲደርስ በነቢዩ ኤርምያስ ቃል "ወዳጅ እስኪመጣ ድረስ ገንዘብሽን ጠብቂ" ተብላ ንዋያተ ቅድሳቱን ዐደራ የተቀበለችው ምድር፤ ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን ሠርቶ፤ ወዳጅ የተባለው የኢዮሴዴቅ ልጅ ሊቀ ካህናቱ ዮሴዕ (ኢያሱ) በነቢዩ ዘካርያስ እንደተነገረ በምርኮ ይለብሰው የነበረውን የሐዘን ልብስ አውልቆ አፍኣዊ ኀጢአት የሚያስተሰርይበትን ንጹሕ የክህነት ልብሱን ለብሶ፣ ንጹሕ ጥምጥም ጠምጥሞ በራሱ ላይ አድርጎ፤ የወርቅ አክሊል ተቀዳጅቶ ሳለ ዐደራዋን የተቀበለችው ምድር ዕጣኑ ሳይጠፋ እየጤሰ፣ መብራቱም እየበራ በተአምራት ዐደራዋን ሰጥታለች (ዘካ ፫፥፫-፭፤፮፥፲፩-፲፪፤ ሐጌ ፪፥፬)።

[167]አርጋኖን ዘጎሙስ፤ ምዕ ፭፥፹፪-፹፯፤፯፥፩





ያን ጊዜ ካህናቱ ኹሉ የክብር ልብስ ተክህኖ ለብሰው መለከት ይዘው፤ የአሳፍ ልጆች ሌዋውያን በጸናጽል፤ ሕዝቡ ቀንደ መለከት በመንፋት እግዚአብሔርን አመስግነዋል (ዕዝ ካል ፮፥፶፱-፷፬)።

በመኾኑም በጊዜው ኢየሩሳሌም ታንጻ ቤተ መቅደሷ ተሠርታ ካህናተ ብሊት የነበሩት እነ ዮሴዕ (ኢያሱ) ከምርኮ ነጻ ወጥተው አፍኣዊ ኀጢአት የሚያስተሰርዩበትን ልብሰ ተክህኖ እንደገና ለብሰው፣ የክህነት ጥምጥማቸውን ጠምጥመው በደስታ ፈጣሪያቸውን ለማመስገን በድጋሚ እንደተነሡ ኹሉ፤ የሰላም አለቃ ጌታን በመውለዷ ምክንያት ኢየሩሳሌም (የሰላም ሀገር) ከተባለች፤ ሰማይና ምድር የማይወስኑት ርሱን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ በመሸከሟ "የእግዚአብሔር ሀገር፤ የእግዚአብሔር መቅደስ" ከተሰኘችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ያጣነውን የልጅነት የጸጋ ልብስ እንደገና መልሶ፤ ለካህናተ ሐዲስ ለሐዋርያት የማሰር የመፍታት ሰማያዊ የክህነት ሥልጣንን አጎናጽፏቸዋልና፤ የመልክአ ማርያም ደራሲ ይኽንን በማነጻጸር በመጽሐፉ ላይ

*"ማርያም ድንግል ለዮሴዕ ሰርጕ ትርሲቱ"* (ድንግል ማርያም የዮሴዕ (ኢያሱ) የልብሱ የክብር ጌጥ አንቺ ነሽ)[168] በማለት አመስግኗታል (ማቴ ፲፯፥፲፰-፲፱፤፳፰፥፳፤ሉቃ ፳፬፥፶፤ ዮሐ ፳፥፳፪-፳፫፤የሐዋ ሥራ ፳፥፳፰)

ኢትዮጵያዊዉ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት ላይ ስለዚኽ ምስጢር

*"ሰበነ ቅድሳት ዘተወፈየኪ ዮሴዕ ለተቀጽሎ*
*አመ ሜጠ እግዚአብሔር ፄዋ ያዕቆብ ለተሣህሎ"*

(እግዚአብሔር የያዕቆብን ምርኮኝነት ይቅር ለማለት በመለሰ ጊዜ ዮሴዕ ለመቀዳጀት የተቀበለሽ የቅድስና ቀጸላ አንቺ ነሽ)[169] በማለት ከገለጸ በኋላ ነቢዩ ዘካርያስ በትንቢቱ የተናገረላት የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን ዳግመኛ

*"ኃብነ ርትዕ እንተ ዘዘካርያስ ዘአዕይንቲሃ ሰብዐቱ*
*ዘተወፈየ ዮሴዕ በዕለተ አስምዑ ሎቱ"*

(በአስሙለት ቀን ዮሴዕ የተቀበላት፤ ዐይኖቿ ሰባት የኾኑላት ቀጥተኛ የዘካርያስ ደንጊያ አንቺ ነሽ)[170] በማለት አስተምሯል።

[168]መልክአ ማርያም፤ ለመታክፍትኪ
[169]አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 9
[170]ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 43



www.ethiopianorthodox.org

# የወርቅ መቅረዝ

ነቢዩ ዘካርያስ በተሰጠው የትንቢት ሀብት እውነተኛውን የዓለም ብርሃን ዐማኑኤልን የወለደችልን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ የምትኾን ኹለንተናዋ የወርቅ የኾነ መቅረዝን ተመልክቶአል (ዘካ ፬፥፩-፪)።

ይኸቺውም ዘካርያስ ያየት መቅረዝ ኹለንተናዋ የወርቅ ሲኾን የዘይት ማሰሮ ሰባት ምንባረ ፈትል እና ሰባት መግጠሚያ ነበሩባት "ወክልኤቱ አዕጹቀ ዘይት መልዕልቴሃ አሐቲ በየማነ ተቀዋመ ማኅቶት ወአሐቲ በፀጋማ" ይላል ኹለት የወይራ ዛፎች አንዱ በማሰሮው በስተቀኝ አንዱ በማሰሮው በስተግራ ኹኖ ተመልክቷል።

ይኸውም ለጊዜው ተቅዋም (መቅረዝ) የእስራኤል፤ ዘይቱ የረድኤት፤ መብራቱ የተድላቸው የደስታቸው ምሳሌ ሲኾን ፍጻሜው ግን መቅረዝ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ወርቁ የንጽሕናዋ፣ የቅድስናዋ፤ ምንባረ ፈትል የማሕፀኗ፤ መግጠሚያው የማኅተመ ድንግልናዋ፤ እሳት የመለኮት፤ ፈትል የትስብእት፤ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ (ሉቃ ፩፥፴፭፤ ማቴ ፩፥፲)፤ በሰባቱ ቧንቧዎች በእያንዳንዱ ያሉት ሰባት ሰባት ፈትሎች በአንድ ላይ ቢቈጠሩ አርባ ዘጠኝ ይኾናሉ (፯x፯=፵፱)፤ ይኸም ለጊዜው የዘሩባቤል የመንግሥቱ ዘመን አርባ ዘጠኝ መኾኑን ሲያሳይ፤ ፍጻሜው ግን አማናዊት መቅረዝ ቅድስት ድንግል ማርያም እውነተኛውን ብርሃን ክርስቶስን ከወለደች በኋላ በዚህ ዓለም የኖረችው መላ ዘመኗ (ዕድሜዋ) አርባ ዘጠኝ መኾኑን ሲገልጽለት ነው።

ይኸነንም ስናስበው ክርስቶስን ፀንሳ ፱ ወር ከ፭ ቀን፤ ከልጇ ጋር ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር፤ በዮሐንስ ቤት ፲፭ ዓመት በድምሩ ፵፱ ሲመላ፤ ጌታን ከመውለዷ በፊት ካለው ፲፭ ዓመት ጋር መላው ዕድሜዋ ፷፬ ይሞላል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በአርጋኖን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ ይኸነኑ የዘካርያስን ትንቢት ሲተረጕም

*"ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ወልደ ሐዶ ካህን ወነቢይ ዐቢይ ርእየ በወርኀ ሣባጥ ተቅዋመ ማኅቶት ዘወርቅ ዘሰብዐቱ መኃትዊሃ ወሰብዐቱ መሳውሪሃ አዕፁቀ ዘይት እምለፌ ወእምለፌ እምየማና ወእምፀጋማ ርእየ ሥነ ግብሪሃ ለመርዓት ብመጽሐፈ መንፈስ ወአንከረ በእንተ ዘርእየ አምሳለ ወአኮ ገሃደ ወብርሃን ዘዲበ ተቅዋም ዘርእየ ዘካርያስ አልቦ ለዘአብርሃ ዘእንበለ ለባሕቲቱ ለነቢይ፤ ወብርሃነ መለኮትሰ ዘኀደረ ላዕሌኪ ሰደዶ ለጽልመት እምላዕለ ሰብእ ወአብርሀ በመለኮቱ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም"*





(ታላቁ ነቢይና ካህን የሐዶ ልጅ የበራክዩ ልጅ ዘካርያስ ማብራያዎቿ ሰባትና የዘይት ማጠጫዎቿም ሰባት የሚኾን ከወዲያና ከወዲኽ ከግራናዋና ከቀኟ የወይራ ቅንበጦች ያሏትን የወርቅ የምትኾን የመብራት መቅረዝን በየካቲት ወር አየ፤ የሙሽራዪቱን የሽልማቷን ውበት በመንፈስ መስታዮትነት አይቶ ግዛዱን ያደደለ ምሳሌውን ስለ አየ አደነቀ፤ ዘካርያስ በመቅረዝ ላይ ያየው ብርሃን ለነቢዩ ብቻ ካልኾነ በቀር ያበራለት የለም፤ በአንቺ ላይ ያደረ የመለኮት ብርሃን ጨለማን ከሰዎች ላይ አርቆ በብርሃነ መለኮቱ በዓለም ኹሉ ዳርቻ አበራ)[171] በማለት የኀጢአትና የሞት ጨለማን ያስወገደ እውነተኛውን ብርሃን ዐማኑኤልን ያስገኘችልን ዘካርያስ በትንቢቱ የገለጻት እውነተኛዪቱ መቅረዝ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን ተንትኖ አብራርቶታል።

አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታም በማሕሌተ ጽጌ የነገረ ማርያም መጽሐፋቸው ላይ ነቢዩ ዘካርያስ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የተመለከታት የወርቅ መቅረዝ የብርሃን እናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስለመኾኗ

*"ዘካርያስ ርእየ ለወርኀ ሣባጥ በሠርቁ*
*ተአምረኪ ለዘይት ማእከለ ክልኤ አዕጹቁ*
*ማርያም ጽዮን ለብርሃነ ትቅዋም ወርቁ*
*ዕፀራኒ በገዳም እመ ወዐለ ውዱቀ*
*ለሕብረ ገጽኪ ጽጌ ኀተወ መብረቁ"*

(የብርሃን የወርቅ መቅረዙ ጽዮን ማርያም ነቢዩ ዘካርያስ በኹለቱ የወይራ አዕጹቅ መኻከል በየካቲት ወር ምልክትሽን አየ፤ ዕፀራም በምድረ በዳ ወድቆ በዋለ ጊዜ (ሰባኤ በገባ ጊዜ)፤ ጽጌ (አበባ) የፊትሽ ደም ግባት ብልጭታው በፊቱ ብልጭ አለ (አንጸባረቀ))[172] በማለት የዘካርያስን ትንቢትና የዕዝራ ሱቱኤልን የነገረ ማርያም የራእይ ምስጢር በማስተባበር ገልጠውታል።

እመቤታችን አማናዊ ብርሃን ፈጣሪያችን ክርስቶስን እንደምትወልድ ልክ እንደ ዘካርያስ ኹሉ ዕዝራ ሱቱኤልም በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ የተናገረውን ምስጢር ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ሲተረጕም

*"ዕዝራ ሱቱኤል እመ አርብዓ ዓመት እም ዘወድቀት ሀገረ እስራኤል ኢየሩሳሌም ወተዄወወ ደቂቀ ጽዮን ወአኀዘ ይላሕዋ ወይብኪ*

[171] አርጋኖን ዘንሙስ ምዕ ፳፥፳-፳፩

[172] አባ ጽጌ ድንግል ፣ ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፳፯



www.ethiopianorthodox.org

*መሪረ በአንተ ዘተንትመ ኦሪት ወተጌወዉ ሌዋውያን እስመ አስተርአየቶ ጽዮን እንዘ ይበርቅ ሕብረ ገጸ እምሕብረ ፀሓይ (ዕዝ.ሱት ፩፥፩)፤ ወአንቀልቀሉ መሠረታተ አድባር እምእውሥአተ ቃላ ወተናዘዘ ዕዝራ ሶበ ርእየ ሥራኄ ስብሐት ዘየዐውዳ (ዕዝ.ሱቱ ፱፥፳፫)፤ ርእየ ጽላሎተ ዚአኪ ኦ ድንግል ወኢርእየ ብርሃነ ገጽኪ ዘበአማን ርእየ ጎሐ ወኢርእየ ፀሓየ ርእየ ዋካ ወኢርእየ ማኅቶተ ጸዳል ወብርሃነ ጽድቅሰ ዘበአማን ብኪ ኮነ ወእምኔኪ ሠረቀ ፀሓየ ቅዱሳን ዘሰደዶ ለጽልመት"*

(ሱቱኤል የተባለ ዕዝራ የእስራኤል ሀገር የምትኾን ኢየሩሳሌም ወድቃ ከጠፋች የጽዮን ልጆች ከተማረኩ በአርባኛው ዓመት፤ ኦሪት ስለጠፋች ሌዋውያንም ስለተማረኩ በፍጹም ያለቅስላት ገርመረ፤ ከፀሐይ ሕብር ይልቅ ፊቷ ሲያንጸባርቅ ጽዮንን አይቷታልና (ዕዝ.ሱቱ ፩፥፩)፤ ከቃሏም ምልልስ የተነሣ የተራሮቿ መሠረቶች ተነዋወጡ፤ ዕዝራም የሚከባትን የምስጋና ብርሃን ባየ ጊዜ ተጽናና ተረጋጋ (ዕዝ.ሱቱ ፱፥፳፫)፤ ድንግል ሆይ የአንቺን ጽላሎት አየ፤ የመልክሽን አማናዊ ብርሃን ግን አላየም፤ ወገግታውን አየ፤ ፀሓዩን ግን አላየም፤ መብራቱንም አየ የፋናውን ጸዳል አላየም፤ እውነተኛው የጽድቅ ብርሃን ግን በአንቺ ኾነ፤ ጨለማውን ያራቀው የቅዱሳን ፀሓይ ከአንቺ ወጣ)[173] በማለት የፀሐየ ጽድቅ የዐማኑኤል እናትነቷን ምስጢር እንደ ወርቅ አንክብሎ እንደ ሽማ ጠቅልሎ አመስግኗታል።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በእንዚራ ስብሐት ላይ ሲተረጉም፦

*"ኦ እግዝእትየ ማርያም ተቅዋመ ወርቅ ዘወልዶ ሐዶ*
*ጸዳለ ብርሃን ውኩይ ለክበበ ርእስኪ ዘየዐውዶ*
*ለጽልመተ ጌጋይ ጽፉቅ ዘየአትቶ ወይሰድዶ*
*ለዘመጽአ እምሕፅነ አቡሁ ወሪዶ*
*ሥነኪ ፈቲዎ ወሞገስኪ ፈቂዶ*
*ዘጸርኪ ርስኖ ወአግመርኪ ነዶ"*

(ድቅድቅ የኀጢአት ጨለማን የሚያስወግደው የሚያሳድደው ብሩህ የኾነ የብርሃን ጸዳል የራትሽን ዙርያ የሚከብበው፤የሐዶ ልጅ የወርቅ መቅረዝ እመቤት ማርያም ሆይ ደም ግባትሽን ወዶ ባለሟልነትሽን ፈቅዶ፤ ከባሕርዩ አባቱ ዕሪና ወርዶ የመጣውን ዋዕዩን የተሸከምሽ ፍሕሙንም (ነባልባላዊ ባሕርዩን) የወሰንሽ ነሽ) በማለት ረቂቁን የቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢር አስተምሯል።

[173] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘገሙስ፤ ምዕ ፳፥፶፫-፶፮





# ነገረ ማርያም በትንቢተ ሚልክያስ
# ክፍል ዐሥራ ኹለት

ነቢዩ ሚልክያስ ከነቢያት መጨረሻው ሲኾን ከሐጌና ከዘካርያስ በኋላ ከ ፬፻፶-፬፻ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነቢይነት ቆይቷል፤ በርሱ ጊዜ አይሁድ ከባቢሎን ተመልሰው ነበር፤ ዕዝራና ነሕምያ ቤተ አይሁድን በሚያስተካክሉበት ጊዜ ሚልክያስም ተባባሪያቸው የነበረ ሲኾን፤ ይኽ ነቢይ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በርካቶች ትንቢታትን ሲናገር የአምላክ እናት እመቤታችንን በታላቅ አዳራሽ (መቅደስ) አምሳል አይቷታል፤ እኔም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በትንቢቱ የተናገረውን የነገረ ማርያም ትምህርት ከዚኽ በታች አስቀምጬዋለኁ።

## የሚልክያስ ንጽሕት አዳራሽ

ይኽ ሚልክያስ ጥበብን በሚገልጽ ምስጢርን በሚያናግር በመንፈሰ እግዚአብሔር በመቃኘት በምዕ ፫፥፩ ላይ

"እነሆ መልእክተኛዬን እልካለኁ፤ መንገድንም በፊቱ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይወጣል" በማለት መላው የሰው ዘር በተስፋ ይጠባበቀው የነበረው፤ ቀደምት አበው ነቢያት ሊያዩት ይፈልጉት የነበረው የአምላክ ሥጋዌን ለማብሠር ቅዱስ ገብርኤልን አስቀድሞ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ለብሥራት በመላክ፤ በአማናዊት መቅደስ በማሕፀነ ማርያም ፱ ወር ከ፭ ቀን የማደሩን ነገር አስቀድሞ በትንቢቱ ተናግሯል።

ነቢዩ ሚልክያስ አስቀድሞ በትንቢት እንደተናገረ የአምላክ መልእክተኛ ቅዱስ ገብርኤል ለብሥራት አስቀድሞ ወደ ቅድስት ድንግል የመላኩን አስደናቂ ምስጢር በርካቶች ሊቃውንት ተንትነው አስተምረዋል (ሉቃ ፩፥፳፮-፳፰)።

ሊቁ አባ ሕርያቆስም ስለዚኽ ምስጢር በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ ሲገልጽ

*"ወሶበ ርእየ ንጽሕናኪ ለሊሁ እግዚአብሔር አብ ፈነወ ኀቤኪ መልአኮ ብርሃናዌ ዘስሙ ገብርኤል ወይቤለኪ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ መጽአ ኀቤኪ ቃል እንዘ ኢይትፈለጥ እምሕጽነ አቡሁ ጸነስኪዮ እንዘ ኢይትገባእ ተዐቍረ ውስተ ማሕፀንኪ እንዘ ኢየሐጽጽ በላዕሉ ወኢይትዌሰክ በታሕቱ ኀደረ ውስተ ከርሥኪ እሳተ [illegible] ዮቂ ወኢመጠኑ"*



www.ethiopianorthodox.org

(ርሱ ቅሉ እግዚአብሔር አብ ንጽሕናሽን ባየ ጊዜ ስሙ ገብርኤል የሚባል ብርሃናዊ መልአኩን ወደ አንቺ ላከ፤ መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ይመጣል የልዑል ኀይልም ይጋርድሻል አለሽ፤ ከአባቱ አጠገብ ሳይለይ ቃል ወደ አንቺ መጣ፤ ሳይወሰን ፀነሽው በላይ ሳይጐድል በታችም ሳይጨመር በማሕፀንሽ ተወሰነ፤ መጠንና መመርመር የሌለበት እሳተ መለኮት በማሕፀንሽ ዐደረ)[174] በማለት መልእክተኛው ቅዱስ ገብርኤል አስቀድሞ ተልኮ የአምላክ መቅደሲ ቅድስት ድንግልን ሲያበሥራት፤ ርሷም ቃሉን በእምነት በተቀበለች ጊዜ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጅ በማሕፀኗ የማደሩን ነገር አስተምሯል።

ከ ፬፻፶፩-፭፻፳፩ ዓ.ም የነበረው ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በልደት ድርሳኑ ላይ ንጉሥ ወደ አዳራሹ ሊገባ ሲል አንጥፉ አሰናዱ ለማለት መልእክተኛውን አስቀድሞ እንደሚልክ ኹሉ፤ ጌታም የሰማይ የምድር ንጉሥ ነውና፤ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም ንጽሕት መቅደሱ ናትና፤ ነገሩን አስቀድማ እንድታውቀው ሲል መልእክተኛውን ቅዱስ ገብርኤልን አስቀድሞ እንደላከላት ሲገልጽ

*"The king wished to send his Son to rehabilitate the earth..."* (ንጉሥ ልጁን ሊልክ የወደደው ምድርን ዳግም ይታደጋት ዘንድ ነው፤ ርሷ (ምድር) ያ ጣያታትን ባመጣውና በነርሱም አማካይነት ባሳታት [illegible] ተይዛ (በክፉ ተወርሳ) ነበርና፤ የርሱ (የጌታ) መልእክተኞች (ነቢያት) [illegible] መውረዱ አስቀድመው የምሥራቹን ለምድር በማብሠር ተናገሩ፤ [illegible] የድንግል ልጅ በመልእክተኞቹ ይበሠር ዘንድ ነበር፤ መልእክተኞች [illegible] በበሳሹ ላይ ጥቃት ሰነዘሩ፤ ርሱ ግን አልፈራም፤ ቀስቶችንም [illegible] ወረወሩበት፤ ርሱ ግን ከምርኮኞቹ አልራቀም፤ ርሱ መሐሪ የኾነውም [illegible] መታከቷንና ክፉው ማሸነፉን ተመለከተ፤ እናም ታዳኞቹን [illegible] (ባሳዳጆ) ያስጥላት ዘንድ አንድያ ልጁን ላከው፤ የመላእክት [illegible] ፊት (መንገድን) ያዘጋጅ ዘንድ ለመልአኩ አመለከተው፤ [illegible] ርሱ (አካላዊ ቃል) ከባሕርይ አባቱ ከአብ ሳይለይ [illegible] ዘንድ ነበር፤ በዙፋኑ ኹኖ ወደ እግሩ መረገጫ ምድር [illegible] ላከው፤ ሰማይ ዙፋኑ ነው ምድርም የእግሩ መረገጫ [illegible] ርሱ የኼደው (የወረደው) ወዴት ነበር? (ኢሳ ፷፮፥፩)፤ [illegible] ፊት መኼዱ አስፈላጊነቱ ለምን ነበር?፤ መልአኩን [illegible] (አምላክ) መውረድ የመጠራቱ ምክንያት ምን ነበር?

[174] አባ ሕርያቆስ [illegible] ማርያም ቍ፰-፶፯





መንፈሳውያን ፍጡራን በፍጥነታቸው ከርሱ ጋር በከፍታ አይደርሱም፤ እሳታማዎች የኾኑት በእሳታዊ ፍጥረታቸው ርሱን አይቀርቡትም፤ አይደርሱበትም፤ የርሱ ፍጥነት (ረቂቅነት) ከኪሩቤል ፍጥነትም በላይ የላቀ ምጡቅ ነው፤ ርሱ ሊነግሥ ቢወድ እንኳ ፍጥነቱ ከሱራፌል የበለጠ (የመጠቀ) ነው፤ የመብረቅ ብልጭታም እንኳን የዛለ በመኾኑ ሊደርስበት አይችልም፤ ነፋስም ርሱን ይይዘው ዘንድ ኀይል የለውም ምክንያቱም የርሱ ፍጥነት (ረቂቅነት) ከነፋሱ የላቀ ነው፤ የርሱ ባሕርይ ንጹሕ፤ በኹሉም የመላ (ፊጣን፣ ረቂቅ) ነው፤ ታዲያ በርግጥ ለምንድን ነው የርሱን መምጣት እንዲያውጅ እንዲያስታውቅ መልአኩን የላከው? ቢባል ያለ ጋብቻ ወግ (እንበለ ዘርዐ ብእሲ) በማሕፀኗ ውስጥ የፀነሰች መኾኗን ጥሮች ጊዜ ብላቴናዪቱ እናት እንዳትደነግጥ (እንዳትሸበር) ነዋ፤ እናም በዚኽ ምክንያት ለእመቤታችን ማርያም አስቀድሞ ያሳውቃት ዘንድ ርሱ መልአኩን ላከው፤ ማን እንደነበረና በርሷ ያደረው ማን እንደኾነ፤ በድንግልናዋ የተሸከመችው ማንን እንደኾነ ያሳውቃት ዘንድ ነው፤ ርሱ (አምላክ) ትእዛዙን ተናገረ፤ መልአኩም ከመላእክት ነገድ ሰማው፤ እናም መልአኩ በጉዞው እንዳይዘገይ በፈጣን ክንፎቹ በችኮላ ወጣ፤ እነዚያ ገብርኤል የሰማቸው ቃላት የተሰወሩ ናቸው ምክንያቱም በርሱ ከኹሉ በላይ በኾነው በምስጢር የተነገሩ ነበሩና፤ በመጻሕፍት ለእኛ የተገለጸልን ርሱ መላኩ ብቻ ነው (ሉቃ ፩፥፳፮-፳፰)፤ ይኹን እንጂ በምን ዐይነት ኹኔታ እንደኾነ አልተሰማም ምክንያቱም የተሰወረ ነውና፤ እነዚያን ርሱ መልአኩ የተማራቸውን (የሰማቸውን) ነገሮች ለእማኟ ብላቴና አስተማረ፤ የሰማውንም ዜና ለተባረከቺው ብላቴና አብራራላት፤ ዐዋጁ ከንጉሡ መኖሪያ ወጣ መልአኩም ተሸከመው፤ ከሰማያውያን ፍጡራን በላይ ከፍ ብሎ በፍጥነት በረረ፤ ከጉባኤዎችም ባሻገር ዐልፎ ኼደ ከሰራዊተ መላእክትም ከማለፍ አልተገታም (አልተከለከለም) ነበር፤ በሰራዊቶች መካከል በረረ አልዘገየም፤ ርሱ የእሳት ነበልባሉን ከፊለው ነፋሱንም ሠነጠቀ፤ የሚነደውንም ፍም ከእግሩ በታች ተረማመደው፤ በፈጣን ነፋስ ላይ ተሳፈረና በነበልባል መንገድም ተጓዘ፤ ርሱ መላእክትን በነገዳቸው ውስጥ ወደ ኋላ ተዋቸውና ከነርሱ ባሻገር ዐልፎ ኼደ፤ ርሱ መላእክትን በነገዳቸው



www.ethiopianorthodox.org

እንዳሉ ትቷቸው በረረ እና ወደታች ወረደ፤ ርሱ ከሰማያዊቷ ከተማ (ከራማ ሰማይ) በላይ ዐለፈና ወደኛ ስፋራ ብቅ አለ፤ ርሱ ከከፍታው በረረ፤ ወደ እመቤታችን ማርያምም ደረሰና በርሷ ፊት አጎነበሰ፤ አገልጋዩ የንጉሡን እናት አያት እናም ራሱን ወደታች ዝቅ አደረገ፤ እናም ደብዳቤውን ዘርግቶ በጨዋ ወግ በዝምታ ጠበቀ፤ መልእክተኛው ቀረበና ሰላም የመላበትን በመንፈሳዊ ጥበብ በምስጢር የተጻፈውን ደብዳቤ ሰጠ፤ በርሷ ፊት ከፈተውና በጥበባዊ አገላለጽ ያነብባላት (ይገልጽላት) ገ/መር (ሉቃ ፩፥፳፮-፴፰))[175] በማለት መልእክተኛው ቅዱስ ገብርኤል ወደ አማናዊት መቅደስ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ከአምላክ ዘንድ የተላከበትን ምስጢር አጉልቶ አስተምሯል፡፡

በመኾኑም ነቢዩ ሚልክያስ "እነሆ መልእክተኛዬን እልካለኊ፤ መንገድንም በፊቱ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል" ያለው ትንቢት በርሷ ፍጻሜውን በማግኘቱ እመቤታችን "የሚልክያስ ንጽሕት አዳራሽ" ተብላ ተጠርታለች፡፡

ሊቁ አባ ሕርያቆስም ይኽነን የሚልክያስን ትንቢት ይዞ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ንጽሕት፤ ጽንዕት፣ ክብርት፣ ልዩ የኾነች እመቤታችንን "ጽርሐ ንጽሕት ዘሚልክያስ" (የሚልክያስ ንጽሕት አዳራሽ አንቺ ነሽ)[176] በማለት ሲያመሰግናት፤ ኢትዮጵያዊዉ የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*"አንቲ ውእቱ ጽርሐ ንጽሕት ዘሚልክያስ ወለፀሓየ ጽድቅ ሞኀተ"*

(የሚልክያስ ንጹሕ አዳራሽና የእውነተኛ ፀሓይ ደጃፍ አንቺ ነሽ)[177] በማለት የፀሓየ ጽድቅ የክርስቶስ ማደሪያ መኾኗን ከሚልክያስ ትንቢት ጠቅሶ አስተምሯል፡፡

[175] Jacob of Serugh, on nativity pp 47-49

[176] አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቊ ፴፯

[177] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 43



www.ethiopianorthodox.org



## ማጠቃለያ

ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ የመጣው ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ቅዱስ ገብርኤል "ጸጋን የተመላሽ ደስተኛዪቱ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መኻከል የተባረክሽ ነሽ" በማለት ታላቅ ምስጋናን ለፈጣሪው እናት ሲያቀርብ፤ ቅድስቲቱ እናት ኤልሳቤጥም የፈጣሪን እናት ስታያት በታላቅ መንፈሳዊ ደስታ ኾና መንፈስ ቅዱስ ዐድሮባት በታላቅ ድምፅም ጮኻ "አንቺ ከሴቶች መኻከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይኾንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ ወደ ዦሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማሕፀኔ በደስታ ዘሏልና፤ ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት" በማለት አመስግናታለች (ሉቃ ፩፥፳፰-፵፭)፡፡

እመቤታችንም ከእንግዲኽ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ በመጣው በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤልና መንፈስ ቅዱስ ዐድሮባት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ባመሰገነቻት በኤልሳቤጥ ብቻ ሳይኾን፤ አስቀድሞም ክቡር ዳዊትም በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ "የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ"(መዝ ፵፬፥፲፪) በማለት እንደ ተናገረ፤ ርሷም ፍጥረት ኹሉ እንደሚያመሰግናት "እነሆም ከዛሬ ዠምሮ ትውልድ ኹሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የኾነ ርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው"(ሉቃ ፩፥፵፱) በማለት እንደተናገረች ንጽሕናዋን ቅድስናዋን በብዙ ሕብረ ትንቢት በተናገሩ፣ በብዙ ሕብረ አምሳል በመሰሉ በአበው ነቢያት ፊንታ፤ ወላዲተ አምላክነቷን በዓለሙ ኹሉ ዞረው ያስተማሩ ቅዱሳን ሐዋርያት እንደተተኩ፤ ከነርሱም በመቀጠል ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ እንደ ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ምእመናን ኹሉ ብፅዕት ነሽ እያሉ የፈጣሪያቸውን እናት ዘወትር ያመሰግኗታል ፡፡

ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸውን ምእመናን ኹሉ ፍጹም ደስ ስለሚያሰኝ ምስጋናዋ በአርጋኖን ምስጋናው ሲገልጽ

*"ሚ መጠን ዕበዩ ተውህበ ለኪ ኦ ወለተ ያዕቆብ፤ ወሚመጠን ጸጋ ተጸጎኪ ኦ ወለተ እስራኤል፤ ወሚመጠን ስብሐት የዐውደኪ ኦ ወለተ ይሁዳ፤ ወሚመጠን ተነግረ ውዳሴ ዚኣኪ ኦ ወለተ ዳዊት፤ ናሁኬ እምኪሩቤል ዐበይኪ ወእምሱራፌል ተለዐልኪ ወእምኵሎሙ ትጉሃን ሰማይ ይፈድፋድ ክብርኪ ወለዝሉፉ ኢይትዌዳእ ስብሐተ ድንግልናኪ፤*

ውድስት አንቲ በኵሉ ዓለም ወስብሕት አንቲ በኵሉ አዝማን ንጽሕት አንቲ በኵሉ ጊዜ፤ ወጽሪት አንቲ በኵሉ ሰዓት ቅድስት አንቲ በኵሉ መካን ወቡርክት አንቲ በኵሉ ልሳን፤ አልቦ ዘይሜንዮ ለላሕይኪ ኢ ጎሕ ወኢብርህ ኢ ፀሓይ ወኢወርኅ ኢ ዋካ ወኢጸዳል ኢጽጌ ገዳም ወኢጽጌ ገነት፤ አልቦ ዘይኤድሞ ለቆምኪ ኢበቀልት ወኢአርዘ ሊባኖስ፤ ወአልቦ ዘይጸዐዱ እምአስናንኪ ኢ ሐሊብ ወኢእብነ በረድ፤ አልቦ ዘይበርህ እምጸዳለ ዐይንኪ ኢ ቤዝ ዘያንበለብል በገጸ ሰማይ ወኢባሕርይ ዘያንጸበርቅ ዲበ ርእሰ ነገሥት ወአልቦ ዘይምዕዝ እምጼና አንፍኪ ወእምጼና አልባስኪ ኢከልበኔ ወኢሐንክስ ወኢአስጻዳዮስ ወኢናርዱ ቅድው ዘዕጹብ ሤጡ ወመዐድም ኵለንታኪ ወክሉል በጸጋ መንፈስ ቅዱስ፤ ኦ ርግብ ንጽሕት እንተ ተለቅሐ ዕጕሊሃ ታሕተ ክነፊሃ ያጌብረኒ ፍቅርኪ ከመ እትናገር ውዳሴ ዚኣኪ ለምንትኒ እትሀከይ ቀዲሐ ጸቃውዕ እስመ ጥዑም ውእቱ ለዘይበልዖ፤ ወለምንትኒ እትሀከይ ቀዲሐ ሐሊብ እስመ ሐዋዝ ውእቱ ለዘይሰትዮ፤ ወለምንትኒ እትሀከይ ቀሲመ ጽጌ ትንቢት እስመ ይኤድሞ ለአንፍ ጼና መዐዛሁ፤ ለምንትኒ እትሀከይ ጽዒጠ አፈወ ሃይማኖት እስመ ይትሜዐዙ አእዳውየ በስኪኖቱ፤ ወለምንትኒ እትሀከይ ነጊረ ዕበያ ለቅድስት ወንጽሕት ድንግል ማርያም ዘበዕብራይስጢ ማሪሃም ወላዲተ አምላክ እስመ ይጥዕም ውዳሴሃ እምጸቃውዐ መዓር ወይሔውዝ እምሐሊብ ወይኤድም እምጽጌያት ወይምዕዝ እምአፈዋት ጽዑማት፤ እነግርኪ ውዳሴ ዚኣኪ ኦ ርግብ ጸዐዳ ወእጸርሕ ኀበ ወልድኪ እንዘ እብል ምላእ አፉየ ስብሐቲከ ከመ እሰብሕ አኰቴተከ ወከመ እንግር ዕበያቲሃ ለቅድስት ወንጽሕት ወላዲትከ ወተመልኢየ እንከ እመንፈሰ ወልድኪ. አነዝር ስብሐተ ድንግልናኪ ወአስተበፅዕ ዕበየኪ"

(የያዕቆብ ብላቴና እመቤቴ ሆይ ምን ያኽል ክብር ተሰጠሽ? የእስራኤል ብላቴና እመቤቴ ሆይ ምን ያኽል ጸጋ ተሰጠሽ? የይሁዳ ብላቴና እመቤቴ ሆይ ምን ያኽል ብርሃን ይከብሻል? የዳዊት ብላቴና እመቤቴ ሆይ የአንቺ ምስጋና ምን ያኽል ተነገረ? እንሆ ከኪሩቤል ይልቅ በለጥሽ ከሱራፌልም ይልቅ ከፍ ከፍ አልሽ፤ ከትጉሃን የሰማይ መላእክት ኹሉ ይልቅ ክብርሽ ይበልጣል፤ የድንግልናሽ ምስጋናም ለዘላለሙ አይፈጸምም፤ በዓለም ኹሉ አንቺ የተመሰገንሽ ነሽ፤ በየዘመናቱም ትከብሪያለሽ፤ በየጊዜውም ኹሉ ንጽሕት ነሽ፤ በየሰዓቱም ኹሉ አንቺ የጠራሽ ነሽ፤ በየቦታው ኹሉም አንቺ የተመረጥሽ ነሽ፤ በአንደበት ኹሉም አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ ደም ግባትሽን የሚያምረው (የሚበልጠው)





የለም፤ የንጋት ውጋገንም ቢኾን! ብርሃንም ቢኾን! ፀሓይም ቢኾን! ጨረቃም ቢኾን! ወዝሽን ለዛሽን የሚመስለው የለም፤ ቁመናሽን የሚመስለው የሚያምረው የለም፤ የሰሌን ዛፍም ቢኾን! የደጋ ዛፍም ቢኾን! ከጥርሶችሽም የሚነጣ የለም ወተትም ቢኾን! የበረድ ድንጊያም ቢኾን! ከዐይንሽ ብርሃን ይልቅ የሚበራ የለም፤ በሰማይ ፊት የሚንቦገቦግ ኮከብም ቢኾን! በነገሥታት ራስ ላይ የሚያንጸባርቅ ዕንቊም ቢኾን! ከአፍንጫሽም መዐዛ ከልብሶችሽም ሽታ የበለጠ የሚሸት የለም፤ ከልበኔም ቢኾን! ሐንክሶም ቢኾን! አስጳዳዮስም ቢኾን! ዋጋው ውድ የኾነ ናርዱ የሚባል ሽቱም ቢኾን! ኹለንተናሽ ያማረ ነው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋም የተጋረደ ነው፤ ገላግልቷን በክንፎቿ ሥር የምታቅፍ (ምእመናንን በቃል ኪዳኗ የምትጠብቅ) ነጭ ርግብ ሆይ፤ የአንቺን ምስጋና እንድናገር ፍቅርሽ ያስገድደኛል፤ የማር ወለላን ለመቅዳት ለምን እሰንፋለኁ? ለሚበላው የጣፈጠ ነው፤ ወተትንስ ለመቅዳት ለምን እሰንፋለኁ? ለሚጠጣው ያማረ የተወደደ ነውና፤ የትንቢት አበባንስ ለመልቀም ለምን እሰንፋለኁ? የመዐዛው ሽታ ለአፍንጫ ያማረ ነውና፤ የሃይማኖት ሽቱን ቀምሞ ለማጣፈጥስ ለምን እሰንፋለኁ? ርሱን በመንካት እጆቼ ይሻተታሉና፤ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ አምላክን የወለድሽ የተመረጠሽ የንጽሕት ድንግል ማርያም ገናንነቷን መናገርስ ለምን እሰንፋለኁ? ምስጋናዋ ከማር ወለላ የበለጠ ይጣፍጣልና፤ ከወተት ይልቅም ያምራልና፤ ከአበቦችም ይልቅ ይወደዳልና፤ ከተቀመሙ ሽቱዎች ይልቅ ይሸታልና፤ ጻዐዳ ርግብ ሆይ የአንቺን ምስጋና እናገራለኁ፤ ወደ ልጅሽ እጮኻለኁ፤ እንዲኽ ስል ምስጋናኽን በአንደበቴ ምላ በምስጋናኽ እንዳመሰግንኽ፤ የተመረጠችና ንጽሕት የምትኾን የናትኽን ገናንነት እናገር ዘንድ፤ ከልጅሽ መንፈስ ተመልቼም የድንግልናሽን ምስጋና እንዘራ እመታለኁ ገናንነትሽንም አደንቃለኁ)[178] በማለት እንደተናገረ፤ ምእመናን ሆይ እኛም እንደ ቅዱሳን አባቶቻችን በፍጹም ተመስጦ ኾነን ከማር ይልቅ የሚጣፍጥ ምስጋናዋን ከአንደበታችን ሳናቋርጥ እናመስግናታለን፡፡

ሰማይ ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀኗ የተሸከመች፤ ኪሩቤል ሱራፌል ዙፋኑን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚሸከሙትን ሰማያዊ መለኮትን በገርባዋ ያዘለች፤ በክንዷ የታቀፈች፤ ሰማይ ምድር ከፊቱ የሚሸሹትን የባሕርይ አምላክን በከናፍሮቿ የሳመችው፤

[178] አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘቀዳሚት ምዕ ፱፥፩-፱



www.ethiopianorthodox.org

ፍጥረታትን ኹሉ በዝናብ አብቅሎ በፀሓይ አብስሎ የሚመግበውን፤ ለቅዱሳን መላእክት ርሱ የገለጸላቸው ምስጋና ምግብ ኹኗቸው እንዲኖሩ ያደረገውን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለውን እግዚአብሔር ወልድን የድንግልና ጡቶቿን ያጠባች የርሷን ፍጹም ክብሯን፣ ምሳሌዎቿን፣ ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋንና፣ የዘላለማዊ ድንግልናዋን ነገር ሰማይ ምድር ብራና፤ በዓለም ያሉ ውቅያኖሶች ኹሉ ቀለም፤ መላእክትና የሰው ልጆች ኹሉ ጸሐፍት ቢኾኑ እንኳ ከቶ ሊፈጽሙ አይቻላቸውም።

ቅድስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም የባሕርይ አምላክን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች የአምላክ እናት የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብርና ቅድስና ዐውቃ በብሉይ ኪዳን ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ድረስ በቅዱሳን አበው በቅዱሳን ነቢያት የተነገረውን ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳል፤ በቅዱሳን ሐዋርያት የተሰበከውን ምስጢር ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ ስትመሰክር ትኖራለች።

እኔም በክፍል አንድ የነገረ ማርያም መጽሐፌና በዚኽ የክፍል ኹለት መጽሐፌ ላይ ቅዱሳን አበው፣ ቅዱሳን ነቢያት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው በብዙ ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳል ከገለጹት ከሰማይ ከዋክብት ከባሕር አሸዋ ይልቅ ከበዛው ክብሯ መኻከል ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጌ እንደጻፍኹኝ፤ እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደ ፊት በተከታይነት በማቀርበው ነገረ ማርያም በሐዲስ ኪዳንና ነገረ ማርያም በሊቃውንት በሚለው መጽሐፌ ላይ የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር በጥልቀት የማቀርበው ይኾናል።

እግዚአብሔር ፈቅዶ በክፍል አንድና በክፍል ኹለት የገለጽኋቸውን ቅዱሳን አበው፣ ቅዱሳን ነቢያት በብዙ ሕብረ ትንቢትና በብዙ ሕብረ አምሳል የተናገሩላትን የቅድስት ድንግል ማርያምን ምሳሌዎቿ ጠቅልዬ ከዚኽ በታች በምስጋና ክፍል ውስጥ ሳሰፍር መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው ቅዱሳን አባቶቻችን ዘንድ የርሷ ፍቅሯ ጣዕመ ፍቅሯ በእጅጉ እንደ በዛ ኹሉ በኛም በኹላችን እንዲኹ እንዲበዛልን በበመኘት ነው።





## ምስጋና

"ድንግል ሆይ አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ንጽሕት ሆይ! ድንግል ሆይ የተመሰገንሽ ቡርክት ሆይ! ድንግል ሆይ የተመረጥሽ ቅድስት ሆይ! የድንግልናሽ ምስጋና በቅዱሳን አበው፣ በቅዱሳን ነቢያት በብዙ ሕብረ ትንቢት የተነገረልሽ በብዙ ሕብረ አምሳል የተመሰለልሽ እመቤታችን ሆይ ዕለተ እሑድ የተባልሽ ነሽ፤ ዳግመኛም በኢየሩሳሌም ሰማያዊት የምትገኝ ታቦት ዘዶር አንቺ ነሽ፤ ድንግል ሆይ የብርሃን መገኛ ዕለተ ሰኑይ፤ ኹለተኛዪቱ ሰማይና አማናዊ ዝናብን የተሸከምሽ ብርህት ደመና ነሽ፤ ገራኅተ ሠሉስ የተባልሽ እመ አዶናይ ሆይ በገነት ያጣነውን የሕይወት ፍሬ በዚኽ ዓለም ያገኘንብሽ የሕይወት ዛፍ ነሽ።

ሔኖክ የተመለከታት በሱራፌ የምትጠበቅ ፍሬዋ የማታልቅ የገነት ዛፍ ድንግል ሆይ የአማናዊ ፀሐይ እናቱ ዕለተ ረቡዕ ነሽ። ከገኑ በፈለሰ ውሃ ልጅነትን ያገናጸፈንን አምላክ በማሕፀንሽ የተሸከምሽ ዕለተ ሐሙስ የተባልሽ ቅድስት ሆይ አዳም የተገኘባት ድንግል ምድርና የዕረፍት መገኛ ዕለተ ቀዳሚት አንቺ ነሽ።

የአዳም የታተመች ጎኑ ምሳሌሽ የሚኾን ከእውነተኛው መልአክ ከቅዱስ ገብርኤል ብሥራትን የሰማሽ የመንፈስ ቅዱስ ቤት ዳግሚት ሔዋን፣ ብርህት ዐይን እመቤታችን ሆይ አዳም ከዕርቃኑ የተሰወረባት የበለስ ቅጠልና የሴቶች ኹሉ መመኪያ ነሽ።

ከገነት በተሰደዱ ጊዜ የአዳምና የሔዋን ተስፋቸው የሕያዋን ኹሉ እናት እመ ብርሃን ሆይ የአቤል የመሥዋዕቱ ማስቀበያ፣ የሴት ቸርነት፣ የሔኖክ መሰወር የታወቀብሽ፤ የሰው ዘር ኹሉ ከዘላለማዊ ሞት በቃል ኪዳንሽ የሚጠበቅብሽ ባለ ሦስት ክፍሏ የኖኅ መርከብ አንቺ ነሽ፤ ለፍጥረት ኹሉ የምሥራች የሚኾን ሰማያዊ ንጉሥን በቤተልሔም ይዘሽ የታየሽ የኖኅ ርግብ እመቤታችን ሆይ የቃል ኪዳን ምልክትነትሽ ዘወትር ጸንቶ የሚኖር ቀስተ ደመናችን ነሽ።

የሴም በረከቱ፣የካም የርግማኑ ትድግና፣ የማቱሳላ የዕድሜው ርዝማኔ፣ የላሜሕ ዕረፍቱ ንጽሕት ድንግል ሆይ አማናዊ ሊቀ ካህናት ዐማኑኤልን ያስገኘሽልን የመልከ ጼዴቅ መሠዊያ አንቺ ነሽ፤ ከወገኖቹ ተለይቶ የወጣው ደጉ አብርሃም በራእዩ የተመለከተሽ ንጽሕት ርግብ እመቤታችን ሆይ ይኽ አባት እግዚአብሔርን በሦስትነቱ ያየብሽ የወይራ ዕንጨትና ሥላሴ የገቡባት አማናዊት ድንኳኑ ነሽ።



www.ethiopianorthodox.org

የዓለም ቤዛን የወለድሽልን አብርሃም በሞርያ ተራራ ላይ የተመለከተሽ ዕፀ ሳቤቅ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናሽ ንግሥታችን ሆይ የአብርሃም የጽድቁ ማኅተም፣ የተከባከባት ርሻውና ወደ ርብቃ ቤተሰብ የላካት የምሥራች መልእክቱ ነሽ።

የሰማይ ደጅ የተባልሽ አማናዊት ቤቴል፣ ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ ያያት የወርቅ መሰላል ሰአሊተ ምሕረት እናታችን ሆይ ሮቤል በአዝመራ ዘመን ያገኘሽ የበረሓ ዕንኮይና ያዕቆብ በገንዳዎቹ አጠገብ ያኖረሽ በትር፣ ዳግመኛም ከጌታ ጋር የተገናኘባት ጵኒኤል የተባልሽ ቦታና ብሩህ ኮከብ የወጣብሽ ምሥራቅ ነሽ።

የያዕቆብ ጥንካሬና በረከት፣ ከመርገም ሞት የሮቤል ፈላጊው ድንግል ሆይ፣ የሴኬም ምድር ወገኖች ሥሮችን የቈራረጡ የሌዊና የስምዖን ተስፋ፣ የአንበሳ ደቦል የይሁዳ የንግሥናው ምልክት ነሽ፣ የእንኮይ ዋጋ የተባለ የይሳኮር የዕረፍቱ ርስት፣ የዛብሎን የወደብ ማደሪያ፣ የንፍታሌም የሽቱ ዘንባባ ነሽ፣ የአሴር የእግሩ መታሻ ቅባት፣ በካም ርስትም የዮሴፍ ገናንነት ነሽ፣ የጋድ የበረከቱ ስፋት የብንያም የታመነች ምድሩ፣ የምናሴ የሰራዊት ብዛት ፣የኤፍሬምም የቡራኬው ጸጋ ነሽ።

መላእክት ከፊቱ ሲቀርቡ የማይቻላቸው እሳተ መለኮት ጌታን በማሕፀንሽ የተሸከምሽ ክብርት ሆይ ሙሴ በአድናቆት የተመለከታት ዕፀ ጳጦስ ነሽ፣ በምድረ ግብጽ አምላክ ከሃሊነቱን የገለጸባት ደመና ዳግመኛም የሕይወት መና የክርስቶስ እናቱ አንቺ ሆይ የሙሴ ደመናና ለ፵ ዘመን እስራኤልን የመራች በብርሃን ያጌጥሽ የደመና ምሶሶ ነሽ።

በቃል ኪዳንሽ ከሞት ወደ ሕይወት የምንሸጋገርብሽ የሙሴ በትሩና ዘላለማዊ ምግብ አማናዊ መናን ያስገኘሽልን የወርቅ መሶብ አማላጃችን ድንግል ማርያም ሆይ የሕይወት ውሃ የዐማኑኤል እናቱ የኮሬብ ቦታ ነሽ፣ አማሌቃውያን ድል የተነሡባት የሙሴ ክንዱ የኀያላን ጌታ እናቱ አመቤታችን ሆይ ልዑል እግዚአብሔር በታላቅ ክብር የተገለጸባት የሲና ተራራ ነሽ።

የአምላክ ማደሪያው የቃል ኪዳን ታቦት በንጽሕና በቅድስና የተጌጥሽ ቅድስት ድንግል ሆይ ኅብስተ ሕይወት ጌታን ያገኘንብሽ እውነተኛዪቱ ገበታና የብርሃን እናቱ የወርቅ መቅረዝ ነሽ፣ አምላክ የመረጣቸው ንዋያተ ቅድሳት በውስጧ ያሉ ጳውሎስ ያደነቀሽ የእውነተኛው ሊቀ ካህናት ማደሪያው የብርሃን ድንኳን አንቺ ነሽ፣



www.ethiopianorthodox.org



ዳግመኛም በካህን አሮን ልብስ ላይ ያለች ዐሥራ ኹለት የአዕናቍ ጌጥ በውስጧ ያለ ጸናጽል፣ አማናዊ እሳትን የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንትና ለአምላክ ብቻ ተለይታ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የተቀመጠች ጣፋጭ ሽቱ አንቺ ነሽ።

ማኅደረ ቃለ አብ የተባልሽ አማናዊት የሙሴ ጽላት ንግሥታችን ድንግል ማርያም ሆይ የሙሴ ርሻው፣ ከኤሽኮል ሸለቆ የተገኘችው የወይን ሐረግ ነሽ፣ ቡሩክ አሮን ይዟት የወጣ የወርቅ ማዕጠንቱ ዳግመኛም ሳይተክላት በቅላ ውሃ ሳያጠጧት ለምልማ፣ አብባ፣ አፍርታ የተገኘችው በትሩ ነሽ፣ ሙሴ በእስራኤል ጉባኤ ኹሉ ፊት የዘመረልሽ ንጽሕት መስክ ሆይ የካሌብ ርስቱ፣ ማርና ወተት የምታመነጭ ኢየሩሳሌምና ኢያሱ በምድረ ርስት የተከላት የምስክር ሐውልት አንቺ ነሽ።

ትውልድ ኹሉ ብፅዕት የሚሉሽ የአምላክ እናት ሆይ የባርቅ ኀይል፣ የኢያኤል በረከት፣ የዮፍታሔ የመሥዋዕቱ መዐዛ ነሽ፣ በኀያሉ ሶምሶን እጅ ከአንበሳ አፍ የተቀዳሽ የማር ወለላ፣ ጽሙን ያስወገደለትን ውሃ ያስገኘሽለት ኀትምት መንሰከ አድግ ዳግመኛም በራሱ ጠጕር ያደረች ኀይሉ አንቺ ነሽ።

የሕይወት ጠል ክርስቶስን ያገኘንብሽ የጌዴዎን ፀምር እመቤታችን ሆይ ዳጎንን ቀጥቅጣው የጣለችው ዐሥሩ ቃላት የተጻፉባቸው ጽላት የተቀመጡባት፣ ዳዊት በፊቱ የዘመረላት ታቦተ ጽዮን ነሽ፣ የሳሙኤል የሽቱ ዕቃ፣ የዳዊት መሰንቆው ነሽ፣ የነቢያት ጉባኤ በኅብረት የዘመሩብሽ አውቴዝራማ የተባልሽ የትንቢት ተራራና ዳዊት የመድኀኒት መሥዋዕት ያቀረበብሽ የኦርና ዐውድማ አንቺ ነሽ።

ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ የመጣው ቅዱስ ገብርኤልና መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ኤልሳቤጥ ያመሰገኑሽ ዓለማትን የፈጠረ ጌታን የወለድሽልን እመቤታችን ሆይ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ዳግመኛም ስድስት ዕርከን ያላት በግራና በቀኝ ዐሥራ ኹለት የወርቅ አናብስት የሚከቧት ዙፋኑ ነሽ፣ የቀርሜሎስ መሠዊያና በአራተኛው ዘመን የዝናብን ውሃ ይዘሽ የታየሽ ብርሀት ደመና ሆይ የኤልያስ የወርቅ መሶብና የድንግልናው ምልክት ያደረጋት የወገቡ መታጠቂያ ነሽ፣ የዓለሙን ምረት ያጣፈጠ የጌታ እናቱ አንቺ የኤልሳዕ ማሰሮና ማድጋ ሆይ የሕዝቅያስ መድኀኒት የበለስ ጫፍ አንቺ ነሽ።

በግፍ የሞተ የናቡቴ የተክል ቦታ የተባልሽ እመቤታችን ሆይ የጦቢት የዐይኑ ብርሃን ነሽ፤ ለዮዲት የቃሏ ጥበብ ነሽ፤ የአስቴር የጸሎቷ መሰላል፤ የኢዮብ የልመናው መቀበያ አንቺ ነሽ፡፡

ወርቀ ዘቦ ግምጃ ለብሰሽ በንጉሡ ቀኝ ቆመሽ አባትሽ ዳዊት የተመለከተሽ ንግሥት እመቤታችን ሆይ ከላይ ተልኮ የመጣው ቅዱስ ገብርኤል በብሥራቱ ደስ ያሰኘሽ የእግዚአብሔር ከተማው አንቺ ነሽ፤ ክንፎቿ በብር የተሠሩ ጐኖቿም በወርቅ የተሸለመች ንጽሕት ርግብ ብሎ ዳዊት የዘመረልሽ ንጽሕት ሆይ ላሕም ወልደ እግዚአብሔርን ያስገኘሽልን ዐዲሲቱ እንቦሳ ነሽ፡፡

የጠለ ሕይወት የዐማኑኤል እናቱ ፀምረ ዳዊት ሆይ የሰማያዊዉ ንጉሥ ማደሪያ የጽዮን ተራራ ነሽ፤ ባንቺ እውነትና ሰላም ሰላምታን የተሰጣጡብሽ፤ ሰው ኹሉ እናታችን ጽዮን የሚልሽ ከተቀደሱ ተራሮች የወጣሽ፤ ልዑል የዘላለም ማደሪያው ሊያደርግሽ የመረጠሽ የልዑል ማደሪያው አንቺ ነሽ፡፡

በእሾኽ መኻከል የሕይወት ፍሬን ያፈራሽ የሰሎሞን የሱፍ አበባ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ የነገሥታት ንጉሥን የተሸከምሽ አማናዊት ዙፋን ነሽ፤ ነውር ነቀፋ ፈጽሞ የሌለብሽ ከሊባኖስ ተራራ የወጣሽ ሙሽራ ነሽ፤ ማንም ሊከፍታት የሚችል የሌለ የተቈለፈች ገነትና የነፍሳትን ጥም ያበረደ የሕይወት ውሃ ካንቺ የፈለቀልን የታተመች የውሃ ጕድጓድ ነሽ፤ ከኹሉ ተለይተሽ የተመረጥሽ ርግበ ሰሎሞን ሆይ ጠቢቡ አባት ከልጅሽ ጋር ከግብጽ የመመለስሽ ነገር ተገልጾለት ፍጽምት የኾንሺቱን አንቺን ሱላማጢስ ብሎ ያመሰገነሽ አንቺ ነሽ፡፡

መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ መንፈስ ቅዱስ ከናትሽ ማሕፀን የጠበቀሽ ንጽሕት ዘር ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ሆይ የመለኮት ፍም ጕጠቱ፤ ኢሳይያስ የተመለከተሽ ክብርሽ ከፍ ከፍ ያለ የአምላክ ዙፋን አንቺ ነሽ፤ እናትነትን ከድንግልና ጋር አስተባብረሽ የተገኘሽ ነቢይት የተባልሽ ቅድስት ሆይ መዐዛ ቅዱሳን ክርስቶስን የወለድሽልን የዕሴይ በትር ነሽ፤ አፍጣኒተ ረድኤት እመቤታችን ሆይ የባሕርይ አምላክ በገርባሽ ታዝሎ ወደ ምድረ ግብጽ የወረደብሽ ፈጣን ደመና አንቺ ነሽ፡፡

ማንም ገልጦ ሊያነባት ሊከፍታት የማይችል የኢሳይያስ የታተመች መጽሐፉ እናታችን ሆይ የሕይወት ፍሬ፣ የሕይወ[illegible] [illegible] ፈጣሪያችን ክርስቶስን እንበለ ዘርዐ ብእሲ በግብረ መንፈስ ቅዱስ [illegible]



www.ethiopianorthodox.org



የወለድሽልን የተጠማሽ ምድርና ዳግመኛም ትውልድ ኹሉ ብፅዕት እያለ ከፊትሽ የሚማለል የነገሥታት ንግሥት አንቺ ብቻ ነሽ፡፡

ነቢዩ ኤርምያስ በትንቢቱ መገርመሪያ የማትለወጪ የሃይማኖት በትርነትሽን የተመለከተሽ ክብርሽ ከፍ ከፍ ያለ የፈጣሪያችን እናት ሆይ ደቀ መዝሙሩ አቤሜሌክ በስሳ ስድስተኛው ዘመን በትኩስነት ያገኘሽ የበለስ ቅርንጫፍ ነሽ፡፡

ነቢዩ ሕዝቅኤል በአድናቆት የተመለከተሽ የሰማይና የምድር ፈጣሪን በክንዶችሽ ታቅፈሽ፤ በገርባሽ ያዘልሽው ኪሩባዊት ሠረገላ ነሽ፤ ዳግመኛም የእስራኤል አምላክ ብቻ ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት የወጣ ለዘላለሙም ያተማት የሕዝቅኤል ምሥራቅ አንቺ ነሽ፡፡

ብሉየ መዋዕል ወልድን እንበለ ዘርዐ የፀነስሽ የእብነ ሕይወት እናቱ ቅድስት ድንግል ሆይ ነቢዩ ዳንኤል ያየሽ ረዥምም ተራራ ነሽ፤ በእሳት ውስጥ የተጣሉ የሦስቱ ሕፃናት የምስጋና ጣዕም ነሽ፤ የሰባ ዘመን ሱባዔን የቈጠረ የዳንኤል የትንቢቱ ክንውን ነሽ፤ ዳግመኛም በተራበ ጊዜ ምግብን ተመግቦ አምላኩን ያመሰገነባት የአናብስት ጕድጓድ አንቺ ነሽ፡፡

ወገኖቹ ያልነበርነውን እኛን ወገኖቹ ያደረገን ዐማኑኤልን ያስገኘሽልን የአሞጽ ምድር ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፤ ከአእላፍ ጊደሮች መሠዋት ይልቅ የርሱ መሠዋት የተሻለ የእግዚአብሔር መገኘት በአንቺ የኾነ የሚክያስ የትንቢቱ ክንውን፤ ዳግመኛም የሕይወት እንጀራ መገኛ አማናዊት ቤተልሔም አንቺ ነሽ፡፡

ዳግመኛም የኢዩኤል የበረከቱ ምንጭ አንቺ ነሽ፤ የእግዚአብሔር መገለጡ በአንቺ የኾነ የአብድዩ የመድኀኒት ተራራ የጽዮን ተራራ አንቺ ነሽ፤ የዮናስ የነፍሱ ጠባቂና ከሲኦል ጕድጓድም የምታወጭው አንቺ ነሽ፤ የናሆም የቍስሉ መድኀኒትና የዕንባቆምም የጸሎቱ መሰላል አንቺ ነሽ፤ የሶፎንያስ ራእይ ፈጻሚና የሐጌም የቤቱ ሽልማት ጌጥ አንቺ ነሽ፡፡

ድንግል ሆይ የኹለቱ ጕልማሶች ክርክር ምሳሌ ባሸነፈለት ጊዜ በንጉሡና በባለሟሎቹ ፊት የዘሩባቤል የቃሉ ጣዕም አንቺ ነሽ፤ ዮሴዕ ያጌጠብሽ የክህነት ልብሱ አንቺ ነሽ፤ አማናዊ ብርሃን ክርስቶስን ያስገኘሽ ዐይኖቿ ሰባት የኾኑላት ቀጥተኛ የዘካርያስ መቅረዝ አንቺ ነሽ፤ የሱቱኤል የልቡናው ጽዋ ነሽ፤ የሚልክያስ ንጹሕ አዳራሽና የእውነተኛ ፀሓይ ደጃፍ አንቺ ነሽ፡፡"

ይቀጥላል

# ዋቢ መጻሕፍት


ሃይማኖተ አበው ፤ 1982፤ ዐዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

መጽሐፈ ቅዳሴ ፤ 1967፤ ዐዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥሏሴ ማተሚያ ቤት

መጽሐፈ ሀሓይ ፤ በብራና በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ

ርቱዐ ሃይማኖት ፤ በብራና በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ

ቅዱስ ቄርሎስ እስክንድርያዊ፤ ድርሳነ ቄርሎስና ተረፈ ቄርሎስ በእጅ ጽሑፍ በብራና የሚገኝ ያልታተመ

ተአምረ ማርያም ፤ 1983፤ ዐዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

አስራደ ባያብል (ሊቀ ጠበብት) ፤ 1998፤ ማሕሌተ ጽጌ ትርጓሜ ፤ ዐዲስ አበ...

______ 2001፤ የሰቆቃወ ድንግል ትርጓሜ ፤ ዐዲስ አበባ፤ ከሃሲ ማተሚ...

መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው ፤1982፤ ዐዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላ... ማተሚያ ቤት

መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ

ነገረ ማርያም ፤ በእጅ ጽሑፍ በብራና የሚገኙ ያልታተሙ

ዳንኤልና ዐሥራ ኹለቱ ደቂቅ ነቢያት፤1998፤ ዐዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ማተ...

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ) ፤ 1958፤ መጽሐፈ ሰዋሰው መግሥ ወመዝገበ... ሐዲስ፤ ዐዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት

ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው ፤ 1983፤ ዐዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፤ በእጅ ጽሑፍ... ያልታተሙ

ድርሳነ ኪዳነ ምሕረት፤ 2001፤ በቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ልማት ኮሚቴ የታተ...

ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ፤ መጽሐፈ ብርሃን፤ በእጅ ጽሑፍ በብራና የሚገኝ ያል...

______ ፤1964፤ መጽሐፈ ብርሃን፤ E.d.c. Conti Rossini corpus Sc... Christianorum Orientulium

Getatchew Haile. *The Mariology of Emperor Zara Yaeq...* Roma

ቅዱስ ያሬድ፤ 1988፤ መጽሐፈ ድጓ፤ ዐዲስአበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተ...

______ ፤ዝማሬ ወመዋሥዕት፤ ዐዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤ...

______ ፤ጾመ ድጓ፤ ዐዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ 2001፤ መጽሐፈ ምስጢር፤ ዐዲስ አበባ፤ በአ... ዘጋሥጫና በአባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም

______. ፤1998፤ መልክአ ሕማማት፤ ዐዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት

______ ፤1967፤ መዐዛ ቅዳሴ፤ ዐዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

______ ፤1987፤ መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ፤ ዐዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

______ ፤መጽሐፈ አርጋኖን፤ ኆኅተ ብርሃን፤ ዕንዚራ ስብሐት በእጅ ጽሑፍ የሚገኙ ያልታተሙ

አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም፤ 1998፤ ማሕሌተ ጽጌ፤ ዐዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፤ ገጽ 623-656

Brock, s. 1994. *Bride of Light: Hymns on Mary from the Syriac Churches.* Kerla, India: St. Joseph's Press.

______. 1989. *Hymns on the Nativity, in Ephrem the Syrian Hymns,* ET by Mc Vey, k., New York

Jacob of Serugh. *On the Mother of God.* 1998. et by Hansubury. St. Vladmir Seminary press New York

______.2005. *Homily on the Perpetual Virginity of Mary.* 2005. et by James Puthuparampil O.I.C. Kerla, India

______ .1997. *Select Festal Homilies.* ET by kollamparampil. Rome

James Puthuparampil O.I.C. *Mariological Thought of Mar Jacob of Serugh (451- 521).* 2005. Kerla, India




www.ethiopianorthodox.org

## በመጽሐፉ ላይ የታላላቅ ሊቃውንት አስተያየት

የነቢያት ዜና ትንቢታቸው የኾነች እመቤታችን ለሐዋርያትም ዜና ስብከታቸው መኾኗ ጉልቶ መጻፉን ተመልክቼዋለኹ፤ በመጽሐፉም ውስጥ ነቢያት በሕብረ ትንቢት የገለጹት የክርስቶስ ሰው መኾን በአንጻሩ ደግሞ በሕብረ አምሳል ተመስሏል፤ በኹለቱም መጽሐፍ ያለው የነገረ ማርያም ምስጢር አቀራረቡ እመቤታችን ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና መውለዷንና ከወለደቹውም በኋላ በኅቱም ድንግልና ፀንታ መኖሯ በምስጢሩ ውስጥ ተገልጿል (ሕዝ ፵፬፥፪)፤ በመልእክትም ቃል ወላዲ... አምላክነቷ ተመስክሮላታልና በኅቱም ድንግልና ፀንሶ መውለድ የእመቤታችን ... ስለኾነ መጽሐፉን ነገረ ማርያም ያሰኘው ይኸ ነው፤ ርሷም ይኸነን አም... ዓመቱ ለእግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ" ብላ በእምነት ተቀብላ ... ይኸም በመጽሐፉ ውስጥ በተጠቀሰው በሊቁ በቅዱስ ኤፍሬም ጽሑፍ ... ጦልናል፤ በመኾኑም "ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል 2" በተባለው ... አስደናቂ መጽሐፍ ይኸ ልዩ ምስጢር በስፋትና በጥልቀት ተተንትኖ ስለ... መጽሐፉን የምታነቡ በሙላ ይኸነን ልዩ ምስጢር እንድትረዱት አሳስባለኹ።

መልአከ ፀሐይ ታፈሰ ደሣለኝ

የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ ኪዳን መምህር

ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን በየድርሳኖቻቸው ሲተረጉሙና ሲያመሰጥሩ እጅግ አድምተው፣ አቍስለውና አብስለው የወላዲተ አምላክነቷን፣ የድንግልናዋንና የምልጃ ባለሥልጣንነቷን (ብውሕተ ትንብልና መኾኗን) አረጋግጠው ያቀረቡበት የመገናኛውና ታላቁ የአስተምህሮ ክፍል ነገረ ማርያም ሲኾን በአሉታዊ መልኩ ደግሞ ትርጉሙንና ምስጢሩን ወደ ውስጥ ገባ ብለው ሳይመለከቱ በእመቤታችን ላይ የተዛባ አመለካከት ያላቸውና ከቅዱሳት መጻሕፍት መሠረተ ሐሳብ የወጡ፣ በጠዋያዊ ፍልስፍና ከሕገ እግዚአብሔር ያፈነገጡ፣ ከአምላክ ከተማ አፈትልከው የጨለማ አበጋዝ ወደሚገዛው ጫካ የፈረጠጡ፣ ዳግም ላለመመለስም በክሕደታዊ ውሳኔ ጸንተው የተቀመጡ የብዙ ብዙዎች ናቸው። ይኹን እንጂ ጥንት እንደ ነበሩ፣ ዛሬም እንዳሉ፣ ወደ ፊትም እንደሚኖሩ ቢታሰብም ይኸ ብሉይ ኪዳናዊ የነገረ ማርያም ምሳሌ በመጽሐፉ አዘጋጂ የቤተ ክርስቲያን ምሁር ትጋት ተተርጉሞና ተመስጥሮ፣ እንደ መገበሪያ ስንዴ ተለቅሞና ተበጥሮ፣ የቅድስናዊ ሕይወቱ እውነት እንደ ቅብዐ ሜሮን ነጥሮ የተገለጠበት ክፍለ መጽሐፍ በመኾኑ የአማናዊቷን ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የሚቃወሙ የባሕርየ ተፈጥሮ ወገኖቻችን "ከዛሬ ገሥሮ ትውልድ ኹሉ ያመሰግኑኛል" የሚለውን የወንጌለ መለኮት ትምህርት ኀይለ ቃል በወርቅ መሶብ ውስጥ ያለ ኅብስት ነውና ይመገቡት፤ ከረሐብ ነፍስ ያጠግባቸዋል፤ በዕንቍ ብርሌ ውስጥ ያለ ወይን ጠጅ ነውና ይጐንጩት ከጽምዐ ነፍስ ያረካቸዋል በማለት መልእክቴን ሳስተላልፍ የዝግጅቱን መልካምነትም በተመለከትኹት መጠን እጅን አደንቃለኹ።

መምህር ዐምደ ወርቅ እስጢፋኖስ

www.ethiopianorthodox.org